# የመንፈሳዊ መሪ

# ተግባርና ግብ

*ከዓለም አቀፍ የተልዕኮ ትምህርት ተቋም ጋር በመተባበር በሪክ ሲ ሃዋርድ ተዘጋጅቶ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሰጪ ኮሚቴ አማካኝነት ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ የተመለሰ ስለመንፈሳዊ እድገት መማሪያ መጽሐፍ*

*ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።*

ማውጫ ገጽ

መግቢያ ------------------------------------------------------------ 3-4

ክፍለ ትምህርት

1. የሚያምኑና የሚከተሉ------------------------------------ 5-27
2. መሪዎች ሰዎችን ያደንቃሉ------------------------------ 28-48
3. አድገው ሌሎችን ያሳድጋሉ------------------------------ 49-71
4. ያቅዳሉ ያደራጃሉ----------------------------------------- 72-90
5. መልእክት ያስተላልፋሉ ---------------------------------- 90-112
6. ችግሮችን መፍታትና ውሳኔዎች ማስተላለፍ -----------112-134
7. ኃላፊነት ይቀበላሉ-------------------------------------------135-151
8. ዓላማችን እግብ ማድረስ ----------------------------------153-172
9. ራሳቸውን ገፋፍተው ሌሎችን መገፋፋት ---------------175-197
10. የሙከራ ፈተና መልሶች ---------------------------------200-205

## *መግቢያ*

ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ትምህርት የሚቀስሙት የጥንቶችን አባቶች በምሳሌነት በመከተልና የተሰጡ መመሪያዎችን አጥብቆ በመያዝ ነው፡፡ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ስለ መንፈሳዊ መሪነት ለማስተማር የተዘጋጁት ዘጠኝ ተከታታይ ትምህርቶች በእነዚህ ሁለት መንገዶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ለመሪነት የተጠሩትን የእግዚአብሔር ሰዎችን ምሳሌነት ለመከተል ከጠራቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸውን መመሪያዎች አስቀድሞ ማወቅና መረዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘብ ለዚህ አገልግሎት ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ የሚረዳ መሆን አለመሆኑን የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይሆንም፡፡ የመንፈሳዊ መሪነትን አገልግሎት ለማዳበር ቅድመ ዝግጅት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ ይህን አገልግሎት ለማዳበርና ተገቢ ያልሆኑ ስህተቶችን ለመቅጨት ይረዳል፡፡

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን እቅድና ዓላማ ሊፈጽም የሚችልበት መንገድ የእርሱን ዓላማና እቅድ ተከትለው ሌሎችም እንዲከተሉ ምሳሌ የሚሆኑና የሚመሩ ሰዎችን በመጥራትና በማስነሣት እንደሆነ ከብሉይም ሆነ ከአዲስ ኪዳን ለመረዳት እንችላለን፡፡ በዚህ መሠረታዊ እውነት ላይ በመመርኮዝ የአንድ መንፈሳዊ መሪ ዓላማና ማከናወን ያለበት ተግባር ማወቅና እንደዚሁም ለዚህ አገልግሎት መጠራቱን ማረጋገጡ ኃላፊነቱን በትክክል በመወጣት ውጤታማ ለመሆን እንዲችል ያግዘዋል፡፡ ለመንፈሳዊ መሪ ወሳኝ የሆኑ ሦስት ነገሮች ከስዎች ጋር መሥራት መቻልና ተግባርን በሚገባ መወጣት እንደዚሁም ለዚህ አገልግሎት መጠራትን ማረጋገጥ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ነው፡፡ እነዚህንም መረዳት፣ ብቃት፣ ጥሪ በማለት በሦስት ቃላት ልናጠቃልላቸው እንችላለን፡፡

**መንፈሳዊ መሪነት** የተሰኘው የመማሪያ መጽሐፍ ስለ አመራር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረቱ ተከታታይ ትምህርቶችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ በአገልግሎት ሰፋ ያለ ልምድ ላላቸውም ሆነ ለጀማሪዎች እንደዚሁም ክርስቲያናዊ የአመራር ሥልጠና ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ እንዲጠቅም ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ ዋና ትኩረቱም የመሪነት ስጦታዎችንና ብቃትን ማዳበር እንዴት እንደሚቻል አስፈላጊውን ገለጻ በመስጠት፣

በመሪዎችና በተከታዮች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ትክክለኛ ግንኙነትና ትክክለኛ ትስስር ማድረግ ላይ ነው።

## የመጽሐፉ ዓላማዎች

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ተከታታይ ትምህርቶች ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

1. የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የአመራርን ሃሳብ ምሳሌ በመስጠት መግለጽ።
2. በመንፈሳዊ አመራር ውስጥ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ተግባርና ዓላማ መግለጽ።
3. በራስህ ሕይወትና በሌሎች ውስጥ ያሉትን የመሪነት ስጦታዎችና ችሎታ ለይቶ በማወቅ ማመዛዘን።
4. የተለየ የመሪነት ችሎታን፣ ብቃትንና ዝንባሌን በማሳየት እነዚህ በሌሎችም ሕይወት እንዲዳብሩ መርዳት።
5. ክርስቲያናዊ ዓላማዎችን ተፈጻሚ በማድረጉ ረገድ ከሌሎች መሪዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የራስህን ድርሻና ኃላፊነት መቀበል።

## የመጽሐፉ አጠቃቀም

መንፈሳዊ መሪነት የተባለው የመማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው በግልም ሆነ በጋራ ሆነው ምእመናን ትምህርቱን መከታተል ይችሉ ዘንድ እንደ አስተማሪ ሆኖ እንዲያገለግል የቀረበ ነው። አንድ ተማሪ በሚገባ ለመማር አስተማሪው የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል እንደሚገባው ፣ ይህም መጽሐፍ የሚሰጠውን መመሪያ በጥንቃቄ መከተል አስፈላጊ ነው።

በእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች ማንበብ፣ የቀረቡትን ጥያቄዎች መመለስ፣ በየክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ የሚቀርቡትን የሙከራ ፈተናዎች በሚገባ ማጠናቀቅ ከእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ተከታታይ ትምህርቶቹን በሚገባ ለመከታተል የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር አስፈላጊ ነው። ለዚህም የጥንቱና ቀለል ባለ አማርኛ የወጣው እትም ቢኖር ለማገናዘብ የሚረዳ ይሆናል።

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## መሪዎችና ተከታዮች

በዚህ ክፍለ ትምህርት በእግዚአብሔር የተመረጡ መሪዎችን ምሳሌነት በመመልከት መንፈሳዊ መሪዎች ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑና የእግዚአብሔርንም ዓላማ ከግቡ ለማድረስ እንዴት ከሌሎች ጋር ተስማምተው መሥራት እንደሚገባቸው እንመለከታለን፡፡

### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ
- የዮሴፍ ምሳሌት
- የመሪነት ባሕሪያት

---

### የክፍለ ትምህርቱ አላማዎች

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፡፡

- መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ስላላቸው ሥፍራ መግለጽ
- በመሪነት አገልግሎታቸው የተሳካላቸውን ሰዎች ባሕርይ መዘርዘር
- ከመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎችም የሕይወት ገጽታዎች የመሪነት ባሕርያት ምሳሌ መሆን የሚችሉትን ለይቶ ማወቅና መግለጽ

-----------------------------------------------------------------------------------------------

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1/ በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የተጻፈውን በጥንቃቄ አንብብ። ተከታታይ ትምህርቶቹን ውጤታማ በሆነ መንገድ መከታተል እንድትችል ይረዳሀል።

2/ ትምህርቱን በማንበብ ለጥናት ማጠናከሪያ የተሰጡትን ጥያቄዎች እንድትመልስ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥንቃቄና በማስተዋል ማንበብህን አረጋግጥ፣ ይህም ትምህርቱን እንደሚገባ ለመረዳት እንድትችል ይረዳሀል።

3/ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የቀረበውን የሙከራ ፈተና ከወሰድክ በኋላ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከሰፈሩት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

## የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ

## መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ

የመንፈሳዊ መሪዎች መኖር ለምን እንዳስፈለገ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ረጋ ብለን በመጠየቅ ብንጀምር፣ ሁለት ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ሰዎች በሚሠሩት ማንኛውንም ሥራ መሪ መኖር እንዳለበት መረዳት እንችላለን፣ አንድ ሣጥን ወይም ጣውላን ለማንሣት፡- "አንተ በዚህ በኩል ያዝ፣ እኔ ደግሞ በዚያ በኩል እይዛለሁ" በማለት መመሪያ የሚሰጥ ሰው ያስፈልጋል። በማንኛውም የሥራ እንቅስቃሴ መሪዎች መኖር አለባቸው። በትምህርት ቤትም ሆነ በቤተክርስቲያን ውስጥ የመሪዎች መኖር አስፈላጊና ወሳኝ ነው። ለምንድነው እንዲህ መሆን ያስፈለገው? የሚሰጠውስ ምክንያት ምንድነው?

1/ ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ/ ሰዎችን በቡድን ለማደራጀት ሐ/ ዓላማን ለመፈፀም

ለ/ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ሌሎችን እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ

## መሪነት ሲብራራ

### ዓላማ 1፡- መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ማብራሪያ ለመስጠት

መሪ የሚያስፈልገው አንድን ዓላማ ለመፈጸም ወይም አንድን ተግባር በሚገባ ለማከናወን እንዲያስችል ነው፡፡ ክርስቲያን መሪ የሚኖረውም እግዚአብሔር መንፈሳዊ ዓላማ ስላለው ዓላማውን እግቡ ለማድረስ መንፈሳዊ መሪነት መኖር አለበት፡፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ ፍቅሩንና ምሕረቱን ለመግለጽ ስለሚፈልግ ይህን ዓላማውን እግቡ ለማድረስ መንፈሳዊ መሪዎችን መምረጥና ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲወዱትና እንዲያመልኩትም ስለሚፈልግ ራሱን የቻለ እቅድ አለው፡፡ ስለ እግዚአብሔር እቅድ ስንናገር ዓላማውን ስለሚፈጽምበት መንገድ መናገራችን ነው፡፡ የእግዚብሔር ፈቃድ በድንገት ወይም በአጋጣሚ የሚፈጸም ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በእቅዱ መሠረት ዓላማው ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚፈጽመውም አስቀድሞ ያውቃል፡፡

በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ልንገነዘበው የሚገባን ሌላው ጉዳይ ደግሞ ሥራውን የሚያከናውነው በመንፈስ ቅዱስ በሚመሩና ከእርሱም ኃይልን በተቀበሉ ሰዎች መሆኑ ነው፡፡ አላማውን ለመፈጸም እግዚአብሔር ሰዎችን ይመርጣል፡፡ በተለያዩ የአገልግሎት መስኮችም ያሰማራቸዋል፡፡

2/ በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በመጻፍ አብረው የሚሄዱትን አመልክት፡፡

1/ መሪው እቅድ አለው 2/ መሪው እቅድ የለውም 3/ መሪው ዓላማው

--- ሀ/ አንድ መሪ ሰዎች ወደቤተክርስቲያን እንዲመጡ ያነሣሣል፡፡

---- ለ/ አንድ መሪ በሚቀጥለው ሳምንት 200 ሰዎች በቤተክርስቲያናችን ስብሰባ

እንዲካፈሉ ማድረግ ነው ይላል፡፡

------ሐ/ በዚህ ሳምንት መትብኘት ያለባቸውን ሰዎች ዝርዝር ለእያንዳንዱ አገልጋይ ይሰጣል፡፡

3/ ይህን ዓረፍተ ነገር ትክክል የሚያደርገውን ፊደሉን በማክበብ አመልክት፡፡ እግዚአብሔር እቅድ አለው ስንል፡-

ሀ/ ሁልጊዜ እግዚአብሔር በአንድ ዓይነት መንገድ ይሠራል ማለት ነው፡፡

ለ/ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የራሱ መንገድ አለው ማለት ነው፡፡

ሐ/ እግዚአብሔር የሚሰራው ያለሰዎች ነው ማለታችን ነው፡፡

መ/ እግዚአብሔር የሚሰራውን አስቀድሞ ያውቃል ማለታችን ነው፡፡

## የመሪነት ማስረጃዎች

### ዓላማ 2፡- መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተካተተ ለመሆኑ ማስረጃዎችን ለማቅረብ

መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ሥፍራ ያለው መሆኑ የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህንን መረዳት የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስንና እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት ሰናጠና ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደረጉትን ነገሮች ስንመለከት እግዚአብሔር በየትኛውም ጊዜ ለተለያዩ ሰዎች አንድ ዓይነት የሥራ እቅድን እንዳልሰጠ ለመረዳት እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር በግለሰቦች አማካኝነት ይሠራል፣ እነርሱም ደግሞ ከጌታ የተቀበሉትን ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎችን ያሳትፋሉ፡፡ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ ሌሎችን ያሳትፋሉ፡፡ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ኃላፊነትን በመስጠት እነዚህ ሰዎች መሪዎች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን በተግባር ለማዋል የሚመሩዋቸውን ሰዎች በቡድን በማደራጀት መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተካተተ የታሪክ ማስረጃ መሆኑ ያመለክታሉ፡፡

በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ በጽሑፍ ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ እቅዱን ለመፈጸም ለመሪነት መመረጣቸውን እግዚአብሔር ለግለሰቦቹ

በሚገልጥላቸው ወቅት ዝርዝር መመሪያዎቹን ጭምር ይሰጣቸዋል። ስለዚህም መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ያላቸው ሥፍራ በሚሰጣቸው መመሪያ ይረጋጣል ማለት ነው።

## የአገልግሎት ስጦታዎች

በኤፌሶን 4፣11-16 እና በሮሜ 12:6-8 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደሚነግረን በቤተክርስቲያን አንዳንዶቹ የመሪነት ሥፍራዎችን እንዲይዙ እግዚአብሔር ሰዎችን ሰጥቷል፣ እነዚህም ሰዎች፦ ሐዋርያት፣ ነቢያት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ናቸው። የእነዚህ ሰዎች የሥራ ድርሻ ደግሞ መሪነት መሆኑ አያጠያይቅም። ከዚህም በተጨማሪ ለመሪነት የሚያበቁ እንደ አስተዳደርና እርዳታን የመሳሰሉ ስጦታዎችን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን አበርክቷል። እነዚህን ስጦታዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የአገልግሎት ስጦታዎች በማለት ይጠሯቸዋል። መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ሥፍራ ያላቸው ስለመሆኑ እነዚህ መንፈሳዊ ስጦታዎች ራሳቸው ማስረጃ ናቸው።

### የመሪነት መስፈርቶችና ኃላፊነቶች

የመንፈሳዊ መሪዎችን መስፈርትና ኃላፊነትን አስመልክቶ ያሉት ማስረጃዎች በብሉይ ኪዳን ለካህናትና ለነገሥታት የተሰጡ መመሪያዎች ናቸው፣ በአዲስ ኪዳንም መሪዎችን በሚመለከት ለመሪነት ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች በግልጽ ተቀምጠዋል። በመሪነት ደረጃ ያሉ ሰዎች በመንፈሳዊ፣ በሞራላዊና በአእምሮአዊ ደረጃ ብቃት ያላቸው ሆነው መገኘት እንደሚገባቸው ሐዋርያት ልዩ ትኩረት ሰጥተውታል።

ስለ እግዚአብሔር ጥሪ፣ ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎችና መሪዎችን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መስፈርቶች በዚህ ክፍለ ትምህርት በቂ ግንዛቤ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎችን በመጠቀስ መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ መካተቱን ማሳየት ብቻ በቂ

አይሆንም። በቤተክርስቲያን በኩል መሪዎችን በመጥራትና በመምራት ዓላማውን በዚህ ምድር ላይ ለመፈጸም በመረጣቸው ሰዎች በኩል እንዴት እንደሚሠራ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ፣ የቤተክርስቲያንና የሌሎችም ክርስቲያናዊ አገልግሎቶች ሕልውና እግዚአብሔር በመሪዎች በኩል እንደ ሠራ ግልጽ የሆነ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል።

4/ ከዚህ በታች አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተሰጥተዋል፣ በጥንቃቄ አንብባቸው። ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት ከፈለግህም ጠቅላላውን ምዕራፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብብ። ከዚያም በኋላ እያንዳንዱን ጥቅስ ቀጥሎ ካሉት ማስረጃዎች ጋር አያይዝ።

1/ ታሪካዊ ማስረጃ　　　3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያዎች

2/ የአገልግሎት ስጦታዎች　　4/ መስፈርቶችና ኃላፊነቶች

---ሀ/ ሂዱና አሕዛብን ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ማቴ 28፣19

---ለ/ ሙሴም ከእሥራኤል ሁሉ አዋቂዎችን መረጠ። በሕዝቡም ላይ ሾማቸው ዘዳ 18፣25።

---ሐ/ ዲያቆናት ልጆቻቸውንና_______________እንደሚገባ ያሳድጉ 1ኛ ጢሞ 3፣12

---መ/ እርሱም አንዳንዶች ሐዋርያት፣ ሌሎችም ነቢያት፣ ሌሎችም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ ኤፌ 4፣11

----ሠ/ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአሔርን መንጋ ጠብቁ 1ኛ ጴጥ 5፣2

---ረ/ ኢያሱም ጽኑአን ሃያላን ሰዎችን መረጠ---- ሰደዳቸው ኢያሱ 8፣3

## የዮሴፍ ምሳሌነት

## ዓላማ 3፡- ከዮሴፍ የሕይወት ልምምድ የመሪነትን መመሪያዎች ለይቶ ለማወቅ

የማሕበረ ምዕመናን የአምልኮ ስፍራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ብዙውን ጊዜ መሪዎች የለፉባትና የደከሙባት ውጤት ናት። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት ሲንቀሳቀሱ ነፍሳት ይድናሉ፣ ክርስቲያኖችም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጋሉ። ይህም አገልግሎት እየዳበረና እየቀጠለ ሲሄድ፣ የመሪነትን አገልግሎት እያሰፋው ይሄዳል። የበለጠ አመራርን የሚጠይቅ ይሆናል።

የመሪነትን ኃላፊነት የሚቀበል ሰው አስተሳሰቡ ለዚያ ስፍራ መሪ ሲሆን የበቃው በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነና ጸሎት እንደሚያስፈልገውም ሊገነዘብ ይገባል። በጥንቃቄ እቅድ በማውጣት ግልጽ መመሪያ ለሌሎች የመስጠት ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት የሚጥረው የጌታ ሥራ እየተሰፋፋ እንዲሄድ የማድረግ ፍላጎት ስለሚያድርበት ነው። ይህን ሁሉ ስንመለከት በውስጣችን የሚያሳድረው ጥያቄ፣ አንድ ክርስቲያን የመሪነትን ኃላፊነት መቀበል ያለበት በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ነው? የሚል ይሆናል።

መሪነትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ስንመረምር ለጥያቄአችን ተገቢውን ምላሽ እናገኛለን። ይህንንም በዝርዝርና በተሟላ መልኩ የምናገኘው ከዮሴፍ ሕይወት ታሪክ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ታሪኩ ከታሪካዊ እውነታ በላይ አድርጎ ይህን ያቆየልን ስለ ሰብአዊ ባሕርይ ስለ መሪነት ምሳሌና ትምህርት እንዲሆነን ነው።

በዚህ ክፍለ ትምህርታችን በምሳሌት የምንከተለው በዚህ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን ብታነበው አይከፋም። ሙሉውን ታሪክ የምታገኘው በዘፍ 39-48 ላይ ሲሆን፣ የጥናታችን ዋና ትኩረት ግን ምዕ 37፣ 39-42፣ 41፣1-25፣ 43፣1-15፣ 24-31፣ 45፣1-15 ላይ ይሆናል።

ቀጥሎ ደግሞ ታሪኩን እጥር ባለ መልኩ በመመልከት የዮሴፍን ባህርይ እናያለን። ዮሴፍ ምን አይነት ሰው ነበር? ለሚለው ጥያቄም ለራስህ መልስ ትሰጣለህ። ለዚህም እንዲረዳን ሦስት ዓይነት ባሕርይ እንመለከታለን። እነርሱም፦ የግለሰቡ ሕይወት ብቃት፣ ሀሳብ፣ ስሜትና ሥራ ናቸው። የአንድ መሪ ስኬት ከነዚህ ሦስት ነገሮች ጋር ይያያዛል።

ስለ መሪነት የተጻፉ አንዳንድ መጻሕፍትን ስታነብ የግለሰቡ ሕይወት ብቃት የመሪነት ተፈጥሮ፣ የመራው ሀሳብና ስሜት የመሪነት ዝንባሌ የመሪው የስራ እንቅስቃሴ ደግሞ የመሪነት ጸባይ በሚሰኝ መልክ መቅረባቸውን

ትመለከታለህ። እዚህ ላይ ግን ሁሉንም እንዲያካትትልን ባሕርይ በሚለው ቃል ነው የምንጠቀመው። ሆኖም እነዚህን አገላለፆች ማወቁ ስለሚጠቅምህ በዚህ ትምህርት ውስጥ አልፎ አልፎ እናነሳቸዋለን።

5/ ተፈጥሮን፣ ዝንባሌንና ፀባይን በሚገባ ለመረዳት እንዲቻል ስለ አንድ መንፈሳዊ መሪ የተነገሩትን ዐረፍተ ነገሮች ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስፈር አብሮ የሚሄደውን አመልከት። 1/ጸባይ 2/ዝንባሌ 3/ ባሕርይ

---- ሀ/ በድሩ ፈገግ እያለ በልበ ሙሉነት ወደፊት ሔደ።

-----ለ/ በድሩ መልካም መሪ እንደሚሆን እምነት አለው።

----ሐ/ በድሩ እውነተኛ ክርስቲያን ነው።

-----መ/ በድሩ በራሱ የሚተማመን ሰው ነው።

-----ሠ/ በድሩ ግልጽ መመሪያ ሰጠ።

## ዮሴፍ በባርነት

ዮሴፍ ያየውን ሕልም በነገራቸው ጊዜ *"ታዲያ እኛ ላይ መሪና አለቃ ልትሆን ታስባለህ?"* በማለት ነበር ወንድሞቹ ያንጓጠጡት። ታላቅ መሪ እንደሚሆን በሕልሙ ቢያይም፣ ወንድሞቹ ግን የነበራቸው አስተሳሰብ እንደሌሎች ብዙ ሰዎች ሁሉ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበር።
የመሪነት ዓላማው የተወሰኑ ሰዎች በሌሎች ላይ የመሰልጠን መብት እንደሚሰጣቸው አድርገው ነበር ያሰቡት።

እግዚአብሔር ስለ መሪነት ያለው ዓላማ ግን እንደዚህ ዓይነት እንዳልነበረ ከዮሴፍ ሕይወት ለመረዳት እንችላለን። ምናልባት ዮሴፍ ሕልሙን ለወንድሞቹ ሲነግራቸው በልቡ ትዕቢት ተሰምቶታል ብለን እናስብ ይሆናል። ሕይወቱን ስንመለከት ግን የምንረዳው ዮሴፍ የሚኩራራና ሌሎችን የሚጫን ዓይነት ሰው እንዳልነበረ ነው። ምናልባትም ከመገረምና ከመደነቅ የተነሣ ሊሆን ይችላል ሕልሙን ለቤተሰቡ የነገራቸው። ለአንድ ዓይነት ዓላማ እግዚአብሔር እንደጠራው ተረድቷል። ይህን ለማለት የምንችለው ወደ መሪነት የመጣው ለራሱ ክብር ላይሆን፣ በእግዚአብሔር

እቅድ መሠረትና ዓላማውን ለመፈጸም እንደሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ ለወንድሞቹ የነገራቸውን ቃል መሠረት በማድረግ ነው።

ምናልባትም ዮሴፍ በወጣትነት ዘመኑ ይህን ላይረዳው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደሚመራው እርግጠኛ መሆኑን ግን መረዳት ይቻላል። መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ***እግዚአብሔርም** <u>**ከዮሴፍ ጋር ነበር**</u>* በማለት ይናገራል። ዮሴፍ ይህን በሚገባ ተገንዝቧል፣ ድርጊቱን ስንመለከት በእግዚአብሔር ምህረት ላይ ያለውን መታመን ለመረዳት እንችላለን።

6/ ከዮሴፍ ሕይወት ልምምድ የእግዚአብሔርን የአሠራር መንገድ ታያለህን? ለምንድነው አግዚአብሔር መሪዎችን የሚመርጠው? መልስህን በተሰጠህ ሥፍራ አስፍር።

ቀናተኞቹ ወንድሞቹ ዮሴፍን ለባርነት ሸጡት፣ ወደ ግብጽ ተወስዶም አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ገዛው። በአጭር ጊዜ ውስጥ መሪ ሆነ፣ ይህም የመካከለኛ አመራር አሰራር ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። ዮሴፍ የተገዛ ባሪያ በመሆኑ የጌታውን ትዕዛዝ መፈጸም ነበረበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የዮሴፍ ጌታ እንደሚገባ ሥራውን ለማከናወን ረዳት ስላስፈለገው መካከለኛ መሪ በመሆን ኃላፊነቱን እንዲሸከም ዮሴፍን መረጠው። ዮሴፍ የጌታውን ቤተሰብና ንብረት የማስተዳድር ኃላፊነት ተሰጠው። መጽሐፍ ቅዱስ ***እግዚአብሔር የዮሴፍን ሥራ ሁሉ አከናወነለት*** ይላል፣ ይህንንም የዮሴፍ ጌታ አስተውሏል። የስኬቱና የመከናወኑ ምክንያት እግዚአብሔር መሆኑን ግልጽ አድርጓል። ***እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር*** ሲባል ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊውን ብርታት ሰጠው ማለት ነው እንጂ ሥራው ቀላል ነበር ማለት አይደለም። ምንም ዓይነት ችግር ወይም ፈተና እንዳይገጥመው አደረገ ማለትም አይደለም። እግዚአብሔር ችግሮቹን የሚወጣበት ጥበብ፣ ድፍረትና እምነት ሰጠው ማለት ነው።

ትልቁ ፈተና የተጀመረው የጌታው ሚስት ከእርሷ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት እንዲያደርግ በተፈታተነችው ጊዜ ነበር። ዮሴፍ ግን *“ሥልጣኔን መከታ በማድረግ እንዲህ ያለውን ነውር አላደርግም፣ ጌታዬ የጣለብኝን እምነት አላጓድልም። በባረከኝ እግዚአብሔር ላይ አላምጽም”* በማለት ፈቃዷን አልፈጸመም። ዮሴፍ ጌታውን የሚያከብርና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ የሚገዛ ሰው እንደነበር በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ሴትየዋ ግን ዘወትር ትንዘንዘው ነበር። ፈቃዷን ባለመፈጸሙም ዮሴፍ ላይ ተቆጣች፣ በመጨረሻም የሐሰት ምክንያት ፈጥራ ወህኒ እንዲገባ አደረገች።

7/ ምንም እንኳ አንድ ሰው በዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ቢሆንም፣ የተዋጣለት መሪ መሆን እንደሚችል ከዮሴፍ ታሪክ መመልከት ይቻላል። ዮሴፍ ነገሩ ሁሉ እንዲከናወን ዋና ምክንያት የሆኑትን ሁለት ነገሮች ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

ሀ/ ከበታቹ ያሉት ሰዎች ሙሉ በሙሉ እንዲታዘዙለት ይፈልግ ነበር።

ለ/ ከእርሱ በላይ ያለውን ባለሥልጣን ያከብር ነበር።

ሐ/ በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ነበር የሚንቀሳቀሰው።

መ/ እግዚአብሔር ሥራውን ቀላል እንደሚያደርግለት ያምን ነበር።

## ዮሴፍ በእስር ቤት

በወህኒ በነበረበት ጊዜ መሪ እንደሚሆን ያለመው ሕልም ጨርሶ እንደማይፈጸም ሳያስብ አልቀረም። የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል፣ ከበታቹ ያሉት ግን በእርሱ ላይ ተነስተውበታል። *“ሰዎች እንደሁ እንደዚህ ናቸው፣ ማመን አይቻልም፣ ታዲያ ምን ዋጋ አለው”* አለማለቱ ራሱ ዮሴፍ እውነተኛ መሪ ለመሆኑ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው።

ዮሴፍ በጣም ብልህ ሰው በመሆኑ ሰዎች ያደረጉበት ትክክል እንዳልነበረ አውቆ እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ አደረገ። በተለያዩ የሕይወት ደረጃ ካሉ ሰዎችም ጋር መልካም ግንኙነት ነበረው። በእሥር ቤት ሆኖ እንኳ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሕልም በዮሴፍ ሕይወት ተጽእኖ ነበረው። እንዲያውም የመሪነት ብቃቱ እንደገና ይበልጥ ጎልቶ በዚያ ስለታየ ምንም እንኳ በዝርዝር ባይገልጽልንም መጽሐፍ ቅዱስ

*“እግዚአብሐር ከዮሴፍ ጋር ነበር፣ ሥራውንም ሁሉ አከናወነለት፣ የወህኒ ቤቱ ኃላፊ በሌሎች እሥረኞችና በወህኒ ቤቱ ላይ ኃላፊ አደረገው”* በማለት ይነግረናል።

እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር መሆኑን የወህኒ ቤቱ ኃላፊ እንዴት አወቀ? አንድ ሰው በወህኒ ውስጥ ሆኖ ከእግዚአብሔር የመሪነት ችሎታ የተሰጠው መሆኑን እንዴት ማሳየት የሚችል ይመስልሃል? የወህኒ ኃላፊው ያየው ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች በአእምሮህ ያዛቸው። ቆየት ብለን የዮሴፍን ታሪክ ስለመሪነት ከተጻፉ ሌሎች መጻሕፍት ጋር ስናነጻጽር ዮሴፍ በሕይወቱ ያሳያቸውን አንድን መሪ ብቁ የሚያደርጉ ባሕርያትን እንመለከታለን።

የንጉሡ ምግብ ቤት ኃላፊና የጠጅ አሳላፊም ከዮሴፍ ጋር አብረው ታስረው ነበር። ኃላፊነት ስለነበረው እነዚህ ሰዎች ከዮሴፍ በታች ነበሩ። አንድ ቀን ከሌላው ጊዜ ይልቅ በጣም አዝነው እንደነበር ተረዳ። ስለዚህም ***ምነው አዝናችኋል?*** በማለት ሲጠይቃቸው የሚያስጨንቁ ሕልሞችን ማየታቸውን ነገሩት። ***“እግዚአብሔር የሕልማችሁን ትርጉም ሊገልጽልን ይችላል”*** አላቸው። ይህም ምን ያህል ከእግዚአያብሔር ጋር የተቀራረበ ሕይወት እንደነበረውና ያለውንም እምነት የሚያሳይ ነው።

እግዚአብሔር የሕልሙን ትክክለኛ ትርጉም ለዮሴፍ ገለጠለትና ትርጉሙን ነገራቸው። የጠጅ አሳላፊው ሕልም ከእሥር እንደሚፈታና ወደ ቀድሞ ሥራው እንደሚመለስ የሚያመለክት ነበር። ዮሴፍም በአጋጣሚው ለመጠቀም እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብ ***“ከእስር ቤት ስትወጣ እኔንም እንዳትረሳኝ፤ ጉዳዬን እንዲያይልኝም ለንጉሱ ንገርልኝ”*** አለው።

ከሁለት ዓመት በኋላ ንጉሱ አንድ አስጨናቂ ህልም አለመ። ሕልሙም እንዲተረጉምለት ምን እንደሆነም ብዙ ሰዎችን ጠየቀ። በመጨረሻም የጠጅ አሳላፊው በእሥር ቤት በነበር ግዜ የገጠመው ትዝ ስላለው ለንጉሱ ስለ ዮሴፍ ነገረው። ዮሴፍንም ከእስር ቤት አወጡትና ሕልሙን እንዲፈታ ንጉሱ ፊት አቀረቡት። እዚህም ላይ ዮሴፍ ስለ ህልሙ ትርጉም ክብሩን ለእግዚአብሔር ሲሰጥ ነው የምንመለከተው።

8/ እግዚአብሔር በነበረው እቅድ መሠረት ዮሴፍን ከእሥር ቤት ለማስወጣት በሌላ እሥረኛ ሕልም ተጠቀመ። ዮሴፍ ስለዚያ ህልም ያወቀው እንዴት ነበር? ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

ሀ/እሥረኞቹ ወደ እርሱ መጥተው ምክር እንዲቀበሉ ዮሴፍ ነገራቸው።

ለ/ ለምን እንዳዘኑ ዮሴፍ እሥረኞቹን ጠየቃቸው።

9/ ለመጨረሻው ጥያቄ የሰጠኸው መልስ ስለ ዮሴፍ ባሕርይ ምን ያመለክትሃል? ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በማክበብ አመልክት።

ሀ/ ከሰዎች ተግባቢ መሆኑን ለ/ ማንነቱን ሰዎች እንዲያውቁለት የሚፈልግ መሆኑን

## ዮሴፍ በድል አድራጊነት

ዮሴፍ ለንጉሡ ***"ሕልሙ የሚያመለክተው የረሃብ ጊዜ እንደሚመጣ ነው"*** አለው። ***"ለሰባት ዓመት ያህል በዚህች አገር በጣም ሰፊ ምርት የሚኖርበት ጊዜ ይመጣል። ከሚያስፈልገው በላይ እህል ይኖራል። ከዚህ በኋላ ደግሞ በዚህ አገር ብቻ ሳይሆን በአካባቢው አገሮች ሁሉ ሰባት የረሀብ ዓመታት ይኖራሉ። ስለዚህም በመልካሞቹ ዓመታት የሚኖረውን የተትረፈረፈ ምርት ማከማቸቱ የችጋር ዓመቶችን ያለምንም ችግር እንድታሳልፍ ይረዳሀል።"***

ንጉሡ በዮሴፍ ጥበብ በመደነቅ ***"የራስህን ሃሳብ ራስህ እንድትፈጽም ዕድል ሰጥቼሃለሁ"*** አለው። ስለዚህም ዮሴፍ ከእስር በመፈታት ከንጉሡ ቀጥሎ የዚያ አገር ባለሥልጣን ሆነ። በእቅዱ መሠረትም ትርፍ እህል በጎተራ በማከማቸት ሁሉም ነገር ልክ እግዚአብሔር በነገረው መሠረት እንዲፈጸም አደረገ። የረሀቡ ጊዜ ሲመጣ የተከማቸውን እህል ለሕዝቡ በማደል ሕዝቡ ከረሃብ ችግር እንዲድን ተደረገ። ከአካባቢው አገሮችም ብዙዎቹ እህል ለመሸመት ይመጡ በነበሩ ሰዎች መካከል የዮሴፍ ዝና እየገነነ በመሄዱ በጣም የተከበረ ሰው ሆነ።

አንድ ቀን ዮሴፍ ከአካባቢው አገሮች ለሚመጡ ሰዎች እህል የመሸጡን ሥራ እየተቆጣጠረ እያለ፣ ዮሴፍ እህል ለመግዛት የመጡትን የገዛ ወንድሞቹን በዓይኑ አያቸው፡፡ የሚያማምሩ ልብሶች በመልበሱና እነርሱ ለባርነት ከሸጡት ዮሴፍ በፍጹም የተለየ በመሆኑ ወንድሞቹ ለይተው ሊያውቁት አልቻሉም፡፡ ዮሴፍ ግን ወንድሞቹ እንደሆኑ ሊያውቃቸው ችሏል፡፡ እንደ አንድ ንጉሥ ወድቀው ሰገዱለት፡፡ በመጨረሻም መሪ እንደሚሆን ያየው ሕልም በትክክል ተፈጸመ፡፡

ዮሴፍ በሥልጣኑ እንዳልተኩራራ፣ ክፉ ያደረጉበትን ወንድሞቹንም መበቀል እንዳልፈለገ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተሰጠው ታሪኩ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ለወንድሞቹ ትምህርት ለመስጠት ነበር አጋጣሚውን የተጠቀመበት፡፡ ይህን ያደረገውም እነርሱን መጥቀም በሚችልበት ሁኔታ በደግነት መንገድ እንጂ ታላቅነቱን በማሳየት አልነበረም፡፡ በመጨረሻም ስሜቱን ለመግለጽ አላፈረም፡፡ በደስታና ለቤተሰቡ ባለው ፍቅር አለቀሰ፡፡ ከሁሉም በላይ በእግዚአብሔር የተመረጠ የተዋጣለት መሪ ያደረገው ደግሞ ዮሴፍ በታላቅ ኃይልና ድል ላይ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር የሚጠቀምበትና መለኮታዊ ዓላማውን የሚፈጽምበት መሣሪያ መሆኑን መገንዘቡ ነበር፡፡

10/ እንደገና ዘፍጥረት 45፣4-13 አንብብ፡፡ አንዳንድ መሪዎች ስላለፈው ስህተታቸውና ጉድለታቸው ሰዎችን ይወቅሳሉ፡፡ ዮሴፍ ወንድሞቹን ወቀሳቸውን? በአጭሩ ግለጽ -------------------------------------------

## የመሪነት ባሕርያት

### ዓላማ 4፡- የመሪነትን ባሕርያት በመረዳት ለመዘርዘርና ምሳሌዎችን ለመስጠት

ስለ መሪነት እንደሚገባ ያጠና ማንኛውም ሰው እንደሚገነዘበው መሪዎች ሁሉ አንድ ዓይነት ባሕርይ አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ በመቶ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ቢኖሩም መሪነትን አስመልክቶ አንድ መጽሐፍ 339 የመሪዎች ባህርያትን በዝርዝር እንዳሰፈረ ይነገራል፡፡ አንዳንድ ጸሐፊዎች ደግሞ መሪነትን በባሕርይ በመተንተን መረዳት አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መወያየቱ ምንም ጥቅም የለውም የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ፡፡

ተፈጥሮ፣ ዝንባሌና ባሕርያት በራሳቸው አንድን የተዋጣለትን መሪ መግለጽ እንደማይችሉ የእኛም እምነት ነው። ይሁን እንጂ በመጠኑም ቢሆን የመሪዎችን ባሕርይ ማጥናቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ግልጽ በመሆኑ ስለ ዮሴፍ ሕይወት በማጥናት ጀምረነዋል። ተፈጥሮው /የሰውየው ማንነት/ ዝንባሌው /ስሜቱና አስተሳሰቡ/፣ ባሕሪው /የሚሰራው ሥራ/፣ በአንድነት ተጣምረው የተዋጣለት መሪ እንዳደረጉት ተመልክተናል።

ለምሳሌም ያህል ዮሴፍ ብልህ እንደነበር ፈርዖን ከተናገረው ከዘፍ 41፣39 ላይ ተረድተናል። እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ በሕይወቱ እቅዱን እስኪፈጽም ድረስ ታግሷልና ታጋሽ እንደነበር መመልከት አያዳግትም። ስለዚህም ብልህነትና ትዕግሥት የአንድ መሪ ባሕርያት ናቸው ማለት እንችላለን። እንዲህም ስለተባለ ማንኛውም ብልህና ታጋሽ ሰው መልካም መሪ መሆን ይችላል ማለታችን አይደለም። በሕይወታችን የመሪነት ባሕርያትን ማዳበር ከፈለግን እግዚአብሔር ብልህነትንና ትዕግሥትን እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን ማለታችን ነው። ብልህና ትዕግሥተኛ ከሆንን ከመሪነት ባሕርያት ጥቂቶቹን አዳብረናል ማለታችን ነው።
መሪነትን አስመልክቶ በርከት ያሉ መጻሕፍት ተጽፈዋል፣ ከእነዚህ ታዋቂ ከሆኑ መጽሕፍት ካገኘናቸው የመሪነት ባሕርያት ጥቂቶቹ እነሆ፡-
1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት ወይም ለሌሎች ማሰብ
2/ እግብ ላይ መድረስና ግብን መምታት
3/ ለሥራው ወይም ለኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት
4/ ስሜታዊ መረጋጋት ወይም ወላዋይ አለመሆን
5/ በቡድን መሥራት 6/ ሥልጣንን ለሌሎች ማካፈል
6/ቃልና ድርጊትን ማጣመርና እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት ነው።

እነዚህን ባሕርያት አንድ በአንድ ስንመረምር፣ ስለመሪነት በተጻፉ ሌሎች መጻህፍት ብቻ ሳይሆን በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳ የአንድ መልካም ክርስትያን ባሕርያት ሆነው መቅረባቸውን እንመለከታለን። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ የሚከተሉትን ባሕርያትንም ያካትታል።

1/ የእግዚአብሔር ጥሪ ወይም ተልእኮ

2/ የክርስቶስን ፍቅር አስተላላፊ አሸንዳ መሆንን መገንዘብ

3/ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መደገፍ

4/ በመንፈሳዊ ሕይወት ለሌሎች አርአያ ሆኖ መኖር

11/ እነዚህን ዝርዝሮች እንደገና አንብብ፣፡ ከዚያ በኋላ በቃልህ በጽሑፍ አስፍር፡፡ በጸሎትና በጾም ጊዜ ሁሉ በልብህ አሰላስላቸው፣ የሥራህ ሁሉ መመዘኛም ይሁኑ፣ ይህም መልካም መሪ ለመሆን ይረዳሀል፡፡

አሁን ደግሞ አብዛኛዎቹ ምሑራን በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን ሰባት የመሪነት ባሕርያት እንመለከታለን፡፡ ዋናው ዓላማችን አንድ መሪ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር ምላሽ ለመስጠት ሲሆን፣ ከተዋጣለት መሪ ባሕርያት ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦችንም በሚቀጥሉት ክፍለ ትምህርቶች በስፋት በመመልከት በቂ ግንዛቤ ለማግኘት እንሞክራለን፡፡

**1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት**

አንድ መሪ ከራሱ እይታ አንጻር ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ከሌሎችም ሰዎች አንጻር ያያል፣ የሌሎችን ስሜት ለመረዳት ይሞክራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ***"ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው"*** ይላል /ሉቃስ 6፣31/ ፡፡ ይህም <u>ወርቃማው ትእዛዝ</u> በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊም ***"ከእነርሱ ጋር እንደታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፣ የተጨቆኑትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ"*** ይላል /ዕብ 3፡3/፡፡ አዛኞችና ሩህሩሆች እንድንሆን የሌሎችንም ሸክም እንድንካፈል ተነግሮናል /1ኛ ጴጥ 3፡8፣ ገላ 6፣2/፡፡ የሌሎችን ስሜት መረዳትና ለሌሎች ማሰብ ለክርስቲያናዊ ሥራ እና አገልግሎት በጣም አስፈላጊ ሲሆን፣ ይልቁንም ደግሞ ለአንድ መንፈሳዊ መሪ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2. ግብ ላይ መድረስ

አንድ መሪ ዓላማና ግብ ይኖረዋል፣፡ ዓላማ ላይ ለመድረስና ግቡን ለመምታት በርትቶ መሥራት አለበት፡፡ መንፈሳዊ መሪ ለራሱና የእግዚአብሔርን ዓላማ በመፈጸም ረገድ አብረውት ለሚሠሩ ሁሉ ዓላማና ግቡን ቁጭ አድርጎ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ሲገልጥ ***"ሽልማቴን ለማግኘት በፊቴ ወዳለው ግብ እሮጣለሁ"፡*** ብሎ በገጽ 15 ይናገራል፡፡ ለፊልጵስዩስ በጻፋቸው መልእክቶቹ ሁሉ ዓላማውን እግቡ የማድረስ ሀሳብና ፍላጎት እንዳለው በግልጽ ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔርን "ዘላለማዊ ዓላማ" ለመፈጸም "ያለውን ዓላማ"፣ ምክንያትና ፍላጎት በተደጋጋሚ ይገልጻል፣ ኤፌ 3፣10-11፣ እና 2ኛ ጢሞ 2፣10 ለምሳሌ ያህል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 3. ብቁ ሆኖ መገኘት

አንድ መንፈሳዊ መሪ ለሥራውና ለኃላፊነቱ ብቁ ሆኖ መገኘት ሥራውን ጥራት ባለው መንገድ በማከናወንና ዓላማውን እግብ ለማድረስ እንዲችል ይረዳዋል፡፡ ሌሎችንም በሥራቸው ለመርዳት የሚያስችለውን መንገድ በመቀየስ ከእርሱ ጋር አብረው ተግተው እንዲሠሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ራሱንም ሆነ ሌሎችን የሚመዝንበትና የሚለካበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መመሪያዎች በሚገባ በማወቅና በመከተል መልካም አርአያ በመሆን ኃላፊነቱን በትጋት በመወጣት ሌሎቹም እንደእርሱ ኃላፊነታቸውን በትጋት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ ዘጸ 35፣36፣ ምሳ 12፣ 27፣22፣ 29:31፣10-30፣ 2ኛ ጢሞ 2፡ ያዕ2፣ 14-16፣2 ጴጥ 1፣5-10 ተመልከት፡፡

## 4. የስሜት እርጋታ

የስሜት መረጋጋት ስንል ወላዋይ አለመሆን ማለታችን ነው፡፡ አንድ መንፈሳዊ መሪ አስተሳሰቡን መጠበቅ አለበት፡፡ ለሚያደርገው ሁሉ ምክንያት ያለውና በራሱ የሚተማመን ረጋ ያለ ሰው መሆኑ ወሳኝ ነው፡፡ በቀላሉ የማይናደድና የራሱ ፈቃድን ብቻ ተከትሎ የሚሄድ እንደዚሁም በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ ሰው መሆን

የለበትም። ሁኔታዎች ሁሉ እርሱ እንደጠበቃቸው ሳይሆኑ ሲቀሩና የተለያዩ ችግሮች ሲገጥሙት ሰላማዊ በሆነና ረጋ ባለ መንፈስ ለገጠሙት ችግሮች መፍትሔ የሚፈልግ ሰው መሆን አለበት። ዳዊት በመዝ 27፡14 ላይ ይህን በሚገባ የሚገልጸው በእግዚአብሔር እንደሚታመን ሰው ሆኖ ***"በርታ ልብህም ይጽና"*** በማለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በኤፌ 4፡31፣ በ2ኛ ጢሞ 4፡5 በ1ኛ ጴጥ 4፡7 ላይ ስለዚሁ የተሰጠውን ምክርና መመሪያ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

## 5. በቡድን መስራት

አንድ መሪ ራሱ የቡድኑ አካል ወይም አባል እንደሆነ ጠንካራ እምነት ሲኖረው፣ ከሌሎች ጋር የሥራ ኃላፊነትን በመጋራት አብሮ መሥራት ደስ ያሰኘዋል። ይህ ዓይነቱ አሠራር በ1ኛ ቆሮ 12ና በኤፌ 4 ላይ አካል ምሳሌነት የተገለጸ ሲሆን፣ አንድ መንፈሳዊ መሪ ማሰብ ያለበት እያንዳንዱ የአካል ክፍል ተደጋግፎና ተሳስቦ የመሥራት ኃላፊነት እንዳለበት ሊሆን ይገባል(ኤፌ 4፣16)። እያንዳንዱ የአካል ክፍል ተደጋጋፊ በመሆኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት ሲሠሩ ውጤታማ የሆኑ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ። ስለዚህም መሪው ከእንደዚህ ዓይነቱ ከሌሎች ተነጥሎ ምንም ውጤታማ መሆን ስለማይችል ከእነዚህ አንዱ መሆኑን አስቀድሞ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## 6. ሥልጣንን ለሌሎች የማካፈል ችሎታ

አንድ መሪ በመልካም ሁኔታ ከሌሎች ጋር ሲሠራ፣ እንደ መካከለኛ መሪ ሆኖ ሥፍራውን ሲቀበል ነው። ሌሎች በታማኝነትና በአክብሮት የሚከተሉት ረዳት እንዲሆኑትም የሚተማመንባቸውን ረዳት እንዲሆኑት ሌሎችን በመሪነት ደረጃ ቢመርጥም፤ የስራው አይነት ከበላይ ሆኖ እንዲቆጣጠራቸው ሊያስገድደው ይችላል። ይህ አሠራር ከቡድን አሠራር ጋር በጣም የተያያዘ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ትህትና፣ መተማመንና መከባበር ናቸው። እውነተኛ መሪ ለሌሎች ከፍተኛ አክብሮት ያለው ሰው መሆን አለበት። የእግዚአብሔር አሠራር ከፍጥረቱ ሁሉ ክቡር በሆነው በሰው ልጅ አማካይነት መሥራት እንደሆነ ለመሪነት የተጠራው ሰው በሚገባ በመረዳት

የስጦታዎቹና የጥሪው ዋና ዓላማ በእርስ በርስ መከባበር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም አስቀድሞ ሊከበር የሚገባው እግዚአብሔር ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ 5፡21 ላይ ስለዚሁ ምክር ሲሰጥ፡- *"እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ"* ጳውሎስ ለሥራ ባልደረቦቹና ረዳቶቹ ያለውን አክብሮት ደጋግሞ ይገልጣል፣ ይህንንም የሚያደርገው ለክርስቲያን መሪዎች ምሳሌ ለመሆን ነው፡፡ ጳውሎስ ለሌሎች ያለውን አክብሮት ከገለጸባቸው ክፍሎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፊል 4፣1-3 ፡ ቆላ 4፣7-14 እና 1ኛ ተሰ 1፡2-4፡፡

### 7. ቃሉን በተግባር በመተርጎም እምነት የሚጣልበት

አንድ መሪ ቃሉን የሚጠብቅና ሌሎችም የሚታመኑበት ዓይነት ሊሆን ይገባል፡፡ ከሌሎች የሚጠብቀውን በግልጽነትና በቅንነት በማስተላለፍ እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግም እገዛ ያደርጋል፡፡ በአንድ ወቅት በስሜት ተነሳስቶ የተናገረውን በሌላ ጊዜ የሚዘነጋ ወይም ለሌሎች አስቀድሞ ሳያስታውቅ ሃሳቡን የሚለውጥ ዓይነት ሰው መሆን የለበትም፡፡ ቃሉን ይጠብቃል፣ ለሌሎች ለሰጠው መመሪያም እርሱ ራሱ ታዛዥ መሆኑንም በተግባር ያሳያል፡፡ ቃልና ሥራን ማጣመር እንዲሁም እምነት የሚጣልበት መሪ ሆኖ መገኘት ለክርስቲያናዊ አገልግሎት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ኢየሱስ ራሱ ሲገልጽ፡- *"ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኃላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም"* ይላል፡፡ ጳውሎስም ይህንኑ በማጽናት በ1ኛ ቆር15፣58 ላይ፡- *"የምትደላደሉ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታም ሥራ የሚበዛላችሁ ሁኑ"* በማለት ይናገራል፡፡ በተጨማሪም በገላ 5፡1ና በኤፌ 4፡14 ይህንኑ አስመልክቶ የተናገረውን ተመልከት፡፡

12/ እዚህ ላይ ስለ ዮሴፍ ዝንባሌና ባሕርይ ሰባት ነጥቦች ተሰጥተዋል፡፡ እያንዳንዳቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከላይ ከዘረዘርናቸው ባሕርያት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ትክክለኛውን ባሕርይ የሚገልጸውን ቁጥሩን ከዐረፍተ ነገሮቹ ፊት በማስቀመጥ አመልክት፡፡

----ሀ/ ዮሴፍ ለፈርያን፣ ሰባት ዓመት የሚበቃ እህል እናጠራቅማለን አለው፡፡

---ለ/ ምንም እንኳ ወይን ጠጅ አሳላፊው ቢረሳውም ዮሴፍ አልተናደደም፡፡

----ሐ/ ሥጋ ዘመዶቹን አልረሳቸውም፣ ለሕዝቡ መልካም ነገር ማድረግ እንዳለበትም ያውቃል፡

---መ/ ምንም እንኳ ያለ በደሉ ግፍ ቢደርስበትም በእግዚአብሔር የሚተማመንና በታማኝነትም ሥራውን ይሰራ ነበር፣

---ሠ/ ዮሴፍ ወንድሞቹ እንደተጸጸቱ ስላወቀ ሊያጽናናቸው ሞከረ፣

---ረ/ አሳዳሪ ጌታውና የወህኒው ኃላፊ ዮሴፍ ነገሮችን በትክክል ያደርግ እንደነበር አዩ፡

----ሰ/ ለአሳዳሪ ጌታው፣ ለወህኒ ኃላፊና ለንጉሡ ታዛዥና አክባሪ ነበር፡

ስለ አንድ መሪ ተፈጥሮ፣ ዝንባሌና ጸባይ ለመረዳት ከመጽሐፍ ቅዱስ የዮሴፍን ታሪክ በሚገባ ተመልከተናል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ምሁራን የመሪዎች ባሕርያትን በተመለከተ ያሰባሰቧቸውን ዝርዝር መሠረት በማድረግ የአንድ መንፈሳዊ መሪ ባሕርይና ከዮሴፍ ሕይወት ሊከተለው የሚገባ ምሳሌ ምን መሆን እንዳለበት በቂ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

ከጌታና ከመጋቢው በታች ሆኖ የሚሰራ በመሠልጠን ላይ መካከለኛ መሪ በትሕትና ላይ የተመሰረተ ዝንባሌ ሊኖረው ይገባል፡፡ ከወንድሞቹም ሆነ ከሌሎች ወጣቶች የላቀ ደረጃ ስላገኘ መኩራራት የለበትም ፡፡ እንደ ዮሴፍ አንድ እውነተኛ መሪ ከበላዩም ሆነ ከበታች ያሉትን ያከብራል፡፡ መልካም መሪ ለሌሎች ከሚሰጠው መመሪያ የበለጠ ያደርጋል፡፡ ከሌሎች ጋር ሆኖም ይሠራል፡፡ የሌሎችን ጥፋት ይቅር ይላል፡፡ በተለያየ ምክንያት ቢያሳዝኑትም ሰዎችን ይወዳል፡፡ አንድ ቀን የተሻለ ውጤት እንደሚያስመዘግቡም ይጠብቃል፡፡ ዮሴፍ ለወንድሞቹ እንዳደረገው ሁሉ የጌታን ፈቃድ ለመፈጸም እንዲችሉ ወደ መንፈሳዊነት ይመራቸዋል፡፡

## የሙከራ ፈተና

ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ነው የምትለውን ፊደል ክበበው፡

1/ "መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ" የሚገልጸው፡-

ሀ/ በመንፈሳውያን ፍጥረቶች አማካኝነት ዓላማውን ይፈጽማል፡፡

ለ/ ዓላማውን የሚፈጽምበት የራሱ ልዩ መንገድ አለው፡፡

ሐ/ ፈቃዱን ለመፈጸም በሰዎች መጠቀም ሞኝነት እንደሆነ ያውቃል፡፡

2/ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ በጣም አስፈላጊው ክፍል ሥራው

ሀ/ በቅኖችና መልካምን ለማድረግ ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች መሰራቱ ነው

ለ/ ዓላማውን ለመፈጸም ኃይልና ማስተዋል ባላቸው መላእክት መጠቀሙ

ሐ/ ሥራውን እንዲሰሩለት በሚያስገድዳቸው ሰዎች መጠቀሙ ነው

3/ ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት የሚያሳየው፡-

ሀ/ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ እርሱም ዓላማውን የሚለውጥ መሆኑን

ለ/ የገዛ ዓላማውና አሠራር መንገዱ እሥረኛ መሆኑ

ሐ/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ አስተማማኝ በሆነ መንገድ መንቀሳቀሱን

4/ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር መሪነት በእግዚአብሔር እቅድ የተካተተ ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡ ማስረጃ ሊሆን የማይችል የትኛው ነው?

ሀ/ መሪነትን አስመልክቶ በመጽሐፍ የተዘረዘሩት መስፈርቶች፣ ኃላፊነቶች

ለ/ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ቀጥተኛ ጥሪና መመሪያዎች

ሐ/ የማሕበረሰቡ ፍላጎት መሪዎች እንደሚያስፈልጉ መግለጹ

5/ በመንፈሳዊ መሪነት ውስጥ የመካከለኝነት አመራር በጣም መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የመካከለኝነት አመራር ስንል፡-

ሀ/ መሪዎች ጌታን ብቻ ይከተላሉ፡፡

ለ/ ሌሎች መሪዎችን ይከተላሉ፣ ስለዚህም ሁሉም የጌታ ተከታዮች ናቸው፡፡

ሐ/ የራሳቸውን ፍላጎትና ጌታን ይከተላሉ፡፡

6/ በዚያ የመንግሥት ባለሥልጣን ቤት በሚያገለግልበት ወቅት ከዮሴፍ ሕይወት የተመለከተናቸው ሁለት የመሪነት ባሕርያት፡-

ሀ/ ባለሥልጣንን ማክበርና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት፡፡

ለ/ ሁሉን ለማስደሰትና በሁሉም ታዋቂ የመሆን ፍላጎት ነበረው፡፡

ሐ/ በሥልጣኑ ያለአግባብ ይጠቀም ነበር።

7/ ዮሴፍ በእሥር ቤት ሳለ በሌሎች የተሳካላቸው መሪዎች የሚታዩ ባሕርያት ታይተውበታል። በእግዚአብሔር ላይ የማያወላውል እምነት፣ በአገልግሎት ታማኝነትና፡-

ሀ/ ነገሮች ሁሉ ወደ መልካምነት እንደሚለወጡ የነበረው ተስፋ

ለ/ ሁኔታዎች ላልሰመሩላቸው ሰዎች መራራት

ሐ/ ሰዎችን መቅረብና ለሌሎች ማሰብ

መ/ ሰዎች እምነት የማይጣልባቸው መሆናቸውን መረዳቱ

8/ ዮሴፍ ብዙ የችግር ዓመታትን ካሳለፈ በኂላም ወንድሞቹ መጥተው ሰገዱለት፣ በዚህ ጊዜ ዮሴፍ ያሳያቸው የመሪነት ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ **"ቀድሞውኑ ነግሬያችሁ አልነበረም?"** በሚል መንፈስ ወንድሞቹ ላይ ታበየ፣ያለፈ ጥፋታቸውን ሊያሳስባቸውም ሞከረ።

ለ/ ብቃት ክህሎት፣ የማያወላውል የመሪነት ውሳኔና ፍትህ

ሐ/ የእግዚአብሔርን እቅድ በመረዳቱ ርሕራሄ ፣ ይቅር ባይነትና ፍቅር አሳያቸው።

መ/ በቀል የእግዚአብሔር መሆኑን፣ የእግዚአብሔርን እቅድ መረዳቱንና የሰዎችን ደካማነት መቀበሉን።

9/ ያለአንዳች ተስፋ መቁረጥ ለሥራው ያሳየው ትጋት ለፈርዖን ከሰጠው ብልህ ምክር ጋር በአንድነት ሆነው ከዮሴፍ ባሕርያት የሚያሳያቸው ሁለት ነገሮች፡-

ሀ/ ብቃትና አዳዲስ ሃሳቦችን አፍላቂ መሆኑን

ለ/ ለእግዚአብሔር መሰጠቱንና የፖለቲካ እውቀቱን

ሐ/ ታጋሽነትና የአስተዳደር ችሎታውን መ/ ትዕግሥቱንና ብልህነቱን

10/ ዮሴፍ አንድ የተዋጣለት መሪ ሲኖረው የሚገባውን ዝንባሌ አሳይቷል። የመከራው ጊዜ ከተፈጸም በኂላ ከአንደኛው በቀር ሁሉንም አድርጓል፡-

ሀ/ መኩራራትና በቀልን አልፈለገም

ለ/ ሌሎችን ለመርዳት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መሳሪያ መሆኑን ተረዳ

ሐ/ በልጅነት ዘመኑ ያያቸውን ሕልሞችና የተነገሩለትን ትንቢቶች ለወንድሞቹ አሳሰባቸው።

11-17/ ለሚከተሉት የመሪነት ባሕርያት ገለጻ ስጥ። በዚህ ትምህርት የተዘረዘሩት ሰባቱ የመሪነት ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው።

- የሌሎችን ስሜት መረዳትና ለሌሎች ማሰብ /Empathy/
- እግብ ላይ መድረስ /ግብን መምታት/
- ለሥራው ወይም ለኃላፊነት ብቁ ሆኖ መገኘት
- የስሜት እርጋታ /ወላዋይ አለመሆን/
- በቡድን መሥራት- ሥልጣን ለሌሎች ማካፈል
- ቃልና ድርጊትን ማጣመርና እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት

11/ ምንም እንኳ በእርሱ እቅድ መሠረት ሁኔታዎች ባይሳኩለትም አንድ መሪ አንገቱን ቀና አድርጎ የሚሄደው ለምንድነው?--------------------------------

12/ ------------ ከበላዮቻቸውና ከበታቾቻቸው ካሉት ሁሉ ጋር አብረው ለመሥራት የሚያስችል የመሪዎች ችሎታ ነው፡፡

13/ የሌሎችን ስሜት ማወቅ፣ ነገሮችንም ከራሱ እይታ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም እይታ የማየት ችሎታ ------------- ይባላል፡፡

14/ አንድ መሪ ቃሉን የሚጠብቅ፣ ለሌሎች ለሚሰጠው መመሪያ እርሱ ራሱ የሚታዘዝ፣ ሀሳቡንም በግልጽ ለሌሎች ማካፈል የሚችልና ሌሎችንም የሚረዳው ------- ------ ስለሆነ ነው፡፡

15/ ፊት ለፊቱ ግብ የሚያኖርና ሀሳቡ ላይ እስኪደርስ ድረስ ተግቶ የሚሠራ መሪ------ ---- ነው፡፡

16/ አንድ መሪ የቡድኑ አካል እንደሆነ ሲያስብ፣ ለሌሎች ፍላጎት ሲጠነቀቅ፣ ከሰዎች ጋር መሥራትም የሚያስደስተው ሆኖ ከተገኘ ያ ሰው ----------- ነው ማለት ነው፡፡

17/ በትጋት የሚሠራ፣ ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስችል ዕውቀት ያለው፣ ሌሎችን የሚረዳበት መረጃ ማሰባሰብ የሚችል፣ ራሱንና ሌሎችን የሚመዝንበት ሚዛን ያለው መሪ------- ይባላል፡፡

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

የመመዘኛዎቹ መልሶች የተቀመጡት በቅደም ተከተላቸው መሠረት ያልሆነበት ምክንያት የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ወዲያው እንዳታይ ለማድረግ ነው፣

7/ ለ) ከእርሱ በላይ ያሉ ሰዎችን ሥልጣን ያከብራል

ሐ) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰራ

1/ ሐ) አንድን ዓላማ ፈጸመ 8/ ለ) ዮሴፍ ወደ እሥረኞቹ ሄደ።

2/ሀ 2/ መሪው እቅድ የለውም ለ/ 3) መሪው ዓላማ አለው ሐ/ 1) መሪው እቅድ አለው

9/ ሀ) ከሌሎች ጋር መግባባት የሚችል ሰው ነበር።

3/ለ/ እግዚአብሔር ዓላማውን የሚፈጽምበት የራሱ ልዩ መንገድ አለው፣

መ/ እግዚአብሔር የሚሠራውን አስቀድሞ ያውቃል።

10/ እንዳይረበሹ ነገራቸው፣ የእግዚአብሔርን እቅድ በማሳሰብ አጽናናቸው።

4/ሀ) 3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያ ለ/1) ታሪካዊ ማስረጃ

ሐ/4) መስፈርቶችና ኃላፊነቶች መ/2) የአገልግሎት ስጦታዎች

ሠ/3/ ቀጥተኛ ጥሪ እና መመሪያ ረ/1) ታሪካዊ ማስረጃ

11/ "የመሪነት ባሕርያት" ከሚለውን ዝርዝር ጋር መልሶችህን አስተያይ

5/ ሀ/3) ፀባይ ለ/2) ዝንባሌ ሐ/1) ተፈጥሮ መ/1) ተፈጥሮ ሠ/ 3) ፀባይ

12/ሀ2/ እግብ ላይ መድረስ ለ/4) የስሜት መረጋጋት ሐ/5) የቡድን ሥራ

መ/7) ቃልና ድርጊትን በማጣመር እምነት የሚጣልበት ሆኖ መገኘት

ሠ/1/ የሌሎችን ስሜት መረዳት ረ/3) ብቁ ሆኖ መገኘት

ሰ/6/ ሥልጣንን ለሌሎች ማካፈል

6/ ዓላማውን ለመፈጸም እግዚአብሔር መሪዎችን ይመርጣል።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## መሪዎች ሰዎችን ያደንቃሉ

በአንደኛው ክፍለ ትምህርት ላይ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የመሪነት ቦታ እንዴት እንደሆነ በመግለጽ፣ በመሪነት ስፍራ ላይ ሆነው የተሳካላቸውን ሰዎች ባሕርያት በመዘርዘር ተመልክተናል። ከዚያም ከመጽሐፍ ቅዱስ የዮሴፍን ምሳሌነት በመውሰድ ለመንፈሳዊ መሪነት ስለተሰጡ መስፈርቶችና ኃላፊነቶች በመጠኑ በመዳሰስ ተገቢውን ግንዛቤ ለማግኘት ችለናል።

በዚህ በሁለተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የምንመለከተው የሙሴን ምሳሌነት በመከተል አንድ መንፈሳዊ መሪ ከሌሎች ጋር ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት እንዴት መሆን እንዳለበትና አብረውት ለሚሠሩ ሰዎች የሚኖረው አስተያየት ምን መሆን እንዳለበትና የመሪነትን ዘዴ እንዴት ማዳበር እንደሚችል እንመለከታለን።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የሙሴ ምሳሌነት
- መሪዎች ስለ ሰዎች ምን እንደሚያምኑ
- የመሪነት ዘዴ እንዴት ማዳበር እንደሚቻል

---

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የሙሴን ሕይወት መሠረት በማድረግ የመሪነትን መመሪያዎች መግለጽና እነዚህ መመሪያዎች በተግባር የሚተረጎሙበትን መንገድ ለይቶ ማወቅ።

- አንድ መሪ አብረውት ከሚሠሩት ሰዎች ጋር ያለው እምነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ።
- የመንፈሳዊ መሪነትን መመሪያዎች አስመልክቶ የተለያዩ የመሪነት ዘዴዎችንና ባሕርያትን መገምገም።

----------------------------------------------------------------------

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1/ በትምህርት 1 ላይ እንዳደረግኸው ሁሉ የክፍለ ትምህርቱን ዓላማዎች አንብብ።
2/ ከዘጸ 2-7፣11-18፣ 35-36 የሙሴን ታሪክ አንብብ። በዚህ ትምህርት የምንጠቀምባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ የምንባብ ክፍሎች ዘጸ 2-3፣ 4:1-17፣31-34፣10-31፣15:22-25፣16፣1-11፣17፣1-15፣19፣9-26፣ 32፣1-14፣ 35፣1-36፣1-7 ላይ የሰፈሩት ናቸው።
3/ ክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ በጥንቃቄ ካጠናህ በኋላ በቅደም ተከተል የሰፈሩትን ጥያቄዎች መልስ:: ከዚያም በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት ጋር በማስተያየት ትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል።

## የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ- የሙሴ ምሳሌነት

### ዓላማ 1 ሙሴ ለመሪነት እንዴት እንደተጠራና የሰጠውን ምላሽ ለመግለጽ

የሙሴ ሕይወት ታሪክ የመሪነት ታሪክ በመሆኑ፣ ስለ መሪነት ከተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ እግዚአብሔር ከመሪዎች ጋር፣ መሪዎች ደግሞ ከሰዎች ጋር ያላቸውን የቅርብ ግንኙነት ለማጥናት የእርሱን ያህል የሚረዳ የለም።

እንደብዙዎቹ የጌታ አገልጋዮች ሙሴም ስለ ሰዎች መቆርቆር የጀመረው ገና ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ ነበር። ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ያሳስበዋል፣ እነርሱን ለመርዳት አንድ ነገር ማድረግ እንዳለበትም ያስባል። በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ግልፍተኝነት ያለበት ነበር። ከእግዚአብሔር ምሪት አለመጠየቁም እውነት ነው።

የፍትሕ መዛባትን በራሱ ጥረት ለማስወገድ ነበር የፈለገው፡፡ ይህም ሙከራው ሰው እንዲገድል አድርጎታል ዘጸ 2፡11-15፡፡  አገር ጥሎ በኮበለለበት ጊዜ እንኳ ይህ ፍትሕ የማስከበርና ለሰዎች የመቆርቆር ስሜቱ አብሮት ነበር፡፡ ይህንንም ለመገንዘብ የምንችለው በዘጸ 2፣16-19 ላይ ውኃ ለመቅዳት መጥተው የነበሩትን ልጃገረዶች እረኞች ባጉላሉዋቸው ጊዜ ካሳየው ተቆርቋሪነት ነው፡፡ ይህም መልካም ሥራው ከዮቶር ጋር ስለአቀራረበው ልጁን ለማግባት በቃ፡፡ አንድ ቀን የአማቹን በጎች በመጠበቅ ላይ እያለ ቁጥቋጦው በሚያስገርም ሁኔታ ሲነድ አየውና፣ በቅርብ ለመመልከት ተጠጋ፡፡ ሙሴ የተረጋጋና የሁኔታዎችን ምንነት ለማወቅ የሚፈልግ፣ ያልተለመዱ ክስተቶችንም ቀረብ ብሎ መረዳት የሚወድ ሰው ነበር፡፡

ከሚነድደው ቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር ***"ሙሴ፣ ሙሴ"*** በማለት ጠራው፡፡ ሙሴም እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመስማት ዝግጁ ሆኖ ***"እነሆኝ"*** በማለት መልስ ሰጠ፡፡ እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥለት ግን በአክብሮታዊ ፍርሐት ፊቱን ሸፈነ፡፡ ጌታም ***"የሕዝቤን መከራ አይቼአለሁ፣ መከራቸውንም ተመልክቼአለሁ፣ ስለዚህም ከዚያ ምድር ላወጣቸው መጥቻለሁ፡፡ ሕዝቤን ከግብጽ እንድታወጣ ወደ ፈርዖን እልክሀለሁና ሂድ"*** አለው፡፡

ከዚህ ላይ እንደገና የምንመለከተው የእግዚአብሔርን የአሠራር ዘዴ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዓላማ ስላለው፣ ዓላማውን ለመፈጸም መሪ መረጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ግን ሙሴ እንደበፊቱ ግልፍተኛ አልነበረም፣፡ የራሱን ደካማነት መረዳት ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ዓላማ ካሰበውና ከጠበቀው በላይ እንደሆነ ተገነዘበ፡፡ እንዲህ ያለውን ትልቅ ዓላማ የከብቶች እረኛ የሆነ እንደ እርሱ ዓይነት ሰው ሊወጣው የሚችል መስሎ ስላልታየው፡- ***"ይህን ለማድረግ እኔ ማነኝ? አንተ እንደላክኸኝስ እንዴት አስረዳቸዋለሁ"?*** በማለት ጠየቀ፡፡

አንድ መሪ ሙሉ ሥልጣን ሊኖረው እንደሚገባ ሙሴ ተረዳ፡፡ ጌታም በድንቆችና በተአምራት መልክ ሥልጣንን እንደሚሰጠውና አብሮት እንደሚሆን እንደዚሁም በሥራው እንደሚረዳው ለሙሴ ቃል ገባለት፡፡ የነገረው ዓላማውን ለመፈጸም

እንዲችል እንደሚረዳው እንጂ ለግል ክብሩ ሽልማት እንደሚያገኝ አልነበረም። ይህም ሁሉ ሆኖ ሙሴ ያለው በማመንታት ላይ ነው።

***"አጥርቼ መናገር አልችልም፣ እባክህን ሌላ ሰው ላክ"*** አለ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ። ትሕትና መልካም ነው። ትሕትና ግን በእግዚአብሔር ካለን እምነት ጋር መመጣጠን አለበት። እግዚአብሔር ተስፋውን እንደሚፈጽም ልንታመንበት ይገባል። አሮን በእርሱ ምትክ ሆኖ እንደሚናገርለት እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው። ሙሴና አሮን የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰበሰቡና የእግዚአብሔርን እቅድ ይነግሩዋቸዋል። ይህን በመሰለ ሁኔታ እግዚአብሔር ለሙሴ መመሪያዎችን እንደሰጠው እያንዳንዱ መሪ ኃላፊነቱን ይረዳል፣ ይቀበላል። አሁን ሙሴ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለእግዚአብሔር ሰጥቷል:: መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ***"ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ"*** ይላል።

1/ ከፊት ለፊት ያለውን ፊደል በመከበብ እውነተኛ የሆነውን መግለጫ አመልክት።

ሀ/ የእግዚአብሔርን ጥሪ እስከሰማበት ሙሴ ለሕዝቡ ደንታ አልነበረውም።

ለ/ እግዚአብሔር ለሙሴ የመሪነት ሥራን ከመስጠቱ በፊት እንኳ ለህዝቡ ያስብ እንደነበር ገልጧል።

መ/ ትሕትናና በእግዚአብሔር መታመን ለአንድ መሪ አስፈላጊ እንደሆነ ከሙሴ ልምምድ መገንዘብ እንችላለን።

ሠ/ የሙሴ መሪነት በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ የተመሠረተ ነበር።

ረ/ ታላቅ ኃላፊነት እንደተቀበለ ሙሴ ተረድቷል።

**እነዚህን ሰዎች ምን ላድርጋቸው?**

## ዓላማ 2 ዮቶር ለሙሴ ከሰጠው ትምህርት ከሰዎች ጋር ለመሥራት አራት መንገዶችን ለመጥቀስና ተግባራዊ የምናደርግባቸውን መንገድ ለማሳየት

የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ምሪት በመቀበሉ ሙሴ የእሥራኤልን ሽማግሌዎችንና ሕዝቡን ከግብጽ ባርነት እንዲወጡ አዘጋጃቸው። የፈርዖን ልብ ደነደነ። እግዚአብሔርም

በምድሩ ላይ መቅሰፍት አወረደ። በመጨረሻም ፈርዖን ሕዝቡ ከግብጽ እንዲወጡ ፈቀደ ዘጸ 12፣31።

ሴቶችና ሕጻናትን እንዲሁም የቤት እንስሳትን ጨምሮ /ስድስት መቶ ሺህ/ ወንዶች ሰዎችን መምራት ምን ያህል ከባድና አስቸጋሪ እንደሆነ መገመት አያዳግትም/ዘዳ 12፣37/። በአገር አቀፍ ወንጌል ዘመቻ ስብሰባ በማዘጋጀት ተሳትፈህ የምታውቅ ከሆነ ያንን ያህል ሕዝብ መምራት ለሙሴና ለረዳት መሪዎቹ ምን ያህል ከባድ ሊሆንባቸው እንደሚችል በቀላሉ መረዳት ትችላለህ።

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ሕዝቡ በስሜት በመንቀሳቀሳቸው እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ማንቀሳቀሱ ከባድ አልሆነም። አንድ አዲስ እንቅስቃሴ ሲጀመር ሰዎች ያለምንም ጥያቄ መሪዎቻቸውን መከተላቸው የተለመደ ሰብአዊ ባሕርይ ነው። ትንሽ ቆይተው ግን ችግሮች ሲገጥሙአቸው ስሜታቸው እየቀዘቀዘ ሲሄድ አንዳንድ ጥያቄዎችን ማንሣት ይጀምራሉ። ማጉረምረም ይጀምራሉ።፣ ከዚያም አልፈው በመሪያቸው ላይ በጠላትነት ይነሳሉ። በሙሴ ላይ የደረሰውም ይኸው ነበር።

2/ ዘጸ 14፣10-12፣15፣23-25፣ 16፣2-3፣ 17፣1-3 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች በእሥራኤላውያን ጉዞ ወቅት ከተፈጸሙ አራት ድርጊቶች የተወሰዱ ናቸው። በእያንዳንዱ ሁኔታ ሕዝቡ ምን አደረጉ? መልስህን በተሰጠው ሰፍራ ላይ አስፍር።

በመጨረሻም ውሀ የሌለበት ሥፍራ ሲደርሱ ሕዝቡ አጉረመረሙ። ሙሴም **"ይኽን ሕዝብ ምን ላድርገው"?** ብሎ ወደ ጌታ ጮኸ። እንደ ሌላው ጊዜ ሁሉ አሁንም እግዚአብሔር የሕዝቡን ችግር ለማቃለል ተአምር አደረገ። እዚህ ላይ ግን እግዚአብሐር በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ከሕዝብ ጋር እንደሚሠራ መጽሕፍ ቅዱስ ተጨማሪ የአሠራር ዘዴን ያሳየናል።

3/ ዘጸ 17፣5 አንብብ። ሙሴ ከእግዚአብሔር ሦስት መመሪዎች ተቀበለ ። ከሕዝቡ ፊት ለፊት መሄድ፣ በትሩን መያዝና ሦስተኛው መመሪያ ምንድነው?

በእሥራኤል ሽማግሌዎች ሁሉ ፊት ሙሴ አለቱን በበትር መታው፡፡ ከዐለቱም ውሃ ወጥቶ ሕዝቡ ሁሉ ጠጡ፡፡ ለዚህ ሽማግሌዎቹ ምስክር ናቸው፡፡ የሙሴን አገልግሎት ልምምድ በቅርቡ የሚካፈሉበት ሁኔታ ተፈጠረላቸው፡፡ እርሱ ሊማሩና ለአገልግሎታቸውም አዲስ እምነትና ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ መሪዎች የአገልግሎት ልምምዳቸውን ለሕዝቡ ያካፍሉ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ደጋግሞ ያሳየናል፡፡ በአዲስ ኪዳንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያው ጳውሎስ ምሳሌዎቻችን ናቸው፡፡

በሚቀጥለው ሁኔታ ደግሞ በመሪዎችና በተመሪዎች መካከል ስለነበረው ቅርርቦሽ ምሳሌያዊ ገለጻ እናያለን፡፡ ሙሴ እያሱን መረጠ፡፡ እያሱ ደግሞ ከእስራኤል ጠላቶች ጋር የሚዋጉ ሌሎች ሰዎችን መረጠ፡፡ በጦርነቱ ጊዜ ሙሴ እጆቹን ለጸሎት ወደ እግዚአብሐር አንሥቶ ነበር፡፡ እጆቹ ዝለው ሲያወርዳቸው ጠላት ያሸንፋል፡፡ ስለዚህም ሙሴ ቁጭ አለና ሌሎች ግራና ቀኝ ሆነው እጆቹን እንዲደግፉ በማድረግ በዚህ ሁኔታ ጦርነቱ በድል ተጠናቀቀ፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴን፣ ***“ይህን ለመታሰቢያ ጻፈው”*** አለው ዘጸ 17፣14፡፡ የአንድን መሪ እጆች እንዳይዝሉ የሌሎች መሪዎች ድጋፍ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ ማንኛውም መልካም መሪ ሁሉ የሙሴም ፍላጎት ዓላማውን እግቡ ለማድረስ ነበር፡፡ ለሥራው ራሱን የሰጠና ትጉህ መሪ በመሆኑ ሥራው እንዲሳካለት የሌሎች ትብብር ያስፈልገዋል፡፡ እርሱ ራሱን በሰጠበት ሁኔታ ሰዎች ለሥራው ራሳቸውን አለመስጠታቸውን ሲያይ ደግሞ ያዝናል፡፡ ሕይወቱን ለመስጠት እንኳ ፈቃደኛ እስኪሆን ድረስ ሕዝቡን ይወዳል፡፡ ይሁን እንጂ መሪነትን የሚመለከት ሌላ ዓይነት ፍቅር መማር ነበረበት፡፡ ይህ ዓይነት ፍቅር ደካማ ሆነው ቢገኙ እንኳ በሰዎች መታመንን፣ ራዕያቸውን መካፈልንና ለግቡ መሳካትም አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማበረታታትን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሙሴ ይህን የተማረው ከአማቹ ከዮቶር ነበር፡፡

ዮቶር ወደ ሙሴ ሲመጣ እግዚአብሔር ያደረገውን ድንቅ ነገርና ስለ ጉዞአቸው ተወያዩ፡፡ ምናልባትም ስለ ሕዝቡ ማጉረምረምና እግዚአብሔርንና እርሱን እንዳሳዘኑ

ሳያጫውተው አልቀረም፡፡ ምናልባትም ለጌታ እንደተናገረው ሁሉ **"ይኽን ሕዝብ ምን ላድርገው?"** በማለት ሳይጠይቀው አልቀረም፡፡

ሙሴ ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ቅርበት ዮቶር በየዕለቱ ይመለከት ነበር፡፡ ምን ያህል ሙሉ በሙሉ ለጌታ ሥራ ሕይወቱን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን እንደሰጠ አይቷል፡፡ ሰዎች በየዕለቱ ወደሙሴ ይመጣሉ፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው እንደዳኛም፣ እንደአማካሪም፣ እንደአገልጋይና ረዳት ሆኖ ነበር ሕዝቡን የሚመራው፡፡ **"ሥራው ከባድ ስለሆነ ብቻህን አትችለውም፣ ስለዚህ ከሰማኸኝ ምክር ልስጥህ"** አለ ዮቶር፡፡ አንደገና ዘጸአት 18፣13-26 አንብብ፡፡ ከዚህ ዮቶር ለሙሴ ከሰጠው ምክር ከሰዎች ጋር ስለ መሥራት አራት ነገሮችን ትመለከታለህ፡፡

1/ ሕግና ደንብ አስተምራቸው፡፡

2/ እያንዳንዱን ሥራ እንዴት እንደሚሠሩ አሳያቸው

3/ ለየግላቸው የተለየ ሥራ ስጣቸው

4/ መካከለኛ መሪዎችን ምረጥና ሥራውን አብረሀቸው አደራጅ፡፡

ሙሴ ላቀረበለት ጥያቄ ዮቶር የመለሰለት እነዚህን ነበር፡፡ ሙሴ እነዚህን ምክሮች ከተቀበለ በመጀመሪያ ደረጃ የሥራ ጫና ይቃለልለታል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሕዝቡም በሥራው ይረካሉ፡፡ እነዚህን ሁለት ነጥቦች ዘወትር ማስታወስ አስፈላጊ ነው፡፡ የተዋጣለት የአመራር ዘዴ እነዚህን እንደሚያጠቃልል በኋላ እንመለከታለን፡፡ ዓላማን እግቡ ማድረስና የሠራተኞችም ፍላጎት ሊሟላ የሚቻለው እነዚህ ሁለት ነጥቦች በሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ነው፡፡

4/ ከሰዎች ጋር ስለመሥራት ዮቶር ለሙሴ የሰጣቸውን አራት ነጥቦች እንደገና አንብብ፡፡ መጽሐፉን እጠፍና በአእምሮህ የያዝካቸውን ጻፍ፡፡ ይህ እያንዳንዱ መንፈሳዊ መሪ ሊከተለው የሚገባ መልካም ምክር ነው፡፡

5/ ዘጸ 18፣22 አንብብ፡፡ በ17፣5 ላይ ከተመለከትነው የመሪነት አሰራር ጋር ተመሳሳይ የሆነ የመሪነት መመሪያ የያዘ መሆኑን ልብ ብለህ አስተውል፡ ያም የሙሴ የሥራ ጫና መቃለል የነበረበት ስለሆነ ነው፡፡

### የእግዚአብሔር ሕዝብና የሙሴ ሕዝብ

**ዓላማ 3 ምንም እንኳ በአንዳንድ ሁኔታ ቢያሳዝኑትም ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ እንደነበር ለመግለጽ**

ሙሴን ታላቅ መሪ ካደረጉት ነገሮች አንዱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየት መቻሉ ነው። እግዚአብሔር ስሙን ለማክበርና ዓላማውንም ለመፈጸም በሰዎች አማካይነት እንደሚሠራ ያውቃል። በቃልም ሆነ በድርጊት ሙሴ እግዚአብሔር ከሰጠው ሕዝብ ጋር አብሮ ለመሥራት የነበረውን ፈቃደኝነት ያሳያል። ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ፣ ለእግዚአብሔር ለመሥራትም ያለው ዓላማ ሰዎችን እንዲወድና ታማኝ እንዲሆንላቸው ረድቶታል።

በዘጸ 18፥15 ላይ ለምን ጊዜውን በብዛት ከሕዝቡ ጋር እንደሚያሳልፍ ዮቶር በጠየቀው ጊዜ ሙሴ የሰጠው መልስ ምን ነበር? **"ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ ወደ እኔ ስለሚመጡ ነው"** ነበር ያለው። ይህም የሚያመለከተው ሕዝቡ አልፎ አልፎ ቢያምጹም፣ ሙሴንም ያለአግባብ ቢወቅሱትም፣ በጌታ ባይታመኑም፣ በልባቸው እግዚአብሔርን ለማወቅና እርሱንም የማገልገል ፍላጎት እንደነበራቸው ነው። ለመማር ይፈልጋሉ። ችግር ሲደርስባቸውም ምክርና እርዳታ ፍለጋ ነበር ወደ ሙሴ ይመጡ የነበሩት። ከሰዎች ጋር ለሚኖራቸው አለመግባባት የጌታን ውሳኔ እንደመጨረሻው መፍትሄ አድርገው ነበር የሚቀበሉት። የእሥራኤልን ጠላት በጀግንነት ተዋግተዋል። የተለያየ ድካም ቢኖርባቸውም ሙሴ እነዚህን መልካምና ጠንካራ ጎኖቻቸውን አስተውሏል።

በዘጸአት ምዕ 32 ላይ እንደምናነበው ሙሴ በሲና ተራራ ላይ የእግዚአብሔር ቃል በሚቀበልበት ወቅት ሕዝቡ የወርቅ ጥጃ ምስል ሠርቶ በባእድ አምልኮ ኃጢአት ውስጥ በወደቀ ጊዜ ሙሴ ከተራራው ሲመለስ ይህን ተመልክቶ ልቡ በሐዘንና በብስጭት እንደተሰበረ ከፈጸመው ድርጊት በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ከቁጥር 7-14 ላይ የተጻፈው በእግዚአብሔርና በሙሴ መካከል የተደረገ ንግግር ዘወትር ልናስታውሰው የሚገባ ነው።

እግዚአብሔር ሙሴን *"ከግብጽ ምድር ያወጣኸው ሕዝብህ ኃጢአት አድርጓል-አሁንም ቁጣዬ እንዲቃጠልባቸው እንዳጠፋቸውም ተወኝ፣ አንተንም ለታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ"* አለው ሙሴ ግን *"አቤቱ ቁጣህ በታላቅ ኃይልና በጽኑ እጅ ከግብጽ ምድር ባወጣኸው በሕዝብህ ላይ ለምን ተቃጠለ? ከመዓትህ ተመለስ፣ ለሕዝብህም በክፉታቸው ላይ ራራ"* ሕዝቡ ደካሞች ስለሆኑ ኃጢአት አደረጉ፡፡ ይበልጥ ትምህርትና ምሪት አስፈለጋቸው፣ ያም ሆኖ የእግዚአብሔር ሕዝብና የሙሴ ሕዝብ ነበር፡፡እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሙሴን ኃላፊ ሲያደርገው ሙሴም በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ኃላፊነቱን ተቀብሎ በእግዚአብሔር እርዳታ በትክክለኛው መንገድ ሲመራቸው ሙሴ ሕይወቱን ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ሰጠ፡፡ በባዕድ አምልኮ ምክንያት ከደረሰባቸው ውድቀትና ጥፋት በኋላ እንደገና አደራጃቸው፡፡ ችሎታቸውን ስጦታቸውን ተጠቅመው የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠሩ ያነሳሳቸውም እርሱ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል አስተማራቸው፡፡ የሚሠሩትን ሥራ ካሳያቸው በኋላ እርሱ ጀምሮት በነበረውን ሥራ እነርሱ እንዲፈጽሙ ተወላቸው፡፡

7/ የሚከተለውን ዓረፍተ ነገር ይበልጥ የተሟላ በሚያደርገው ፊደል በማክበብ አመልክት፡፡ ምንም እንኳ አልፎ አልፎ ቢያሳዝኑትም ሙሴ ከሕዝቡ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ የሆነበት ምክንያቱም፡-

ሀ/ ያን የሚያህል ሕዝብ መምራት ክብር ስለሆነ

ለ/ ማደግና መዳበር የሚችል ብርታት እንደነበራቸው ስላስተዋለ

ሐ/ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመፈጸም ያላቸውን ፍላጎት ስላየ

መ/ በእነርሱ አማካይነት እግዚአብሔር እንዲከብር ስለፈለገ

ሠ/ የመሪነት ችሎታውን ማሳየት ስለፈለገ

**መሪዎች ስለ ሰዎች ምን እንደሚያምኑ**

**ዓላማ 4 ዮቶር ሰለ እግዚአብሔር ሕዝብ የነበረውን ግንዛቤ ለመግለጽ**

ዮቶር ለሙሴ የሰጠውን መልካም ምክር ከሰዎች ጋር አብሮ ለመሥራት የማያስችል ከመሆኑም በላይ፣ አጠር ባለ መልኩ ስንመለከተው ከተከታዮቹ የበለጠ መልካም ነገርን እንዲጠብቅ የሚያደርግ ምክር ነበር።

አንዳንድ ስለ መሪነት ጥናት ያደረጉ ምሁራን አንድ መሪ የሚወስደው እርምጃ በሕዝቡ ላይ ያለው እምነት ውጤት እንደሆነ ይናገራሉ። እንደእነዚህ ምሁራን አባባል ለሰዎች ያሉን እምነቶችና ግምቶች ይባላሉ። ከሰዎች የምንጠብቀው ነገርና ስለ እርሱም ያለን አመለካከት እንደዚሁም የምንወሰደው እርምጃ በእነዚህ ግምቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ወጣቶች በእድሜ ከገፉት ሰዎች ይልቅ ይበለጥ ጠንካሮች ናቸው የሚል ግምት ሊኖረን ይችላል። ስለዚህም አንድ የምናንቀሳቅሰው ከባድ ነገር ቢኖር ከባድ የሆነውን ሥራ ወጣቶች እንዲሠሩት እናደርጋለን። ይህን ቢኖር ከባድ የሆነውን ሥራ ወጣቶች እንደሚቀበሉም ተስፋ እናደርጋለን። አንድ ሰባኪ የሚናገረው ነገር ስለ ምዕመኑ ያለውን እምነት እንዴት እንደሚያሳይ እንመልከት። ለምሳሌ ያህል ምዕመኑን “ለግል ጉዳያችሁ ከምታባክኑት ሰፊ ጊዜ ውስጥ ጥቂቱን ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት ልታውሉት ይገባል” ቢላቸው ይህ ሰባኪ የሚያሳየው ምን ግምቶች ነው?

ሰባኪው ለሕዝቡ ያለው ግምት፡-

1/ ሰዎች ጊዜያቸውን የሚያባክኑት ለደስታ ብቻ እንደሆነ

2/ በጊዜ አጠቃቅም ራስ ወዳዶች እንደሆኑ

3/ መሥዋዕትን ስለሚጠይቅ ጊዜያቸውን ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት እንደማይፈልጉ

4/ ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ ነፍሳትን ወደ ጌታ ያመጡ እንደነበር

በሰባኪው ግምት ሕዝቡ ደስታን ስለሚወድ ነፍሳትን ወደ ጌታ ለማምጣት ደንታ የላቸውም፣ ስለዚህም ለነርሱ ያለው ግንዛቤ በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ነፍሳትን ወደ ጌታ እንዴት ማምጣት እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይፈልጋል። የሚያስፈለገውን መስዋዕትነት ቢከፍሉ ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት እንደሚችሉ እምነት አለው ማለት ነው።

ስለሆነም፡- እንዴት ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት እንደሚችሉ ትምህርት እንደሚሰጥ ይነግራቸዋል እንበል። ስለዚህም ”ላልዳኑ ሰዎች የምስራቹን ቃል

ስለማካፈል በይበልጥ መማር ትችላላችሁ" ቢላቸው ግምቶቹ በይበልጥ ይህን ይመስላሉ፡-

1/ ነፍሳትን ወደ ጌታ ማምጣት ደስ ያሰኛቸዋል፣ እንዴት እንደሚያመጡ ግን አያውቁም፡፡ ስለዚህ ሥልጠና ያስፈልጋቸዋል፡፡

2/ ጊዜያቸውን በሥልጠናውና ነፍሳትን ወደጌታ ለማምጣት ቢያውሉት ፈቃደኛ ናቸው፡፡

3/ ስላልዳኑ ሰዎች ያስባሉ

እንግዲህ ከዚህ እንደምንመለከተው ሰባኪው ለሕዝቡ ከፍተኛ ግምት አለው፣ ይሁን እንጂ ሥልጠና ይጎድላቸዋል፡፡ ስለዚህም ያላቸውን ችሎታ ለማጎልበት እንዲጠቀሙበት ይፈልጋል፡፡

8/ የተሻለ መልስ ነው የምትለውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡

ሀ/ ያለምንም ድርጅት ሰዎች እንደሚገባ መሥራት ይችላሉ

ለ/ አብዛኞቹ ሰዎች የግል ችግራቸውን ያለ ረዳት መፍታት ይችላሉ፡

ሐ/ እንደሚገባ ካስረዷቸው ሰዎች መመሪያን ለመቀበል ዝግጁ ናቸው

ሠ/ አብዛኞቹ ሰዎች በሚያደርጉት ውሳኔ እምነት ሊኖረን ይገባል

## የአመራር ዘዴ እንዴት እንደሚዳብር

## ዓላማ 5 የመሪነትን ባሕርይ ምሳሌዎች፣ ስለ ሰዎች ከተሰጡ ግምቶች ጋር ለማዛመድ

ስለ ሰዎች ያለን ግምቶች የመሪነትን ዘዴ በማጎልበት ረገድ እንዴት ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የመጀመሪያው ጥናት እንዳቀረበው የብዙዎቹ መሪዎች ባሕርያት የተመሠረቱት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ግምቶች ላይ ነው፡፡ ግምቶቹም ሰዎች ሥራ ስለማይወዱ በተቻላቸው መጠን ከሥራ ይሸሻሉ፡፡ ይፈልጋሉ ኃላፊነትን ለማስወገድ እንጂ ለመቀበል አይፈልጉም ፡፡ ሰፊ ግቦች ላይ ለመድረስ ያላቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል ዓላማዎችንና ግቦችን በአገር አቀፍ የወንጌል ማስፋፋት፣ እንቅስቃሴ መሳተፍ ድርጅታዊ ዓላማዎችንና ግቦችን የሚጠይቅ ነው፡፡

ከጥናቱ የተገኘው ከዚህ ተቃራኒ የሆነው አመለካከት ደግሞ እነዚህ ግምቶች የሚያጠቃልሉት ከዚህ የሚከተሉትን ነው፡፡ ሥራ የሰዎች ተፈጥሮአዊ ባሕርይ በመሆኑ ሊርቁት ወይም ሊያስወግዱት ዝንባሌ የላቸውም፡፡ ሰዎች ዓላማዎችን እግቡ ለማድረስ በፈቃደኛነት ይሠራሉ፡፡ ሰዎች ኃላፊነትን መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ ኃላፊነትንም ይሻሉ የሚል ነው፡፡

በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ጥቂቶቹ ብቻ ሳይሆኑ በጠቅላላው ብዙ ሰዎች ሰፋፊና ትላልቅ ግቦችን ለመምታት የግላቸው አስተዋፅኦ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ብዙ ሰዎች ገና ሥራ ላይ ያልዋለ ችሎታና ኃይል አላቸው፡፡ ሰዎች ዋጋ ይኖራቸዋል ብለው ለሚያምኑባቸው ዓላማዎችና ግቦች ራሳቸውን ለመስጠት ዝግጁ ናቸው፡፡

አሁን ደግሞ ስለ ሰዎች ያለን ግምት እንዴት የመሪነት ስልትን ወይም ዘዴን ለማዳበር እንደሚረዳን ግንዛቤ ለማግኘት ብንሞክር ስልት ወይም ዘዴ የሚለውን ቃል አስቀድመን መግለጽ ይኖርብናል፡፡ የባሕርያት ክምችት ወይም ሥራዎቻችንን የምናከናውንበት መንገድ በማለት ስልት ወይም ዘዴ የሚለውን ቃል ልንገልጸው እንችላለን፡፡ ስለ መሪነት የተጻፉ አብዛኛዎቹ መጻሕፍት ጥቂት የአመራር ስልቶችን አስፍረዋል፡፡ አብዛኞቹ ፀሐፊዎች የገለጹአቸው ሁለት ስልቶች ሲሆኑ አንደኛው ገደብ የሌለው ስልጣን ያዘለ ሲሆን፣ ሌላው ብዙሐኑ የሚሳተፉበት የአመራር ስልት ነው፡፡ ገደብ የሌለው ሥልጣን ያዘለ የአመራር ስልትን የሚከተል መሪ ብዙኀኑን ይቆጣጠራል፡፡ ውሳኔዎችን ሁሉ የሚያደርገው ራሱ ነው፡፡ ደንቦችን የሚያወጣውና ተፈጻሚም የሚያደርጋቸው እርሱ ራሱ ነው፡፡ ከበታቹ ሆነው እንዲሠሩ ዝርዝር መመሪያ ይሰጣቸዋል፡፡ በቅርበትና በግል ማንኛውንም እንቅስቅሴ ይቆጣጠራል፡፡

ብዙኃኑን በሚያሳትፍ በአመራር ስልት የሚጠቀም ሰው በቡድኑ ውስጥ ሆኖ ነው እርሱ ራሱ የሚሠራው፡፡ ደንቦቹን እንዲያወጡ ይመራቸዋል፡፡ ውሳኔ በመስጠት እንዲሳተፉ ያደርጋቸዋል፡፡ የሌሎችን ምክርና አስተዋጽኦ ይጠይቃል፡፡ ለአንዳንድ የቡድኑ አባላት አንዳንድ አስፈላጊ ኃላፊነቶችን ይሰጣቸዋል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያውን የጥናት ግምት የሚቀበል መሪ አብዛኞቹ ሰዎች ቸልተኛ፡ ሰነፍና ሥራ የማይወዱ እንደሆኑ ያስባል፡፡ “ግፊት” ሊሰጣቸውና ከበላይ ሆነው እንዲቆጣጠሩዋቸው ያስፈልጋል የሚል እምነት አለው፡፡ ምሪት፣ ቁጥጥር፣ መገፋፋትና ተግሳጽ ያስፈጋልጋቸዋል ይላል፡፡ ስለዚህም እንዲህ ያለ እምነት ያለው መሪ ሰዎች እሚፈለገው ግብ ላይ እንዲደርሱ ከተፈለገ ሙሉ ለሙሉ ልንቆጣጠራቸው ያስፈልጋል በማለት ያስባል፡፡ ውሎ አድሮ ፈላጭ ቆራጭ ይሆናል፡፡

ሁለተኛውን የጥናት ግምት አመለካከት የሚከተል ሰው ሰዎች ሥራ ወዳዶች እንደሆኑና እሚፈለገው ግብ ላይ ለመድረስ ኃላፊነትን የመቀበል ፍላጎት እንዳላቸው ያምናል፡፡ ለዚህም አንዳንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በችሎታቸውና በስጦታዎቻቸው በመጠቀም ተሳትፎ እንዲኖራቸውም ያደርጋል፡፡ ይህን ሁሉ የሚያደርገው ፈቃደኛነታቸውን በማክበር ነው፡፡ እንዲህ ያለው መሪ ብዙኀኑን የሚያሳትፍ መሪ ነው፡፡

9/ ገደብ ከሌለው የአመራር ስልትና ብዙሃኑን ከሚያሳትፈው የአመራር ስልት የምትከተለው የትኛው እንደሆነ ምክንያትህን ጭምር በመግለጽ መልስህን በተሰጠው ስፍራ አስፍር፡፡ ----------------------------

እርግጥ ነው፣ ሥራ የማይወዱ አንዳንድ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ይልቅ ክትትልና ቁጥጥር ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡ ለዓላማው መሳካት አስፈላጊ ሆኖ እስካገኘው ድረስ መሪው ዝርዝር መመሪያዎችን መስጠት፣ ማስፈጸምና በአቋሙም የማያወላውል ሆኖ መገኘት አለበት፡፡ መልካም መሪዎች እንደሰዎቹ ዓይነትም እንደ ሁኔታዎቹ ልዩነት የአሠራር ዘዴያቸውን በመለዋወጥ ይጠቀማሉ፡፡ በኋለኛው ትምሕርታችን ስለዚህ ብዙ የምናጠናው ይኖረናል፡፡

እዚህ ላይ በጣም ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን ጉዳይ ግን የአመራር ስልታችን የሰመረና የተዋጣልን መሪዎች መሆን የምንችለው ለሰዎች በሚኖረን ግምት መጠን መሆኑን ነው፡፡ ክርስቲያኖች ዋጋ እንዳለው ለሚያምኑበት ዓላማና ግብ ራሳቸውን ይሰጣሉ፡፡ ምክር ፍለጋ ወደ ሙሴ ይመጡ እንደነበሩት ሰዎች ሁሉ ክርስቲያኖችም

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልጋሉ። የክርስቶስን አካል በመገንባቱ ሥራ ይሳተፋሉ። ከጌታ የተቀበሏቸው ስጦታና ችሎታዎች አሏቸው። በጌታ ሥራ በሚደርጉት ተሳትፎ ደስታና ክብር ይሰማቸዋል። ስለዚህም ያላቸውን ስጦታና ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚረዳቸውን መሪ ይፈልጋሉ። በእግዚአብሔር እቅድ መሠረት የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠሩ ሲነገራቸውም ሙሴ ይህንኑ ነበር ያደረገው።

10/ ዘጸ 35፣1-36፣7 አንብብ። ከሙሴን የአመራር ባሕርይ ያገኘውን ምላሽ መሠረት በማድረግ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚከተሉት ግምቶች ሊኖሩን ይችላሉ። እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር ከትክክለኛው ጥቅስ ጋር አዛምድ። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘኸው ከአንድ የበለጡ ጥቅሶች መጠቀም ትችላለህ።

| ግምቶች | ጥቅሶች |
|---|---|
| ---------ሀ/ ሰዎች ግልጽ መመሪያ ይፈልጋሉ | 1/ 35፣10 |
| ---------ለ/ ሰዎች ግልጽ ግብ ይፈልጋሉ | 2/ 36፣2 |
| -------ሐ/ ብዙ ሰዎች ለመሥራት ፈቃደኛ ናቸው | 3/ 35፣21 |
| --------መ/ ብዙ ሰዎች ለመስጠት ፈቃደኛ ናቸው | 4/ 35፣35 |
| ------- ሠ/ ሰዎች ሞያን መማር ይችላሉ | 5/ 35፣1-3 |
| ----- ረ/ ሰዎች ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ዕውቀትና ችሎታ አላቸው | 6/ 35፣34 |

ብዙ ስለ አመራር ጥናት ያደረጉ ምሑራን እንደሚያምኑት ሰዎች በችሎታቸው እንደተጠቀሙበት ከተረዱ በተሻለ ሁኔታ ይሠራሉ። ዋጋ እንዳለው የሚያምኑበትን ነገር እንዲሠሩ ቢነገራቸው ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ለሥራው ይሰጣሉ። ስለ ሠሩትም ሥራ ምሥጋና ይፈልጋሉ።

የመገናኛው ድንኳን ሲሠራ ሙሴ የተጠቀመባቸው መመሪያዎች በጌታ ሥራም በጣም አስፈላጊ ነው። ሙሴ ለግለሰቦች እውቅና በመስጠት ስላላቸው ስጦታና ችሎታ በመመሪያ ደረጃ ክብሩን የሰጠው ለእግዚአብሔር ነበር። ይሁን እንጂ የዚያ ስጦታ፣ የሙያ እውቀትና ችሎታ ባለቤት የሆኑትን ሰዎች ስም በዝርዝር ያስታውቅ ነበር /ዘጸ 35:30-35/

ይህን ውብና አስደናቂ ዓለም የፈጠረ እግዚአብሔር እጹብ ድንቅ የሆነ ልብስ ተክህኖ ለአሮን ከሰማይ ሊያወርድለት ይችል አልነበረምን? እግዚአብሔር ግን ያደረገው እንደዚያ አይደለም፡፡ አስፈላጊው ችሎታና ፈቃደኝነት ያላቸው ባለሙያዎችን ሙሴ እንዲመራና እንዲያስተባብር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነ፡፡

እንግዲህ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ያላቸውን ፍላጎትና በሥራ ለመተርጎም ያላቸውን ፈቃደኝነት የምንገነዘብ ከሆነ፣ የመሪው ዋነኛ ሥራ ምን መሆን እንዳለበት መረዳት አያዳግተንም፡፡ የመሪው ሥራ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ባላቸው ሞያ እንዲጠቀሙ እነዚህን ሰዎች ማቀናጀት ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለውም በሰዎች ችሎታ እምነት ሲኖረንና እነርሱን ወደ ጌታ የማምጣቱን እውነተኛ የሆነ ፍላጎት ሲኖረን ነው፡፡

11/ ለምሳሌ ያህል ማሕበረሰቡን የመንፈሳዊ ሥነ-ጽሑፍ ዘመቻ እንድትመራ ብትመረጥና መሪ ብትሆን ለዚሁም ሥራ የሚረዱህ ክርስቲያኖች ፍላጎቱ እንዳላቸውና ለመሥራትም ፈቃደኛ መሆናቸውን ካረጋገጥህ በኋላ ከሚከተሉት የትኛውን ታደርጋለህ?

ሀ/ ለእግዚአብሄር ሥራ ራስን የመስጠትን አስፈላጊነት መስበክ

ለ/ ሥራው መንፈሳዊ ግቦችን ለመምታት የታለመ መሆኑን መግለጽ

ሐ/ ለአገልግሎት በሚወጡበት ጊዜ ሌላ ሥራቸውን ሁሉ እርግፍ አድርገው እንዲተውት ማድረግ

መ/ አንዳንድ ሥራዎችን መስጠትና ጥያቄ እንዲያቀርቡ ጊዜ መስጠት

ረ/ አሁን ደግሞ ለምን እነዚህን እንደመረጥህ በሌላ ወረቀት ላይ ምክንያቶችህን አስፍር፡፡

በመሪነት ከተለያዩ ቡድኖች ጋር ሆነን ስንሰራ ግለሰቦች በሕብረት ሆነው ሲሰሩ የሚኖራቸውን ብርታት፣ችሎታና መንፈሳዊ ኃይል እንመለከታለን፡፡ ይህም የደስታችን ምክንያት ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶችን ሁኔታዎች የማያመቻቹ ሰዎች ግን ችግር ይጋብዛል፣ ሥራቸው አይሳካም፣ ክርስቲያናዊ ግቦችም ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

ከሙሴ ምሳሌነት እንደተረዳነው የእግዚአብሔር ሕዝብ የእርሱም ሕዝብ መሆናቸውን ተመልክተናል። በዚህም ምክንያት በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ያላቸውን ችሎታና ኃይል እንዲያዳብሩ ሊረዳቸው ቻለ። ይህም መንፈሳዊ አመራር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንድንገነዘብ ያደርገናል። ሰው ከሰው ጋር ለሚኖረው ግንኙነት አራት መመሪያዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። እነዚህ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች በሥራ ላይ ከዋሉ ለአንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ችግር መፍትሔ ሊያስገኙ እንደሚችሉ ይታመናል።

1/ ስለ ሁኔታው ያለህን ሃሳብ ወይም ስሜት ሰዎች በግልጽ እንዲያውቁልህ አድርግ። አንዳንድ ጊዜ መሪዎች የቡድኑን ድካም የሚናገሩት ሌሎች እንጂ ለራሳቸው ሥራው ለሚመለከታቸው ወገኖች አይደለም።

2/ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ በመወያየት እርስ በርስ እንዲረዳዱ አድርግ

3/ የተለያዩ ሃሳቦችን እንዲያቀርቡና የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙበት ዕድል ስጣቸው። ይህን የሚያደርጉ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መምረጥና ኃላፊነትን ወስደው እንዲሠሩ ለማድረግ ይረዳል።

4/ ስላከናወኑት መልካም ተግባር ለሰዎች አድናቆትህን ግለጽላቸው፡ ለእነርሱ ያለህን ቅን አመለካከትም እንዲረዱ አድርግ።

12/ ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎች የማይከተል መንፈሳዊ መሪ ቢያጋጥምህና አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮችን እንድትለግሰው ቢጠይቅህ ምን ሃሳብ እንደምትሰጠው በዝርዝር አስፍር።_________________________________________________

**የሙከራ ፈተና**

ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሻለ መልስ ነው ብለህ የምታስበውን ፊደል በመክበብ አመልከት።

1/ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ዓላማ ስለነበረው ሙሴን ለመሪነት ጠራው፣ በድንቆችና በተአምራት መልክ ሥልጣኑን ሰጠው። ከዚህም ሌላ፡-

ሀ/ በሕይወት ዘመኑና በዘላለም ሕይወቱ እንደሚሸልመው ተስፋ ሰጠው

ለ/ ከጠላቶቹ ጥቃትና ከወዳጆቹም ነቀፋ እንደሚጠብቀው ተስፋ ሰጠው

ሐ/ በሥራው ታዋቂ እንደሚሆንና እንደሚከበር ተስፋ ሰጠው

መ/ አብሮት እንደሚሆንና ታላቁን ዓላማውን እንደሚፈጽም ተስፋ ሰጠው

2/ እንደ ብዙዎቹ መሪዎች ሁሉ ሙሴ ስለ ሰዎች የሚያስብ ቢሆንም ከሚከተሉት በአንዱ ግን ይህን አይደለም የምንመለከተው፡

ሀ/ ስለሰዎች ደንታ ነበረው ለ/ ሕዝቡ ስላሉበት ሁኔታ ያስብና እነርሱን ለመርዳት አንድ ነገር ማድረግ ይፈልግ ነበር፡፡

ለ/ በጣም ትሁት ስለነበር የጌታን ጥሪ መቀበል አልፈለገም

ሐ/ በሕዝቡ ላይ የሚደረገውን ግፍ ለማስቆም ቆርጦ ተነሳ

3/ ከግብጽ የመውጣቱ ፍልሰት ሲጀመር አንድ የምንመለከተው ሰብዓዊ ባሕርይ አለ፡፡ አዲስ እንቅስቃሴ ሲጀመር ሰዎች በስሜት ይነሳሉ፣ መሪውንም ይከተሉታል፡፡ ውለው አድረው ችግሮች ሲመጡ ግን፡-

ሀ/ ስሜታቸው ይቀዘቅዛል፣ በረባ ባልረባውም መሪውን ይወቅሱታል

ለ/ ከዓላማቸው ይዘናጋሉ ሐ/ አመራሩ በአስቸኳይ እንዲለወጥ ይፈልጋሉ

መ/ ዓላማና ግባቸውን በአዲስ መልክ መገምገም ይጀምራሉ

4/ ውሃ ወደሌለበት ሥፍራ ሲደርሱ ሙሴ በጣም ተቸገረ፣ በዚህ ወቅት ከሙሴ ሕይወት የምንመለከተው ልምምድ ወይም ተሞክሮ ሌላ የመሪነት መመሪያ ያሳየናል፡፡ የአገልግሎት ልምምዶች ሸክም፡-

ሀ/ ሰዎችን ላዲስ ራዕይ ለማነሳሳት አስደናቂ ተአምራትን ይጠይቃል

ለ/ ከሌሎች መሪዎች ጋር የምንከፋፈለው ጉዳይ ነው

ሐ/ መሪው ብቻውን በርትቶ ቢጸልይ ሸክሙ ይቃለልለታል፡፡

መ/ አልፎ አልፎ ከረጅም ጊዜ ግቦቻችን ማረፍና አሁን ባለንበት ልምምድ ብቻ መርካት አለብን፡፡

5/ በረፋዲም ጦርነት የመሪነት መመሪያ ይገኛል፣ እግዚአብሔር ሙሴን፣

ሀ/ የጦርነቱን ታክቲክና የተደረገውን ቅስቀሳ በጽሑፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

ለ/ ወደ ውጊያው ስለሚሔዱ መካከለኛ መሪዎችና መሪውን ስለሚረዱት ተከታዮቹ በጽሑፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

ሐ/ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሰፈር ሊኖር ስለሚገባ ሞራል ነገረው፡፡

መ/ ለጦሩ ስለሚያስፈልገው ዝግጅትና የጌታን ውጊያ ለመዋጋት ስላላቸው ፈቃደኝነት በጽሁፍ እንዲያሰፍር ነገረው፡፡

6/ ሙሴ ስለ መሪነት ሌላ ትምህርት መማር ነበረበት፡፡ መሪነት፡-

ሀ/ ተገቢውን ሥራ ባይፈጽሙም እንኳ ሰዎችን መቀበልን ይጠይቃል

ለ/ በሕዝቡ መካከል ያለውን ቸልተኝነት በዝምታ ማለፍን ይጠይቃል

ሐ/ ቀድሞ ከነበረው ያነሰ ግብን ማስቀመጥ ያስፈልጋል

መ/ ራዕይ ለማካፈልና የታቀደውን ግብ እንዲመታ በሌሎች መታመን፡-

7/ ዮቶር ስለመሪነት ምክር ለሙሴ ሰጥቶት ነበር። ምክሮቹን በተግባር ቢያውላቸውን የሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች እንደሚሆኑ ነግሮታል።

ሀ/ ሰዎቹ ታማኝ ይሆናሉ፣ የታቀደውም ግብ ይሳካል።

ለ/ ሥራው ይቃለልለታል፣ ሰዎቹም ይደሰታሉ

ሐ/ ሙሴ በሕይወት ይኖራል፣ የሕዝቡም ፍላጎት ይሟላል

መ/ ሙሴን የሚተኩ ወጣት መሪዎችን ማፍራት ይቻላል፣ ሙሴም ለዘለቄታው ታላቅ ሆኖ ይኖራል።

8/ ሙሴን ታላቅ መሪ ካደረጉት ነገሮች አንዱ፡-

ሀ/ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማየት መቻሉ

ለ/ ቀድሞ ከነበረው ይልቅ ይበልጥ ለማከናወን የነበረው ራዕይ

ሐ/ ነገሮችን እውነቱ ባለበት ሁኔታ ይመለከታል እንጂ ሃሳባዊ አለመሆኑ

መ/ ከሕዝቡ ሁኔታ ጋር ለመጣጣም ከእነርሱ ዝቅ ያለ ነገርን መጠበቁ

9/ ሙሴ ሕጉን ለመቀበል ወደሲና ተራራ ወጥቶ በነበረበት ጊዜ ሕዝቡ ኃጢአት አደረጉ፣ እግዚአብሔር ሙሴን ***"ሕዝብህ"*** አለው፣ ሙሴ ደግሞ እግዚአብሔርን ***"ሕዝብህ"*** አለው። ስለ መሪነት ከዚህ የምናገኘው መመሪያ ምንድነው?

ሀ/ ሕዝቡ የእግዚአብሔር እንደመሆናቸው መጠን ተገቢውን ጥንቃቄ እንደሚደረግላቸው መሪዎች በእግዚአብሔር መታመን እንዳለባቸው

ለ/ እግዚአብሔር ሕዝቡን በኃላፊነት ለመሪዎች ሰጥቷል። ስለዚህ በእግዚአብሔር መታመንና ኃላፊነቱን መቀበል አለባቸው።

ሐ/ ሥራው የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ እንደመሆኑ መጠን መሪዎች ይህን ያህል አገልግሎት ሊከብድባቸው አይገባም

መ/ በመሠረቱ መንፈሳዊ ሥራ እግዚአብሔርና ሰው በኃላፊነት የሚወጡት ሥራ ነው።

10/ ዮቶር የሰጣቸውን ምክሮች በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል

ሀ/ "በመጀመሪያ ሕግ አውጣ ከዚያ በኋላ እንዲሰሩ ለሕዝቡ ንገራቸው፡"

ለ/ "ሕዝቡ ያለምንም ማወላወል እንዲታዘዙ ንገራቸው"

ሐ/ "ጽኑ ሥነ-ሥርዓት አስተምራቸው። ያጓደሉትን ግን ቅጣቸው"

መ/ በሕዝቡ ውስጥ ያልተጠቀመበት እምቅ ችሎታ አለ፣ ይህን ችሎታቸውን ሥራ ላይ እንዲያውሉት አድርግ።

11/ አንድ ሰባኪ "ለአንዳንድ የግል ጉዳዮቻችሁ ያለአግባብ የምትጠቀሙበትን ገንዘብ ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች ለማዳረስ እንዲቻል መስጠት አለባችሁ!" የሚል ከሆነ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር ሌሎችን ሁሉ ማለቱ ነው።

ሀ/ ሰዎቹ ራስ ወዳድ ስለሆኑ ገንዘባቸውን ለግላቸው ብቻ ያውሉታል

ለ/ መስዋእትነትን የሚጠይቅ በመሆኑ ሌሎችን ወደጌታ ማምጣት አይፈልጉም

ሐ/ በተፈጥሮአቸው መልካምና እምነት የሚጣልባቸው ናቸው

መ/ ፈቃደኛ ቢሆኑ ኖሮ ወንጌል ላልደረሳቸው ማዳረስ ይቻል ነበር።

12/ ሰባኪው ሕዝቡ በጌታ ሥራ መሳተፍ ደስ እንደሚላቸው፣ ስላለባቸውም ኃላፊነት ለመማር ፈቃደኛ መሆናቸው በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን ዓላማ እንደሚፈጸም ፍላጎት እንዳላቸው ቢገልጽላቸው ኖሮ ለሕዝቡ ያለው ግምት ምን ዓይነት እንደሆነ ነበር የሚያመለክተው?

ሀ/ ዝቅተኛ ግምት እንዳለው ለ/ ከፍተኛ ግምት እንዳለው

ሐ/ መጠነኛ ግምት እንዳለው መ/ ምንም ግምት እንደሌለው

13-14/ ከሚከተሉት ምሳሌዎች የትኛው ዓይነት የአመራር ስልት እንደተንጸባረቀ ከተመለከትክ በኋላ ይህ ዓይነቱ የአመራር ስልት በመሪውና በሕዝቡ ላይ የሚኖረውን የረጅም ጊዜ ተጽእኖ የራስህን አስተያየት ስጥ።

13/ አንደኛው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሰዎች ሁሉ ሰነፎች መሆናቸውንና በቅርበት ሊቆጣጠሯቸው እንደሚገባ ያምናል። ጥሩ ሲሰሩ ያመሰግናቸዋል፣ ጥሩ ካልሰሩ ግን ቅሬታውን ይገልጽላቸዋል። ሁሉንም ግብና እቅድ የሚያወጣው ራሱ ነው። ዝርዝር መመሪያ ይሰጣል ተግባራዊነቱንም በቅርብ ሆኖ ይከታተላል። ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ይህን የአመራር ስልት በተሻለ ሁኔታ የሚገልጸው?

ሀ/ ስልቱ ብዙሐንን እንደሚያሳትፍ

ለ/ የሚከተለው በሥልጣን የተሞላ የአመራር ስልት እንደሆነ

ሐ/ በአንድ ሰው የተማከለ የአመራር ስልትን

14/ ሌላው የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ደግሞ ደከመኝን የማያውቅ ሠራተኛ ነው። እንደ እርሱ ሌሎችም የሚያምኑበትንና ራሳቸውን የሰጡበትን ሥራ መሥራት እንደሚፈልጉም ያምናል። በሕዝቡ ውስጥ ያለውን ገና ያልተጠቀመብትን ችሎታና

ኃይል ያያል፡፡ አስፈላጊውን መመሪያ ያወጣል፣ ውሳኔ በመስጠቱ ላይ ግን ሁሉንም ያሳትፋል፡፡ የእያንዳንዱን ሰው ችሎታና ክህሎት በማዳበር ያምናል፡፡ አስተያየት እንዲሰጡና አስተዋጽኦ እንዲያደርጉም ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ስለ መልካም ሥራቸው በሕዝብ ፊት ነው የሚያመሰግናቸው፡፡ የትኛውን ዓይነት አመራር ስልት ነው የሚከተለው?

ሀ/ ብዙሐኑን የማያሳትፍ የአመራር ስልት

ለ/ ሰዎች ኃላፊነት እንዲቀበሉ የሚያደርግ የአመራር ስልት

ሐ/ በአንድ ሰው ዙሪያ ያተኮረ የአመራር ስልትን

መ/ ብዙኃኑን የሚያሳትፍ የአመራር ስልትን

**አጭር መልስ**

ትክክለኛውን በባዶው ስፍራ በማስፈር ያልተሟላ ዐ/ነገሩን የተሟላ አድርግ፡፡

- በአንድ ሰው ላይ ያተኮረ አመራር - ብዙኃንን ያቀፈ አመራር
- ገደብ የሌለው ሥልጣን ያዘለ አመራር

15/ አንድ መሪ ብቻውን አስፈላጊዎቹን ውሳኔዎች ሲያደርግ፣ ብቻውን ዝርዝር መመሪያ ሲሰጥና ቁጥጥር ሲያደርግ------------- አመራር ስልት ይባላል፡

16/ በቡድኑ ውስጥ ሆኖ የሚሰራ፣ ውሳኔና ሀሳብ በመስጠት የሚያሳትፍ ለሰዎችም ኃላፊነትን የሚያካፍል-------- አመራር ስልት ይባላል፡፡

17/ ሰዎች ሁሉ ሰነፎች እንደሆኑና ለሥራ ማንቀሳቀስ እንዳለበት የሚያምን የሚከተለው የአመራር ስልት ------------ ነው፡፡

18/ ስለ አመራር የጻፉ ብዙ ምሁራን እንደሚሉት ሰዎች በተሻለ መንገድ ለመሥራት ፈቃደኛ የሚሆኑት የተሰጣቸውን ስራ በሚገባ ማከናወናቸው ለዚህም ----------- ካገኙ ነው፡፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

7 /ለ/ መዳበር የሚገባው ችሎታ እንዳላቸው ያውቃል::

ሐ/ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ያውቃል

መ/ እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲከብር ይፈልጋል

1/ ሀ/ ሐሰት እግዚአብሔር ሳይጠራው በፊት እንኳ ሙሴ ስለሰዎች ያስባል

ለ/ እውነት ሐ/ ሐሰት አብሮት እንደሚሆን እንጂ እግዚአብሔር ሌላ ተስፋ አልሰጠውም መ/ እውነት ሠ/ እውነት ረ/ እውነት

8/ ሐ/ እንደሚገባ ከተረዱት ብዙ ሰዎች ሕግን ለማክበር ፈቃደኛ ናቸው

መ/ ብዙ ሰዎች የአመራር ችሎታ አላቸው

ሠ/ ተገቢውን ውሳኔ እንደሚያደርጉ በአብዛኛዎቹ ሰዎች መታመን

2/ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፣ አማረሩ ተነጫነጩ

9/ በአንድ ሰው ላይ ያተኮረ ዓይነት አመራር አስተያየት ነው ያለው

3/ አንዳንድ ሽማግሌዎችን ይዞ መሄድ ነበረበት

10/ሀ/5/35/፡1-3 ለ/1/35፡10 ሐ/2/36-32 መ/3/35፡21 ሠ/6/35፡34 ረ/4/35፣35

4/ ካለፈው ምንባብ መልስህን አስተካክል

11/ የተሻሉት ምርጫዎች "ለ" "መ" ና "ሠ" ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ሕዝቡ ወደ ስብሰባው የመጡት የጌታን ሥራ ለመሥራት ነው የሚል ሀሳብ ካለህ

ሀ/ አስፈላጊ አይደለም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስብከት የምታደርግ ከሆነ ሰዎችን እንዳልተረዳሃቸውና እንደማታደንቃቸው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ የአሁኑ ግብ ለዘላቂው ትምህርትና የሕይወት ዓላማ መሠረት ስለሆነ፡፡ የአሁኑ ግብ ለዘላቂው ትምህርትና የሕይወት ዓላማ መሠረት ስለሆነ፡፡ ለ/ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመንፈሳዊ አመራርም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመ/ እና በረ/ የተሰጡት መልሶች በሰዎች ላይ ያለንን አመኔታ ያሳያሉ፡፡

12/ መልስህ ከዚህኛው በመጠኑ ሊለያይ ይችላል፡፡ ቀጥሎ ጠቃሚ የሆኑ አንዳንድ ነጥቦች ተሰጥተዋል፡-

1/ የሚረዳህን ምረጥ ተገቢውን ሥልጠና ስጠው፡

2/ ለእያንዳንዱ ሰው የግሉን ሥራ ስጥ

3/ በወቅቱና በቅደም ተከተሉ መሰረት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እያንዳንዱ የማለዳ ጸሎት እንዲኖረው አድርግ፡፡

4/ ተገቢውን ስልጠና ከሰጠህ በኃላ የክርስቲያናዊ ሥነ-ጽሑፍ የሚሆን ሰው አስቀምጥ፡፡

5/ እያንዳንዱ ሰው የድርሻውን እንዲወጣ ኃላፊነት ስጠው

6/ ፕሮግራሙን ለማሻሻል ውይይት እንዲያደርጉ ለስብሰባ ጥራቸው፡፡

7/ ለቤተክርስቲያኑ እድገትና ለነፍሳት ወደጌታ መምጣት እያንዳንዱ ሰው ያረገውን አስተዋጽኦ አሳያቸው

6/ ሌሎች ሰዎች ሸክሙን ስለሚካፈሉ

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## አድገው ሌሎችን ያሳድጋሉ

በሁለተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የሙሴን ምሳሌነት በመከተል ለመንፈሳዊ መሪ የሚሆኑ መመሪያዎችን ለማግኘት ከመቻላችንም በላይ በነዚህ መመሪያዎች መሠረት የተለየዩ የአመራር ስልቶችንና ባሕርያትን ተመልክተናል። በተጨማሪም አንድ መሪ አብሮ ስለሚሠራቸው ሰዎች ሊኖረው የሚገባ እምነትና ግምት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል።

በዚህ በሦስተኛው ክፍል ትምህርት ላይ ደግሞ የበርናባስን፣ የጳውሎስንና የጢሞቴዎስን ምሳሌነት በመከተል ተጨማሪ የመሪነት መመሪያዎችን በመቀበል፣ መሪዎች ራሳቸው አድገው ሌሎችን ለማሳደግ እንዴት እንደሚያግዙ እንመለከታለን።

ስለመሪነት በሚኖረን ጥናትም ልዩ ትኩረት የምንሰጠው ጉዳይ ይሆናል። ለቤተክርስቲያኑ ይበልጥ ማደግና ቀጣይነት እግዚአብሔር ያለውን እቅድ ያጠቃልላል። ይህንንም ይበልጥ ግልጽ የሚያደርጉልን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችንና አሰራሮችን እንመለከታለን። እንደ ክርስቲያን መሪዎች እንዴት ማደግና መብሰል እንዳለብን እንማራለን።

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የጳውሎስ ምሳሌነት
- መሪዎች ይጠራሉ፣ ያድጋሉ
- መሪዎች ሌሎች እንዲያድጉ ይረዳሉ

---------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የበርናባስን፣ የጳውሎስንና የጢሞቴዎስ ሕይወትን አስመልክቶ ለመሪነት የተሰጡ መመሪያዎችን።

- መሪዎች ይጠራሉ፣ ከዚያም በኋላ ያድጋሉ የሚለው መግለጫ ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ፡፡
- እንደ መንፈሳዊ አገልጋዮችና መሪዎች ሆነው እንዲያድጉ ሌሎችን የምትረዳበትን መንገዶች መግለጽ፡፡

-----------------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ 1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስን በጥንቃቄ አንብብ፡፡ በተጨማሪም የሐዋርያትን ሥራ ምዕራፍ 19ኝን አንብብ፡፡

2/ ትምህርቱን ለመከታተል ስለሚረዳህ የትምህርቱን አከፋፈልና ዓላማዎች በሚገባ አጥና፡፡ ትምህርቱን ካጠናቀቅህ በኋላም የሙከራ ፈተናውን በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት በትክክል ያልመለስካቸውን አስተካክል፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ- ጳውሎስ ምሳሌነት**

## ዓላማ 1 በበርናባስና በጳውሎስ መቀራረብ የሚታየውን የመሪነት መመሪያዎችን ለይቶ ለማወቅ

***"እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያስገርም ተአምራት ያደርግ ነበር"*** /የሐዋ 19፣11/፡፡ ጳውሎስ ለተለየ ዓላማ የተመረጠና በመንፈስ ቅዱስ ኃይልም የተሞላ ሰው ነበር፡፡ እኛ ተአምር ብለን የምንጠራቸው በሕይወቱ ከታዩት አስገራሚ የተባሉትን ነገሮች ያህል በቤተክርስቲያን ምሥረታ ታሪክና በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ልዩ የሆነ ሥፍራን ለሙላት የተመረጠውም አስገራሚ በሆነ መንገድ ነበር፡፡ ከጳውሎስ ሕይወት እግዚአብሔር በሰብአዊ መሪ መሣሪያነት እንዴት እንደሚሠራ እናያለን፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጳውሎስን ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመለከተው /ያኔ ሳኦል በመባል ነበር የሚታወቀው/ ሰዎችን የመማረክ ችሎታ ነበረው፡፡ የራሱ የሆነ ዓላማዎችና ግቦች ነበሩት፡፡ ለዓላማውም በርትቶ የሚሠራ ነው፡፡ ቆራጥ እርምጃ ይወስዳል፡፡ ዓላማውን ለመምታትም ሌሎችን ያደራጃል፡፡ በሌሎች መልካም መሪዎች የሚታዩትን ባሕርያት አጠቃልሎ ይዟል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን እነዚህ

ችሎታዎቹን ሁሉ የክርስቶስን ሥራ ለማፍረስ ነበር የሚያውላቸው /ሥራ 7፣51-8፡3ና 9፡2/። ይሁን እንጂ በአንድ ትልቅ የጦር መርከብ ላይ ጠጠር የመወርወርን ያህል ለአጉል ዓላማ የዋለው የጳውሎስ ጉልበትም በእግዚአብሔር እቅድ ፊት ደካማ እንደሆነ የምንመለከተው ብዙም ሳንቆይ ነው።

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን የማይለወጥና የማይሸነፍ እቅድ ስንመለከት ኢየሱስ በዚህ ምድር በነበረበት ወቅት አስደናቂ ነገሮችን አድርጓል። ሁላችንም እንደምንስማማበት ግን ከሥራው ሁሉ የሚበልጠው ለሰው ልጅ ደህንነት ሲል በመስቀል ላይ መሞቱ ነበር። እርሱ ወደ ክብሩ ከተመለሰ በኃላ ጀምሮት የነበረውን ሥራ እንዲያጠናቅቁ መሪ የሚሆኑ ሰዎችን ማሰልጠኑ ደግሞ ሁለተኛውና ዋነኛ ሥራው ነበር። ደቀ መዛሙርቱን አስተማራቸው። ከዚያም የመጨረሻ መመሪያዎችን ሰጣቸው፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እነዚህ መመሪያዎች የእያንዳንዱ ክርስቲያን ትውልድ ዋና መመሪያዎች ሆነዋል። ***"ሂዱና ስበኩ አስተምሩ"*** በማለት አዘዛቸው። ደቀ መዛሙርቱም ለኢየሱስ ታዘዙ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኂላም ሌሎች ብዙ መሪዎችን አፈሩ። ቀጣይነት ያለው የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴም ተጀመረ።

ቤተክርስቲያን በተቋቋመችበት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ብዙ መከናወን የሚገባቸው ጉዳዮች ነበሩ። ቅዱስ ቃሉም መንፈሳዊ እንቅስቃሴያቸውን /ማስተማርና መፈወስ የመሳሰሉትን/ ብቻ ሳይሆን ማደራጀት፡ ጠቃሚ ውይይቶችን ማድረግና አዳዲስ ሠራተኞችን መርጦ ማሰልጠን ያጠቃልል እንደነበር ይዘረዝራል። እነዚህ እንቅስቃሴዎችን ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ ከተሳተፉት መሪዎች አንዱ በርናባስ የተባለ ታማኝና አዋቂ ክርስቲያን ነበር። እርሱና ሌሎች በአንድነት ሆነው መደረግ ስላለባቸው ነገሮች ውሳኔ ያሳልፉ ነበር። በአዳዲስ አማኞች የእምነት ማጠናከሪያ ትምህርት ማስተማር፣ ድሆችን መርዳት፣ አዳዲስ ማሕበረ ምዕመናንን ማደራጀት ከእንቅስቃሴያቸው ጥቂቶቹ ናቸው። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ለእያንዳንዱ ሥራ ተገቢው ችሎታ ያላውን ሰዎች ይሾማሉ።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ለአሕዛብ ወንጌልን የማዳረሱን ተግባር ገና አልተያያዙትም ነበር። ማንኛቸውም ቢሆኑ ይህን ሥራ ለመምራት የተዘጋጁ ሆነው አልተገኙም። ደቀመዛሙርቱ ይበልጥ የለመዱት የራሳቸውን ወገኖች የአይሁዳውያንን ባሕል ነበር።

እግዚአብሔር አረማውያንንም በወንጌል እንዲደርሱ እንደሚጠብቅባቸው በሚገባ የተረዱ አይመስልም።

ይሁን እንጂ የማይሻረውና የማይለወጠው የእግዚአብሔር ዓላማ የሰዎችን ሁሉ መዳን የሚያጠቃልል በመሆኑ እነዚህን ዓላማዎች ለመፈጸም እግዚአብሔር ሰዎችን ጠራ፣ ሥራ ሰጣቸው፣ ዓላማውን እግቡ እንዲያደርሱም መራቸው።

ይህን የእግዚአብሔር እቅድ ለመፈጸም ደግሞ ጳውሎስ ትክክለኛው ሰው ሆኖ ተገኘ። እንደ እውነቱ ከሆነ የእውቀትና የጥበብ ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ነው፣ ገና ጳውሎስ በጌታ ከማመኑ በፊት እንኳ እነዚህ ነገሮች በጳውሎስ ሕይወት ውስጥ መኖራቸውን እግዚአብሔር አይቷል። ጳውሎስ የተለወጠው በአስደናቂና ባልተለመደ መንገድ ሲሆን ይህ እግዚአብሄር ፈቃዱን ለጳውሎስና ለሌሎች ይበልጥ ግልጽ የሚያደርግበት መንገድ ነበር። ***"ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእሥራኤል ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው"*** በማለት በሐዋ ሥራ 9:15 ላይ መሰከረለት።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለጳውሎስ /ሳውል/ በደማስቆ መንገድ ላይ በድምጽ እንደሆነ የተገናኘው ከሐዋ ሥራ 9፣1-6 ላይ ከተጻፈው ለመረዳት እንችላለን። ከዚያም በኃላ የምንመለከተው ጳውሎስ ለተጠራው ጥሪ ብቃት እንዲኖረው እግዚአብሔር በሌሎች ሰዎች አማካይነት ሲጠቀም ነው፡ ጳውሎስ ከክርስቲያኖች ጋር እንዲሠራ ቢጠራም እነርሱ ግን በእርሱ ላይ ጥያቄ ነበራቸው። እንዲያውም ተጠራጥረውታል፣ ይህም ይበልጥ ጳውሎስን ትሑት የሚያደርግበት የእግዚአብሔር መንገድ ነበር። የጌታ ወንጌል ተቃዋሚ እንደነበር ስለሚያውቁ በኢየሩሳሌም የነበሩ ደቀመዛሙርት ሊቀበሉት እንኳ አልፈለጉም። ስለበርናባስ ስናስብ ደግሞ በሐዋ ሥራ 9፣ 26-28 ላይ ከተጻፈው የምንረዳው እግዚአብሔር የመሪነት ችሎታ የሰጠው ሰው እንደሆነ ነው። ሌሎች አማኞችም ያከብሩታል፣ ያምኑታል። ይህንንም ሌሎችን ለመርዳት ሲጠቀምበት ነው የምናየው። መሪነቱ የተረጋጋና ለሰዎችም የሚያስብ በመሆኑ የጳውሎስ ወዳጅና ረዳት ሊሆን በቃ።

ግራ የተጋቡት ደቀ መዛሙርት "ይህ ክርስቲያኖችን ሲያንገላታና ሲያሳስር የነበረ አይደለም? ታዲያ እንዴት እርሱን ማመን ይቻላል?" በማለት ከእርሱ ለመራቅ ሲሞክሩ፣ በርናባስ ከሐዋርያት ጋር ጳውሎስን በማስተዋወቅ ለወንጌል አገልግሎት ስለ

መጠራቱ ገለጸላቸው፡፡ በርናባስ በሚችለው መንገድ ሁሉ ጳውሎስ አገልግሎቱን በጀመረባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የበርናባስ ወዳጅነትና እርዳታ ብዙ ጠቅሞታል፡፡

1/ ስለበርናባስ ምን ታስባለህ? ከበርናባስ ድርጊት የምትመለከተውን ቢያንስ አራት የመሪነት ባሕርያት ዘርዝር፡፡

2/ ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡ እግዚአብሔር በርናባስና ጳውሎስ የመሪነቱን ሥፍራ እንዲይዙ የፈለገው፡-

ሀ/ ጳውሎስ የተሻለ መሪ ስለ ነበርና የበርናባስን ስፍራ እንዲይዝ፣

ለ/ በቤተክርስቲያን ላለው ሥራ የተለያዩ መሪዎች ስለሚያስፈልጉ፣

ሐ/ ያለበርናባስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት ስለማይችል፡

በርናባስ ስለ ሰዎች የሚያስብ እንደነበር አስቀድመን ተመልከተናል፡፡ እንዲህም ስንል ራሱን በጳውሎስ ሥፍራ አስቀምጦ አየ፣ ስለዚህም ባልንጀራው ሆነ ማለታችን ነው፡፡ ሰዎችን ፈርቶ የሚወላውል ዓይነት ሰው አልነበረም፡፡ በተረዳው የእግዚአብሔር ፈቃድ ጽኑ አቋም ነበረው፡፡ ምናልባትም በበርናባስ ሕይወት ከሁሉ ይልቅ ጎልቶ የሚታየው የመሪነት ባሕርዩ መሪነትን ከሌሎች ጋር ለመካፈል ፈቃደኛ መሆኑ ነበር፡፡ ሌሎች መሪዎችን ለመርዳትና ለማገዝ የሚያመነታ ሰው አልነበረም፡፡ በእግዚአብሔር እቅድ ውሰጥ ጳውሎስ የተለየ ሥፍራ እንዳለው በርናባስ ያውቃል፡፡ በርናባስም እንዲሁ የራሱ ስፍራ አለው፡፡ በቤተክርስትያን ውስጥ የነበረው የተለያየ ሥራ የተለያዩ መሪዎች እንደሚያስፈልጉት በሐዋ ሥራ 11፣ 22-30 ከተጻፈው ለመረዳት እንችላለን፡፡

## የመሪነት መመሪያዎች ተግባራዊ ሲሆኑ

### ዓላማ 2 ስለ መሪነት የተማረውን ጳውሎስ እንዴት ተግባራዊ እንዳደረገ ለመግለጽ

ጳውሎስና በርናባስ በአንድነት ሆነው ውጤታማ ቡድን አደራጁ፡፡ ወንጌልን በማስፋፋትና ቤተክርስቲያንን በማቋቋም ሰፊ የአገልግሎት መስክ ነበራቸው፡፡ በርናባስ ሌሎች ሠራተኞችን ማሳደግ የሚወድ ሰው በመሆኑ ብዙም ሳይቆይ አንድ ሌላ ሰው ወደዚህ ቡድን እንዲቀላቀል አደረገ፡፡ በሐዋ ሥራ 12፣ 24 ላይ እንደምናነበው የዚህ ሰው ስም ዮሐንስ ሲሆን ማርቆስ ተብሎም ይጠራል፡፡

በመሠረቱ ዮሐንስ ማርቆስ ታላቅ ችሎታ ቢኖረውም የአገልግሎት ሥራ ግን በጣም አስቸጋሪ ነበር። ከለመደው የኢየሩሳሌም አኗኗሩ ተለይቶ በጉዞው አስቸጋሪነትና ውጣ ውረድም ተሰላቸ። ስለዚህም የመጀመሪያው ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን በማከናወን ላይ እያሉ በመካከል አቋረጠና ወደ አገሩ እንደተመለሰ በሐዋ ሥራ 13፡13 ላይ የተጻፈው ቃል ይነግረናል። በኋላም በርናባስ ይህን ይቅር በማለት ለሌላ አገልግሎት ይዞት ለመሔድ ቢስማማም ጳውሎስ ግን ፈቃደኛ አልነበረም /ሐዋ 15፣36-39/።

በዚህ ወቅት የጳውሎስ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በጌታ ሥራ ላይ ነበር፣ ስለዚህም እንደ እርሱ ሙሉ በሙሉ ለጌታ ሥራ ራሳቸውን ያልሰጡ ሰዎችን በትዕግሥት ማለፍ እማይችልበት ደረጃ የደረሰ ይመስላል። በርናባስ ግን የእግዚአብሔር ዓላማ የሚፈጸመው በሰዎች ተሳትፎ እንደነበረ በሚገባ ስለተገነዘበ በአንድ ወቅት ጳውሎስን እንደረዳው ሁሉ፡ አሁን ደግሞ ከወጣቱ አገልጋይ ጎን ሆኖ ሲረዳው እናያለን።

በጳውሎስና በባርናባስ መካከል አለመግባባት በተፈጠረበት ጊዜ እንኳ የእግዚአብሔር እቅድ ሲፈጸም ነው የምናየው። ምንም እንኳ በወቅቱ ጳውሎስ ዮሐንስ ማርቆስን ለመቀበል ባይፈልግም የኋላ ኋላ  ግን አሳቡን ለውጦ እንደ ሀቀኛ ሥራ ባልደረባው አድርጎ ተቀብሎታል /ቆላ 4፡10፡2ኛ ጢሞ 4፡11/። በጣም ደስ የሚለው ደግሞ ጳውሎስ የበርናባስን ምሳሌነት መቀበሉ ነበር፣ እርሱም በተራው ታላቅ የመሪነት ችሎታ ያለውን ወጣት መርጦ ሲያሰለጥነውና ሲመራው ማየት በጣም ደስ የሚል ነው። የዚህ ወጣት ስም ጢሞቴዎስ ይባላል።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ካስተማረ ወዲህ በአስተማሪና በተማሪ መካከል ስላለው መቀራረብ ትልቅ ምሳሌ የሚሆነን በጳውሎስና በጢሞቲዎስ መካከል የነበረው መቀራረብ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እንደጳውሎስ ጢሞቴዎስም በአይሁዳውያን ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ነበረበት። ድጋፋቸውም ያስፈልገው ነበር /ሐዋ ሥራ 16፡1-3/። አባቱ ግሪካዊ ስለነበር አኗኗሩ እንደ አይሁዳውያን ባሕል መሠረት አልነበረም። ለምሳሌ ያህል አልተገረዘም፣ መገረዝን አስመልክቶ በወቅቱ በቤተክርስቲያን ውስጥ አለመግባባት ተፈጥሮ ነበር። ያልተገረዘ ሰውን አንደ ጓደኛ በመቀበሉ ታላቁ ሐዋርያ ጴጥሮስ ነቀፋ ደርሶበታል /ሐዋ ሥራ 11፣ 1-3/፡

ስለዚህም በወቅቱ ጳውሎስ "እኔ ትኩረት የምሰጠው ለራሴ አገልግሎት ብቻ ነው" ለማለት በቂ ምክንያት ነበረው። እንዲህ ቢያደርግ ኖሮ ምናልባት ለሌላው ሰባኪ

ድጋፍም ሆነ የምክር አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አይኖርበትም ነበር። እርሱ ግን እንደዚያ አላደረገም። ጢሞቴዎስ ለአገልግሎት መጠራቱን ጳውሎስ ያውቃል። ወጣትነቱና ካደገበት ሕብረተሰብ የተነሳ ግን በችሎታው እንደሚገባ መጠቀም አልቻለም። ለዚህ ነው ለጢሞቲዎስ ***"መሪ መሆን ተገቢና መልካም አገልግሎት ነው። እርግጥ ነው ትንቢት ተነግሮልሃል፣ ይሁን እንጂ በእምነት መጽናትና ችሎታዎችን ማዳበር ግን ያንተ ፈንታ ነው"*** በማለት በ1ኛ ጢሞ 1፣18-19፣3፡1 ላይ *መመሪያ* የሰጠው። አላስፈላጊ ንትርክ ላለመፍጠር ሲል የአይሁዳውያን ሕግና ባሕል እንዲከበር ጳውሎስ ጢሞቲዎስን አሳስቦታል፣ ሌላው ቀርቶ እንዲገረዝ እንኳ ነግሮታል። ያም ሆኖ ግን ***"ወጣት በመሆንህ ማንም አይናቅህ"*** በማለት በ1ኛ ጢሞ 4፣12 ላይ ያበረታታዋል።

ምንም እንኳ አገልግሎት ቢበዛለትም የወንጌልን ዓላማ ለመፈጸም ከተሰማሩ መሪዎች አንዱ እንጂ ብቸኛ አለመሆኑን ጳውሎስ ዘንግቶ አያውቅም።፣በ2ኛ ጢሞ 1፣8-11 ላይ፣ ***"እግዚአብሔር ለቅድስና ጠርቶናል። ይህ እኛ ባደረግነው የተነሳ ሳይሆን ከርሱ ዓላማና ጸጋ የተነሳ ነው"።*** ከዘላለም ዘመናት በፊት ለሰዎች የተገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው። ***"እኔ… ሰባኪና ሐዋርያ አሕዛብንም አስተማሪ እንድሆን ተሾምሁ"*** በማለት ጳውሎስ ይናገራል።

ስለ ጥሪው እርግጠኝነት የሚሰማው ጳውሎስን የመሰለ ታላቅ መሪ ገና ጀማሪ ከሆነ ወጣት ጋር ስለ መሪነትን መወያየቱ የሚያስገርም ነው። **እኔ እራሴ በተጠራሁበት የእግዚአብሔር ዓላማና ፀጋ መሠረት አንተም ለመሪነት ተጠርተሃል** ይለዋል። ***"ጢሞቲዎስ ሆይ፣ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ። ስጦታህንም ችላ አትበል አነሳሳው ትጋ፣ በአገልግሎትህና በአኗኗርህ እደግ"*** ነው እያለ ይመክረዋል /1ኛ ጢሞ 4፡14-15፣ 6፡20፣2ኛ ጢሞ 1፣6/።

በዚህ ብቻ አላቆመም፣ እርሱም በተራው የእግዚአብሔርን *ሥራ* ለማድረስ ሌሎች *መሪዎችን* እንዲያሳድግ ወጣቱን *መሪ* ይመክረዋል። ***"…. ከእኔ የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ"*** በማለት ይነግረዋል /2ኛ ጢሞ 2፡2/።

3/ እዚህ ላይ ስለ በርናባስ አንዳንድ ዓረፍተ ነገሮች ተነግረዋል። ጳውሎስ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ የበርናባስን ምሳሌት እንደተከተለ በተሰጠው ስፍራ አስፍር።

ሀ/ በርናባስ የመሪነት ልምምዱን ለጳውሎስ ለማካፈል ፈቃደኛ ነበር።

ለ/ በርናባስ የጳውሎስን መጠራት ተቀብሏል።

ሐ/ የነበረውን ተቀባይነት መሠረት በማድረግ በርናባስ ሌሎች ሐዋርያት ጳውሎስን እንዲቀበሉት አድርጓል፡፡

መ/ ጳውሎስ አገልግሎቱን እንዲጀምር በርናባስ ረዳው

**መሪዎች ይጠራሉ ከዚያም ያድጋሉ**

**ዓላማ 3 መሪነት የመጠራትና የማደግ ምሳሌዎችን ለመግለጽ፡፡**

ጳውሎስ እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደጠራው በጣም እርግጠኛ ነበር፡ ምናልባትም ከዚህ በፊት ስለ አገልግሎት ስጦታዎች አጥንተህ ይሆናል፡፡ በተለያየ መስክ እንዲያገለግሉ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን መሪዎችን ሰጥቷል፡፡ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሰጣቸውም ነቢያትን፣ መጋቢዎችንና መምህራንን ወንጌላውያንንና ሐዋርያትን ያጠቃልላል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በርናባስ ጳውሎስን የተቀበለው እግዚአብሔር እንደጠራው ስላወቀ እንደነበረ መዘንጋት የለበትም፡፡ ጳውሎስን ለሌሎች ባስተዋወቀበት ጊዜ የተናገረውም ይህንኑ እውነት ነበር፡፡ ለጳውሎስም መጠራት እርግጠኛ መሆኑንም ሲገልጽ እንመለከታለን፡፡ ለአገልግሎቱ መሠረት የሆነውም ይኸው ጥሪ ነበር፡፡

ጳውሎስም እንዲሁ ጢሞቴዎስ ለአገልግሎት መጠራቱን ሲረዳለት እንመለከታለን፡፡ ይሁን እንጂ አዲሱ መሪ ማደግ፣ መዳበርና መብሰል የሚያስፈልገው ወጣት ነበር፡፡ ጢሞቲዎስ የመሪነት ችሎታውን ማዳበር፣ መንፈሳዊ እውቀትንና ሰዎችን መረዳትን እንዲሁም ሚዛናዊ ፍርድን መማር ያስፈልገዋል፡፡ ስለዚህም የመሪነት ችሎታውን እንዲያዳብር ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ብዙ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መመሪያዎች ሰጠው፣ ይህን ያደረገው ግን የጢሞቲዎስ መሪነት መለኮታዊ ማረጋገጫ እንዳለው ከተረዳ በኋላ ነበር /1ኛ ጢሞ 4፡14/፡፡ እንግዲህ ጳውሎስ በጢሞቲዎስ ውስጥ ያለውን የመሪነት ችሎታ የተረዳው በዚህ መለኮታዊ ጥሪ መሠረታዊነት ነበር ማለት እንችላለን፡፡

እርግጥ ነው ጳውሎስም ሆነ ጢሞቲዎሰ አገልጋዮችና ሰባኪያን ናቸው፡፡ ስለ እነርሱ የምናስበው በጣም የተለዩ ሰዎች እንደነበሩ አድርገን ነው፡፡ ሰባኪያን ስላልሆኑ፣ ሙሉ ጊዜያቸውን ስላልሰጡ መንፈሳዊ መሪዎችስ? እነርሱስ ጥሪ ይኖራቸው ይሆን?

በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ የተለየ ጥሪ ያላቸው ሰዎች መኖራቸው እውነት ነው። አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በእግዚአብሔር የተጠሩና እንደ መንፈሳዊ መሪነታቸው በምእመኑ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው አገልጋዮች ወይም መጋቢዎች ያስፈልጓቸዋል። ብዙውን ጊዜ እንደተለመደው እነዚህ ሰዎች የተካኑበት ልዩ ትምህርት ስለሚኖራቸው ሙሉ በሙሉ ጊዜያቸውን ለወንጌል አገልግሎት ይሰጣሉ። አባላቱ ሁሉ ሊከበሩ የሚገባቸውና ያከበሩዋቸው፣ አጥቢያ ቤተክርስቲያናቱን በተመለከተ በማንኛውም የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ላይ ምክር ሊጠየቁ ይገባል።

ሙሉ ጊዜን ለአገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ እያንዳንዱ ክርስቲያን ለተለያየ የአገልግሎት መስክ ሊጠራ ይችላል። ጥሪውና ስጦታው ያላቸው መሪዎች እንኳ ሳይቀሩ ተጨማሪ ትምህርትና እድገት እንደሚያስፈልጋቸው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ከጻፈው መልእክት ለመረዳት እንችላለን። ይህም ማንኛውንም ክርስቲያን በእምነትና በልምምድ እያደገ ይሄዳል ወደሚል ማጠቃለያ ያደርሰናል። ስጦታዎችንና ችሎታዎቻችንን ሙሉ በሙሉ በጌታ ሥራ እንድናውላቸው ካስፈለገ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ያስፈልጉናል፡-

1. የእግዚአብሔር ጥሪ በእኛም ሆነ በሌሎች ሕይወት ያለውን ዓቢይ ሥፍራ መገንዘብ፣
2. የራሳችንን ስጦታ ማዳበርና ሌሎችም ስጦታዎቻቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት፣

4/ ቀጥሎ ያሉት ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ የተናገራቸው ናቸው። ስለማደግ በሚናገሩት ፊት 1 ስለጥሪ እና ስለማደግ በሚናገሩት ፊት ደግሞ 2 ቁጥር በመጻፍ አመልክት

1/ እድገት 2/ ጥሪና እድገት

-----ሀ/ "እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ"/1ኛ ጢሞ 4፣7/

----ለ/ "በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል"/1ኛ ጢሞ 4፣14/

---ሐ/ "ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ"/1ኛ ጢሞ 5፣21/

---መ/ "አንድም እንኳ በአድልዎ አታድርግ" /1ኛ ጢሞ 5፣21/

----ሠ/ "የተሰጠህን አደራ ጠብቅ"/1ኛ ጢሞ 6፡20/

5/ ትክክለኛ የሆነውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ/ ለአገልግሎት መጠራት ስንል ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲሆኑና የአገልግሎት ተሳታፊ እንዲሆኑ መጠራታቸውን ማለታችን ነው

ለ/ አንድ ክርስቲያን ለመሪነት መጠራቱ የአገልግሎት መሠረት ነው።

ሐ/ በእግዚአብሔር የተጠራና አንዳንድ ስጦታዎች ያሉት መሆኑ አዲሱ መሪ መልካም መሪ ለመሆን የሚያስችል ነገር ሁሉ አለው ማለት ነው።

መ/ የእግዚአብሔርን ጥሪ ያገኘና እግዚአብሔር እንዲጠቀምበትም የሚፈልግ መሪ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም የእድሜ ልክ ትምህርትና እድገት ያስፈልገዋል።

6/ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብ፣ ከጥቅሶቹ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎችም መልስ ስጥ።

ሀ/ ኤፌ 4፣11-16 እግዚአብሔር ለሕዝቡ የአገልግሎት ስጦታዎችን የሰጣቸው ለምንድነው? ------------------------------

ለ/ 1ኛ ቆሮ 12፣4-11 የአገልግሎት ስጦታዎች የተሰጡት ለማነው? -----

ሐ/ ሮሜ 8፣29 አማኞች አስቀድሞ የተወሰኑት ለምንድነው?-----------

መ/ ኤፌ 1፣4-5፣11-12 እግዚአብሔር አማኞችን አስቀድሞ የወሰናቸው ለምንድነው? ------------

ሠ/ 2ኛ ጴጥ 3፡18 አማኞች ምን እንዲያደርጉ ነበር የታዘዙት -----

## የመሪው እድገት ሲገመገም

**ዓለማ 4 ስለ አመራር እድገት እውነተኛ መግለጫዎችን ለይቶ መረዳት**

የአመራር እድገትን እንደሚገባ ለመረዳት ከተፈለገ መሪ የሚለው ቃል ያካተተውን ሀሳብ መረዳት አለብን። የተለያዩ ነገሮችን እንዲያከናውኑ ሰዎች በእግዚአብሔር እንደሚጠሩ እናውቃለን። እግዚአብሔር ከጠራቸው ሰዎች አንዳንዶቹ መሪዎች አልነበሩም። ከሌሎች ልቀው የተገኙ ግለሰቦች ብቻ ነበሩ። ከእነርሱም ውስጥ ነቢያትን እናገኛለን። የነብያት ምሳሌ የሚሆኑት ነብዩ ኢሳያስና መጥምቁ ዩሐንስ ሲሆኑ፣ በብዙ ሰዎች ዘንድ ተሰሚነት ስለ ነበራቸው ለጌታ ክብር አስገኝተዋል። የነብያት ዋናው ተልዕኮአቸው እግዚአብሔርን መልእክት ማስተላለፍ እንጂ ከሌሎች ጋር ሆነው መሥራት አልነበረም።

እነዚህን እንደከዋክብት ደምቀው የሚታዩ ሰዎች ሌሎች በጣም ያደንቁአቸዋል። ብዙውን ጊዜ ታዋቂነት አላቸው፣ በጌታ ሥራም ውጤታማ ናቸው። ይሁን እንጂ የሰዎችን ትኩረት የሳቡት ወደራሳቸው ብቻ ስለሆነ ውሎ አድሮ ታዋቂነታቸው ይደበዝዛል፣ ምንም ትተው የሚያልፉት ዘላቂ ነገር አይኖራቸውም። ከእነርሱ በኃላ ሥራቸው እንዲቀጥል ሌሎችን ሲያሰለጥኑ አንመለከትም፣ የጀመሩት ሥራ ቢኖርም አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ ይቋረጣል።

አንዳንዶች መሪዎች ደግሞ አለቃ ወይም ተቆጣጣሪ ዓይነት ናቸው፡፡ ዋናው ትኩረታቸው የሥራው መሠረት ላይ ነው፡፡ አለቃ ስለ ሆኑ ብቻ ሌሎች አሜን ብለው እንዲታዘዙዋቸው ይፈለጋሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ታላላቅ ነገሮች ሲሠሩ ይታያል፡፡ ከእነርሱ በታች ያሉ ሰዎች ሁሉ ደስተኛ አይደሉም፡፡ ለሥራውም ስሜት የላቸውም፣ ለጊዜው የተሰጣቸውን ብቻ እንጂ ከዚያ አልፈው የሚታይ ተግባር አያከናውኑም፡፡

እውነተኛ መሪ ለመሆን የምትፈልግ ከሆነ ምናልባትም ከሌሎችም ጋር አብረህ ለመሥራት ሰዎችን የምትወድና የምታከብር መሆን አለብህ፡፡ ልብ ብለህ ብታስታውስ ጳውሎስ ጢሞቲዎስን የሚናገረው በሁለት አቅጣጫ ነው፡፡ በአንድ በኩል ስለ ራሱ ስለ ጢሞቴዎስ ሕይወትና ፀባይ መመሪያ ይሰጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለሌሎች ምን ማስተማር እንዳለበት ይነግረዋል፡፡ ይህን በሚመስል ሁኔታ ለጢሞቲዎስና መልእክቱን ለምናነብ ሁሉ አንድ መሪ ለሥራውና ለሕዝቡ ምን ያህል ማሰብ እንዳለበት ምሳሌ ይሰጠናል፡፡ አንድ መሪ ያለማቋረጥ ይማራል፣ ያድጋል፣ ሌሎች እንዲማሩና እንዲያድጉም ይረዳል፡፡

ከጳውሎስ መልእክቶች ምሳሌ የሚሆኑን አንዳንድ ነጥቦች፡-

**ጢሞቲዎስ የሚማረው፡-** እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሱን ማስለመድ፡፡

**ጢሞቲዎስ ለሌሎች የሚያስተምረው፡-** እግዚአብሔርን መምሰል ላሁኑና ለሚመጣው ሕይወት እንደሚጠቅም፡፡

**ጢሞቲዎስ የሚማረው፡-** በቃል፣ በሕይወት፣ በፍቅር እና በንጽሕና ለአማኞች ምሳሌ መሆንን፡፡

**ጢሞቴዎስ ለሌሎች የሚያስተምረው፡-** አንድ መሪ ያለነቀፋ መሆን እንዳለበትና መሪው የገዛ ራሱን ቤተሰብ ማስተዳደር የማይችል ከሆነ እንዴት የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ማስተዳደር ይችላል?

**ጢሞቲዎስ የሚማረው፡-** ከከንቱ ፍልስፍናና ክርክር መራቅ

**ጢሞቲዎስ ለሌሎች የሚያስተምረው፡-** በሰዎች መካከል የማያስፈልግ ጸብ፣ ጭቅጭቅና ሁከት መኖር እንደሌበትና እርስ በርስ መተማማትም እንደማይገባ ነው፡፡

**ጢሞቲዎስ የሚማረው፡-** ልክ እንደ ገዛ አባቱ አድርጎ መምከር እንጂ ሽማግሌውን ፈጥኖ እንዳይገስጽ። ወጣቶቹን እንደ ወንድሞቹ፣ በዕድሜ የገፉ ሴቶችንም እንደእናቶቹ መመልከት እንደሚገባው

**ጢሞቲዎስ ለሌሎች የሚያስተምረው፡-** ለራሳቸው ቤተሰብ በማሰብና መርዳት ሰዎች ሃይማኖታቸውን በተግባር ማሳየት እንዳለባቸው፣ እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ምሳሌዎች እውነተኛ መሪ ከሚመራቸው ሰዎች ብዙ የራቀ እንዳልሆነ የሚያሳዩ ናቸው። የራሳችንን ችሎታ ለማዳበር የተሻለ ዘዴ ሌሎች የራሳቸውን ችሎታ እንዲያዳብሩ በማድረግ ነው። ተገቢውን ሥልጠናና ትምህርት ስላገኙ ብቻ ወዲያውኑ ሌሎችን ለመምራት እንደሚበቁ አልነበረም ለጢሞቲዎስ የተነገረው። እውነተኛ መሪዎች ዘወትር እንደሚማሩና ሌሎችን ዘወትር እንደሚያስተምሩ ነበር የተነገረው።

7/ ትክክለኛውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት። የተሳሳተውን መግለጫ በማስተካከል በተሰጠው ስፍራ አስፍር።

*ሀ/ ታዋቂ ወይም ዝነኛ መሆን ማለት መሪ መሆን ማለት ነው።-----*

*ለ/ እውነተኛ መሪዎች የሌሎችንም ችሎታ ያከብራሉ። ---------------*

*ሐ/ አንድ መሪ ሌሎችን ከመርዳቱ በፊት የራሱን ስጦታዎች ሙሉ በሙሉ ማሳደግና ማዳበር አለበት። --------------------*

*መ/ የጳውሎስ አመራር ስልት ልክ የአንድ "አለቃ" ዓይነት ነበር። --------*

*ሠ/ አንዳንድ ታዋቂና ዝነኛ ሰዎች ጥሩ መሪዎች አልነበሩም። ------------*

***መሪዎች ሌሎችን ያሳድጋሉ***

***ዓላማ 5 ሌሎች ስጦታዎቻቸውንና ችሎታዎቻቸውን እንዲያዳብሩ አንዳንድ መሪዎች የተጠቀሙባቸውን ዘዴዎች በምሳሌነት ለመጥቀስ***

ከበርናባስ፣ ከጳውሎስና ከጢሞቲዎስ የምንማረው ምሳሌነት ለዘመናችን መሪዎች የሚጠቅሙ ምሳሌዎችን ነው። ዛሬም ቢሆን እግዚአብሔር በሰዎች በኩል ስለሚሠራ ለዚህ አገልግሎት ሰዎችን ይጠራል፣ የተጠሩትም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ

ያድጋሉ። ከዚያም የመሪነትን ኃላፊነት ለመቀበል ዝግጁ ሲሆኑ፣ የመሪነትን ስፍራ ይይዛሉ።

የረጅም ጊዜ ልምምድ ያላቸው በሳል መሪዎች ሰዎችን እንዴት ለመሪነት እንደሚመርጡና እንዴት ሊያሳድጉዋቸው እንደሚችሉ ያውቃሉ። ወጣት ክርስቲያኖችና ጀማሪ መሪዎች የሌሎችን ምክርና ምሪት መቀበል ይኖርባቸዋል።

ምናልባትም በመሪነት አገልግሎትህ ማከናወን ከሚገቡህ ነገሮች ዋናው ሌሎች የመሪነት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል የወጣቶች መሪ ከሆንህ ሌሎች ወጣቶች በቤተሰብ አባሎች፣ በትምህረት ቤት ጓደኞቻቸው ላይ ኃላፊነት እንዲኖራቸው ልታሳድጋቸው ትችላለህ። በመካከለኛ ዕድሜ ያሉትን ወንዶች የምትመራ ከሆነ ደግሞ በቤተሰባቸውና በሥራ ቦታቸው መምራት እንዲችሉ ልትረዳቸው ትችላለህ። እያንዳንዱ ክርስቲያን የተለያየ የአመራር ሥልጠና ያስፈልገዋል።

8/ ቅዱሳት መጽሐፍት የሚያስተምሩት ክርስቲያን መሪዎች፡-

ሀ/ ከሚመራቸው ሰዎች እድሜ የበለጡ እንዲሆኑ

ለ/ ለመጋቢነት አገልግሎት የተጠሩ እንዲሆኑ

ሐ/ እርስ በርስ እንዲከባበሩና እንዲረዳዱ

መ/ መሪ መሆንን እንዳይፈልጉ ያስተምራሉ

9/ ውጤታማ የሆነ መሪነት ወጣት መሪዎችን የማሳደግ አስፈላጊነት ይረዳሉ። የመሪነት ችሎታ ያላቸው ወጣቶችን ከመረጡ በኃላ፡-

ሀ/ የመሪነት ሥልጠና ወደሚያገኙበት ይልኳቸዋል።

ለ/ እድገታቸውንና ብስለታቸውን ለጥቂት ዓመታት ይከታተላሉ።

ሐ/ እየሰሩ መሰልጠን የሚችሉበት ሁኔታን ያመቻችላቸዋል።

መ/ የተለያየ የኃላፊነት ሸክምን ይጭኑባቸዋል።

## እንዴት ሌሎችን ማሳደግ እንደሚቻል

### ዓላማ 6 የመሪነት ውጤታማ የሆኑ መመሪያዎችን ለመግለጽ

ስለ መሪነት የተጻፉ የመጀመሪያዎቹ መጻሕፍት ትኩረታቸው ንግድ-ነክ ተቋሞችና የኢንዱስትሪ ውጤቶች ላይ ሲሆን፣ እነዚህ መጻሕፍት የሚናገሩት ሠራተኞቹ

የመሪውን ወይም የአለቃውን ፈቃድ መፈጸም እንደነበረባቸው ነው። እነዚህን መጻሕፍት ያነበቡ አንዳንድ ክርስቲያን መሪዎችን ከመጽሐፍቱ ያገኙዋቸውን አንዳንድ ዘዴዎች ሥራ ላይ ማዋል ጀመሩ። ስለ መሪነት የተደረጉ አብዛኛዎቹ ጥናቶች ትኩረት የሰጡት የሥራ ሞያን በሚመለከቱ ዘዴዎች ላይ ነበር። ውጤታማ በሆነ መንገድ የጌታን ሥራ ለመሥራት ፍላጎት የነበራቸው አንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ሥልጣናቸውም የማጠናከርና ሌሎችን የመቆጣጠር ፍላጎት አደረባቸው። በዚህም ምክንያት አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ነገሮች እንደሚያከናውኑ ተከታዮቻቸውን ሰዎችን መቀስቀስና ማነሳሳት ጀመሩ።

ዛሬ ግን የኢንዱስትሪ መሪዎች፣ የመንግሥትና የትምህርት ተቋሞች መሪዎች እነዚህ ዘዴዎች ተገቢውን ውጤት ሊያስገኙ እንዳልቻሉ ተስማምተዋል። ሌሎች የተሻሉ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችን እንዳገኙ ይናገራሉ። እነዚህ አዳዲስ የአመራር ዘደዎች በመባል የቀረቡት መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች ከተጠቀሙባቸው የአመራር ዘዴዎች ጋር በጣም ተመሳሳይ መሆናቸውን ስንረዳ ብዙም ሊያስገርመን አይችልም።

መሪነትን በተመለከተ ረጅም ጊዜ የወሰዱ ብዙ ጥናቶችን ያካሄዱ በመጨረሻ አንድ መንገድ ብቻ መሠረታዊና ውጤታማ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህም ለሰዎች በማሰብና ጥንቃቄ በማድረግ ላይ የተመሠረተ የአመራር ስልት እንደሆነ ይናገራሉ። እኛም ይህን እውነት ከመጽሐፍ ቅዱሳችን ስለተረዳነው፣ በጥበብና ፍሬያማ በሆነ መንገድ ከሰዎች ጋር ለመሥራት ከቅዱሳት መጻሕፍት የበለጠ የተሻለ መመሪያ ሊኖር እንደማይችል ተገንዝበናል።

10/ ትክክለኛውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ/ ቀደም ብለው ስለአመራር ተጽፈው የነበሩ የዘመናችን መጻሕፍት አጠንክረው የሚያመለክቱት ሰዎች የአለቃቸውን ፈቃድ እንዲያደርጉ መቀስቀስና መነሳሳት እንዳለባቸው ነበር።

ለ/መሪዎቻቸው መልካም ነው ብለው የሚያምኑበትን የሚሠሩ ሰዎች በአጠቃላይ ሥራቸው የተሳካላቸው ናቸው።

ሐ/ መሪነትን አስመልክቶ በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንድ ዓይነት የአመራር ስልት ብቻ መሠረታዊና ፍሬያማ መሆኑን አረጋግጠዋል፣ ይኸውም ለሰዎች ማሰብ ወይም መጠንቀቅ ነዉ።

መ/ መሪዎች ሥራቸውን ለማከናወንና ለሚመሩዋቸውም ሰዎች የሚያስቡ ከሆነ ሸክማቸውን ከሌሎች መሪዎች ጋር እየተጋሩ ነው ማለት ነው፣ ከዚህም የተነሳ ሸክማቸው ይቀልላቸዋል፣ ዓላማቸውም ግቡን ይመታል፣ የሕዝቡም ችግር መፍትሔ ያገኛል (ከሙሴ ምሳሌት እንደተረዳነው።)

መሪነትን አስመልክቶ ዕውቀቱ ባላቸው ባለሞያዎች የተጻፉት መጻሕፍት ያቀረቡዋቸውን የአሰራር መንገዶች ስንመለከት ደግሞ ሁሉም ነጥቦች ከበርናባስና ከጳውሎስ አሰራር ጋር የሚጣጣሙ ሆነው እናገኛቸዋለን።

**በምትመራቸው ሰዎች ውስጥ ያለውን ችሎታ ልብ ብለህ አስተውል፦** በክርስቲያናዊ አሰራር ይህ በሌሎች ሕይወት ያለውን የእግዚአብሔርን ጥሪ እና ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መለኮታዊ ስጦታ ያጠቃልላል።

**ሰዎች የተለያዩ መሆናቸውን ተቀበል፦** አንዳንድ ጊዜ የተለያየ አመለካከት ሁሉ ችግር እንደሆነ አታስብ። ምንም እንኳ የጳውሎስና የጢሞቲዎስ አገልግሎት የተለያየ ቢሆንም፣ ሁለቱም ተቀባይነት እንዳገኙና ለጌታም ሥራ የየግላቸውን አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ አትዘንጋ።

**የሰዎች የተለያዩ ባሕርይ ወይም ስጦታ ላሉበት ሁኔታ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እንዲቀበሉ እርዳቸው፦** ተቀባይነት እንዳገኙ እንዲሰማቸው በሌሎች መሪዎች ፊት ድጋፍህን ስጣቸው። ተገቢ ሥፍራውን እንዲያውቁም አግዛቸው። እንደ አሕዛብ ሐዋርዋያነቱ ጳውሎስ ተገቢውን ሥፍራ በማወቁ ደስተኛ መሆኑን እንደተናገረው አስተውል።

**ከእነርሱ የሚጠበቀውንና የሚፈለገውን በትክክል እንዲረዱ አግዛቸው፦** እያንዳንዱ ሰው የግሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችል ሁኔታው የሚጠይቀውን ዝንባሌና ባሕርይ አብራርተህ አስረዳ። ከምትጠብቅባቸው ወይም ከምትፈልግባቸው ነገር በስተጀርባ ያለውን ምክንያት አሳውቃቸው። አዳዲሶቹ ሰዎች ስለ ሌሎቹ ማንነት እንዲያውቁ እርዳቸው። ይህንንም ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ከላካቸው መልእክቶች መመልከት

ይቻላል፣ስላለፈው ሲነግረውና ለወደፊቱም ሲያዘጋጀው እንመለከታለን፡፡ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ ግልጽ መመሪያና ሥልጠና ነበር የሰጠው፡፡

**እንደ ሠራተኝነታቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ ሰዎች አድርገህ እንደምታስብላቸውና እንደምትጠነቀቅላቸው ይወቁ፡-** ለሰዎች ማሰብ ወይም መጠንቀቅ ስንል ሐቅና እውነት ባለበት ሁኔታ እንጂ እንዲሁ ላይ ላዩን በማስመስል አይደለም፡፡ ይህንን በአንደበታችን እንደምንገልጸው ሁሉ በድርጊትና በምናሳየው ዝንባሌም ልንገልጸው እንችላለን፡፡

**ለመልካሙ ሥራቸው አድናቆትና አክብሮትህን ግለጽላቸው፡-** እዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ ይገባናል፡፡ አድናቆትን መግለጽ ስንል በግለሰቡ ዙሪያ ብቻ የሚሽከረከር አድናቆት ማለታችን አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል፡- **እወድሃለሁ በጣም ጥሩ ሰው ነህ** ብትለው ለጊዜው ደስ ደስ ሊለውና መልካም ስሜትም ሊሰማው ይችል ይሆናል፡፡ ስጦታዎቹንና ችሎታዎቹን በማዳበር ደረጃ ግን ምንም አይጠቅመውም፡፡ የግለሰቡን ችሎታና አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብሃል፡፡ ሰዎች ስላከናውኑት ተግባር አድናቆትና ታዋቂነትን ይፈልጋሉ፡፡ ለሰዎች አድናቆትን የመግለጫ መንገድ፡- በእውነቱ ያወጣኸው ፕሮግራም በጣም ግሩም ከመሆኑ የተነሣ ለችግራችን ትክክለኛ መፍትሔ ሊሆነን ችሏል የሚለው ሊሆን ይችላል፡፡

**ሌሎችን ማሳደግና ማዳበር የአንተኑ የራስህን ውጤታማነት እንደሚያሰፋው በትክክል ተረዳ፡-** ፉክክር ወይም ውድድር በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ምንም ሥፍራ የለውም፡፡ አንድ መሪ ሌሎች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ከመርዳት ወደኋላ የሚል ከሆነ የራሱ ችሎታም ይጫጫል፡፡ መሪዎች ትኩረታቸው ሁሉ በራሳቸው ላይ ስለሆነና ጠንካራ ባለሥልጣን ስለሆኑ ብቻ በሌሎች ዘንድ ታማኝነትን፣ በራሳቸውም ሆነ በጌታ ፊት በራስ የመተማመንን ችሎታ ያዳብራሉ ማለት አይደለም፡፡ ለራሳችን ዋጋ መስጠቱ መልካም ነው፡ ግን ይህ ሊሆን የሚገባው የጌታ ባርያዎች መሆናችንን ሳንዘነጋ ነው፡፡

በሙያው ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚነግሩን ለራሳችን የሚኖረን ግምት ሌሎች ለእኛ ያላቸው ግምት ውጤት ነው፡፡ ለራሳችን ክርስትያናዊና ትክክለኛ ግምት

የምናዳብርበት የተሻለው መንገድ ሌሎች ለጌታ ሥራ ጠቃሚ መሆናቸውን እንዲረዱና ተገቢውን ግምት ለራሳቸው እንዲያዳብሩ በማድረግ ነው፡፡ አንድ መሪ ተቀባይነቱ ማደግና ሥራውን ፍሬያማ ሊሆን የሚችለው ሌሎችን ሲረዳና የእርሱን ያህል የሥራ ብቃት ባላቸው ሰዎች ሲከበብ ነው፡፡ መሪው አንድ ቀን ሥፍራዬን ይነጥቁኛል የሚል ከሆነና የሌሎችን አስተዋፅኦ ግምት ውስጥ የማያስገባ ከሆነ ራሱም ደካማ ይሆናል፡፡

**በተቻለ መጠን ያቀድከውን ግብና የወሰንከውን ውሳኔ ለሌሎችም አሳውቅ፡-** ራስህ ያቀድከውን ዓላማ እግብ ለማድረስ በሰዎች ከመጠቀም ይልቅ ዓላማው የግልህ ብቻ ሳይሆን የእነርሱም ዓላማ መሆኑን እንዲያምኑበት አድርግ፡፡ በአገልግሎት የሚረዳህ እንዳልሆነ ግልጽ አድርገው፡፡ የራስህን ዓላማ የሚመስል እነርሱም የራሳቸው ዓላማ ይኖራቸዋል፡፡ የራስህ ዓላማ እግብ ላይ ለማድረስ የምትችለው እነርሱም አስታወቀሀቸው ዓላማ ላይ ሲደርሱ ብቻ ነው፡፡ እንደ አንድ አካል ሆኖ ለመሥራት ይህ መሠረታዊ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ እነርሱ የወሰኑትን ውሣኔ ብቻ ሌሎች በአገልግሎታቸው እንዲረዷቸው የሚፈልጉ መንፈሳዊ መሪዎች ውለው አድረው መውደቃቸው የማይቀር ነው፡፡ ከሌሎች ጋር አብረው ውሳኔ የሚያሳልፉ መንፈሳዊ መሪዎች ግን ይሳካላቸዋል፣ ይከናወንላቸዋል፡፡ እንደዚህ ዓይነት መሪዎች ሥራዬን ሥራልኝ የሚሉ ሳይሆን የጌታን ሥራ አብረን እንሥራ የሚሉ ናቸው፡፡

**ሰዎች ሥርዓት አክባሪና ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ እርዳቸው፡-** ትክክለኛ መመሪያ ከተሰጣቸውና በሚስማሙበት እቅድ መሠረት የሚሠሩ ሰዎች የተሻለ የሥራ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ ተገቢውን የሥራ እቅድ ማውጣት እንጂ ሕግና ደንብ ማብዛቱ ውጤት አይኖረውም፡፡ አንድ ትክክለኛ መሪ እቅድ እንዴት እንደሚያወጣና ያወጣውን እቅድን መቼ እንደሚያጠናቅቅ እንደዚሁም አብረውት የሚሠሩትንና ለሥራው የሚያስፈልጉትን ነገሮች የማደራጀት ግዴታና ኃላፊነት አለበት፡፡

**ራስህን ለመገምገም የሚረዱ ጥያቄዎች፡-** ከጌታ ምን ዓይነት ስጦታዎች ወይም ችሎታዎች እንደተቀበልህ ታስባለህ? እስከ አሁን ድረስ ስለ መንፈሳዊ መሪነት የሰጠናቸው ተከታታይ ትምህርቶች እነዚህን ችሎታዎችህንና ስጦታዎችህን እንድታዳብር ያደረገልህ አስተዋጽኦ አለ? በመሪነትህ እንድታድግ የሚረዱህን ከመጽሐፍ

ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ምን ተማርህ? ከተማርካቸው ውስጥ ሌሎችን ለመርዳት የምትጠቀምባቸው ነገሮች አሉ?

11/ ትክክለኛ የሆነው መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡

ሀ/ አንድ መሪ እንደሚገባ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የሚመራቸውን ሰዎች ችሎታ መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ሥራው እንዲሳካና የሰዎችም ችግር መፍትሔ እንዲያገኝ ለተለያዩ ሁኔታዎች ያላቸውን በጎ ገጽታ እንዲቀበሉ ማድረግ ከአንድ መሪ የሚጠበቅ ነው፡፡

ሐ/ ለሰዎች በመደጋገም እንደምትወዳቸው የምትነግራቸው ከሆነ፣ ስለ አሠራር ዘዴህ አልገለጽክላቸውም ማለት ነው፡፡ ይህንንም እነርሱ ራሳቸው ይረዱታል፡፡

መ/ ለሰዎች አስተዋጽኦ አድናቆትንና እውቅናን ስትሰጥ ከግለሰቡ ጋር እንጂ ከሥራ ወይም ካከናወኑት ተግባር ጋር መያያዝ የለበትም፡፡

12/ መንፈሳዊ መሪዎች የሌሎችን የመሪነት ችሎታ ሲያዳብሩ ከሚከተሉት ውስጥ አጥብቀው ሊረዱት የሚገባው የትኛውን ነው?

ሀ/ መሪዎች ሌሎች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርጉት ጥረት ውሎ አድሮ የራሳቸውን ታዋቂነት እንደሚያደበዝዘው፡፡

ለ/ መሪዎች የሌሎችን አስተዋጽኦና ለሥራው መሳካት የሚሰጧቸውን ጥቆማ ችላ የሚሉ ከሆነ ከሩቅ ሆነው ቢቆጣጠሩ ይበጃቸዋል፡፡

ሐ/ መሪዎች የራሳቸው ማንነትና ሥልጣን ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ ሌሎች ያምኑባቸዋል፡፡

መ/ አንድ መሪ ስለ ራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ማዳበር የሚችለው ሌላው ሰው ስለ ራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያዳብር ሲረዳ ወይም ሲያግዝ ነው፡፡

13/ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር ፍሬያማ የአመራር መመሪያዎችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ውጤታማ የአመራር መመሪያ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ/ አንድ መሪ አስቀድሞ እቅድ ያወጣል፣ እቅዱን መቼ እንደሚያጠናቅቅም ይወስናል፣ ለእቅዱ ተግባራዊ መሆን የሚረዱትን ሰዎችና ነገሮችን ሁሉ ያደራጃል፡፡

ለ/ አንድ ፍሬያማ መሪ ጥርት ያለ መመሪያን ይሰጣል፣ ባወጣው እቅድ መሠረትም በርትቶ ይሠራል፡፡

ሐ/ ውሳኔዎችን ብቻውን የሚያሳልፍ፣ ኃላፊነትን ሁሉ በግሉ የሚይዝ መሪ ሌሎችን ይማርካል፡፡

መ/ አንድ መሪ ውሳኔ እንዲያሳልፉ ሌሎችን ይጋብዛል፣ ግቡ የእርሱ ሳይሆን የጋራቸው መሆኑንም ያስረዳል፡፡

## የሙከራ ፈተና

1/ ተቀባይነት ያለውና የተከበረ መሪ እንደ መሆኑ መጠን በርናባስ የሚከተሉት ጠቃሚ የመሪነትን መመሪያዎችን በተግባር አሳይቷል፡፡ የነበረውን ተቀባይነት ምክንያት በማድረግ፡-

ሀ/ እርሱ የሚስማማበትን እንዲቀበሉ በሐዋሪያነት ሥልጣኑ ተጠቅሟል

ለ/ የሌሎችን ችሎታ ለማዳበር እገዛ አድርጓል፡፡

ሐ/ ለቤተሰቡ አባሎች ከፍተኛውን ሥፍራ ሰጥቷል፡፡

መ/ ዝናውንም ሆነ ተቀባይነትን እንዳያጣ ጥንቃቄ አድርጎአል፡፡

2/ ጳውሎስና በርናባስ በጣም የተለያዩ ሰዎች መሆናቸው እውነት ስለመሪነት የሚያስተምረን ሌላው ነገር፡-

ሀ/ የአንድ መሪ ውጤታማነት ውሱን መሆኑን

ለ/ ከፍተኛውን ሥልጠና የሚያገኙ ወጣት መሪዎች ሊወጣቸው እንደሚችል፡፡

ሐ/ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው የተለያየ ችግር የተለያዩ መሪዎች የሚያስፈልጉት መሆኑን

መ/ ጥቂት ጥሩ መሪዎችን ለማግኘት ብዙ መሪዎችን ማሰልጠን አስፈላጊ መሆኑን፡፡

3/ በወቅቱ ጳውሎስ፣ ዮሐንስ ማርቆስን አለመቀበሉ ይበልጥ ትኩረት የሰጠው ለአገልግሎቱ እንደነበር ያሳየናል፡፡ በርናባስ ግን በአገልግሎት ዘላቂና ፍሬያማ ውጤት ለማግኘት በተፈለገ መደረግ ያለበት ነገር፡-

ሀ/ መሪዎች በቁጥር አነስተኛ እንዲሆኑ ፖሊሲ ማውጣት

ለ/ የአስተማሪውን ውጤታማነት የሚያዳብሩ የሰለጠኑ መሪዎችን ማፍራት

ሐ/ እንደ እርሱ ሁሉ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ግትርነት የማያስፈልገው መሆኑን የሚሰማቸውን የወንጌል መልእክተኞችን ቡድን ማደራጀት

መ/ በወጣት መሪዎች ምክንያት ሥጋት ላይ የማይወድቁ መሪዎችን ማጠናከር

4/ ከሚከተሉት ውስጥ ከኢየሱስ እንዲሁም ከበርናባስና ከጳውሎስ የምንመለከታቸውን የመሪነት ስልት ይበልጥ የሚያሳየን የትኛው ነው?

ሀ/ መመሪያና ምክር መስጠት፣ ከመምህሩ እንዲማሩ፣ የተማሩትን በተግባር እንዲያሳዩ ማድረግ፣ ውጤታቸውን መገምገም፣ የሚሠሩትንም ሥራ መስጠት

ለ/ ሥራውን በመመልከት እንዲማሩ ዕድል መስጠት

ሐ/ ስለ ክርስቲያናዊ መሠረታዊ ትምህርትና አመራር፣ ስለ ሞራል፣ ስለ አገልግሎትና ሥራን ለእግዚአብሔር አሳልፈው እንዲሰጡ ተደጋጋሚ ትምህርት መስጠት

መ/ መንፈሳዊ ዝንባሌና ተገቢው ትምህርት ያላቸውን መምረጥ፣ ለአጭር ጊዜ አብረው እንዲቆዩ ማድረግ፣ ለአገልግሎት እንዲወጡ ማድረግና የሚቻል ከሆነ የሥራ ውጤታቸውን አልፎ አልፎ መገምገም

5/ የጳውሎስን አመራር ዘዴ ይበልጥ ትክክል ነው ለማለት የምንችለው፡-

ሀ/ ለመሪነት ያበረታታል፣ ይህንም የሚያደርገው ፍላጎታቸውን በማየት ነበር

ለ/ የአገልግሎት ችሎታን ለመመልከት ንቁ ነበር፣ ጥሪ ያላቸው ሰዎች ሥራቸው እንዲጀምሩ ያደፋፍራል

ሐ/ ለጥሪው ምላሽ መስጠትን ለግለሰቡ ይተዋል

መ/ በተለይም ደግሞ ሰዎች የመሪነት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያደርገው ከብዙ ጊዜ ቆይታ በኃላ ነበር

6/ **"መሪዎች ይጠራሉ ከዚያም ያድጋሉ"** የሚለውን ዐረፍተ ነገር ይበልጥ ሊያብራራልን የሚችለው፡-

ሀ/ የአንድ መሪ ጥሪ ከእድገቱ ይበልጣል

ለ/ መማር የመጠራትን ያህል አስፈላጊ አይደለም

ሐ/ መሪነት የእግዚአብሔርና የሰዎች ኃላፊነት ነው

መ/ ከጥሪው መሪነትን ያገኛል፣ ከዕድገቱ ደግሞ ውጤታማ የሆነ አመራርን ችሎታ ያዳብራል፡፡

7/ መንፈሳዊ መሪዎች ለዚህ ኃላፊነት የተጠሩት በልዑል እግዚአብሔር መሆኑን በመገንዘብ፣ ለሌሎች መሪዎችና የቤተክርስቲያን አባላት ምላሽ መስጠት የሚገባቸው፡

ሀ/ በጥሪያቸው መሠረት እንዲንቀሳቀሱ ሊያበረታቷቸው ይገባል

ለ/ ስለ መሪነትና አስተዳደር ሥልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት

ሐ/ የመሪነት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የተማሩትን ሥራ ላይ ማዋል የሚችሉበትን መንገድ በማዘጋጀት

መ/ ለመሪነት ሥልጠና ሊያገኙ ወደሚችሉበት ትምህርት ቤት በመላክ

8/ ይህ የመጠራትና የማደግ ጉዳይ ወደሚከተለው ማጠቃለያ ይመራናል፡፡ ይኸውም ችሎታችን ሙሉ በሙሉ በጌታ ሥራ ላይ ለማዋል ከተፈለገ በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጥሪ አስፈላጊነት መገንዘብና፡-

ሀ/ የራሳችንን ስጦታዎች ማዳበር

ለ/ የሌሎችንም ጥሪ መቀበልና ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት

ሐ/ ሌሎችን ማገልገልና ስጦታዎቻቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት

መ/ ስጦታዎች ማዳበርና ሌለችም የራሳቸውን እንዲያዳብሩ መርዳት

9/ ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛ መሪ ያልሆኑትንና ትክክለኛ መሪ የሆኑትን የበለጠ የሚያመለክቱት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ ለራሳቸው ትኩረት የሚሰጡ ተዋንያን ዓይነት ናቸው፣ ስለ ሥራው ቀጣይነት ምንም እቅድ የላቸውም፡፡

ለ/ የአለቅነት መንፈስ አላቸው፣ ስለ ሥራው እንጂ ስለ ሰዎች አይቸግሩም

ሐ/ እውነተኛ መሪዎች ለሥራውና ለሰዎች ያስባሉ፡፡ ራሳቸው ያድጋሉ ሌሎችንም ያሳድጋሉ

መ/ ከላይ ያየሀቸው ሀ፣ለ እና ሐ የሁለቱን ልዩነት በሚገባ ያመለከታሉ

10/ ቀደም ብለው ስለ መሪነት የተጻፉት መጻሕፍት ሰዎች የመሪውን ፈቃድ እንዲፈጽሙ መገፋፋትና መነሳሳት እንዳለባቸው ያመለክታሉ፡፡ በቅርቡ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ግን እነዚህ ዘዴዎች፡-

ሀ/ በጣም ውጤታማ መሆናቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ለ/ ተገቢውን ውጤት እንደሚያስገኙ አረጋግጠዋል

ሐ/ በፍጹም ውጤታማ አለመሆናቸውን አረጋግጠዋል

መ/ ምናልባት በድሮ ጊዜ ውጤት ሊኖራቸው እንደሚችል አረጋግጠዋል

11/ የዘመኑ ጥናት እንደሚያመለክተው ግን በጣም መሠረታዊና ውጤታማ የሆነነው የመሪነት ስልት፡-

ሀ/ አመራሩ በብዙኃኑ እንዲሆን ሚያደርግ ነው፡፡

ለ/ አስተዳደሩ በጋራ እንዲሆን የሚያጠናክረው ነው፡፡

ሐ/ አስተዳደሩ በተወሰኑ ባለስልጣኖች እጅ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

መ/ ለሰዎች በመጠንቀቅና በማሰብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

12/ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር የቀሩት ከአመራር ባለሞያዎች የተወሰዱ ናቸው፡፡ ከአመራር ባለሞያዎች ያልተወሰደው የትኛው ነው?

ሀ/ የምትመራቸውን ሰዎች ስጦታና ችሎታ አስተውል

ለ/ ሰዎች የተለያዩ መሆናቸውን ተቀበል

ሐ/ ሰዎች የሚጠበቅባቸውንና የሚፈለግባቸውን በትክክል እንዲረዱ አድርግ

መ/ ምንም እንኳ የተለያዩ ቢሆኑም ሰዎች ለሚፈለገው ተግባር የግላቸውን አስተዋጽኦ ሊኖራቸው እንደሚችል አሳውቃቸው

ሠ/ ለችግሮች መፍትሔ መሻቱንም ሆነ ውሳኔ መስጠቱን ለግልህ አድርገው

13/ የቤተክርስቲያኑ መሪ ሌሎችን ለማሳደግ በጣም ይፈራል ለዚህም ምክንያቱ ከእርሱ ይልቅ የሰዎች ትኩረት እነርሱ ላይ ይሆናል የሚል ሥጋት ስላለው ነው፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ እንደዚህ ዓይነቱን የቤተክርስቲያን መሪ ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርጉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ ለሰዎች እንደሚያስብ ማሳወቅ

ለ/ ሌሎችን ማሳደግ የራሱን ፍሬያማነት ማሳደግ እንደሆነ መረዳት

ሐ/ በሚቻለው ሁሉ ዓላማውንም ሆነ ውሳኔ መስጠቱን ለሌሎች ማካፈል

መ/ ሰዎች ልዩነታቸውን እንዲቀበሉ ማድረግ

14/ አንድ መሪ የራሱን ውጤታማነትና ተቀባይነት ማሳደግ የሚችለው፡-

ሀ/ ሌሎችን ሲረዳና ብቁ በሆኑ ሠራተኞች ሲከበብ

ለ/ በጠንካራ ቁጥጥር ሥራው በጊዜው እንዲጠናቀቅ ሲያደርግ

ሐ/ መሪነቱን ለብቻው ሲይዝና ጥቃቅን ሥራዎችን ለበታቾቹ ሲያከፋፍል

መ/ ከሰዎች ጋር ሲሠራ ተቆጣጣሪነቱንና ውሣኔ መስጠቱን ለግሉ ሲይዝ

15/ ዓላማን በማስቀመጥና ውሳኔ በማሳለፍ ረገድ ከሁሉም የተሻለው አመራር

ሀ/ የራስህን ዓላማ እግቡ ለማድረስ ሌሎች እንዲሠሩልህ ማድረግ

ለ/ የግል ግብህ አገልግሎት ነው በማለት ዓላማህን መሸሸግ

ሐ/ ለሌሎች ደንታ ያለህ መስለህ በመቅርብ ሥራው እንደሠራልህ ማድረግ

መ/ ይህ የሁላችንም ሥራ ነው ለማለት ያስችልህ ዘንድ በዓላማህና በውሳኔህ ሌሎችን ማሳተፍ

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

7/ ሀ/ ሐሰት /ብዙውን ጊዜ ታዋቂ ሰዎች ሁልጊዜ ጥሩ መሪዎች አይደሉም/

ለ/ እውነት ሐ/ ሐሰት /እውነተኛ መሪ በየጊዜው ይማራል፣ ያድጋል/

መ/ ሐሰት /ጳውሎስ የሚከተለው ስልት የመምከርን ነበር/ ሠ/ እውነት

1/ ምናልባትም የሚከተሉትን ገልጸህ ይሆናል፡፡ ለሰዎች ማሰብ፣ የስሜት መረጋጋት፣ መሪነትን ለሌሎች ማካፈል፣ የቡድን ሥራ ወይም በትምህርት አንድ የተዘረዘሩትን ሌሎች ባሕርያት ዘርዝረህ ይሆናል፡፡

8/ ሐ/ ሌሎችን ማክበርና መርዳት

2/ለ/ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሥራዎች የተለያዩ ሰዎች ይፈልጋሉ

9/ ሐ/ እየሰሩ እንዲማሩ ማድረግ

3/ሀ/ በወጣቱ የእግዚአብሔር ጥሪ መኖሩን ስለተረዳ መሪነትን እንዲያዳብር ጳውሎስ ጢሞቲዎስን ረድቶታል

ለ/ ጳውሎስ በመልእክቱ ስለ ጢሞቴዎስ ጥሪ ገልጿል /1ኛ ጢሞ 4፣14/፡፡

ሐ/ ጢሞቴዎስ አብሮት የሚሰራ መሆኑን ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ገልጾላቸዋል /ሮሜ 16፡21/፡፡ እንደ እርሱ ሁሉ ጢሞቴዎስም የጌታን ሥራ የሚሠራ መሆኑን ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ጽፏል፡፡ /1ኛ ቆሮ 16፣10/፡

መ/ ጳውሎስ በጢሞቲዎስ ውስጥ የነበረውን የመሪነት ችሎታን ተመልክቷል /የሐዋርያት ሥራ 16፡1-3/

10/ሀ/ እውነት ለ/ ሐሰት ሐ/ እውነት መ/ እውነት

4/ ሀ/ 1/ ዕድገት ለ/2/ መጠራትና እድገት ሐ/1/ዕድገት መ/1/ እድገት

ሠ/2/ መጠራትና እድገት

11/ ሀ/ እውነት ለ/ እውነት ሐ/ ሐሰት መ/ ሐሰት

5/ ሀ/ ሐሰት ለ/ እውነት ሐ/ ሐሰት መ/ እውነት

12/ መ/ አንድ መሪ ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤን ማዳበር የሚችለው ሌላው ሰው ስለ ራሱ ትክክለኛ ግንዛቤን እንዲያዳብር ሲረዳ ነው፡፡

6/ሀ/ ለአገልግለት በማዘጋጀትና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ማድረግ

ለ/ ለእያንዳንዱ አማኝ ለጋራ ጥቅም

ሐ/ ክርስቶስን በመምሰል፣ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግ

መ/ ቅዱስና ነቀፋ የሌለባቸው ልጆቹ መሆን፣ የእግዚአብሔርን ስም ማስከበር

ሠ/ በጌታ ጸጋና እውቀት ማደግ፣ በሥራ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት መብሰል፡፡

እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለው ዓላማ ፍሬያማነትና እድገት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የዕድገት ሂደት ደግሞ በአገልግሎት በመሳተፍና በሌሎች አስተዋይ መሪነት አማካይነት ነው የሚፈጸመው፡፡ ከእያንዳንድ ጤናማ መንፈሳዊ ሕይወት እድገት እንደሚጠበቅ 2ኛ ጴጥሮስ 3፣18፣ ዩሐንስ 15/1-8 እና ሌሎችም ይህን የሚያመለክቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ይኖራሉ፡፡

13/ ሐ/ ብቻውን የማይወስን ኃላፊነቱንም ሁሉ ለሌሎች የሚያጋራ መሪ ሌሎቹን ያነሣሣል፡፡

# ክፍለ ትምህርት አራት

## መሪዎች እቅድ ያወጣሉ፣ ያደራጃሉ

በሦስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የበርናባስንና የጳውሎስን እንደዚሁም የጢሞቴዎስን የመሪነት ምሳሌነት በመውሰድ ለመንፈሳዊ መሪነት ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎች ላይ በማተኮር ለመሪነት የተጠሩ ሰዎች እንደሚያድጉና ሌሎችን መንፈሳዊ አገልጋዮችና መሪዎችም እንዲያድጉ ለማድረግ የሚረዱበትን መንገድ ተገንዝበናል፡፡

በዚህ በአራተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የዳዊትን ምሳሌነት በመከተል የምናተኩረው ለመንፈሳዊ መሪነት ጠቃሚ የሚሆኑ መመሪያዎች ላይ ሲሆን፣ እቅድ ስለማውጣትና ስለ ማደራጀት ጠቃሚ የሆኑ ግንዛቤዎችን ለማግኘት እንሞክራለን፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የዳዊት ምሳሌት
- መሪዎች ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ
- መሪዎች ያደራጃሉ

------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስትጨርስ ከዚህ በታች የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- የዳዊት ሕይወትን መሠረት በማድረግ አንዳንድ የመሪነት መመሪያዎችን መግለጽና ተግባራዊ ማድረግ
- ድርጅት የሚለውን ሃሳብ መግለጽና ለድርጅታዊ አሠራር የሚረዱ አንዳንድ መመሪያዎችን ማስረዳት

---------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ ስለ ዳዊት ሕይወት መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን በማንበብ ስለመሪነት ምሳሌ የሚሆኑ ባሕርያትን ተመልከት። ስለዚህም የሚረዱህ የመጽሐፍ ቅዱስ የንባብ ክፍሎች 1ኛ ሳሙ 16፣1-22፣ 17፣21-58፣ ምዕራፍ 22-26፣ ምዕ 30፣ 2ኛ ሳሙ 5:1-7፣ 7:1-25 ፣ 1ኛ ዜና 17-19 እና 22-29 ናቸው። የአሁኑ ንባብ ዋና ዓላማ ዳዊት የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው መሆኑን ለማመልከት ነው። የዳዊትን ሕይወት ምሳሌነት በጥንቃቄ ብትመረምር ስለመሪነት ብዙ መማር ትችላለህ።

2/ ትምህርቱን እንደሚገባ አጠናቅ፣ በተለመደው ሁኔታም ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

3/ በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ያለውን የሙከራ ፈተና ውሰድ። መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትከውን ካለ አስተካክል።

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ - የዳዊት ምሳሌነት**

**ዓላማ 1 ከዳዊት ድርጊቶች ውስጥ ቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ችሎታ የሚሰጡትን ገለጻ ለመገንዘብ**

እስከ አሁን ድረስ የተመለከትነው የተለያዩ ሰዎች ምሳሌትን ነበር። ማለትም በመሪነት ላይ ስላሉ ሰዎችና አብረዋቸው ስለሚሠሩ ሰዎች። በዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ ትኩረታችንን ከሰዎች ላይ አንሥተን ሥራው ላይና ሥራውን ለመሥራት በሚያስፈልገው ጉዳይ ላይ እናደርጋለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌያችን የሆነው ዳዊት ለአንድ መልካም መሪ የሚያስፈልጉትን

ባሕሪያት ሁሉ የሚያሟላ መሪ ሲሆን፣ ስለዚህ ሰው በጣም የሚያስገርመው ነገር አስደናቂ ውጤቶችን ለማግኘት ያለው ብቃትና ችሎታ ነው።

ዳዊት የተለያዩ የሕይወት ልምምዶች አሉት። እረኛ፣ ወታደር፣ ባለቅኔ፣ አፍቃሪ አባትና ንጉሥ ነበር። ጀግና ነበር፣፣ በአንድ ወቅት በበደለኝነት ስሜት ቢሰቃይም፣ በደሉ ይቅር ተብሎለት እንደገና ተነሥቷል። የሕይወትን ውጣ ውረድ የምናየው ከዚህ ሰው ታሪክ ነው። የእግዚአብሔር እቅድ ምን ያህል ጥልቅና አስገራሚ እንደሆነም የሚያስረዳ ነው። ዳዊት ወደፊት ለሚጠብቀው ሥራ አስፈላጊው የሕይወት ተመክሮና እውቀት ተሰጥቶታል። የአካል ጥንካሬን፣ ድፍረትንና በራስ መተማመንን ያዳበረው በጎችን ሲጠብቅና ከማንኛውም አደጋ ሲከላከላቸው ነበር። ከበጎቹ ጋር ብቻውን በነበረበት ጊዜ ስለራሱ ለማሰብ በቂ ጊዜ ነበረው። ነገሮችን ማሰላሰልና ሃሳቦቹንም ውብ በሆኑ ቃላት መግለጽንም ተምሯል።

የሕይወት ጅማሬው በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም፣ ለመሪነት የተጠራው ሳሙኤል በቀላልና ሊገባው በሚችል መንገድ ለንጉሥነት በመረጠው ጊዜ ነበር /1ኛ ሳሙ 16፡1-22/። ***"የእግዚአብሔር መንፈስ በዳዊት ላይ በኃይል ወረደ"*** በሁኔታው በልቡ እየተደነቀ ከተቀባ በኋላ ወደዚያው ወደ እረኝነቱ ተመለሰ። በኋላም በንጉሥ ሳኦል ቤተ መንግሥት ተራና ትሁት አገልጋይ ሆኖ አገለገለ።

ሁሉም ፈርተውና ተርበትብተው በነበረበት ጊዜ ዳዊት ታላቁ ጎልያድን እንደሚገጥመውና እንደሚያሸንፈው በድፍረት መናገሩ ትህትናውን የሚያሳይ ድፍረት እንደሆነ ይታሰባል። ለዚህ ነበር ታላቅ ወንድሙ ዳዊትን **አንተኮ ትዕቢተኛ ነህ** በማለት የገሰጸው/1ኛ ሳሙ 17፡28-32/።

ማንኛውም እውነተኛ መሪ ሊኖረው የሚገባውን ነገር ለማሳየት ግን ዳዊት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም። ትህትናና አንድን ነገር ለማድረግ በወኔ መነሳሳት ለዳዊት ተቃራኒ አይደሉም። ዳዊት ጎልያድን በገደለበት ጊዜ እንደተረጋገጠውም ብዙውን ጊዜ ሁለቱ የማይነጣጠሉ ናቸው።

የሚሠራው ሁሉ በራሱ ጉልበት እንዳልሆነ ዳዊት ያውቃል። የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወርዶበታል፣፣ ስለዚህም በድፍረትና በመተማመን መናገር ይችላል። ዳዊት በወኔ በተሞሉ ቃላት የሚኩራራ አልነበረም። እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ

እንደሚገባ ማከናወን እንደሚችል ብቻ ነበር የተናገረው፡፡ ***"ከዚህ በፊት አንበሳና ድብ እንኳ ገድያለሁ"*** በማለት ተናግሯል ዳዊት /1ኛ ሳሙ 17፤ 34-37/፡፡

ያለምንም ወንጭፍና ድንጋይ እግዚአብሔር ጎልያድን መግደል እንደሚችል እናምናለን፡፡ ድንጋዩ በተአምር ተነስቶ ያለዳዊት ወይም ያለወንጭፍ እርዳታ ሊገድለው እንደሚችል እናውቃለን፡፡ ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር አንድ የሚሠራው ነገር ሲኖረው አስፈላጊውን ችሎታ ባዳበሩ ሰዎች እንደሚጠቀም ነው የምንመለከተው፡፡ ዳዊት ደግሞ ያንን ችሎታ አዳብሯል፡፡ ችሎታና ኃይሉን አሳይቷል፡፡ ምንም እንኳ ኃይሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ ቢያውቅም ቸልተኛ ወይም ሞያ የሌለው ሰው አልነበረም፡፡ በረጅም ጊዜ ልምዱ የተማረውን ነበር ሥራ ላይ ያዋለው፡፡ ወንዝ ወርዶ አስፈላጊ ድንጋዮች ሰበሰበ፡፡ በጥንቃቄ በእረኛ ኮሮጆው ውስጥ አኖራቸው እንጂ እንዲሁ የማይረቡ ድንጋዮችን እንዳልሰበሰበ ካሠራሩ ስልትና ሥርዓትን እንመለከታለን፡፡

ራሳችንን ለመገምገም የሚረዱን ጥያቄዎች ከማቅረባችን በፊት አስቀድመህ መዝ 144፡1 ላይ የተጻፈውን አንብብ፡፡ ዳዊት በራሱ ችሎታ ቢታመንም ክብሩን ለራሱ እንዳላደረገ ከዚህ ምንባብ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ዳዊት እንዴት ነው ብቁ የሆነው? አንተስ ምን ዓይነት ችሎታ ወይም ስጦታ አለህ? እግዚአብሔር እጆችህን አሰልጥኗቸዋልን? ለጣቶችህስ እውቀት ሰጥቷቸዋልን? እነዚህ ያዳበርካቸው ችሎታዎችን አንድ ቀን ለጌታ ሥራ እንደምታውላቸው ታስባለህን?

### ዳዊት መሪያቸው ሆነ

በአስደናቂ ሁኔታ ድል ከተቀዳጀ በኃላ ዳዊት ክብርና ምሥጋናን አገኘ፡፡ ወዲያውኑ በሺህ የሚቆጠር ሠራዊት መሪ መሆን ይችል ነበር፡፡ ዳዊት ግን በአጋጣሚው በመጠቀም ዝነኛ መሆንን አልፈለገም፤፡ ይህም ትሕትናውን ነው የሚያሳየው፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ በፈቃደኝነት ለሳኦል ይታዘዝ ነበር፡፡ በመዋቅሩ ውስጥ ራሱን አስገባ፡፡ ልክ እንደ ወታደር ታዘዘ፡፡ በተደጋጋሚ ባስመዘገበው ድልና ባካበተውም ልምድ ምክንያት ዕድገትን አገኘ፡፡ ለሃገሪቱ ዕድገት በሚያስፈልጉ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ይሳተፍ ነበር፡፡

1/ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልግ ነበር፡፡

2/ ከበላዮቹም ሆነ ከእርሱ በታች ካሉት ጋር ባለው ግንኙነት ታማኝና ለሌሎችም አሳቢ ነበር፡፡

3/ ሁልጊዜ የተሻለና ብቃት ያለው ሆኖ ለመገኘት ይጥራል፣ ለዚህም ክብርን ለእግዚአብሔር ይሰጣል።

ሁላችንም እንደምናውቀው በመጨረሻ ዳዊት ተስፋ የተገባለትን ሁሉ አግኝቷል። ይሁንና መላው እስራኤል ብቻ ሳይሆን፣ በአካባቢው ያሉ ጠላቶቹንም ገዝቷል። ይህም ብዙ ጊዜውን በጦርነት እንዲያሳልፍ ቢያደርገውም ድፍረትና ችሎታውን አዳብሮለታል።

በንጉሥነት ሥልጣኑ ከተደላደለ በኋላ የዳዊት ትልቁ ፍላጎት ለቃል ኪዳኑ ታቦት ማረፊያ የሚሆን ቤተ መቅደስ መሥራት ነበር። እግዚአብሔር ግን አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ማሟላት እንጂ ቤተ መቅደሱን መሥራት የእርሱ ድርሻ እንዳልሆነ ገለጸለት /1ኛ ዜና 22፡1-4/። ይህንንም ለማከናወን ያደረው እንቅስቃሴ የማደራጀትና የአሠራር መዋቅርን በመዘርጋት ረገድ ዓይነተኛ ምሳሌ ሆኗል።

## *ዳዊት ሰፊ ዝግጅት አደረገ*

ዳዊት በረጅም ጊዜ የጦርነት ዘመኑ ብዙ ምርኮ አግኝቷል። ያገኘውንም ምርኮ ለእግዚአብሔር ቤት ግንባታ ቁሳቁሶችን ለማሟላት እንዳለበት አሰበ። /1ኛ ዜና 22፡1-14/። 1ኛና 2ኛ ዜና ስናነብ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር የነበረውን ግንኙነት በስፋት እንመለከታለን። የእነዚህ መጻሕፍት ዐቢይ መልእክት አምልኮ ወይም ታምራት ሳይሆን እቅድ ማውጣት፣ ማደራጀት፣ የሥራ ዝርዝር እና ለሥራው ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው።

ዳዊት ድንጋይ ጠራቢዎችንና ሌሎች ሠራተኞችን ቀጠረ። ለሥራው የሚያስፈልጋቸውን ድንጋይ፣ ብረት፣ ነሐስና ግንዶችን አቀረበላቸው ። የሥራው ተቆጣጣሪዎችን፣ ዳኞችን፣ ዘበኞችንና ሙዚቀኞችን አደራጀ። ለእያንዳንዳቸው ግልጽና የማያሻማ ሥራ ነበር የመደበላቸው። ቅድመ ዝግጅቶቹ ሁሉ ግልጽና ጥርት ያሉ መሆናቸው የብዙ ሥራና ጸሎት ውጤቶች መሆናቸውን ያሳያል።

ዳዊት ልጁ ሰለሞንን፡- ***"የአምላክህን የእግዚአብሔርን ሕግ ትጠብቅ ዘንድ እግዚአብሔር ጥበብንና ማስተዋልን ይስጥህ--- ለእግዚአብሔር ቤት መቶ ሺህ መክሊት ብር፣ ሚዛንም የሌላቸውን ብዙ ናስና ብረት አዘጋጀሁ-- በአንተም ዘንድ ብዙ ሠራተኞች አሉ"*** አለው/1ኛ ዜና 22፡12-15/

ለቤተመቅደሱ ግንባታ፣ ዕቃ ቤት፣ ውስጠኛው ክፍልና የአደባባዮቹን እቅድ ሁሉ ሰጠው፡፡ ***"የእግዚአብሔር መንፈስ በልቡ እንዳስቀመጠለት"*** /1ኛ ዜና 28፡11-12/፡፡ ***"የሥራውን ሁሉ ምሳሌ አውቅ ዘንድ"*** አለ ዳዊት ***"በእግዚአብሔር እጅ ተጽፎ መጣልኝ"*** (1ኛ ዜና 28፡19)፡፡

ዳዊት የተለያየ የሕይወተ ልምምድ አለው፤፡ ብዙ ውጣ ውረድም አሳልፏል፡፡ በዚህ ሁሉ ግን በዓላማው ጽኑ ነበር፡፡ አልሞና አስተካክሎ በወነጨፈው ድንጋይ የጎልያድን ግንባር እንደመታ ሁሉ እቅዱ ያለምንም ስህተት ተፈጻሚነት እንዲኖረው ይጥር ነበር፡፡ ድካሙን ይቀበላል፣ ተጸጽቶም ንስሐ ይገባል፡፡ ጥበብና ማስተዋልን የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑንና ለሌሎችም ጥበብና ማስተዋልን እንደሚሰጥ ያምናል፡፡

ጊዜው እያለፈ ሲሄድ ሥራውን ለሠራተኞቹ ኃላፊነቱንም ለሰለሞን የሚሰጥበት ወቅት መጣ፡፡ በኢየሩሳሌም ታላቅ ስብሰባ አድርጎ ለወደፊት ያለውን እቅድ ግልጽ አደረገላቸው፡፡ ምንም የዘነጋው ነገር አልነበረም፡፡ ምንም የሚያወላውልበት ነገር አልነበረም፡፡ የሚሠሩትን የሚያውቁ **"ወንድሞች"** በማለት ነበር ስለ ሠራተኞቹ የተናገረው፡፡ ሥራውን በተመለከተም እርስ በርስ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ያውቃሉ፡፡ ለሥራው ስለሚያስፈልገው ነገርና የሚጠይቀውንም መስዋዕትነት ያውቃሉ፡፡ ራሱን ሳያስታብይ ዳዊት ለሥራው መረጃ ይሆናቸው ዘንድ ስሜቱንና ሥራውን ሁሉ ገለጸላቸው፡፡ ***"የአምላኬን ቤት ስለወደድሁ ለመቅደሱ ካዘጋጀሁት ሁሉ ሌላ የግል ገንዘቤን የሚሆን ወርቅና ብር አለኝና ለአምላኬ ቤት ሰጥቼዋለሁ"*** በማለት የማያወላውል ዓላማውን ነገራቸው (1ኛ ዜና 29፡3) ፡፡ ራሱን በሥራው በማሳተፉም ሌሎች ለማገልገልና ያላቸውንም እንዲሰጡ መልካም አርአያ ሆነላቸው፡፡ ሕዝቡ አመራሩን የተቀበሉት በታላቅ ደስታ ስለ ነበር ደስ እያላቸው ራሳቸውንና ያላቸውን ሁሉ ለጌታ ሰጡ፡፡

ዳዊት ጸለየ፤፡ ሕዝቡንም በአምልኮ መራ፡፡ **እግዚአብሔር አምላካችሁን አመስግኑ** አለ በሕዝቡ ሁሉ ፊት፡፡ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ (1ኛ ዜና 29፡10-20)፡፡ ወደ ትምህርቱ መጀመሪያ ሄደህ የዊሊያምና የኮሚቴውን ሁኔታ ተመልከት፡፡

1/ ከዳዊት ምሳሌት በአመራር ስልት ልንከተላቸው የሚገቡን ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ዘርዝር ፡፡------------------------------

2/ የዳዊትን ምሳሌነት ባለመከተል የሚያስከትለውን ሦስት ነገሮች ዘርዝር ------------ - ----------------- -------------------

3/ ዳዊት ጎልያድን ለመዋጋት ያደረገውን ውሳኔ የሚያሳየው

ሀ/ ትዕቢተኛነቱን ለ/ ከሌሎች ልቆ ለመታየት መፈለጉን

ሐ/ ለመሪነት የተፈጠረ መሆኑን

መ/ እንደሚጠቀምበት በጌታ ያለው እምነት

4/ ዳዊት አንበሳና ድብ መግደሉን ሲገልጽ፡-

ሀ/ በሐቅ በተደገፈ ማስረጃ ነበር

ለ/ ከወንድሞቹ ይልቅ የእምነት ሰው መሆኑን ማሳየቱ ነበር

ሐ/ ለንጉሥነት መመረጡን መግለጹ ነበር

5/ ዳዊት በጥንቃቄ አምስት ድንጋዮችን መረጠ፡፡ ይህም የሚያመለክተው፡-

ሀ/ እምነት የሌለው መሆኑን ለ/ በቂ ልምድና ብቃት ያለው መሆኑን

ሐ/ ችሎታውን ለሕዝቡ ለማሳየት ያለውን ፍላጎት

መ/ በሳኦል መሣሪያ ለመጠቀም አለመፈለጉን

## መሪዎች ያቅዳሉ፣ ያስተባብራሉ

### ዓላማ 2 ከእቅድ በስተጀርባ ያለውን ዓላማ ለመግለጽ

እቅድ በጥንቃቄ ማሰብንና በጽሑፍ ማስፈርን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ማንኛውም ውጤታማ ሊሆን የሚችል ሥራ በእነዚህ በሁለቱ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ማቀድ ከዚያም ማስተባበር ናቸው፡፡ አውቀውትም ይሁን ሳውቁት ሰዎች ሁሉ እቅድ ያቅዳሉ፡፡ አንድ ነገር እንዴት መሠራት ወይም ምን መምሰል እንዳለበት በአእምሮ የምንቀርጸው ምስል በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ሰብዓዊ ባሕርያት አንዱ ነው፡፡ የተለያዩ ሁኔታዎች ሲገጥሙን ምን እንደምናደርግ አስቀድመን እቅድ እናወጣለን፣ አስቀድመን ሥራውን በአእምሯችን እንሠራዋለን፡፡ በተለይም ለመሪነት የተጠሩ ሰዎች ይህን የሚያደርጉት ሌሎች ከሚያደርጉት ይልቅ ጥርት ባለና መልክ ባለው ሁኔታ ነው፡፡

ስለ መሪነት የተደረጉ ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት እቅድ ማውጣት በዝርዝር ጉዳዩች ውስጥ የመጀመሪያውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ መሪዎች እቅድ ማውጣት አለባቸው፣፡ በጥንቃቄ እቅድ የማውጣታቸውን ያህል በዚያው ልክ ሥራውም ይከናወንላቸዋል፡፡ እስቲ አሁን ደግሞ እቅድ ማውጣት ስለሚያካትታቸው ጉዳዮች እንመልከት፡፡

1/ **ሁኔታዎችን መገምገምና መገመት፡-** መሪዎች የአሁኑን ሁኔታ በጥንቃቄ ያጠናሉ፡፡ ከአሁኑ ሁኔታ ተነስተውም የወደፊት ምን እንደሚመስል ወይም ምን መምሰል እንዳለበት ይገምታሉ፡፡

2/ **ዓላማና ግብ ያስቀምጣሉ፡-** መሪዎች ጥርት ያለ ሀሳብ ነው ያላቸው፡፡ ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ ምክንያት አላቸው፡፡ የእያንዳንዱን ሥራ ዓላማ ያውቁታል፡፡ ውጤቱ ምን እንደሚሆንም ይረዱታል፡፡ እዚህ ላይ ውጤት የምንለው ነው፡፡ መልካም እቅድ ሁሉ ግብ አለው፡፡ ይህንንም ወደፊት በስፋት እንመለከተዋለን፡፡

3/ **ለሥራው ዝርዝር መመሪያን ማውጣት፡-** በመሪነት አሠራር ሂደት ውስጥ ይህ መርሐ ግብር ፕሮግራም ይባላል፡፡ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት ግባችንንም ለመምታት ለምንወስደው እያንዳንዱ እርምጃ ሁሉ ዝርዝሮችን ያካትታል፡፡

4/ **የነገሮች ቅደም ተከተል፣-** የጊዜ ቅደም ተከተልን ማዘጋጀት ግብን ለመምታት ወይም በፕሮግራም መሠረት ለመንቀሳቀስ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ተገቢውን የጊዜ ቅደም ተከተል ካልመደብንለት በቀር ማንኛውም ግብ ወይም ፕሮግራም ፍሬ አልባ ነው የሚሆነው፡፡

5/ **የሚያስፈልገውን ዘዴ ጥርት ባለ መንገድ መዘርዝር፡-** የምናወጣው እቅድ ተግባራዊና በሥራ ሊተረጎም የሚችል ዓይነት መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም መሪዎች ማንኛውንም ነገር ለማከናወን የሚያስችላቸው ጥርት ያለ የአሠራር ዘዴ አላቸው፡፡

6/ **የገንዘብ አቅምን መተመን፡-** በመሪነት ጥናት ውስጥ ይህ በጀት መመደብ ይባላል፡፡ አብዛኞቹ እቅዶች ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፣፡ ገንዘቡን ከየት እንደምናገኝ፣ የት እና ምን ላይ እንደምናውለው ጥናት ያስፈልገዋል፡፣ ይህን ለማድረግ ደግሞ ኃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኛ መሆንን ይጨምራል፡፡

7/ **ለሥራው ብቁ የሚሆኑ ተገቢ ሰዎችን መምረጥ፡-** መሪዎች አንድ ፕሮግራም ወይም ፕሮጀክት ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስፈልጉና ሰዎቹ ስላላቸው ችሎታና እውቀት ጥናት ያደርጋሉ፡፡ ለተገቢው ሥፍራ ተገቢ ሰዎችን መምረጥ እቅዳችንን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ በጣም ወሳኝነት አለው፡፡

8/ **የአሠራር ፖሊሲና መለኪያን ማዘጋጀት፡-** እያንዳንዱ እቅድ የራሱ ፖሊሲ አለው፡፡ እንዲህም ሲባል ክርስቲያኖች የሚመሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ ሃሳብና የቤተክርስቲያን ወይም የሌላ መንፈሳዊ ድርጅት የበላይ ባለሥልጣኖች በሚሰጣቸው መመሪያ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸውን ነጥቦች በጥያቄ መልክ መዘርዘር ብዙ መሪዎች ይበልጥ የሚረዳ ሆኖ አግኝተውታል። ለነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ ለእቅድ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ያመለክተናል።

1/ ለምንድነው ይህ ሥራ መሰራት ያለበት? አሁን ያለህበትን ሁኔታ

2/ ምንድነው ማከናወን ያለብኝ? ጥርት ያለ ግብ እንዲኖርህ ይረዳሃል

3/ እንዴት ነው መሠራት ያለበት? ዝርዝሮችን ለማውጣት ይረዳሃል።

4/ መቼ ነው መሠራት ያለበት? ይህም ጊዜን ለመመደብ ይረዳሃል።

5/ ሥሪውን ለማከናወን የተሻለው መንገድ የትኛው ነው? ይህ የተለያዩ የአሠራር ዘዴዎችን እንድትመርጥና እንድታመዛዝን ይረዳሃል።

6/ በምንድነው ሥራውን ማከናወን የምንችለው? ይህ በጀት እንድትመድብና ለሥራው የሚያስፈልጉ ነገሮችን እንድታሰባስብ ይረዳሀል።

7/ ከነማን ወይም ከማን ጋር ነው የምሠራው? ይህ ሰዎችን እንድትመርጥና ለተገቢው ሥራ ተገቢው እውቀትና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች እንድትመድብ ይረዳሀል።

8/ ለሠራተኞቹ ምን አይነት መመሪያ ወይም መመዘኛ ቢኖራቸው ይመረጣል?

## የተለያዩ የእቅድ ዓይነቶች

ብዙ መሪዎች በሦስት ዓይነት እቅዶች መጠቀምን ይመርጣሉ። እነርሱም፡-

1/ የዓመቱን እንቅስቃሴና የድርጅቱን አሠራር የሚያካትት እቅድ።

2/ የኮሚቴ ስብሰባ፣ የሠራተኞች ሥልጠና ፕሮግራምን የመሳሰሉትን የሚያካትት ዝርዝር የእንቅስቃሴ እቅድ።

3/ ኮንፍራንስ ወይም ልዩ ፕሮግራምን የሚያካትት የግል ፕሮጀክት

እቅድ ማውጣት በጥንቃቄ ማሰብንና በጽሑፍ ማስፈርን እንደሚጠይቅ ተመልክተናል። ይህ በጽሑፍ የሰፈረ እቅድ በሠነድ መልክ ይያዛል። ብዙ የተዋጣላቸው መሪዎች የረጅም ጊዜና የዕለታዊ ዝርዝር ጉዳዮች እቅድ ያወጣሉ።

## መደረግ ያለበት

1/ **እያንዳንዱ መሪ ለዕለታዊ ውሎው ዝርዝር እቅድ ያወጣል፡-** ይህንንም በማንኛውም ወረቀት ወይም ለዚሁ በተዘጋጀ ደብተር ላይ ማስፈር ይቻላል። የዕለታዊ ዝርዝር ጉዳዮች ፡- ቀጠሮን፣ መሠራት ያለበትን፣ ለሌሎች የሚሠጠውን ሥራ፣ መጻፍ ያለበት

ደብዳቤን፣ መደረግ ያለበት የስልክ ጥሪ፣ ከማን የቴሌፎን ጥሪ እንደሚጠብቅ፣ የሚያስፈልጉ ነገሮችን፣ ገንዘብ-ነክና ሌሎች ጉዳዮች።

2/ **የቀን መቁጠሪያ፡-** ማንኛውም መሪ ሁለት የቀን መቁጠሪያ ያስፈልገዋል። አንደኛው ተለቅ ያለ ሲሆን፣ አንዳንድ ነገሮችን ለመጻፊያ ሥፍራ ሊኖረው ይገባል። ይህ ዓይነቱ የቀን መቁጠሪያ በረጅም ጊዜ እቅድ የሚውል ነው። ለዚሁ ተብለው የተዘጋጁ ካሌንደሮችን ማግኘት ካልተቻለ አመቺ በሆነ ሁኔታ ማዘጋጀት ይቻላል። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ቀኖችን ማስታወስ እንዲቻል በትንሹ ካሌንደር ምልክት ይደረግበታል።

3/ **ማስታወሻ ደብተር፡-** ትንሹ ካሌንደር የደብተር ገጽ ወይም ደግሞ ሁልጊዜ በኪሳችን የምንይዘው ማስታወሻ ደብተር ሊሆን ይችላል። አንድ ትክክለኛ መሪ የዕለታዊ ውሎውንና ወደአእምሮው የሚመጣለትን ጠቃሚ ሃሳቦች በጽሑፍ ያሰፍራል። የሚፈልጋቸውን ሰዎች ስም፣ የቴሌፎን ቁጥርና አድራሻ ይጽፋል።

4/ **የሥራ እቅድ ማስፈሪያ ወረቀት፡-** ዋና ዋና ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚኖረን እቅድ በዝርዝር በጽሑፍ መስፈር ይኖርበታል። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ቀን
- የመሪው ስም
- እቅዱን በማውጣት የተሳተፉ የሌሎች ሰዎች ወይም ኮሚቴ ስም
- የፕሮጀክቱ ስም፣ የሥራ ዝርዝርና ግቦች
- እያንዳንዱ ሰው የተሰጠው የሥራ ዓይነት
- ለእያንዳንዱ ሥራ የሚያስፈልጉ ነገሮች
- እያንዳንዱ ሥራ የሚጠናቀቅበት ቀን

5/ እቅድን ለማውጣት የሚያስፈልጉ ወይም የሚደረጉ ነገሮችን ዝርዝር እንደገና አንብብ። ከዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀመጠውን ፎርም አጥናው። ልክ አንድ ትልቅ እቅድ የማውጣት ኃላፊነት እንዳለብህ አድርገህ አስብ። ለዚሁ ተግባር የሚረዳህን ወረቀት በማዘጋጀት ወይም በተዘጋጀው በመጠቀም እቅድህን በትክክል አስፍር። ይህ በጣም የሚጠቅምህ ልምምድ ነው።

**ማስተባበር**

ማስተባበር ስንል እቅዱን በተግባር መተርጎም ማለታችን ነው፡፡ እቅዱን ካጠናቀቅህ በኋላ የሚቀጥለው ጉዳይ አስፈላጊውን ነገሮች ሁሉ በማመቻቸት ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ ሥራ ላይ ማዋል ነው፡፡ ማስተባበር ትክክለኛ ሰዎች በትክክለኛው ጊዜ በትክክለኛው ሥፍራ መሆናቸውን፣ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ማሟላትንና እንዴት ሥራውን በጋራ መሥራት እንዳለባቸው እንዲረዱም ማድረግን ይጠይቃል፡፡

እንዴት እቅድ እንደምታወጣ እንዲረዱህ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደገና ተመልከት፡፡ በጥያቄዎቹ ላይ የተዘረዘሩ ጉዳዮች ምንድናቸው?

6/ የሚከተሉትን አዛምድ፡- 1/ ጊዜ 2/ ሥራው 3/ ሰዎች

4/ ዘዴው 5/ አስፈላጊ ነገሮች 6/ ግቡ

-----ሀ/ ሥራውን የሚሰራው ማነው? ---መ/ ሥራው የሚሠራው መቼ ነው?

----ለ/ ሥራው የሚሰራው በምንድነው?------ሠ/ እንዴት ነው የሚሠራው?

---ሐ/ መከናወን ያለበት በምንድነው? ------- ረ/ ሥራው የሚሠራው የት ነው?

**ልናሰላስላቸው የሚገቡ ጥያቄዎች**

ስለዳዊት አመራር ታሪክ እንደገና ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት፡፡ መልካም አስተባባሪ ነበርን? እቅዶችን በሚገባ የሚያመዛዝን ነበርን? መቅደሱን ለመሥራት ከነበረው እቅድ ጋር በተያያዘ መልኩ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መስጠት ትችላለህ?

7/ ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ከእቅድ በስተጀርባ ያለውን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ የሚገልጹት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ በመሠረቱ እቅድ ማውጣት ስንል የምናስበው ግብ ላይ መድረስ ነው

ለ/ የሥራ ሂደትን የተሳካ ለማድረግ የምናደርገው ሙከራ እቅድ ይባላል

ሐ/ የሥራ ሂደታችንን አስቀድሞ ለመወሰንና ወደግባችን ለመድረስም የምናደርገው ሙከራ የሚገጥሙን ሁኔታዎችን ሁሉ ለመወጣት ቅድመ ዝግጅት እቅድ ይባላል፡፡

መ/ እያንዳንድ ሰው መዋቅሩ ውስጥ የሚኖረውን ሥፍራና ያለበትንም ኃላፊነት የምንወስነው በእቅድ ነው፡፡

**አንዳንድ ችግሮችና መሰናክሎች**

**ዓላማ 3 በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎችን ለመጥቀስ**

አንዳንድ ጊዜ መሪዎች "**ለሁሉም ነገር እቅድ አውጥቼ ነበር፣ ታዲያ ምን ዋጋ አለው?-----------**" ሲሉ ሰምተህ ይሆናል፡፡
"አብረውኝ ያሉ ሠራተኞች መመሪያ አይቀበሉም"
"አለቃዬ በየጊዜው ሀሳቡን ይለዋውጣል"
"ረዳቴ ታሟል"
"ሁኔታው ሁሉ እኔ ከጠበቅሁት በፍጹም የተለየ ነው"

ምናልባትም እንዲህ ያሉ ዓላማህን የሚያጨናግፉ ሁኔታዎች ገጥመውህ ይሆናል፣ ወይም ሊገጥሙህ ይችላሉ፡፡ በጥንቃቄ ያወጣኸውን እቅድ ሰዎች ላይቀበሉህ ይችላሉ፡፡ ስለዚያ ፕሮጀክት ምንም እቅድ ወይም ጥናት ያላደረገ ሌላው ሰው ሲዋጣለትና ሲከናወንለትም ታይ ይሆናል፡፡ ይህ ግን ምክንያት ሊሆንህ አይገባም፡፡ እቅድ ማውጣት ብቻውን መሳካትን ወይም መከናወንን እንደማያስገኝ ማወቅ አለብህ፡፡ አንዳንድ ሰዎች እቅድ ላለማውጣት ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት ይህንን ነው፡፡

ልናስብባቸው የሚገቡን ሌሎች ሁለት እንቅፋቶችም አሉ፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ መሪዎች ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይልቅ በእቅዳቸው ይታመናሉ ብለው ይከሷቸዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሥራችንን እንቅስቃሴ እንደሚመራ ሁሉ እቅድ ስናወጣም እንደሚመራን ከመጽሐፍ ቅዱስ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህም እቅድ ማውጣትን ሆነ የሥራ መርሐ ግብርን የሚነቅፉ ሰዎች በቤተክርስቲያን መኖራቸው ብዙም ሊያስደንቀን አይገባም፡፡

ምናልባትም ትክክለኛ እቅድን ለማውጣት ዋናው እንቅፋት የሚሆንብን ነገር ጊዜ የሚወስድና በርትተን መሥራትን የሚጠይቅ በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ በጥንቃቄ ማሰብና ሀሳብንም በጽሑፍ ማስፈር አስቸጋሪ ሥራዎች ናቸው፡፡ ምስክርነትህን በሕዝብ ፊት ቆመህ ከማሰማት በጽሑፍ ማስፈሩ ምን ያህል አዳጋች እንደሆነ አንተው ራስህ ልታየው ትችላለህ፡፡ ስንናገር ጌታ እንደሚመራን ሁሉ ስንጽፍም ሊመራን ይችላል፡፡ ስለዚህም በድንገት ስንናገር መንፈስ ቅዱስ እንደሚመራን የምናምን ከሆነ እቅዳችንን በጽሑፍ ስናሰፍር ግን አይመራንም ብሎ ማሰቡ ምክንያታዊ ሊሆን አይችልም፡ መሪው በሥራው ይበልጥ ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ እንደዚህ ያለው አለመግባባት ጨርሶ መወገድ አለበት፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጋር ጊዜን መስጠትና በርትቶ መስራት በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው፡፡

8/ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎችን ዘርዝር------------ ---------------- ------------------ ቀጥሎ አንዳንድ መሰናክሎችን ለማስወገድና ውጤታማ እቅዶችን እንድታወጣ የሚረዱ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

1/ እቅድህን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት አሳልፈህ ስጥ፡- በጸሎትህ አስባቸው

2/ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት እቅዶችህን ለመለወጥ ዝግጁ ሁን፡- ዝርዝር እቅዶችን ማውጣትና እንደሁኔታው አስፈላጊነት እቅዶችን ለመለወጥ መዘጋጀት ብዙ ጊዜ መሪዎችን የሚገጥማቸው ችግር ነው፡፡

3/ ሁሉም እቅዶች ተግባራዊ ይሆናሉ ብለህ አታስብ፡- አንድ መሪ ምንም እንኳ የመጀመሪያ እቅዱን መለወጥ ቢኖርበትም እቅዶችን ማውጣትና በእቅዱ መሠረትም መንቀሳቀስ ሥራውን ፍሬያማ እንደሚያደርግለት በሚገባ ያውቃል፡፡ ከብዙ ሁኔታዎች እንደሚታየው ምንም እንኳ ሁኔታዎች ቢለወጡም እንደሚገባ እቅድ ያደረገ መሪ የሌሎችን አክብሮትና ትብብር ያገኛል፡፡ የሚቻል ከሆነ ሊገጥሙህ የሚችሉ ችግሮችንም አስብባቸው፡፡ ሊደረጉ ይችላሉ የምትላቸውንም ለውጦች አስቀድመህ ለማሰብ ሞክር፡፡

4/ ትላልቅ ግቦች ላይ ለመድረስ ስለሚረዱ ትናንሽ ግቦች አስብ፡- ለምሳሌ ያህል በአጥቢያ ቤተክርስቲያንህ ለሚደረገው ኮንፍራንስ ምግብ ለማዘጋጀት ትልቁ እቅድህ ሊሆን ይችላል፣ ምግቡን የምታኖርበት ሥፍራና ለምግብ የሚሆኑ ነገሮችን ማግኘት ትንሹ እቅድህ ሊሆን ይችላል፡፡ ትንንሽ ግቦች ላይ ለመድረስ የምታደርገው እቅድ በከፍተኛው እቅድህ ላይ ይህን ያህል ጉዳት ሲያደርሱ ሊለወጡ ይችላሉ፡፡ ትናንሽና ትልልቅ ስለሚባሉት ዓላማዎች በሌላ ትምህርት እንነጋገርባቸዋለን፡፡

5/ በሥራው የሚሳተፉ ሰዎች ሁሉ እቅዶቹን እንደሚገባ መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን፡፡ ዳዊት ለሕዝቡ እንዴት እቅዶቹን እንደገለጸላቸውና ዓላማና ፈቃደኝነታቸውንም እንዲያሳዩ ዕድል እንደሰጣቸው አስተውል፡፡ የእቅዶችህን ዓላማና ጠቀሜታ አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች ግለጽላቸው፡፡ ለሚያደርጉት አስተዋጽኦም ምሥጋናህንና አድናቆትናን ግለጽላቸው፡፡ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ እቅዶችህን ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመስጠት አብረውህ በጸሎትና በምሥጋና እንዲሳተፉ አድርግ፡፡

መሪዎች ያደራጃሉ

## ግብ 4 የተለያዩ ድርጅታዊ ዓይነቶችን በመግለጽ ለድርጅታዊ አሠራር የሚጠቅሙ ነገሮችን ለማቅረብ

እቅድ ማውጣት ስንል የእቅዱን ሂደትና ለሥራው እንቅስቃሴ የሚረዳ የጽሑፍ ሠነድ ማዘጋጀትን እንደሚያካትት ተመልክተናል፡፡ ድርጅት የሚለው ሀሳብም እንዲሁ ሁለት ዋና ዋና ሀሳቦች የሚያካትት ሲሆን፣ በመጀመሪያ ለሥራው ብቃት ያላቸውን ሰዎች ማሰባሰብ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተደጋግፎ ለመሥራት የሚያስችላቸውን መዋቅርና አስተማማኝነት ያለው እቅድ መንደፍ ነው፡፡

### የድርጅት ዓይነቶች

ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን ወታደራዊ አደረጃጀት ነው፡፡ ዋናው መሪ ከፍተኛ ሥልጣን አለው፡፡ ሥራው የሚከናወነው በምክትሉና በመካከለኛው መሪዎች አማካይነት ነው፡፡ የእያንዳንዱ ሰው ሥራ ከእርሱ በላይ በሆነው ሹም ቁጥጥር ሥር ይሆናል፡፡ የሠራተኞቹ ግንኙነት ከቅርብ አለቆቻቸው ጋር እንጂ ከዋናው መሪ ጋር አይደለም፡፡

ሌላው የአደረጃጀት ዓይነት አብዛኞቹ የዘመናችን ድርጅቶች የሚከተሉት ዓይነት ነው፡፡ አንድ ዋና መሪ ይኖራል፡፡ ምክርና መመሪያ የሚሰጡት እውቀቱና ችሎታው ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ለዋናው መሪ ምክርና መመሪያ ይሰጡታል፡፡ እርሱም ለመካከለኛ መሪዎች ምክርና መመሪያ በመስጠት ሥራውን ያስፈጽማል፡፡

ሦስተኛው የድርጅት ዓይነት የንግድ እንቅስቃሴን ወይም ካምፓኒን በተመለከተ እንደ ሥራው ዓይነት ተቀጣሪው ከተለያዩ የበላይ አለቆች ሥር በመሆን ሥራውን የሚያከናውንበት ነው፡፡ መሪዎቹም ጉዳይ ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት ከሥራው ጋር እንጂ ከሰዎች ጋር አይደለም፡፡

አብዛኛው ክርስቲያናዊ አሠራር ሦስቱን የአደረጃጀት ዓይነቶች ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ዋናው መሪ መጋቢው ሲሆን፣ ረዳት መጋቢዎችም ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ የእሁድ ትምህርት ቤትና የመዘምራን ክፍል ኃላፊዎችን የመሳሰሉ መካከለኛ መሪዎችም ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ የመዘምራኑ ቡድን በቡድን መሪ ሥር ሲሆን፣ የቡድኑ መሪ ደግሞ ከረዳት መጋቢው ሥር ይሆናል፡፡ ቤተክርስቲያን እንዲህ ያለውን የአሠራር ዘዴ የምትጠቀምበት በመጠኑ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ እንደምናየው መሪዎቹ ሁሉ ከመጋቢው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ስለዚህም አሠራሩ የቡድን አደረጃጀት መሥመር

ዓይነት ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ሥራዎች እንደመኖራቸው መጠን በሥራው አማካኝነት መሪዎቹ ሁሉ እርስ በርስ ይገናኛሉ።

የተለያዩ ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ስላሉ መጋቢው ከሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ውስብስብና ባለብዙ መልክ ነው። መጋቢው የማሕበረ ምዕመኑ መንፈሳዊ መሪ ነው። በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ዋና መሪ እንደ መሆኑ መጠን ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ባለው ግንኙነት የበላይ ነው። ለምዕመኑ የምክር አገልግሎት መስጠትና ማስተማርም የእርሱ ኃላፊነት ነው። ፍሬያማ የሆነ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረን ከተፈለገ የመጋቢውን የተለያየ የሥራ ድርሻ ልንረዳለት ይገባል።

መንፈሳዊ መሪ አስተማሪና ምክር ሰጪ እንደመሆኑ መጠን መጋቢው ከእያንዳንዱ ምዕመን ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ይሁን እንጂ እንደ ዋና መሪነቱና አስተዳዳሪነቱ ግን ኃላፊነትንና ሥልጣንን ካካፈላቸው ከሌሎች መሪዎች ጋር መሥራት ይኖርበታል። እንዲህ ያለው የሕብረት አሠራር የቤተክርስቲያኑን ሥራ ፍሬያማ ያደርገዋል። በዚህ መልክ መደራጀቱ በጣም ጠቃሚ ነው። ለሁሉም ወገኖች ሥራውን ቀላል ያደርገዋል። ረዳቶቹ ሥራውን እንደሚወጡ መጋቢው በረዳቶቹ ላይ ሙሉ እምነት ይኖረዋል። መካከለኛው መሪ ከቡድኑ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ይበልጥ ፍሬያማ ይሆናል። በመዋቅሩ ውስጥ የሚኖራቸውን ሥፍራና ጥያቄ፣ ሲኖራቸውም ምን እንደሚያደርጉ ስለሚያውቁ ሠራተኞቹ በራስ የመተማመን ስሜት ይኖራቸዋል።

## መሪውና ድርጅቱ

### ዓላማ 5 መሪው ከድርጅቱ ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ለመግለጽ

ብዙ መሪዎች ከድርጅቱ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በሁለት መንገድ ነው። በመጀመሪያ በድርጅቱ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ሥፍራ ያውቃሉ። በሁለተኛ ደረጃ በራሳቸው ኃላፊነት ዙሪያ እንዴት እንደሚያደራጁ ሊያውቁ ይገባል። አስቀድመን እንደተመለከትነው ውጤታማ የአመራር ስልት በራሱ በመሪው ጥረትና የሚሠራበት መዋቅር ውጤት ነው። ደካማ አመራር ያለው ጠንካራ ድርጅት መዋቅር አልባ ሊሆን ይችላል። ደካማ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ያለ መልካም መሪም እንዲሁ ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል። በመንፈሳዊ ሥራ፣ ሥራውን በሚገባ ለማከናወንና ዓላማን እግቡ ለማድረስ ሁለቱም ያስፈልጋሉ።

ስለዚህም የመሪነት ሥልጣን ስትቀበል መዋቅሩን እንደሚገባ መረዳት አለብህ ማለት ነው። የድርጅቱን አስተዳደር ሰንጠረዥ አጥናው። የሥራ ድርሻህን እንዲያብራሩልህ የበላዮችህን ጠይቃቸው። የሚጠበቅብህን እወቅ። ምናልባትም በጽሑፍ የሠፈረ የሥራ ዝርዝር ሊሰጥህ ይችላል፡ አንተም ሆንህ ሌሎች ጥርት ያለ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ ነው የሚፈለገው። ሌሎችን በበላይነት እንድትመራ ከተፈለገም፣ የሥራ ድርሻህን ለሌሎች ለማሳወቅ ስብሰባ መጥራት ሊያስፈልግህ ይችላል።

## እንዴት እንደምታደራጅ

አዲስ ድርጅትን እንድታዋቅር ወይም ቀድሞ የነበረውን እንድታሻሽል ከተፈለገ ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎብሀል ማለት ነው። ቀጥሎ መመሪያ ሊሆኑህ የሚችሉ አንዳንድ ነጥቦች ተሰጥተዋል፡-

1/ የሥራ ዝርዝሮችን ወይም ደግሞ ግላማዎቹን እግብ ለመድረስ መደረግ ያለበትን የሥራ ዝርዝር አውጣ።

2/ ለሥራው መሳካት ምን ያህል ሰዎች እንደሚያስፈልጉህ በማጥናት የእያንዳንዱን ሰው የሥራ ድርሻ ዘርዝር ።

3/ የአንዱ የሥራ ድርሻ ከሌሎች የሥራ ድርሻ ጋር ያለውን ግንኙነት አንተም ሆንህ ሌሎች በደንብ እንድትረዱት ሠንጠረዥ አውጣ።

4/ ተገቢ ሰዎችን በተገቢው ሥፍራ አድርግ። (ትክክለኛ ሰዎችን እስክታገኝ ድረስ የፈጀ ጊዜ ቢፈጅ ኃላፊነት በሚጠይቅ ሥፍራ ላይ ማንንም አታስቀምጥ። ከዚህ ይልቅ ተገቢውን ሰው ፈልገህ አሰልጥን።

5/ በተቻለ መጠን አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች አስፈላጊውን መረጃ ስጣቸው። አንድ ጊዜ ለሁሉም ገለጻ ከሰጠህ በኃላ ግር ያላቸውን ነገር እንዲጠይቁ እድል ስጣቸው።

6/ እያንዳንዱ ሰው ያለበትን ኃላፊነት (ተጠያቂነት) በግልጽ አስቀምጥ። እያንዳንዱ ሠራተኛ የሚጠበቅበትን፣ መብትና ግዴታውን ምን ድረስ እንደሆነ ይወቅ። እቅድ ለማውጣት በሚጠቅሙ ማለትም መቼ? የት? እንዴት? በሚሉ ጥያቄዎች ተጠቀም። የሥራ ውጤታቸውን እንዴት በጽሑፍ እንደሚያሰፍሩና እንዴት ሪፖርት እንደሚያቀርቡ አስተምራቸው። ሥራው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ወሰን፣ የድርጅቱን አሠራር ፖሊሲ አብራራላቸው። አንተም ሆንህ ሌሎች ከተመክሯቸው እንዲማሩና

ለወደፊቱም መሻሻል እንዲያደርጉ ሥራውን የምትገምተው፣ ውጤቱንም የምትመዝኑበት ዘዴ ይኑራችሁ።

10/ ከድርጅቱ ጋር በሚኖረው ግንኙነት መሪው፡-

ሀ/ በድርጅቱ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅ አለበት

ለ/ የሚጠበቅበትን ማወቅ አለበት።

ሐ/ በመዋቅሩ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅ አለበት።

መ/ የሥልጣኑ ገደብ ምን ያህል መሆኑን ማወቅ አለበት።

*የሙከራ ፈተና*

**እውነት ወይም ሐሰት፡- በእያንዳንዱ እውነት በሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ባለው ክፍት ቦታ "እ"፡ ሐሰት በሆነው ዐረፍተ ነገር "ሐ" ፊደልን በመጻፍ በተሰጠው ቦታ መልስህን አስፍር።**

-----1/ ከዳዊት ሕይወት እንደምንመለከተው ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ጥሪ የሚመጣለት በተፈጥሯዊ ችሎታው አስቀድሞ መጠቀም ሲችል ነው።

----2/ ትህትናና ድፍረት አስፈላጊ ባሕርያት ናቸው። ደፋሮች የምንሆነው እግዚእብሔር የብርታታችን ምንጭ መሆኑን ስለምናውቅ ነው። የትህትናችን መሠረት ደግሞ ክብሩ ሁሉ የእግዚአብሔር መሆኑን ስለምናውቅ ነው።

------- 3/ ዳዊት በጎልያድ ላይ የተቀዳጀው ታላቅ ድል መሪ አድርጎታል። ስለዚህም የራሱን ፈቃድ ለማሟላት ነጻ ነበር።

------- 4/ ከዳዊት ህይወት የምንመለከታቸው ሶስት የአመራር ዘዴዎች፡-

1/ ዘወትር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈልግ ነበር።

2/ ከበላዮቹም ሆነ ከበታቾቹ ጋር በነበረው ግንኙነት ፍጹም ታማኝ ነበር።

3/ ክብርን ለእግዚአብሔር እየሰጠ ምንጊዜም የተሻለና ብቁ ሆኖ ለመገኘት ይጥር ነበር።

---5/ ምንም እንኳ ዳዊት ቤተመቅደስን ለመሥራት ባይፈቀድለትም ለቤተመቅደሱ ግንባታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሟላት ነበረበት። ይህ የሥራ ክፍፍል ዳዊት የመገንባት ብቃት እንዳልነበረው ነው የሚያመለክተው።

--- 6/ እቅድ ማውጣት በሃሳባችን የምናደርገው ቢሆንም አስፈላጊው ነገር ማሰቡ ሳይሆን በተግባር መፈጸሙ ላይ ነው፡፡

----7/ ዳዊት ካደረገው ዝግጅት የምንመለከተው ምሳሌ በሥራ ክፍፍል ከብዙ መሪዎች አንዱ መሆኑን ነው፡ አንዱ ያዘጋጃል፡፡ ሌላው ይሠራል፡፡ ይሁን እንጂ ሥራውን ተፈጻሚ የሚያደርግ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

----8/ መቅደሱን ለመገንባት ካደረገው ዝግጅት መልካም የአመራር ባሕርያትን እንመለከታለን፡፡ እቅድ ነበረው፡፡ ለሠራተኞቹ አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጥ ነበር፣፡ ለመቅደሱ ሥራ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልቷል፡፡

------9/ ያለበቂ እቅድ የሚደረጉ ነገሮች ብቻ ናቸው ሁለቱ መሠራት ያለባቸው፡፡

-------10/ እቅድ ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህም አስፈላጊ የሚሆነው ወጪንና የብዙ ሰዎችን ተሳትፎ በሚጠይቅ ሥራ ብቻ ነው፡፡

-----11/ በመሠረቱ እቅድ የአእምሮ ሥራ ብቻ ነው፡፡

------12/ እቅድ ማውጣት ለሥራው መሳካት ዋስትና ነው፡፡

------13/ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች **ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይልቅ የተደገፍከው ፕሮግራምህን ነው** በማለት መሪውን ሲወቅሱ ይሰማል፡፡ ስለዚህም በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ “ዕቅድ” ማውጣት እንቅፋት እንደሆነ ይታሰባል፡፡

-----14/ እግዚአብሔር ሥራችንን እንደሚባርክ ሁሉ እቅዳችንንም መባረክ እንደሚችል ቅዱሳት መጻሕፍት ያሳያሉ፡፡

-----15/ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት እንዲለወጡ ሆነው የተዘጋጁ ይሆናሉ፡፡

------16/ ድርጅት ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዴት ግንኙነት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በሚያሳይ እቅድ ላይ ውጤታማ ለሆነ ሥራ የግንኙነት መስመር መዘርጋት ነው፡፡

------17/ የሕዝቡ ፍላጎት እንዲሟላ መሪውም እንዲከበር ከተፈለገ የድርጅቱ የሥልጣን መስመር መከበር ይኖርበታል፡፡

------18/ በዋናው መሪና በሌሎች መሪዎች መካከል አለመግባባት እንዳይኖር በየግዜው ተገናኝተው መወያየት አለባቸው፡፡

-----19/ በመካከለኛው መሪ ሥር ያለ ግለሰብ ወደ ዋናው መሪ ቢሄድ ዋናው መሪ መካከለኛውን መሪ ሳያሳትፍ ለጉዳዩ እልባት ሊሰጥ ይችላል፡፡

----20/ ክርስቲያናዊ አገልግሎት እንደሚገባ እንዲሠራ ከተፈለገ መልካም ድርጅትና መልካም አመራር ሊኖር ይገባል።

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

1/ መልስህ ሊሆኑ የሚችሉ፡- ለእግዚአብሔር ሥራ እቅድ ነበረው። ሰዎች ራሳቸውን እንዲሰጡ ጠየቀ። ሰዎች እንዲሠሩ ለመገፋፋት ስለ ሥራው በስሜት ተናገረ።

2/ አስቀድሞ እቅድ እንዳላወጣ፣ ግልጽ መመሪያ እንዳልሰጠ አስፈላጊውን ነገር እንዳላሟላ ማስተዋል ይኖርብሃል።

3/ መ/ ጌታ እንደሚጠቀምበት እምነት ነበረው።

4/ ሀ/ ያለበትን ደረጃ በሀቅ አስደግፎ ተናገረ።

5/ ለ/ ሥልጠናና ብቃት

6/ የአንተ መልስ

7/ ሀ/ 3/ሰዎች ለ/5/ቁሳቁሶች ሐ/6/ዓላማዎች መ/1/ጊዜ ሠ/4/ ዘዴዎች ረ/2/ሥፍራ 8/ሐ/ የሥራውን ሂደት ለመወሰን የምናደርገው 6/የአንተ መልስ ሙከራ እቅድ

9/ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ ሊገጥሙን የሚችሉ ሦስት መሰናክሎች፡-

1/ እቅዶች ሁልጊዜ ተፈጻሚ አይሆኑም

2/ እቅድ ስለሚያወጡ ክርስቲያኖችን ሰዎች ሊወቅሷቸው

3/ እቅድ ጊዜንና በርትቶ መሥራትን ይጠይቃል።

10/ ሐ/ በመዋቅሩ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ማወቅና አስፈላጊ ሰዎችን ማደራጀት

## ክፍለ ትምህርት አምስት

# መሪዎች መልዕክት ያስተላልፋሉ።

በአራተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የዳዊትን ምሳሌነት በመከተል ያገኘናቸውን የመሪነት መመሪያዎችን እንዴት በሥራ ላይ ለመተርጎምም እንደምንችልና ድርጅት በሚለው ሃሳብ ላይ በማተኮር የድርጅት ዓይነቶችንና መመሪያዎችን ተመልከተናል።

በዚህ በአምስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የኢያሱን የመሪነት መመሪያዎች እንደ ምሳሌ በመውሰድ በሥራ በመተርጎም የሚያስፈልገውን ጥረት በማድረግ በመሪነት ሥራ ላይ ላለ ሰው ከሌሎች ጋር ግንኙነት እያደረገ ወቅታዊ መልእክቶችን ማስተላለፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የኢያሱ ምሳሌት
- መልእክትን የማስተላለፍ ሂደት
- መሪዎች አለመግባባቶችን ያስወግዳሉ

--------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፡፡

- የኢያሱን ሕይወት አስመልክቶ የአመራር አሠራሮችን በመከተል እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርጋቸውም መግለጽ፡፡
- ግንኙነትና መልእክት ማስተላለፍ የሚለውን ሃሳብ መግለጽ፡፡ መሪነትን በተመለከተ የመልእክትን በትክክል ማስተላለፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ፡፡
- ውጤታማ መሪ ለመሆን ሰዎች የሚሰጡትን አስተያየት ማዳመጥና ምላሽ መስጠት አስፈላጊነቱን ለመግለጽ፡፡

--------------------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 1፣3፣1-13፣ 4፡1-8፡ 6፡6-17፡ 18፡፣21 43-45 እና ምዕራፍ 22 አንብብ፡፡

2/ የክፍለ ትምህርቱን ማጠናከሪያ እንደሚገባ አጥና፡፡ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን መልስ፡፡

3/ በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር መልሶችህን በማስተያየት የተሳሳትከው ካለ አስተካክል፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ**

**የኢያሱ ምሳሌነት**

## ዓላማ 1 መጽሐፈ ኢያሱን መሠረት በማድረግ መልእክቱን ለሰዎች ለማስተላለፍ ምሳሌነቱንና፣ የተጠቀሱትን ሰባት ዓይነት መልእክትን የማስተላለፊያ ዘዴዎችን ለመግለጽ

ከኢያሱ ሕይወትና ሥራ ለአንድ መሪ የሚያስፈልጉትን አብዛኛዎቹን ባሕርያት ለመቅሰም ይቻላል። ተከታይ መሆንን፣ በኋላም ደግሞ መሪ መሆንንና ሌሎችን ማበረታታትን የተማረው ከሙሴ ነበር። ከሰዎች ጋር አብሮ ለመጋራት አንዳንድ ችግሮች ገጥመውታል። የጌታን ምሪት ባለመሻቱም አንዳንድ ስህተቶችን ፈጽሟል። በጥንቃቄ አቅዶችን አውጥቷል። ድፍረት ለተሞላበት ሥፍራ ምሳሌ ሆኗል። በሰላዮቹና በረዓብ ሲያደርግ እንደተመለከትነውም የሚፈልገውን ዓላማ ግብ ላይ ለማድረስ በሌሎች አማካይነት ሰርቷል።

ኢያሱ የዓይነተኛ መሪና በሌሎች ሁኔታዎችም ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ሰው ለመሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለንም። ይሁን እንጂ በዚህ ትምህርት አንዱን በጣም አስፈላጊ የሆነውን የኢያሱን ሕይወት ገጽታ ብቻ ነው የምንመለከተው። በተዋጣለት ሁኔታ መልእክትን ለሰዎች ማስተላለፍን በሚገባ የተረዳ መሪ በመሆኑ እንደሚገባ ተግባር ላይ በማዋል ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር እንዴት እንደሚገናኝ የሚያውቅ መሪ መሆኑ ተመስክሮለታል።

አንድ መሪ ሃሳቡን ወይም መልእክቱን እንደሚገባ ለሌሎች ማስተላለፍ ሳይችል ሲቀር የሚፈጠር ችግር ይኖራል። ምንም እንኳ ሰዎቹ ብቁዎች ቢሆኑም ሥራ ሲበዛባቸውና መልእክትን በትክክል ማስተላለፍ ሳይችሉ ሲቀሩ ጌታን በቅንነት ለማገልገል የሚፈልጉ ቢሆኑም በቀላሉ አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል።

በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አልፎ አልፎ አለመግባባት ሊፈጠር እንደሚችል ከመጽሐፈ ኢያሱ የምንመለከተው አንድ ምሳሌ ሊሆነን የሚችል ታሪክ አለ። የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገዶች እኩሌታ ከዮርዳናስ ወንዝ በስተምሥራቅ የርስት ድርሻቸውን ተቀብለው እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምዕራብ ርስታቸውን መውረስ ከነበረባቸው ሌሎች እስራኤላውያን ጋር አብረው ሄዱ። ውጊያው በድል ከተጠናቀቀ በኋላ ኢያሱ ባረካቸውና ወደ ርስታቸው ተመለሱ (ኢያሱ 22)።

በከነዓን ምድር ወዳለው ወደ ዮርዳኖስ አቅራቢያም በመጡ ጊዜ የሮቤል ልጆችና የጋድ ልጆች የምናሴም ነገድ እኩሌታ በዚያ በዮርዳኖስ አጠገብ ታላቅ መሰዊያ ሠሩ።

ይህም ሌሎች ነገዶችን በጣም ስላስቆጣቸው ሊወጓቸው ተነሡ፡፡ የእግዚአብሔር መሰዊያ መኖር ያለበት በሴሎ ብቻ እንደሆነ ከዚያ በፊት ስምምነት ተደርጎ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የእውነተኛው አምላክን አምልኮ ከሌሎች አሕዛብ አምልኮ መሠዊያ ለመለየት ነበር፡፡ ስለዚህም ወንድሞቻቸው ከእምነት እንዳፈነገጡና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳፈረሱ አሰቡ፡፡

የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ተደናግጠው "**በዚህ ሥፍራ መሥዋዕት የማቅረብ ዓላማ የለንም፡፡ በፍጹም አልተረዳችሁንም፡፡ እኛ ሁላችን በሴሎ እውነተኛውን አምላክ የሚያመልኩ ወገኖቻችን አካል መሆናችንን ሁሉም እንዲያውቅልን እንፈልጋለን፣፡ እግዚአብሔርን ማክበር እንጂ በእርሱ ላይ የማመጽ ዓላማ የለንም፡፡ ዋናው ዓላማችን የሚቀጥለው ትውልድና እኛም የእርሱ ሕዝብ መሆናችንን እንዲያውቁ መታሰቢያ እንዲሆን ብቻ ነው ይህን መሠዊያ የሠራነው**" አሏቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ በፊት ጎን ለጎን ሆነው ጠላትን ሲዋጉ የነበሩ ወንድሞች አሁን ደግሞ እርስ በርስ ለመዋጋት መዘጋጀታቸውን ነው የሚያስረዳው፡፡ ይሁን እንጂ መሠዊያው የተሠራበትን ትክክለኛ ዓላማ በመረዳታቸው ሳይዋጉ ቀሩ፡፡ የዓላማ መግባባት በመኖሩም ሁሉም ደስ አላቸው፡፡

1-3 መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 22 ካላነበብህ አሁኑኑ አንብበው፡፡ በተለይም ከ11-24 ያሉትን ቁጥሮች በጥንቃቄ አንብባቸው፡፡ ከዚያም በኋላ እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር የተሟላ የሚያደርገውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡

1/ በገሊሎት መሰዊያ መሰራቱን እስራኤላውያን ሲሰሙ፡-

ሀ/ የተሠራበትን ምክንያት አወቁ ሐ/ የተሠራበትን ምክንያት ገመቱ

ለ/ የተሠራበትን ምክንያት ጠየቁ

2/ እስራኤላውያን ተቆጥተው ለውጊያ የተነሱት፡

ሀ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢአት በማድረጋቸው

ለ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢያት አድርገዋል ብለው ስላሰቡ

ሐ/ ሌሎች የሚያደርጉት ሁሉ ትክክል መስሎ ስለማይታያቸው

3/ የእስራኤል ሕዝብ ተወካይ ወደ ሌሎች ነገዶች ሄደው፡-

ሀ/ ለምን መሰዊያውን እንደሰሩ ጠየቋቸው

ለ/ መሰዊያውን እንዲያፈርሱ ጠየቋቸው

ሐ/ በእግዚአብሔር ላይ አምጻችኋል ብለው ወቀሷቸው፡፡

4/ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስወገድ እስራኤላውያን ምን ማድረግ ነበረባቸው? -------------------------------

5/ የተፈጠረውን አለመግባባት ለማስወገድ የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ምን አደረጉ?-------------------------------------------

ኢያሱን የመሰለ መሪ ያስፈለገበትን ምክንያት ለመገንዘብ ስለሚረዳን ይህ ታሪክ በጣም ጠቃሚ ነው። በዚያን ወቅት ለእያንዳንዱ እርምጃ ግልጽና ጥርት ያለ መመሪያ ማስፈለጉን ጌታ አውቋል። አዲስ ሕይወት እየጀመሩ ስላሉበት ሁኔታ ማወቅ ስለተሳናቸው ከጌታ ዘንድ መልእክት የሚቀበልና ለሕዝቡም መመሪያ የሚሰጥ ጠንካራ መሪ አስፈለጋቸው።

ታላቅ የጦር መሪ እንዲሆን ኢያሱን ያሰለጠነው ሙሴ ነበረ። ከዚህም በበለጠ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃልና ቃሉን መከታተልን ተምሯል። ለመሪነት የጠራውም ራሱ እግዚአብሔር ከመሆኑም ሌላ ***"ለአባቶቻችሁ እሰጣችኃለሁ ብዬ የማልኩላቸውን ምድር ለዚህ ህዝብ ታወርሳለህና ጽና፣ አይዞህ-----አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና አይዞህ አትፍራ-------"***(ኢያሱ1፣ 6-9) የሚል ተስፋ የተሰጠው ሰው ነበር።

ምናልባትም ኢያሱ ስለራሱ ዝቅተኛ ግምት ያለውና ፈሪ ሳይሆን ስለማይቀር ሊሆን ይችላል እግዚአብሔር እየደጋገመ አይዞህ የሚለው። ስለጥሪው እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ግን ድፍረቱንና በራስ መተማመኑን ሲያስመስክር እናገኘዋለን። መሪነቱን የጀመረው፣ ***"አምላካችሁ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጣችሁ ምድር እስከ ሦስት ቀን ይህን ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ልትወርሷት ትገቡባታላችሁና ስንቃችሁን አዘጋጁ"*** የሚል የማያሻማ ትእዛዝ በመስጠት ነበር። (ኢያሱ 1፣10-11)።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ኢያሱ ግልጽ የሆነ መልእክት ለሕዝቡ ሲያስተላልፍና መልእክቱን ለማስተላለፍ የሚያስችለውን ችሎታ እንዳዳበረ እንገነዘባለን። በመጽሐፈ ኢያሱ ሰባት መልእክትን ወይም ሀሳብን ለሰዎች ያስተላለፈበትን መንገዶችን እናገኛለን። እያንዳንዱን በዝርዝር ለመረዳት እንዲረዳህና ለወደፊቱ በቀላሉ ልታገኛቸው እንድትችል ኢያሱ ያስተላለፋቸውን መልእክቶች በመጽሐፍ ቅዱስህ ላይ አስምርባቸው።

**መመሪያ ቃላት**

መጽሐፈ ኢያሱ 2:1፣ 3:2-4፣ 9:8፡ 3-8

ባለሥልጣኖቹ ወደ ሰፈር ሄደው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለሕዝቡ ነገሯቸው። ለጉዟቸውም ሆነ ለሚደርጉት ውጊያ የሚሰጣቸውን መመሪያ ሕዝቡ በትክክል መስማትና መረዳታቸውን ማረጋገጥ የኢያሱ ዓይነተኛ ባሕርይ ነበር። የሚያስፈልግ ከሆነም መመሪያዎቹን ደግሞ ደጋግም ይነግራቸዋል። አስፈላጊውን ሥራ ለተለዩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ይሰጣል። በኃላፊነት ለሚሳተፉትም የሥራ ድርሻቸውን ያብራራላቸዋል። **"ስሙ፡ አድምጡ"** በማለት የሚሰጣቸውን መመሪያ በትክክል እንዲቀበሉ ያነቃቸዋል (ኢያሱ 3፤9)። ምንም አድበስብሶ የሚያልፈው ነገር የለም። የሥራ ድርሻውን እንዲወጣ ለእያንዳንዱ ሰው በቂ መረጃ ይሰጠዋል።

በጥንቃቄ የሚሰጥ መመሪያን ተቀብለው ሰላዮቹ ወደ ረሐብ ሲሄዱ፣ የዮርዳኖስን ወንዝ ሲሻገሩ በኢያሪኮ መውደቅና ዘመቻ ሲያደርጉ በተገኘው ውጤት መመልከት ይቻላል። በጣም ጥቂት ከሆኑ ሰዎች በስተቀር ሕዝቡ **"ኢያሱ እንዳዘዛቸው አደረጉ"** (ኢያሱ 4፡8።) የሚያደርጉትንና የሚጠበቅባቸውን እንደሚገባ ስለሚያውቁ በፍጹም መተማመንና እርስ በርስ በመተባበር ሥራቸውን አከናወኑ።

**የማበረታቻ ቃል**

መጽሐፈ ኢያሱ 3፡5፤ 10፡24-25፤ 23፡5

ኢያሱ ሕዝቡን፡- ***"በቅርቡ በእነዚህ ነገሥታት አንገት ላይ እግራችሁን አኑሩ፣ እግዚአብሔር በምትወጓቸው በጠላቶቻቸው ሁሉ ላይ እንዲህ ያደርጋልና አትፍሩ፣ አትደንግጡ፡ ጽኑ አይዞአችሁ"*** አላቸው (ኢያሱ 10፡24-24)። ድልንም ሆነ ማበረታታትን ከሕዝቡ ጋር በመካፈሉ የሚያገኙት ድል አንድን ሥራ ከማከናወን በላይ መሆኑን እንዲገነዘቡ ይረዳቸው ነበር። ወደፊት ለሚደረገው ነገርም ተስፋ ስለሚሆን፣ ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሔር በረከት ማስረጃ ነው። በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ በእምነት እየበረቱ በመሄዳቸው የሚጠበቅባቸውን በፍጹም ልባቸው ለማከናወን በቁ።

**ትእዛዛትና ሥርዓት- መጽሐፈ ኢያሱ 6፡16**

እንደ ጦር መሪነቱ ኢያሱ ለሕዝቡ ቀጥተኛና የማያወላውል ትእዛዝ መስጠት እንዳለበት ተረድቷል። ኢያሪኮ በወደቀችበት ጊዜ ከሆነው ሁኔታ እንደምንመለከተው አንድ መሪ ከሕዝቡ ፍጹም ታዛዥነትን የሚጠብቅበት ወቅት ይኖራል። ኢያሱ ለተከታዮቹ የሚያስብና የሚያከብር መሪ ምሳሌ ነው። በዚያው መጠን ሕዝቡም ይተማመኑበትና ያከብሩትም ጀመር። ስለዚህም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፍጹም

ይታዘዙለታል። ይህ መሪዎች በተለይም ደግሞ ከወጣቶች ጋር የሚሠሩ መሪዎች ሁሉ ሊከተሉት የሚገባ ምሳሌ ነው።

***መረጃ (ትምህርት)*** - *መጽሐፈ ኢያሱ* 24-1-13

ኢያሱ ለሕዝቡ ታሪካቸውንና ዓላማቸውን አስገነዘባቸው። እንደ አንድ አስተዋይ መሪ ሁሉ ለሕዝቡ ተገቢውን መረጃና አስፈላጊውን ነገር ማሳወቅ ለሥራው መቃናት አስተዋጽኦ እንዳለው ያውቃል። መሠረታዊው እውነትና የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት የጌታን ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ በአዲስ መልክ ሊቀርብላቸው ይገባል። ኢያሱ የእግዚአብሔርን ቃል ደግሞ ደጋግሞ ይነግራቸው ነበር እንጂ **"ይህንን ድሮም ታውቁታላችሁ"** የማለት ልማድ አልነበረውም። መልእክትን ወይም ሀሳብን ለሕዝቡ የማስተላለፍ ጉዳይ አንድ ጊዜ ብቻ ተጠናቅቆ የሚያበቃ ጉዳይ አይደለም። ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው።

**ማግባባት (ምክር) - መጽሐፈ ኢያሱ 23፡6-16፣ 24፣14-24**

ብዙውን ጊዜ በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ መልእክት ወይም ሃሳብ የሚተላለፈው በምክር ወይም በስብከት መልክ ነው። ብዙ መሪዎች ሁሉም የሕዝብ ግንኙነት የዚህ ዓይነት እንደሆነ ያስባሉ። የመሪዎችን ፈቃድ እንዲፈጽሙ አዘውትረው ሰዎችን ይመክራሉ። ያበረታታሉ። ይሁን እንጂ ሰዎችን ከሚገባ በላይ ማነሳሳትና መገፋፋት ውጤት አልባ ይሆናል። ኢያሱ ሰዎችን ስለማበረታታት መልካም ምሳሌ ይሰጠናል። ወደፊት ስለሚጠብቃቸው ነገር ለሕዝቡ እንዲናገር የመራው ራሱ ጌታ ነበር። ከኢያሱ ንግግር አራት ዋና ዋና ፍሬ ሃሳቦችን የምንረዳው ውጤታማ የሕዝብ ግንኙነት በእነዚህ ነጥቦች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ነው።

**1/ ለአእምሮ የሚስማማ ጥሪ ማቅረብ፣-** ***"ከዚህ በፊት የሆነውን ሁላችሁም ታውቃላችሁ፣፡ ስለዚህም ያንን ያደረገ እግዚአብሔር ወደፊትም እንደሚያደርግ ማመን አይከብዳችሁም"*** (ኢያሱ 23፡14-16)።

2/ **ማስጠንቀቂያ፡** ***"እምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ቃል ስታፈርሱ --- በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድባችኃል"*** (ኢያሱ 23፡23፡16)።

3/ **ማበረታታት፡** ***"በጣም በርቱ"*** (ኢያሱ 23፡6)።

4/ **ምርጫና ውሳኔ እንዲያደርጉ ዕድል መስጠት፡** ***"የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ"*** (ኢያሱ 24፡15)

በንግግር መልእክትን ወይም ሃሳብን ማስተላለፍ እንደሚቻል ሁሉ በጽሑፍም ማስተላለፍ ይቻላል። ኢያሱ ሁኔታዎችን በጽሑፍ ያሰፍርና የእንቅስቃሴውንም ሪፖርት ይቀበል ስለነበር ከአንድ መሪ የሚጠበቀውን አድርጓል። ምናልባትም መልክ ባለው ሁኔታ በፋይል መያዙ ብዙ መሪዎች ይስማሙበታል። እግዚአብሔር የመረጣቸው መሪዎች ስለእርሱና ስለሕዝቡ በጽሑፍ ባያስተላልፉልን ኖሮ ምንኛ ብዙ ነገሮች ባመለጡን ነበር።

**በምሳሌ መልእክትን ማስተላለፍ- መጽሐፈ ኢያሱ 4:1-9**

"የእነዚህ ድንጋዮች ነገር ምንድነው?" መልእክት ማስተላለፍ ሲባል ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ከአንድ ሰው ወደ ሌላው መልእክትን ማስተላለፍ ወይም ሃሳብን መግለጽ ማለታችን ነው። ይህም ሊደረግ የሚችለው በንግግር በጽሁፍና ምሳሌያዊ በሆኑ ነገሮች በመጠቀም ጭምር ነው። ኢያሱ በድንጋይ ክምር ተጠቅሞ አስፈላጊ የሆነ መልእክትን ለሕዝብ አስተላልፏል። በቤተክርስቲያን ውስጥ የምንመለከታቸው እንደ መስዊያ፣ መዘምራንና ካህናት የሚለብሱዋቸው ልብሶች ተምሳሌታዊ በሆነ ሁኔና መልእክትን የምናስተላልፍባቸው መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። መንበርከክ፣ እጆችን ወደ ላይ መዘርጋት፣ ማጨብጨብ ተምሳሌታዊ መልእክቶች ናቸው። አንድ መልካም መሪ ከአካል እንቅስቃሴውና ገጹ ላይ በሚነበበው ሃሳብ ሰዎች ትርጉሙን መረዳት አለመረዳታቸውን እርግጠኛ ይሆናል። ስለዚህም በቃል የሚተላለፈውን ያህል በተምሳሌታዊ መንገድ ማስተላለፍም ውጤት አለው ማለት ነው።

6/ በመጽሐፈ ኢያሱ የተመለከትካቸውን ሰባቱን የመልእክት የማስተላለፊያ መንገዶችን ለማስታወስ ሞክር። ከዚያ በኋላም ቁጥሩን በክፍቱ ስፍራ በመሙላት አብረው የሚሄዱትን አመልክት።

1. መመሪያ 2.ማበረታታት ትእዛዝ 3. ትእዛዝ 4. መረጃ

5. ማግባባት 6. በጽሑፍ ማስፈር 7. ምሳሌዎች

------ሀ/ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፣፡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን (ኢያሱ 24-15)።

----ለ/ ኢያሱ በድንጋዮቹ ላይ የሙሴን ሕግ ጻፈባቸው(ኢያሱ 8፣32)

---ሐ/ ወደዚህ ቀርባችሁ የአምላካችሁን የእዚአብሔርን ቃል ስሙ አለ (ኢያሱ 3:9)

---መ/ ከእናንተም ሰው ሁሉ በእሥራኤል ልጆች ነገድ ቁጥር በጫንቃው ላይ አንድ አንድ ድንጋይ ይሸከም (ኢያሱ 4፡5-6)።

-----ሠ/ አትፍሩ፣ አትደንግጡ፣ ጸኑ አይዞአችሁ (ኢያሱ 10-25)

---ረ/ የእሥራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" (ኢያሱ 24-2)

----ሰ/ እናንተ ግን እርም ካደረጋችሁት በኋላ እርም ከሆነው ነገር ራሳችሁን ጠብቁ (ኢያሱ 6፡18)።

## የመልእክት ማስተላለፊያ ሂደት

### ዓላማ 2 የመልእክት ማስተላለፊያ ሂደትንና የሚገጥሙ መሰናክሎችን ለመግለጽ

እስከ አሁን ድረስ ለሰዎች መልእክትን ስለማስተላለፍ በርከት ያሉ ምሳሌዎችን ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ስለ ሂደቱ በመተንተን አስፈላጊውን ግንዛቤ ለማግኘት እንሞክራለን። ቀደም ሲል የተመለከትናቸውን አንዳንድ ዝርዝሮችን ለማስታወስ ያህል፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ልናስተላልፈው የምንፈልገው መልእክት ወይም መልእክቱን ለማስተላለፍ የሚፈልግ ሰው ይኖራል። ሰውየው አንድ ዓይነት ፍላጎት ወይም ትርጉም ያለው መልእክት ማስተላለፍ ይፈልጋል። ይህም ሀሳቡን፣ ስሜቱን ወይም ደግሞ አንድ ዐይነት መረጃ የሚገልጥ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ መልእክቱ የሚተላላፍለት ተቀባይ ሰው ይኖራል። መልእክቱ የሚቀበል ሳይሆን የራሱ ስሜትና ግንዛቤ ያለው ነው፣ ምናልባትም በዚህ በሚተላለፍለት መልእክት ላይ የራሱ ተጽዕኖ ይኖራል። መልእክቱን አስተላላፊው ሰው ሌሎች ሰዎች ሊገባቸው በሚችል ትክክለኛ የሆነ መንገድ ለማግኘት መልእክቱን የማስተላልፊያ ዘዴዎችን መምረጥ አለበት። መልእክት የምናስተላልፍበት ዋናው ዓላማ ተቀባዩ መልእክቱን በምንፈልገው መንገድ እንዲረዳልን ለማድረግ ነው።

ብዙዎቻችን ይህን ማድረግ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ አንረዳም። በሚተላለፈው መልእክትና ተቀባዩ መልእክቱን በሚቀበልበት ሁኔታ መካከል አንዳንድ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከሰዎች ጋር ስለምንግባባበት ሂደት ማወቅ እንደሚገባ ለመረዳት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ መሰናክሎችን በጣም ይጠቅመናል። ከዚያ በኃላ ደግሞ እነዚህን እንቅፋቶች እንዴት ማስወገድ እንደሚቻልና ውጤታማ በሆነ መንገድ

እንዴት መልእክታችንን ለሰዎች ማስተላለፍ እንደሚቻል የሚረዱንን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

1/ **ቋንቋ፡-** አንዳንድ ቃላት ከአንድ በላይ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ አንዳንድ ቃላት ደግሞ ልዩ ትርጉም የሚሰጡባቸው ስፍራ ይኖራል፡፡ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ልዩ ወይም ምሳሌያዊ የሆነ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለዚህም ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በዮሐ 3፡1-12 ላይ እንደገና መወለድ የሚለውን ቃል ኒቆዲሞስ በምን ዓይነት መንገድ እንደተረዳው አስተውል፡፡ (ዮሐ 3፡1-12 አንብብ) መልእክቱን የሚያስተላልፈውም ሆነ መልእክቱን የሚቀበለው ሰው ቃላቱን በተመሳሳይ መንገድ የማይረዱ ከሆነ እንደሚገባ ተላልፏል ለማለት ያዳግታል፡፡

2/ **ምሳሌዎች፡-** ብዙውን ጊዜ መልእክትን የምናስተላልፈው በንግግር በመግለጽ አይደለም፡፡ አንዲት ሴት ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላትን አክብሮትና ፍቅር በመመልከት ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት እንደተነሳሳች አንድ መጋቢ መስክሯል፡፡

ይህ ቀና በሆነ መልኩ በምሳሌያዊ ቋንቋ መልእክት የሚተላለፍበት መንገድ ነው፡፡ የሰውነት እንቅስቃሴያችን፣ የእጅ አሰናዘራችን፣ በገጻችን የሚነበበው ሁኔታና ድምፃችን ከምንናገረው ጋር የማይጣጣሙ ከሆነ እንቅፋት ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚወድ እየተናገረ መጽሐፍ ቅዱሱን ቢወረውረው ወይም ደግሞ በአቧራ እስኪሸፈን ድረስ ችላ ቢለው ምንድነው የሚያስተላልፈው መልእክት? የአክብሮትና የፍቅር ወይስ የንቀትና የጥላቻ?

3/ **ባሕላዊ አመለካከቶች፡-** እያንዳንዱ ሕዝብ፣ ጎሳ፣ ነገድ ወይም ቡድን የራሱ ባሕል አለው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ባሕላችን ከሌሎች ሁሉ የላቀና ከሌሎች ይልቅ ትክክለኛ እንደሆነ እናስባለን፡፡ ለምሳሌ ያህል በአንዳንድ ባሕሎች ሴቶች ከመጨባበጥ ይልቅ ጉንጭና ጉንጫቸውን ያነካካሉ፡፡ እንደዚህ ዐይነት ባሕሎችን የማናከብር ከሆነ ትክክለኛ መግባባት ሊኖረን አይችልም፣ እንዲያውም ጸብ ሊፈጠር ይችላል፡፡

4/ **አግባብ የሌለው ጥላቻ፡-** በእግዚአብሔር ፊት ከራሳችን ጋር እኩል እንደ ሆኑ ከማንገምታቸው ሰዎች ጋር መግባባት አዳጋች ነው፡፡ ከንቀት የተነሳ አለመግባባት እንደተፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ በርከት ያሉ ምሳሌዎች ይሰጠናል፡፡ አይሁዳውያን ሳምራውያንና ሌሎች አሕዛብን ከእነርሱ ያነሱ አድርገው ይመለከታቸው ስለነበር ሌላው ቀርቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንኳ እንዳይቀበሉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡ እንዲህ

ዓይነቱን አግባብ የሌለው ጥላቻ እንዲያስወግድ ለጴጥሮስ በራዕይ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር (የሐዋ 10)፡፡

5/ **የደረጃ መበላለጥ፡-** አንዳንድ ሰዎች በደረጃቸው ከእነርሱ ከሚያንሱም ሆነ ከሚበልጡ ጋር ግንኙነት መፍጠር ያስቸግራቸዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ገበሬ ከሜካኒክ ይልቅ እንደርሱ ገበሬ ከሆነ ሰው ጋር በሀሳብ መግባባት ይቀለዋል፡፡ ለሠራተኞቻቸው ስለ ጌታ መመስከር የሚከብዳቸው ብዙ ሀብታም ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ለአለቆቻቸው ወይም ለአሰሪዎቻቸው መመስከር የሚከብዳቸውም ብዙ ክርስቲያኖች አሉ፡፡ ይህንን በሚመሳሰሉ እንቅፋቶች ምክንያትም ለጌታና ለሰዎች ያለን ፍቅር ውጤት አልባ ይሆናል፡፡ አንድ የተዋጣለት መሪ ግን በተለያየ ደረጃ ካሉ ሰዎች ጋር መግባባትና ሃሳቡንም ለማስተላለፍ መቻል አለበት፡፡ ለዚህም የመጀመሪያው ደረጃ ችግሩን መረዳትና ከዚያ ትሕትና በተሞላበት መንገድ ለማስወገድ መጣር ነው፡፡

6/ **የዕድሜና የጾታ ልዩነት፡-** ከደረጃ መበላለጥ ጋር በቅርበት የተያያዘው ሌላው እንቅፋት ደግሞ የጾታ ልዩነት ነው፡፡ ሽማግሌዎች ከወጣቶች ጋር በሀሳብ መግባባት ያዳግታቸዋል፡፡ ትኩረታቸውና ፍላጎታቸው በጣም ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ጊዜ የቡድኑ መሪ በታቀደው ፕሮጀክት ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡ ከሆነ በመጋቢው ቤት የራት ግብዣ እንደሚደረግላቸው ተናገረ፡፡ ወጣቶቹ የሚፈልጉት ግን በሐይቁ ዳርቻ መንሸራሸርን እንጂ ከመጋቢው ጋር ራት መብላትን አልነበረም፡፡ ይህም መሪውን አናደደው፡፡ የታቀደው ፕሮጀክትም ውጤታማ ሳይሆን ቀረ፡፡

በዘመናችን በጣም በመስፋፋት ላይ ያለው እንቅስቃሴ የሴቶች እኩልነት ነው፡፡ አስተዋይ ክርስቲያን መሪዎች ይህን በቸልታ አይመለከቱትም፡፡ በጉዳዩ ያስቡበታል፡፡ ይጸልዩበታል፣ የእያንዳንዱን ጾታ ችግር ለመረዳትና መፍትሔም ለመሻት ይሞክራሉ፣ አዳጋች ቢሆንም እንኳ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ሥፍራ ያለው መሆኑን ስለሚያስታውቃቸው በጣም ይጠቅማቸዋል፡፡

7/ የተማርከውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሌሎች መልእክት ማስተላለፍ ምን ማለት እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ፡፡------------

8/ የተማርከውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መልእክት ለሌሎች ለማስተላለፍ እንቅፋት ስለሆኑ ጉዳዮች ስንነጋገር ምን ማለታችን እንደሆነ በራስህ ቃላት ግለጽ፡፡----------

9/ አንድ ዓይነት እንቅፋት በመፈጠሩ ከሰዎች ጋር አለመግባባት ወይም የሀሳብ መተላለፍ ገጥሞህ እንደሆነ የራስህን ልምምድ አስፍር-------------

## የጠለቀ አስተሳሰብ አስፈላጊነት

## ዓላማ 3 ለሰዎች መልእክትን በማስተላለፍ ሂደት የጠለቀ አስተሳሰብን አስፈላጊነት ለመግለጽ

የመልእክቱ ተቀባይ ግንዛቤና አስተሳሰብ በመልእክቱ ትርጉም ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል ቀደም ሲል ተመልክተናል፡፡ በሌላ አነጋገር የመልእክቱ ትርጉም የሚወሰነው በተቀባዩ የጠለቀ አስተሳሰብ መሠረት ነው፡፡ ስለዚህ በተገቢው መንገድ መልእክታችንን ማስተላለፍ ከመቻላችን በፊት መልእክቱ የሚተላለፍለት ሰው ስላለው ግንዛቤ አስቀድሞ ማወቅ ይረዳል፡፡

በከፊል ቢሆንም የአንድ ሰው አስተሳሰብና ግንዛቤ የዕድሜ፣ የጾታ፣ የደረጃ መበላለጥና የባሕል የመሳሰሉት ነገሮች ውጤት ናቸው፡፡ ሌሎች ሁለት ዓበይት ጉዳዮች ደግሞ የግለሰቡ ባሕርይና የሕይወት ልምምድ ናቸው፡፡ መልእክት ለሌሎች ስለ ማስተላለፍ ጥናት ያደረጉ ጠበብት አንድ ዓይነት መልእክት እንዴት የተለያየ ግንዛቤ ሊያሳድር እንደሚችል ለመረዳት እንዲያመቻቸው በሰብአዊ ባሕርይ ምድቦች ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ መሠረት አራት ዓይነት የሰብአዊ ባሕርይ ምድቦች ሲኖሩ እነርሱም፡-

1/ **የሐሳብ ሰዎች፡-** መሪው ማንኛውንም ነገር ምክንያታዊ በሆነና ሐቅን በተመረኮዘ መንገድ እንዲያብራራላቸው የሚፈልጉ፡፡

2/ **የስሜት ሰዎች፡-** ስሜታቸውን የሚያነሳሳና የሚያነቃቃ ነገር የሚፈልጉ

3/ **የማየት ሰዎች፡-** እንዴት እንደሚሠራ ለማየት ምሳሌዎች የሚፈልጉ

4/ **የተፈጥሮ አስተዋይነት ያላቸው ሰዎች፡-** በፍጥነት ወደ ማጠቃለያ ሃሳብ የሚደርሱና የተሰወሩ ትርጉሞችን የማግኘት ችሎታ ያላቸው፡፡

በቡድኖቻቸው ውስጥ እነዚህ አራት የባሕርይ ዓይነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚገነዘቡ መሪዎች ለሁሉም የሚስማማ የተመጣጠነ መልእክትን ያቀርባሉ፣ አንዳንድ ሰዎች ለምን ከሌሎች ይልቅ መልእክቱን ፈጥነው እንደሚረዱ ወይም እንደሚቀበሉ ይገነዘባሉ፡፡ በትክክለኛው መንገድ ግለሰቦችን ያቀርባሉ፡፡ ውጤት ባለው መንገድ ሥልጠናና ምሪት ይሰጣሉ፣ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ባህርይ እንዳለው ያውቃሉና ሰዎች መልእክታቸውን በተሳሳተ መንገድ ቢረዳባቸውም እንኳ አይናደዱም፡፡

ሌላው የባሕርይ ዓይነቶችን የምንመድብበት መንገድ ደግሞ ሰዎች በሚያሳዩት በሌሎች የመደገፍና በሌሎች ከመደገፍ ነጻ የመሆንና በራስ የመተማመን ዝንባሌ ነው፡፡ በሌሎች መደገፍን የማይፈልጉ በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች ግን የራሳቸውን ሃሳብ የመግለጽ ዕድል እንዲሰጣቸው የሚፈልጉ ናቸው፡፡ መሪው ዝርዝር መመሪያዎችን እንዲሰጣቸው ሳይሆን አጠቃላይ መመሪያ ብቻ እንዲሰጣቸውና የራሳቸውን የፈጠራ ችሎታ እንዲያዳብሩ የሚፈልጉ ናቸው፣ እነዚህ የተለያየ ዓይነት ባሕርይ ያላቸው ሰዎች አንድን መልእክት በእንዴት ያለ ሁኔታ እንደሚረዱት እንዲያውቅ በማድረግ ለመሪው ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጠዋል፡፡

ማንኛውም ግንዛቤና አስተሳሰብ ባለን ልምምድ ላይ የተደገፈ ነው፡፡ ማንኛውም ዓይነት መልእክት የማስተላለፊያ መንገድ ልምምድን ለሌሎች በማካፈል ላይ ሊደገፍ የሚችል ነው፡፡ እንዲህም ሲባል የሚተላለፈው መልእክት ተቀባይነት የሚኖረው አስተላላፊውም ሆነ ተቀባዩ በጋራ የሚግባቡበት ቋንቋ ሲኖራቸው ነው ማለት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ሰው አንድን ነገር በተለየ ሁኔታ እንዲያይ የሚያደርገው የራሱ ልምምድ ሊኖረው ይችላል፡፡

ይህም በአስከፊ ጦርነት መሳተፍ፣ በአስፈሪ ማዕበል ውስጥ ማለፍ፣ ወይም እንደስራ አይነቱና የጋብቻ ህይወቱ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለ ሥፍራ፣ ሰዎችና አንዳንድ አስተሳሰቦች ያለን ትርጉም ካሳለፍነው ልምምድ የተነሳ በአስደናቂ ሁኔታ ሊለወጥ ይችላል፡፡ ስለዚህም የሰዎችን ልምምድ በምንረዳበት መጠን በዚያው ልክ ከእነርሱ ጋር ሃሳብ ለሀሳብ መግባባት እንችላለን ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ግንኙነት ከዚህ የጋራ ተሞክሮ መነሳት አለበት፣ የምናስተላልፈው ማንኛውም መልእክት ከተቀባዩ የሕይወት ልምምድ ወይም ተሞክሮ ጋር መጣጣም ይኖርበታል፡፡

10/ የአንድ የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ ከሥራው ጋር የተያያዘ ስብሰባ በመምራት ላይ እያለ "**በጣም ትንንሽ ለሆኑ ሕፃናት የተለየ ክፍል ያስፈልገናል፡፡ አስፈላጊውን ቁሳቁስ ካሟላን ደግሞ በዚሁ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ክፍል አለ**" በማለት ተናገረ፡፡

አንዲት የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ የሆነች "**እምን ለሕፃናት የሚሆኑ መጻሕፍትና ለማስተማሪያ የሚረዱ ብዙ ሥዕሎች ያስፈልጉናል**" አለች፡፡ የአምስት ልጆች እናት የሆነች ሌላ አስተማሪ ደግሞ "**ለሕፃናት መቀመጫ የሚሆኑ ምቹ**

**ወንበሮችና ጥቂት አሻንጉሊቶች ያስፈልጉናል"** በማለት ተናገረች፡፡ በዚህ ውይይት የተብራሩት የትኞቹ መገለጫዎች ናቸው?

ሀ/ መሪው ሃሳቡን በትክክል አለማስተላለፉ

ለ/ የመጀመሪያዋ አስተማሪ በራስ የመተማመን ባሕርይ ያላት መሆኗ

ሐ/ ልምምድ በግንዛቤና በአስተሳሰብ ላይ ተጽእኖ ያለው መሆኑ

መ/ የልጆች እናት የሆነችው አሳቢ አስተማሪ መሆኗ

11/ ከላይ የጠቀስነውን የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊ ይህን ትምህርት የጀመርንበትን ምሳሌያዊ ገለጻ እንደገና ተመልከት፡፡ ባስቀመጥነው ሰብአዊ ባሕርይ ምድብ ውስጥ እንድታስቀምጠው ብትጠየቅ የትኛው ምድብ ውስጥ ታስቀምጠው ነበር?------

በሌሎች የሚደገፍ ወይም በራሱ የሚተማመን ዓይነት ሰው እንደሆነ ብትጠየቅስ ምን ብለህ ትጠራው ነበር?-----------------------------

**መልእክትን የማስተላለፊያ እንቅፋቶችን ያስወግዳሉ**

**ዓላማ 4 መሪዎች በራሳቸውና በሚመሯቸው ሰዎች መካከል አርኪ በሆነ መንገድ እንዴት መልእክት ለማስተላለፍ እንደሚችሉ ለመግለጽ**

እስካሁን ድረስ መልእክትን ወይም ሃሳብን ለሰዎች በማስተላለፍ ረገድ መሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ተመልክተናል፡፡ ይህም ስሕተት የሚያስተላልፉትን መልእክት ወይም ሀሳብ ሰዎች ሁሉ ይረዱልናል ብለው ማሰባቸው ነው፡፡ በትክክለኛ መንገድ መልእክትን ማስተላለፍ ውስብስብ ጉዳይ ስለሆነ መልእክታችንን አድማጮች ሊረዱልን በሚችሉት መንገድ ማስተላለፍ የሚቻልበት ሁኔታ ላይ በማተኮር እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ሃሳቦችን እናቀርባለን፡፡

1. **ማስተላለፍ የምትፈልገውን መልእክት እወቅ፡-** መልእክቱን አንተ ራስህ እንደሚገባ መረዳትህን አረጋግጥ፡፡ ለሌሎች ከማስተላለፍህ በፊት ራስህ ለራስህ ተናገረው ወይም በጽሑፍ ግለጸው፡፡ የተድበሰበሰ ሳይሆን ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማ ይኑርህ፡፡ የሀሳብህን ዝርዝር ዋና ዋና ነጥቦች በማስታወሻ ላይ የማስፈር ልምድ ይኑርህ፡፡
2. **በሚቻልህ መጠን መልእክቱን ስለምታስተላልፍላቸው ሰዎች ዕወቅ፡-** አንድን መልዕክት ወይም ሀሳብ ሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ሊረዱት

እንደማይችሉ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ይሁን እንጂ የሰዎችን ግንዛቤ፣ የስብዕና ዓይነቶችንና የተለያዩ ተሞክሮዎችን እንደሚገባ የሚረዱ መሪዎች መልካም ውጤት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ስለሰዎች ብዙ ባወቅህ መጠን፣ በዚያው ልክ ተሞክሯቸውን ትካፈላለህ፣ በዚያው ልክ በአጥጋቢ ሁኔታ መልእክትህን ልታስተላልፍላቸውም ትችላለህ፡፡

3. **ትክክለኛው ግልጽ በሆነ አነጋገር ተጠቀም፡-** ግልጽና ቅንነትን በሚያንጸባርቁ ቃላት እንጂ፣ ወደኋላህ የምትለው ነገር ያለህ ይመስል ንግግርህ ድብስብስ አይሁን፡፡ በሚቻልህ መጠን አፍረጥርጠህ ንገራቸው፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ነገር እንደሚሆን እገምታለሁ በሚሉ ድብስብስ ቃላትን አስወግድ፣ ችግር ካለ ለሁሉም በግልጽ ተናገር እንጂ ስሙን ለመግለጽ የማትፈልገው ሰው አንድ ጥፋት እንዳጠፋ አትናገር፡፡ ሰዎች ላይረዱህና ምናልባትም ሊጎዱ ወይም ሊናደዱ ይችላሉ፡፡
4. **ምላሽ እንዲሰጡ አበረታታቸው፡-** መልእክትህን እንደሚገባ ተረድተው እንደሆነ ከምታረጋግጥበት መንገድ አንዱ እንዲጠይቁና ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ ነው፡፡ ዘወትር መረጃዎችን ስጥ፡፡ ይህንንም ለቡድኑ የሚያስተላልፉ ሰዎችን መምረጥ ትችላለህ፡፡ ማንኛውንም አስተዋፅዖ በአክብሮት እንደምትቀበል በቃልህም ሆነ በድርጊትህ አሳያቸው፡፡

12/ ስለ አፍኬ ታስታውሳለህን? ለትክክለኛ መልእክት ማስተላለፊያ ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች፡-

ሀ/ ማስተላለፍ ስለምትፈልገው መልእክት ደህና ዕውቀት መኖር

ለ/ ግልፅና ጥርት ባለ አነጋገር መጠቀም

ሐ/ ስለምትናገራቸው ሰዎች ማወቅ የሚቻልህን ያህል ማወቅ

## ማድመጥ መልእክትን የማስተላለፍ አንደኛው ክፍል ነው

የተዋጣላቸው መሪዎች መልእክትን የማስተላለፋቸውን ያህል ሌሎችንም ያደምጣሉ፡፡ ማድመጥ አራት ሂደቶችን ያካትታል፡፡ የመጀመሪያው መስማት ነው፡፡ እንዲህም ሲባል የድምጽ ርግብግቢትን መቀበል ማለታችን ነው፣ ሁለተኛው ትኩረት መስጠት ነው፡፡ ብዙ ድምጾችን እንሰማለን፣ የምንሰማቸውን ድምጾች ሁሉ ግን ትኩረት አንሰጣቸውም፡፡ ከምንሰማቸው ድምጾች መካከል አንዱን ስንመርጥ ግን ትኩረት

ሰጥተነዋል ማለት ነው፡፡ ትኩረት ከሰጠነው ደግሞ መልእክቱን ለመረዳት ዝግጅት አድርገናል ማለት ነው፡፡ የመጨረሻውና አራተኛው ማስታወስ ነው፡፡ መልእክቱን ተቀብለን በአእምሯችን ውስጥ ሰናኖረው ሁሉንም የማድመጥ ሂደቶችን አሟላን ማለት እንችላለን፡፡ በትክክል አደመጥህ የሚባለው ሌላው ሰው ለተናገረው ትኩረትህን ስትሰጠው ነው፡፡ ይህም ጥረትን ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ ያህል አዋቂዎች ሕፃናት ሲናገሩ ይሰማሉ፣ ሆኖም በሚገባ አድምጠውታል ማለት አይደለም፡፡ ይህን ያህል ጠቃሚ እንዳልሆነ ስለምናስብ ትኩረት አንሰጠውም፡፡ ራስህን የበላይ አድርገህ የምትመለከት ከሆነ የሌላውን ሀሳብ መቀበል ያዳግትሃል፡፡ ከቸኮልህ ወይም አእምሮህ በሌላ ጉዳይ ተይዞ ከሆነ ቃላቱን ብቻ ትሰማለህ፣ እንዲያውም እንደሚገባ ሳታደምጥ መልስ መስጠት እንኳ ትችላለህ፡፡

ፍላጎት ካለህ የማድመጥ ችሎታን ማዳበር ይቻላል፡፡ “**ይህ ሰው ሊናገር የሚፈልገውን እንደሚገባ ማድመጥ አለብኝ**” በማለት ራስህን ሥርዓት በማስያዝ ሰውየው ሊናገር የሚፈልገው ዋጋ ያለው ነገር ዋጋ ሊኖረው እንደሚችል እመነ፡፡ እንደሚገባ ማድመጥ የምትፈልግ ከሆነ የሚከተሉትን ተግባር ላይ አውል፡፡

1/ ሃሳብህን በሙሉ በሚናገረው ነገር ላይ አድርግ፡፡

2/ የሚናገረው ነገር እንዳስደሰተህና በንቃት እየተከታተልህ መሆኑን በአካልህና በዓይኖችህ ግለጽ፡፡

3/ በምንም ዓይነት ተናጋሪውን አታቋርጥ፡፡

4/ ተናጋሪው መልእክቱን እስኪጨርስ ድረስ አለመስማማትህን አትግለጽ፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን ራስህን በማነቃነቅና ወደፊት የምትግባቡበትን ነጥብ አድምጠው፡፡

5/ አጠቃላይ መልእክቱን ተረዳ እንጂ፣ የተወሰኑ ቃላት ላይ አታተኩር፡፡

6/ ትዕግሥተኛ ሁን፣ ችኩልትንና ለሌላ ጉዳይ መጣደፍህን አታሳይ፡፡

7/ ያልተረዳኸው ካለ ጥያቄ አቅርብ፣ ጥያቄህ ረጋ ያለና ዓላማ ያለው ይሁን፡፡

8/ መልእክቱ ካበቃ ባኋላ አስተያየት ስጥ እንጂ በስሜት ተገፋፍተህ አትስጥ፡፡

9/ መልእክቱን ለማመዛዘንና ትክክለኛ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችልህ ከተነገረው ውስጥ ሃቁን ከሃሳቡ ለመለየት ሞክር፡፡

10/ ተናጋሪው ከአንተ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚጠብቅ ጥረት አድርግ ምናልባት ከአንተ የሚፈልገው መረጃ፣ እርዳታ ወይም ደግሞ በሀሳቡ መስማማትህንና ከጎኑ እንደምትቆም ማወቅ ሊሆን ይችላል፡፡

13/ ከቡድኑ አባሎች አንዱ "**ሠይጣን እቅዳችንን አደናቅፎብናል፣ በመሆኑም ስድስት ሰዎች ስብሰባችን ላይ አልተገኙም። ምን ማድረግ አለብን?**" ሲል ተናገረ። የቡድኑ መሪ ግን፡- "**ሁሉንም ነገር ሠይጣን ላይ አታሳብብ**" የሚል ምላሽ ነበር የሰጠው። ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማድመጥ መሪው ማሟላት ያቃተው ነገር ምንድነው?"

**የማሻሻያ አስተያየት መቀበል**

የተሳካላቸው መሪዎች መልእክት ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎችን ሰምተው እንዴት ማሻሻል እንዳለባቸው የውቃሉ፡1 መልእክት የማስተላለፍ ሂደት ከተናጋሪው ተነስቱ አድማጩ ዘንድ ይደርሳል። ከዚያም መልእክቱ ይመለስና ተናጋሪውው ዘንድ ይደርሳል፣ ይህ ሂደት የማደርሰው መልእክት በቃል ወየም ስሜትን በመግለጽ ሊሆን ይችላል። ስለማድመጥ ስንነጋገር እነደተመለከትነው በትክክል ማድመጠ ምላሽ ወይም አስተያየት መስጠትን ይጠይቃል።

ሰዎች ከመሪው ጋር ሃሳብ ለመለዋወጥ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ምላሽ ካላገኙ እንደተናቁ ያስባሉ፣ ወይም መሪውን ይንቃሉ። ምላሽ የሚሰጥ ከሌለ ሰው በሌለበት በባዶ ክፍል ውሰጥ ተናግሮ እንደመውጣት የሚቆጠር ነው፡1 ይህ ለሰዎች ከመናገር በጣም የራቀ ነው። ልዩቱ ባዶ ስፍራ ብቻ ሳይሆን ምላሽ የሚሰጥህ ባለመኖሩ ጊዜ በከንቱ መባከኑ ነው። መሪው መልካም ምላሽ የማይሰጣቸው ከሆነም ሰዎች የማያመች ስሜት ነው የሚሰማቸው።

መልእክት በማስተላለፉ ሂደት አስተያየት መስጠትና መቀበል ተናጋሪውና ሰሚው በትክክል መግባባታቸውን ለመረዳት ያስችላል። አንዳንድ ጊዜ በሰዎች ገጽታ ላይ የምንመለከተው መልእክትህን በሚገባ መረዳታቸው ወይም አለመረዳታቸውን ነው።

አስተያየት የመስጠትና የመቀበል ሌላው ጠቀሜታ ደግሞ ስለ ራስህ ያለህን ግምት እንድታዳብር ማድረጉ ነው። መሪው አስተያየት የሚሰጠው ሰዎችን ለማበረታታትና የታሰበውን ብቃትና ችሎታ እንዲረዱ ለማድረግ ነው። ስህተታቸውን በማሳየትና በማንኳጠጥ የምንሰጠው አሉታዊ አስተያየት ግን ሰዎችን ተስፋ ሊያስቆርጣቸውና ራሳቸውን ብቃት እንደሌላቸው አድርገው እንዲያስቡ ሊያደርጋቸው ይችላል።

የምንሰጠው አስተያየት በከፍተኛ ደረጃ የሥራ እንቅስቃሴው ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። ከመሪዎቻቸው የሚፈልጉትን አስተያየት የማያገኙ ሰዎች ሥራቸውን በሚገባ ለመወጣት እንደሚያዳግታቸው በዚህ ላይ በማተኮር የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ።

መልካም የሥራ እንቅስቃሴ በከፊልም ቢሆን በራስ የመተማመን ውጤት ነው፡፡ ከዚህም በላይ እያንዳንዱ ሠራተኛ ሥራውን በሚገባ መረዳቱን መገንዘብ ለመሪው ልብ እረፍት ይሰጣል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አስተያየት የምንሰጠው ቢሆንም፣ የተዋጣላቸው መሪዎች ግን ፍሬያማና ውጤታማ የሆነ አስተያየት የሚሰጡት በሚገባ ተረድተውና ሆን ብለው ነው፡፡ በመንፈሳዊ አገልግሎት ሰዎችን ስትመራ የምትሰጠው አስተያየት የተሠራውን ሥራ በመገምገም ለተሻለ ውጤታማነት እገዛ ለማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል የመምህራንን ቡድን እየመራህ ከሆነ የማስተማር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ልትረዳቸው ትወዳለህ፡፡ በቡድንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ በሚኖርህ ውይይት የተገኘውን ውጤት ወይም ለእነርሱ ያለህን አመለካከት ለመሰንዘር እድል ታገኛለህ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አስተያየት ለመስጠት የሚረዱህን ነጥቦች በማጥናት በሥራ ላይ ለማዋል ሞክር፡፡

1/ **ግምት የምትሰጠው ለሥራው እንጂ ለግለሰብ አይሁን**፡፡ ለሥራው ቸልተኛ ነው ወይም ለእግዚአብሔር ሥራ ግዴለሽ ነው የሚለውን ሃሳብ ሳትሰነዝር፡- "**ይህ ሥራ መሻሻልና በሚገባ መሠራት አለበት**" በል፣

2/ **ገምጋሚ ከሆኑ ቃላት ይልቅ ገላጭ በሆኑ ቃላት ተጠቀም**፡፡ አንድን አስተማሪ ሰነፍ ነህ ከማለት ይልቅ በቂ ጥናት ወይም ዝግጅት ማድረግ አለብህ ማለት ይሻላል፣

3/ **አስተያየት የምትሰጥበት ጊዜ ወሳኝነት አለው**፡- አንድ ሠራተኛ እገዛ ወይም ምክር ሲጠይቅህ የሚቻል ከሆነ ወዲያውኑ ምላሽ ስጠው፣ ሰዎች ተሰፋ በቆረጡበት ሁኔታ ወይም ደግሞ በቂ የውይይት ጊዜ ሳይኖር እርማት መስጠት አይቻልም፡፡

4/ **የምትሰጠው ምላሽ መጠን በጣም አሰፈላጊ ነው**፡- ብዙውን ጊዜ እንደሚታየው በጣም የተመጠነ አስተያየት መስጠት ይሻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መሪው ሰዎች እርግጠኛነት እንዳይሰማቸው ማድረግ የለበትም፡፡

14/ ለሰዎች መልእክት የማስተላለፍን ሂደት በአጭሩ ግለጽ፡፡-----------------

15/ መልእክትን ወይም ሃሳብን በማስተላለፍ ረገድ የመሪዎች ዋና ዋና ኃላፊነቶች ምንድናቸው?-----------------------------------------------------

**የሙከራ ፈተና**

እንደ እስራኤል መሪነቱ ኢያሱ ጠቃሚ የመሪነት መመሪያዎችን አሳይቷል፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ካሳያቸው መመሪያዎችን ጋር አብሮ የማይሄደው?

ሀ/ ኃላፊነትን ለሚጋሩት ሁሉ ስለሥራው መመሪያና ገለጻ ይሰጥ ነበር፡፡

ለ/ የሚሰጣቸውን መመሪያ በትክክል እንዲፈጽሙ ይነግራቸዋል፡፡

ሐ/ ያለፈውን ትውልድ ችግር እያነሳ እነርሱንም የሚጠብቃቸው ያው እንደሆነ ይነግራቸዋል፡፡

መ/ የሕዝቡን እምነት ያበረታታና ያሳድግ ነበር፡፡

2/ እስራኤል የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ ማወቅ አለባቸው፡፡ መረጃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህንንም እንዳይዘነጉት ኢያሱ በሚያሳምን አነጋገር መንፈሳዊ ግዴታዎቻቸውን ነግሯቸዋል፡፡ ይህ ለረጅም ጊዜ የሚተላለፍ መረጃ፡-

ሀ/ ሲወርድ ሲዋረድ በሚተላለፍ መልኩ መልእክትን በቃላት መግለጽ

ለ/ ሀይማኖታዊ ሥርአቶችን የሚፈጽሙና ለሕዝቡ የሚያብራሩ ካህናትን ማደራጀት ነው፡፡

ሐ/ ላለፈው ዋጋ የሚሰጥ ባሕልን ማዳበር፡፡

መ/ የመንፈሳዊ ሕይወት ኃላፊነቶችንና መብቶችን ለሌሎች የሚያስተላልፉ መዝገቦች፡፡

3/ ጃስፐር በሰዎች ወደተሞላ ቤተክርስቲያን ገባ፡፡ አምልኮው ምሥጋናው፣ የቃሉ አገልግሎትና ሌላው ቀርቶ መሠዊያውና በቤተክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ቁሳቁሶች እንኳ ሳይቀሩ የተለየ ስሜት አሳድረውበታል፡፡ ይህም ስሜቱ የምን ውጤት ነበር?

ሀ/ ተምሳሌታዊ በሆነ ሁኔታ መልዕክትን ማስተላለፍ

ለ/ ጽኑ እምነት ስለነበረው

ሐ/ ለሀይማኖታዊ ልምዶች ከሚገባ በላይ ንቁ በመሆኑ

መ/ ለመንፈሳዊ ነገሮች ልዩ ግምት በሚሰጥ ባህል ውስጥ በማደጉ

4/ መልዕክት ለሌሎች ሰዎች የማስተላለፍ ሂደት አላማው የመልእክቱ ተቀባይ

ሀ/ የሚተላለፈውን መልእክት እንደሚገባ እንዲሰማ ማድረግ ነው ለ/ የመልእክቱ አስተላላፊ እንዳቀረበው ትርጉም እንዲረዳ ማድረግ ነው

ሐ/ መረዳት በሚገባው መንገድ የተነገረውን መልእክቱን መረዳት ነው

መ/ ተናጋሪውም ሆነ አድማጩ ተመሳሳይ ግንዛቤ አላቸው፡፡

5/ ትክክለኛ የሃሳብ መግባባት ተፈጥሯል ማለት የሚቻለው፡-

ሀ/ ተናጋሪውና ሰሚው በአንድ ዓይነት ሁኔታ እውነቱን መገንዘብ ሲችሉ

ለ/ ለሕይወት ተመሳሳይ ግንዛቤ ሲኖራቸውና የሚወድዱትም ሆነ የሚጠሉት ተመሳሳይ ሲሆን፡፡

ሐ/ ቃላትን በተመሳሳይ መንገድ መረዳት ሲችሉ፡፡

መ/ ለምሳሌያዊ አነጋገሮች አንድ ዓይነት ግንዛቤና መረዳት ሲኖራቸው፡፡

6/ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪው አገር ሰዎች ሰላምታ የሚሰጣጡት ጉንጭ ለጉንጭ በመሳሳም ነው፡፡ ከውጭ አገር ከተመለሰ ወዲህ ግን አስተማሪው ይህን ልማድ ችላ በማለቱ ሰዎች ቅር ተሰኝተዋል፡፡ ባሕሉን ባለመጠበቁና በዚህም ምክንያት ሰዎች ቅር ስለተሰኙበት ምንድነው ማለት የሚቻለው?

ሀ/ የአገሩ ሰዎች አግባብ የሌለው ጥላቻ አላቸው

ለ/ የሰንበት ትምህርት ቤቱ አስተማሪ ከፍተኛ በደል ፈጽሟል

ሐ/ አስተማሪውና ጓደኞቹ የባህልን ጉዳይ መመርመር አለባቸው

መ/ መልዕክት ማስተላለፊያው መንገድ ተቋርጧል

7/ መልእክት ማስተላለፍ ሂደት የመጨረሻ ውጤት፡-

ሀ/ የመልዕክቱ አስተላላፊ ያሰበውን ትርጉም መያዝ

ለ/ ማንኛውን አድሎ የሌለው ምስክር ትርጉሙን ማግኘት

ሐ/ የመልእክቱ ተቀባይ ትርጉሙ ሲገባው

መ/ ትርጉሙን በቃላቶቹ ትርጉም በግልጽ ሲያመለክት፡፡

8/ መልእክታቸውን ሲያስተላልፉ መሪዎችን የሚፈጽሙት ትልቅ ስሕተት፡-

ሀ/ ሰዎች ሁሉ መልእክታችንን ሊረዱልን ይችላሉ ብለው ማሰባቸው

ለ/ የሚናገሩትን ሁሉ አድማጮች ይረዱታል ብለው ማሰባቸው

ሐ/ በመሪዎችና በተከታዮቻቸው መካከል ያለው ስፍራ በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ግንኙነት ማድረግ ይቻላል ብለው ማሰባቸው

መ/ አብዛኞቹ ሰዎች መልእክታችንን ይረዱልናል ብለው ማሰባቸው

9/ መልእክት በመቀበልና በማስተላልፍ ውስጥ ማድመጥ ከፍተኛ ሥፍራ ስላለው እንደሚገባ አደመጥን ማለት የምንችለው፡-

ሀ/መልእክቱን ስንሰማ ለ/ ለመልእክቱ ሙሉ ትኩረታችንን ስንሰጠው

ሐ/ ስንሰማ፣ ትኩረታችንን ስንሰጠውና መልእክቱን ስንረዳ

መ/ መልእክቱን ተረድተን በአእምሯችን ውስጥ ስናኖረው

10/ አንድ መልእክት ተገቢ ምላሽ አግኝቷል የሚባለው መልእክቱ ከተቀባዩ ተነስቶ ወደ ተናጋሪው ሲመለስ ነው፡፡ ክሚከተሉት ውሰጥ አስተያየት መስጠት ከአንዱ በቀር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ከእነዚህ አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ አስተያየት ተናጋሪውና ሰሚው በትክክል እንዲግባቡ ያደርጋል

ለ/ አስተያየት ሰዎች ስለ ራሳቸው ያላቸውን ግንዛቤ የሚያዳብሩበት ነው

ሐ/ አስተያየት መሪው መመሪያዎችን ለማውጣት የሕዝቡን ስሜት እንዲገመግም ያስችለዋል፡፡

መ/ አስተያየት ሠራኞቹ ለሥራው በሚያደርጉት አስተዋፅኦ ላይ ከፍተኛ ውጤት አለው፡፡

11/ የሚከተሉትን የመልእክት ማስተላለፊያ እንቅፋቶች ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በመጻፍ ከትክክለኛ ገለጻቸው ጋር አዛምድ፡- 1/ ቋንቋ 2/ ምሳሌ

3/ ባሕል 4/ ንቀት 5/ የደረጃ መበላጥ 6/ እድሜና ጾታ

7/ ሰብአዊ ባሕርይ

------ ሀ/ አንድን ሰው ከሌሎች የሚለየው

-----ለ/ አንድን ትውልድ ከሌሎች የሚለያቸውና የወንዶችንና የሴቶችን ባሕርይ የሚገልጸው

-------ሐ/ ትርጉም የሚሰጥ የቃላት ቅንጅት

------መ/ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆናቸውን

-------ሠ/ የደረጃ መበላለጥ አለመቀበል

-------ረ/ አንድን ሰው ከእርሱ ካነሱት ወይም ከበለጡት ጋር ትክክለኛ ግንኙነት እንዳይኖረው የሚያደርግ

-----ሰ/ ያለምንም ቋንቋ መልእክትን ማስተላለፍ የሚቻልበት መንገድ

12/ የተሳካ የመልእክት ማስተላለፍና መቀበል እንዲኖር የሚረዱ ሀሳቦችን ቁጥሩን በተሰጠው ስፍራ በማስቀመጥ ከትክክለኛው ገለጻ ጋር አዛምድ፡፡

1/ የምትናገረውን ማወቅ 2/ አድማጮችህን ማወቅ 3/ አድማጮችህን ማክበር

4/ ትክክል፣ ግልጽ በሆነ ቋንቋ መጠቀም 5/ ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡ ማበረታተት

-------ሀ/ የሰዎችን ግንዛቤ የሰብአዊ ባሕርያቸውንና ልምምዳቸውን አስቀድሞ ለማወቅ ወስን፡፡

------ለ/ የተድበሰበሱ ቃላትን በማስወገድ ግልጽነት ባለቸው ቃላት ተጠቀም

-----ሐ/ ጥያቄ እንዲያቀርቡና ሃሳብ እንዲሰጡ በማድረግ ሃሳባቸውን ተቀበል

-----መ/ ለሰዎች፣ ለችሎታቸውና ለስጦታዎቻቸው እንዲሁም ለስሜቶቻቸው በእኩልነት አድናቆት ይኑርህ፡፡

-------ሠ/ ማስተላለፍ የምትፈልገውን መልእክት እንደሚገባ አጥንተኸው እንደሆነ ለማወቅ እንዲረዳህ በማስታወሻህ ላይ በቅደም ተከተል ያሰፈርካቸውን በመጠቀም ልምምድ አድርግ፡፡

መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ ደግሞ "ሐ" በመጻፍ መልሰ ስጥ

------13/ መሪው የተለያዩ የሰብአዊ ባሕርይ ዐይነቶችን መረዳቱ የተመጣጠነ

መልእክቱን እንዲያቀርብ ከማስቻሉም በላይ ከሰዎች ጋር በተሻለ ሁኔታ

እንዲያቀርብ ይረዳዋል፡፡

---- 14/ በሌሎች የሚደገፍ ሰው ከበላዩ ካሉት ሰዎች ዝርዝር መመሪያ ይፈልጋል፣፡

ከሌሎች ይልቅ ትኩረት ይሻል፡፡

እንዲጫኑት አይፈልግም፣፡ ስለ ሥራውም

ዝርዝር መመሪያ እንዲሰጠው አይፈልግም፡፡

------- 16/ መልእክት አስተላላፊውና ተቀባዩ የጋራ የሆነ ልምምደ ካላቸው በመካከላቸው ተገቢ ግንኙነት እንዲኖር ሁኔታዎች ሁሉ ተሟልተዋል ማለት ነው፡፡

-----7/ በአንድ ማሕበረሰብ የሚኖሩ ሰዎች በአንድ ዓይነት መንገድ እንዲያስቡ የሚያደርጓቸው ተመሳሳይ ልምምድ አላቸው፡፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

8/ የሕዝብ ግንኙነት እንቅፋቶች ስንል የተናጋሪው በሚፈልገው መንገድ የመልእክቱ ትርጉም ወደ ሰሚው እንዳይደርስ የሚያደርግ ማንኛውንም መሰናክል ማለታችን ነው፡፡

1/ሐ/ ምን እንደተሰራ አስቡ

9/ መልሶችህ   2/ለ/ ሌሎች ነገዶች ኃጢአት ሰርተዋል ብለው አሰቡ

10/ ሐ/ የሕይወት ተሞክሮ በግንዛቤ ላይ ጫና አለው

3/ ሐ/ በእግዚአብሔር ላይ እንዳመጹ አሰቡ

11/ ንቁ፡- ይህም ማለት ቶሎ ብሎ ወደማጠቃለያው ሃሳብ የሚደርስና ስውር መልእክቶችን የሚረዳ ሰው ማለት ነው በራሱ የሚተማመን፡፡

4/ ኃጢአት አድርገዋል ብለው ከማሰባቸውና ለጦርነት ከመዘጋጀታቸው በፊት ለምን ያንን መሰዊያ እንደሰሩ ሌሎች ነገዶችን ሊጠይቋቸው ይገባ ነበር፡፡

12/ ሐ/ በተቻለህ መልእክቱን ስለምታስተላልፍላቸው ሰዎች እወቅ፡፡

5/ ምን እያደረጉ እንደሆነ ለመግለጽ ለእስራኤላውያን መልእክተኞችን ሊልኩባቸው ይችሉ ነበር፡፡

13/ አምስተኛውን ሕግ አላሟላም፣ ማለትም በተወሰኑ ቃላት ላይ ከማተኮር ይልቅ አጠቃላይ ትርጉሙ ላይ ማተኮር ይገባው ነበር፡፡

6/ሀ/5/ ማበረታታት ለ.6/ በጽሑፍ ማስፈር ሐ1/መመሪያ መ.7/ምሳሌያዊ ቋንቋ ሠ/2/ማበረታታት ረ.4/መረጃ መስጠት ሰ.3/ትእዛዝ መስጠት

14/የሰጠኸው መልስ ከእኔ መልስ ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል፣፡ መልእክት ሰሚው ተቀባዩ ሊቀበለውና ሊረዳው የሚችለውን መልእክት ያስተላልፋል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ተቀባዩ ለመልእክት ሰጪው መልእክት ያስተላልፋል፡፣ ይህም ምላሽ ወይም አስተያየት ይባላል፡፡

7/ መልስህ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የተላለፈ መልእክት ትርጉም ማግኘት ማለት ነው፡፡

15/ መሪው፡፡ 1/መልእክት ግልጽ ለማድረግ 2/ መልእክቱን በትክክል መረዳታቸውን እርግጠኛ መሆን 3/ ምላሽ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

# ችግሮችን መፍታትና ውሳኔዎች ማስተላለፍ

በአምስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የኢያሱን የመሪነት ምሳሌ በመከተል፣ ለመሪነት ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም መልእክትን ስለ ማስተላለፍና ስለ መቀበል እንደዚሁም ለማሻሻል የሚረዱ ገንቢ አስተያየቶች መስጠት ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳላቸው ጠለቅ ያለ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

በዚህ በስድስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የነህምያን የመሪነት ምሳሌ በመከተል ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ከተመለከትን በኋላ መንፈሳዊ መሪ ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት ምን ምን ማድረግ እንዳለበት እንማራለን፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የነህምያ ምሳሌነት
- መሪነት ችግሮች መፍታትን ይጠይቃል

- መሪነት ውሳኔ ማድረግ ይጠይቃል
- የቡድን ኃይል

-------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ።

- ስለ መሪነት ከነህምያ ሕይወትና ምሳሌት መመሪያዎችን መግለጽና እነዚህን መመሪያዎችን በመሪነት አገልግሎትህ ተግባራዊ በማድረግ ችግሮችን የመፍታት ቅደም ተከተል ትረዳለህ።
- ውሳኔ ማሳለፍንና እንዴት እንደምትመዝናቸው ትመለከታለህ።
- ሰለቡድን ኃይል መጠነኛ ገለጻ መስጠት ትችላለህ፣ ስለሁለቱ የቡድን ኃይል ገጽታዎችም ትወያያለህ።

------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ ጠቅላላውን መጽሐፈ ነህምያን ማንበብ በጣም እንደሚጠቅምህ እናስባለን። በተለይም ደግሞ ከ1-5፣ 6፡15-7፡3፣8 ምዕራፎችን ልዩ ትኩረት ስጣቸው።

2/ በተለመደው ሁኔታ ለጥያቄዎቹ መልስ ስጥ፤፡ መልስ ሰጥተህ ከጨረስህ በኋላ ከመመዘኛው ጋር መልሶችህን አመሳክር።

3/ ክፍል ሁለት /ትምህርት 4-6/ ከልስ

**የነህምያ ምሳሌነት**

**ዓላማ 1 ከነህምያ ሕይወት የመሪነት ባሕርያትንና አሠራርን ለመረዳት**

አይሁዳውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ቂሮስ ባወጀበት ዘመን ነህምያ በፋርስ ቤተ መንግሥት የወይን ጠጅ አሳላፊ ነበር። የነበረበት ደረጃና ታዋቂነቱ መልካም ዕድል አስገኝቶለታል። ሀብትም መብትም ነበረው። ይሁን እንጂ ልቡ በወገኖቹና በሚወዳት አገሩ ላይ ስለነበር የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረሱን ሲሰማ አለቀሰ፣ ጸለየ። እግዚአብሔር ለአንድ ዓይነት ትልቅ ሥራ እንደ ጠራው ተሰማው (ነህ ምዕ/ 1 ና 2 ተመልከት)

ንጉሡ ይህን ተመልክቶ:- ***ለምንድነው ያዘንኸው?*** በማለት ጠየቀ። ***"አገራችን ፈርሳለች፣ ቅጥሯም ተቃጥሏል፣ ስለዚህም ሀዘንና ውርደት ደርሶብናል"*** በማለት ነህምያ መለሰ። ***"ታዲያ ምን ለማድረግ አስበሃል?"*** በማለት ንጉሡ ነህምያን ጠየቀው።

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ እስከዛሬ ድረስ በጽሑፍ ከተሳለፉልን ሁሉ የሚበልጠውን ስለ መሪነት ከፍተኛውን ጉዳይ የምንመለከተው። ነህምያን ያነሳሳው ጉዳይ ለአምላኩና ለሕዝቡ ከተማ ለኢየሩሳሌም የነበረው ፍቅር ነው። ካለውና ከነበረው ሁሉ አስበልጦ ኢየሩሳሌምን ይወዳል።

ነህምያ ራዕይ አለው። አጠቃላይ ሁኔታውን ካወጣ ካወረደ በኋላ አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት አሰቧል፣ ዓላማውን በትክክል አልሟል። ዓላማውን እግቡ ለማድረስ የሚያስችለው ምን እንደሆነ ተረድቷል። በልቡ ያለውን ሃሳብ ለንጉሡ ከመናገር ወደኋላ አላለም። ለንጉሡ አክብሮትን መስጠት እንዳለበት ሳይዘነጋ በድፍረት ***"ወደ ይሁዳ ሄጄ የፈረሰውን የአባቶቼን አገር እንድሠራ እንድትፈቅድልኝ እፈልጋለሁ"*** በማለት ተናገረ።

ለትክክለኛው ሰው የልቡን ሃሳቡን ሲያካፍልና ያለውን እቅድ አሳማኝ በሆነ መንገድ እንዲያቀርብ በማስቻል እግዚአብሔር ነህምያን ሲመራው እናያለን። ***"ምን ያህል ቀን ያስፈልግሃል?"*** በማለት ንጉሡ ነህምያን ጠየቀው። ነህምያ:- ***"እኔም የሚያበቃኝን ጊዜ ነገርሁት"*** ይላል ። አነጋገሩ በእርግጠኝነት የተሞላ ነበር እንጂ ይሆናል አይሆንም የሚል የማመንታት መንፈስ አልነበረውም። ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ ነህምያ ንጉሡን:- ***"የይለፍ ደብዳቤ ይጻፍልኝ፣ ለሥራው የሚያስፈልገኝን እንዳገኝም ከንጉሡ ደን ባለው እንጨት እንድጠቀም ፈቃድ ይሰጠኝ"*** ሲል ጠየቀ።

ቀጥሎ ደግሞ ነህምያ በኢየሩሳሌም ቅጥር ዙሪያ እየተመላለሰ የጉዳትዋን መጠን በጥንቃቄ ሲመረምር እንመለከታለን፣፡ በዚህም ወቅት ምን መደረግ እንዳለበት በአእምሮው እቅድ ሳያወጣ እንዳልቀረ መገመት ይቻላል። አስፈላጊውን መረጃ ካሰባሰበና ትክክለኛ የእግዚአብሔር ምሪት መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ የሀገሬውን ካህናት፣ ሹማምንትና ባላባቶች ሰበሰበና ስለ ጉዳዩ አዋያቸው ምዕ 2።

እቅዱንና ምን ለማድረግ እንደፈለገ በግልጽና በቅንነት አስረዳቸው፡፡ ስለ ሁኔታው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ሐቁን እንዲቀበሉ አደረጋቸው፡፡ የእርሱ ዓላማ የእነርሱም ዓላማ መሆኑን በሚገባ ካሳያቸው በኋላ ***"ከሐፍረትና ከውርደት እንድንድን ኑ የኢየሩሳሌምን ከተማ ቅጥሮችን እንሥራ"*** በማለት አነሣሣቸው፡፡ እያንዳንዱ ወገን በቤቱ አቅራቢያ ያለውን ቅጥር እንዲሠራ ተናገረ፡፡ እያንዳንዱ ወገን የሠራውን ለማወቅም የጽሑፍ ማስረጃ ይይዝ ነበር ምዕ 3፡፡

በአብዛኞቹ መሪዎች ላይ እንደሚደርሰው ሁሉ ነህምያም ከውስጥ ከራሱ ወገኖችና የውጪ ጠላቶቹ ችግር ፈጥረውበት ነበር፣ ጠላቶቹ ሥራውን ለማገድ በውጊያ ሠራተኞቹንም ተስፋ በማስቆረጥ በስድብ ተስፋ ለማስቆረጥና ሥራውን ማገድ ቢሞክሩም አልሆነላቸውም፡፡ ነህምያ ሰዎቹን ራሳቸውን ከጠላት እየተከላከሉ ሥራውን እንዲቀጥሉ ሰዎቹን በማደራጀት እርሱ ራሱም አብሮአቸው እየሠራ ያበረታታቸው ነበር፡፡ (ነህምያ 4፡14)፡፡

ዛሬ ወይም ነገ ጠላቶቻችን አደጋ ይጥሉብናል በሚል ሥጋት ውስጥ ሆነው እንኳ ሰዎቹ ሌትና ቀን እየሠሩ ነበር፣ አንዳንድ ሰዎች ግን በሌሎች እንዴት እንደሚጠቀሙ ተመልክቶ ነህምያ በጣም አዘነ፡፡ በምርኮ በነበሩበት ወቅት አንዳንዶች ብዙ ሀብት አጠራቅመዋል፣ ሌሎች ደግሞ በቂ ምግብ እንኳ አልነበራቸውም፡፡ ከርታታ የሆኑ ድሆች እንዴት እንደሚበዘበዙ ተመልክቶ ለሃብታሞች አላደላም፣ የራሱን ከፍተኛ ሥፍራም አላስጠበቀም፡፡ ***"የምታደርጉት ትክክለኛ አይደለም፣ ድሆችን መበዝበዛችሁን አቁሙ"*** በማለት በግልጽ ነገራቸው፡፡ እንደመንፈሳዊ መሪነቱ ሠራተኞቹ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልሠሩና እርስ በርሳቸውም በሠላም መኖር ካልቻሉ ምንም ዓይነት ትርጉም ያለው ሥራ መሥራት እንደማይቻል ተገንዝቧል፣ የሥራውንም ያህል ሰዎች አስፈላጊ መሆናቸውን በሚገባ ተረድቷል፡፡

ነህምያ የይሁዳ አገር ገዢ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በመብቱ አልተጠቀመም፡፡ ለራሱ ብቻ የሚበቃውን መልካም ምግብ ከማዘጋጀት ይልቅ ከችግረኞች ጋር ነበር የሚመገበው፡፡ በግሉ ለሚያስፈልገው ጉዳይ በቂ ገንዘብ ስለነበረው ለሚሠራው ሥራ ደመወዝ አይቀበልም ነበር፡፡ ለራሱ ሃብትና ርስት ከማብዛት ይልቅ ሙሉ በሙሉ ራሱን ለሥራው ሰጠ፡፡ ነህምያ የሚፈልገው ግብ ላይ

ደርሷል፣ የኢየሩሳሌም ቅጥር በ52 ቀናት ተሠራ፣ ስለዚህም የተዋጣለት መሪ ነበር ለማለት አንድም ቅር የሚያሰኝን ጉዳይ አይኖርም።

1/ ቀጥሎ ያሉት ዐረፍተ ነገሮች የአንድን መሪ ባሕርይ ወይም ኃላፊነት ያመለክታሉ። በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስፈር አብረው የሚሄዱትን አመልክት።

| **የመሪዎች ባሕርያት** | **የመሪነት ሥራዎች** |
|---|---|
| 1/ ለሌሎች ማሰብ | 4/ እቅድ ማውጣት |
| 2/ ብቃት | 5/ ማደራጀት |
| 3/ ጥሪ | 6/ ሌሎችን ማነሳሳት |

---ሀ/ ነህምያ ኝንዳናፍርና እንዳንዋረድ ኑ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች እንሥራ“ አለ።

----ለ/ የፈረሱትን ቅጥሮች በጥንቃቄ ከተመለከተ በኋላ ለቅጥሩ መሥሪያ የሚያገለግለውን ቁሳቁስ ሁሉ አቀረበ።

----ሐ/ የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ መሆኑን ተናገረ።

---መ/ ሀብታምም ቢሆን የድሆች ጉዳይ ግድ ይለው ነበር።

----ሠ/ ለንጉሡ ምን እንደሚናገር አሰበ።

----ረ/ ለእያንዳንዱ ወገን ራሱን የቻለ ሥራ ሰጠ።

## መሪዎች ለችግሮች መፍትሔ ይሻሉ

### ዓላማ 2 ችግርን የመፍታት ሂደት ምን እንደሚያካትት ለመግለጽ

ከነህምያ ሕይወት ታሪክ በአጭሩ የመሪነት ባሕርያትና አሠራር እንዳሉት አይተሃል። የነህምያን አመራር ጠንካራ ጎን በእግዚአብሔር በመታመን ችግሮችን የመፍታትና ውሳኔን የማሳለፍ ችሎታ ማሳየቱ ነው።

ስለ መሪነት ጥናት ያደረጉ ምሁራን አንዳንድ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ንድፎችን አቅርበዋል። ከእነዚህም ሦስቱና ዋና ዋናዎቹ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

**የመጀመሪያ ደረጃ:-** ችግሩን መረዳትና አንድ ነገር ለማድረግ መወሰን

1. አጠቃላይ ሁኔታዎችን እንደሚገባ መመርመር

2. ችግሮቹን በዝርዝር መመርመር

3. መወሰን የሚገባውን መወሰን

**ሁለተኛ ደረጃ፡-** መፍትሔዎችን መምረጥና እርምጃ መውሰድ

2. መውሰድ ያለብህን አማራጭ መምረጥና እንዴት ሥራ ላይ እንደምታውለው ቅደም ተከተሉን መዘርዝር

3. አንድ ነገር ማድረግና የድርጊቱን ቅደም ተከተል መቆጣጠር

**ሦስተኛው ደረጃ፡-** ውጤቱን መገምገም፣ ውጤቱ አጥጋቢ ካልሆነ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ

1. ትክክለኛውን ችግር አግኝቻለሁ? 3. ትክክለኛውን እርምጃ ወስጃለሁ?

2. ትክክለኛውን መፍትሔ መርጫለሁ?

እነዚህን ሦስት የችግር መፍቻ እርምጃዎች ከነህምያ የመሪነት ልምምድ መመልከት ይቻላል፡፡ ችግር ስንል የታቀደውን ግብ እንዳንመታ፣ የታሰበውን ውጤት እንዳናገኝ እንዲከፋንና እንድናዝን የሚያደርገን ማንኛውንም ነገር ማለታችን ነው፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ሲገጥመን ዓላማችን ይጨናገፋል፡፡ ችግሩ ግልጽ በሆነለት ጊዜ ነህምያ አዘነ፡፡ ችግሩ ከሞት የተረፉት አይሁዳውያን በከፍተኛ ሃዘንና ውርደት ላይ መሆናቸው ነበር፡፡ ነህምያ ለመልእክተኞቹ ጥያቄ ማቅረቡን አስተውል፡፡ ከንጉሡ እርዳታ ከመጠየቁ በፊት ሁኔታውን በጥንቃቄ ማጥናት ነበረበት፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ እርሱ ራሱ ችግሩን በግል አጠና፡፡ ይህ ችግርን የመፍቻ የመጀመሪያውን እርምጃ ያመለክታል፡፡ ሁኔታውን በትክክል ለማወቅ፣ ችግሩ ምንድነው? በማለት መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

ከአጠቃላይ ችግሮች መካከል አንዱን ነጥለህ መፍትሔ ፈልግለት፣፡ ከዚህ ታሪክ እንደምንመለከተው የችግሩ አጠቃላይ ገጽታ የሕዝቡ ውርደትና ጉስቁልና ነበር፡፡ ነጠላው ችግር ደግሞ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስና መቃጠል ነበር፡፡ ነህምያ በሁኔታዎቹና በችግሮቹ መካከል የነበረውን ግንኙነት ተረድቷል፡፡ የሕዝቡ ውርደትና ጉስቁልና ምክንያት የሆነው የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ሲሆን፣ ይህንንም በትክክል ገልጾታል፡፡ ይህ ሁለተኛው እርምጃ ችግሩ ምን እንደሆነ ከታወቀ በትክክል መግለጽ ነው፡፡

ነህምያ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ወሰነ፡፡ ከዚያ በኋላ እርምጃ በመውሰድ፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን አረጋገጠ፡፡ የመጀመሪያው ችግር ብቻ ሳይሆን ሌሎች ችግሮችም ሲነሡ ነህምያ በተለማመደው ችግርን የመፍቻ ስልት ይጠቀም ነበር፡፡

2-3 በሚከተሉት ምሳሌዎች አጠቃላይ ሁኔታዎች ተሰጥተዋል፡፡ ችግሮቹን በተናጠል ከተመለከትክ በኋላ ለችግሩ ተገቢ መፍትሔ ሊሆን የሚችለውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡

2/ ከነህምያ 4 ላይ እንደምንመለከተው አጠቃላዩ ሁኔታ የአይሁዳውያን መሰደብና መጠቃታቸው ነበር፡፡

ሀ/ ዋናው ችግር ሳምራውያንና አሞራውያን በአንድነት እየዶለቱባቸው ነበር፡፡

ለ/ የቅጥሩን ሥራ ተደናቀፈ

ሐ/ አይሁዳውያን በብርቱ አጉረመረሙ

ነህምያ የተጠቀመበት መፍትሔ፡-

መ/ የጠላትን ሠራዊት ማጥቃት

ሠ/ ራሳቸውን የሚከላከሉበት መሣሪያ ለሠራተኞቹ መስጠት

ረ/ ለሚያጉረመርሙ አይሁዳውያን መስበክ

3- ከነህምያ 5 ላይ እንደምንመለከተው አጠቃላዩ ሁኔታ ሕዝቡ በአይሁዳውያን ወንድሞቻቸው ላይ ማጉረምረማቸውና ክስ ማቅረባቸው ነበር፡፡ ዋናው ችግር፡-

ሀ/ ድሆቹ ገንዘብ መበደር ነበረባቸው ሐ/ አለአግባብ መጠቀም በዝቶ ነበር

ለ/ ወንዶችና ሴቶች ልጆች በባርነት ተሸጠዋል

ነህምያ የተጠቀመበት መፍትሔ፡-

መ/ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲጠብቁ ነገራቸው

ሠ/ ሕዝቡ እርስ በርስ እንዲዋደዱ ተናገረ

ረ/ ድሆችን የሚረዳ የበጎ አድራጎት ድርጅት አቋቋመ

ትክክለኛውን መፍትሔ መስጠት እንዲያስችለን ከአጠቃላይ ሁኔታው ችግሮችን በተናጠል መለየት እንደሚገባን ከእነዚህ ምሳሌዎች ለመረዳት እንችላለን፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚከሰተው ችግር መፈታት ያለበት በአንድ ሰው ሳይሆን በቡድን ነው፡፡ በዘመናችን የመሪነት አሰራርም ይኸው ነው፡፡ እስቲ ሰዎች በቡድን ሆነው የሚከሰቱ ችግሮችን በቀላሉ ለመፍታት ይችላሉ?

5/ ሦስቱን የችግሮች ማቃለያ እርምጃዎችና የሚያካትቱዋቸውን ነጥቦች ጻፍ?------------
---------------------------

## መሪዎች ውሳኔ ያሳልፋሉ

### ዓላማ 3 ውሳኔ ማሳለፍ ማለት ምን እንደሆነ ትክክለኛ መግለጫ ለመስጠት

ውሳኔ ማሳለፍ ችግርን ከማቃለል ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው፡፡ በአእምሯችን አውጥተን አውርደን በቅደም ተከተል የምንወስዳቸው እርምጃዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ዋናው ልዩነት ሥራው እየቀጠለ እንዲሄድ በብዙ ዕለታዊ ሁኔታዎች ላይ ውሳኔዎች ማሳለፍ ማስፈለጉ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ሁኔታ መደረግ ያለበት ወይም መወሰድ የሚገባው እርምጃ ካሉት አማራጮች መካከል ተመርጦ ሊወሰድ ይገባል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ምን መደረግ እንዳለበት ወይም ምን መደረግ እንደሌለበት መሪው በግሉ የሚወስንበት ጊዜ ይኖራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከበላዮቹ ጋር ሆኖ ውሳኔ በማሳለፉ ተግባር ይሳተፋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን ውሳኔ በማሳለፉ ውጣ ውረድ ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ይፈልጋል፡፡

### ነህምያ ውሳኔ አደረገ

ነህምያ ምን ያህል ውሳኔዎች አደረገ? ለምሳሌ ያህል ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ፈቃድ እንዲሰጠው ንጉሡን ለመጠየቅ ወሰነ፡፡ በዚያ ዘመን የነገሥታትን ፈቃድ መቃወም ስለማይቻል፣ ይህን ማድረግ ችግር የሚያስከትል ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ሞትን እንኳ ሊያስከትልበት ይችል ነበር፡፡ ከንጉሡ የጠየቀው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንዲፈቀድለት ብቻ ሳይሆን የይለፍ ደብዳቤና ለሥራው የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ጭምር ጠየቀ፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ቅጥሩን እንደሚገባ ተዘዋውሮ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን ለሚመለከተው አቀረበ፡፡ በልቡ የነበረውን ሸክም ለሌሎች ማካፈል እንዳለበት ወሰነ፡፡ ፊት ለፊት ጦርነት ይግጠማቸው ወይስ ራሱንና ሥራውን ይከላከል? ድሆችን ይበዘብዙ የነበሩት ሃብታሞችን በመገሰጹ የራሱን ደረጃ እንኳ ለማጣት የወሰነ ሰው ነበር፡፡

አለአግባብ መጠቀማቸውን እንዲያቆሙና የወሰዱትንም እንዲመልሱ ውሳኔ እንዲያደርጉ ጠየቃቸው፡፡ ከሁሉም ሁኔታዎች እንደምንመለከተው ነህምያ መረጃ ያሰባስብ ነበር፡፡ ይህም ሁኔታውን ወይም ችግሩን በግልጽ እንዲረዳ አደረገው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ውሳኔ ለማድረግ ድፍረትና ብልሃት አገኘ፡፡ ለመንፈሳዊ መሪዎች ጥሩ

ምሳሌ የሚሆነው በቂ መረጃዎች ማሰባሰቡ፣ የሚመጣውን ችግር ለመቀበል መዘጋጀቱ፣ ሁኔታውን አብረውት ለሚሠሩ ሁሉ ግልጽ ማድረጉ፣ እርሱ ራሱ ውሳኔ ከማድረጉም በላይ ሌሎችም የራሳቸውን ውሳኔ እንዲያደርጉ ዕድል መስጠቱ ነው፡፡

ውሣኔ ለማድረግ የሚረዱ እርምጃዎች

1. በጌታ ሙሉ እምነት ይኑርህ፡፡

ውሳኔ በማድረግ ሂደት ውስጥ እምነት የራሱ ሥፍራ አለው፡፡ መጽሐፈ ነህምያን ስናነብ የነህምያ እምነት በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ ላይ እንዳልነበረ እናያለን፡፡ ይሁን እንጂ በመለኮታዊ ኃይል እግዚአብሔር ቅጥሩን እንዲሠራ አልጠየቀም፡፡ የኢያሪኮን ቅጥር ያለማንም እርዳታ እንዳፈረሰ ሁሉ እግዚአብሔር ያንንም ቅጥር በቀላሉ መሥራት ይችል ነበር፣ ይሁን እንጂ ከነህምያና አብረውት ከነበሩ ሰዎች ጋር መሥራትን ነው እግዚአብሔር የመረጠው፡፡ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎች "ተፈጥሮአዊ" ብለው በሚጠሩት አማካይነት ይሠራል፡፡ ነህምያን የመሳሰሉ ሰዎች ግን ተፈጥሮአዊ ነገሮችን የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፈቃድ ለመፈጸም ይጠቀሙባቸዋል፡፡

2. **መረጃዎችን አሰባስብ**

ሁኔታዎችን በሚገባ ከተረዳህ በኋላ በግልጽ ዘርዝራቸው፡፡ መልካም ውሳኔዎች በሐቅ እና በእውቀት ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ከሌሎች ያገኘሽው መረጃ ትክክል መሆኑን አረጋግጥ፡፡ ሁኔታዎችን አንተው ራስህ መርምር ወይም ደግሞ ሌላው መርምሮ ሪፖርት ያድርግልህ፡፡ ፈጥነህ ማጠቃለያ ላይ አትድረስ፣ ወይም ስሜታዊ ሰዎች አንድ ውሳኔ ላይ እንድትደርስ አይገፋፉህ፡፡

3. **አማራጭ መንገዶችን ዘርዝር**

በአንዳንድ ሁኔታዎች ምንም ላለማድረግ ትወስናለህ፡ ወይም ሁኔታዎቹ ይለወጡ እንደሆነ ለማጣራት እስክትችል ድረስ ውሳኔውን ታዘገያለህ፡፡ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ችግሩ ብዙ መፍትሔዎች ይኖሩታል፡፡ ስለዚህም እውነተኛ መሪዎች **"ምንም ምርጫ የለኝም"** አይሉም፡፡

4. **ጠቃሚና ጎጂ ጎኖችን አስብ**

ስለሚጠይቀው ኃላፊነት ስለሚያስከትለው ውጤትና ሊገጥሙህ ስለሚችሉ እንቅፋቶች ዘርዝር፣ ለተለያዩ አማራጮች ስለሚያስፈልገው ወጪ ወይም ጥረት አስብ፡፡

ከሁኔታዎች ጋር ራስህን ለማስተካከል ፈቃደኛ ሁን፡፡ ለምሳሌ ያህል አንዱ ስለ ሥራው በቂ እውቀት ይኖረው ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ዘግይቶ ይመጣ ይሆናል፤፡ ባለው እውቀት ለመጠቀም እንዲቻልህ መዘግየቱን በቸልታ እለፈው፡፡

5. **በውሳኔህ ተሳትፎ ስለሚያደርጉ ሰዎች አስብ**

   ውሳኔህ በሌሎች ላይ ምን ተጽዕኖ እንደሚያሳድር አስቀድመህ ለመረዳት ሞክር፡፡ እርምጃ ከመውሰድህ በፊት የማን ወይም የእነማን ሀሳብና ምክር መከተልና መቀበል እንደሚያስፈልግህ እወቅ፡፡

6. **ችሎታ ካላቸው ሰዎች ሃሳብ ተቀበል**

በዚህ ጉዳይ ላይ የእናንተን እርዳታ እሻለሁ ብለህ ለመናገር አታመንታ፡፡ የእነርሱን የሃሳብ እርዳታ በመሻትህ እፍረት ሊሰማህ አይገባም፡፡ ስለምታሳልፋቸው ውሳኔዎች የሌሎችን በማሳተፍ አስተያየት ማግኘት ብርታት እንጂ ድክመት አይደለም፡፡

7. **ውሳኔዎችህን መርምር**

ወደኋላ ሄደህ ነገሮችን ገምግም፣ እንዲህም ሲባል በቅንነት ነገሮችን መመርመር ማለታችን እንጂ አንድትጸጸትና ውሳኔ ላለማድረግ እንድትሻ አይደለም፡፡ ካለፉት ስህተቶችህ ለመማር ሁልጊዜ ዝግጁ ሁን፡፡

**የሚገጥሙ መሰናክሎች**

1. **ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች አለመኖር**

   መሥራት ያለብንን አጥርተን ካላወቅን በቀር እርምጃ ለመውሰድ ወይም ውሣኔ ለማድረግ ያዳግታል፡፡ መወሰን ያለበት ምን እንደሆነ በሚገባ ለማወቅ መሰራት ያለበትን አስቀድሞ ማወቅ ይረዳል፡፡ ከዚያም መወሰን ያለበት ምን እንደሆነ በግልጽ ይታወቃል፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለማድረግ እርግጠኛ ሳትሆን ስትቀር የሥራው ዓላማ ምን እንደሆነ ራስህን ጠይቅ፡፡ ግልጽ የሆኑና ጥርት ያሉ ዓላማዎች መኖር ብዙ ችግሮችን ያቃልላል፡፡

2. **አለመረጋጋት**

   ውሳኔ ለማድረግ መሰናክል የሚሆን ሌላው ነገር አለመረጋጋት ነው፡፡ መሪው እርምጃ መውሰድ ይፈራ ይሆናል፡፡ ይህም የራስ ሰብአዊ ባሕርይ ውጤት ወይም ደግሞ ያለበትን ኃላፊነት እንደሚገባ ባለመረዳቱና ከሌሎች መሪዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ባለማወቁ የሚመጣ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡ አስቀድመን

እንደተመለከትነው በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ አብዛኛዎቹ መሪዎች ያላቸው ሥፍራ የመካከለኛ መሪነት ሥፍራ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የወጣቶችና የእሁድ ትምህርት ቤት መሪዎች ኃላፊነታቸውንና ከመጋቢው ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንደሚገባ መረዳት አለባቸው፡፡ ውሳኔያቸውን እንደሚደግፍ እርግጠኛ መሆን አለባቸው፡፡ እርግጠኛ ካልሆኑ ግን ምንም ውሳኔ አያደርጉም፡፡ ከመጋቢው የሚፈልጉትን እርዳታ ለመጠየቅ ደግሞ ይፈራሉ፡፡

3. **ለውጥን መፍራት**

ብዙውን ጊዜ በለመድነው ሁኔታ መኖርን እንፈልጋለን፡፡ በመጠኑ ቢሆንም ማንም ለውጥን ይቃወማል፡፡ ወዲያው መቀበል አይፈልግም፡፡ የሰዎችን ምላሽ ስለሚፈራ መሪው ውሳኔ ለማድረግ ያመነታል፡፡ እውነተኛ መሪ ግን የለውጥን አስፈላጊነት ይቀበላል፡፡ ሌሎችም አስፈላጊነቱን እንዲቀበሉ ለማድረግ ይሞክራል፡፡

4. **በቅንነት ሐቅን ለመቀበል አለመፈለግ**

ብዙውን ጊዜ በመንፈሳዊ ሥራ ውስጥ እንደሚታየው እምነት ማጣት መስሎ ስለሚታዩት ነገሮች መገምገምን እንፈራለን፡፡ መሪዎች ሰዎች ምን እንደሚሰማቸው ለማወቅ ጥያቄ ማቅረብ ስለሚፈሩ በቂ መረጃ ሳይኖራቸው ውሳኔ ያሳልፋሉ፡፡ የሰዎችን ችግር እንደሚገባ ካልተረዳንና ሁኔታዎችንም እንደሚገባ ካላገናዘብን ትክክለኛ ውሳኔ ማድረግ አንችልም፡፡

**ውሳኔ የማድረግ ዘዴዎች**

ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ መሪዎች ውሳኔ በማድረግ ረገድ ቡድኑን ይመራሉ፡፡ ቡድኑ የሚሳተፍበት ጊዜ እንደ ሁኔታዎቹ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ ያህል ቡድኑ በቂ ልምምድ ከሌለው ውሣኔ በማሳለፉ ጉዳይ የበለጠ ኃላፊነት የሚኖረው መሪው ነው፡፡ አባሎቹ ብቁና ልምምድ ያላቸው ከሆኑ ግን የበለጠ ኃላፊነት እንዲኖራቸው ሊበረታቱ ይገባል፡፡ ውሣኔ የማድረጉ ዘዴ እንደ ሁኔታው ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች መሪው ሙሉ በሙሉ ሥልጣን ስለሚኖረው እርሱ ብቻ ሁሉንም ውሳኔዎች ያደርጋል፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ አብረውት የሚሠሩት የተሟላ ሥልጣን ስለሚኖራቸው በየግላቸው ውሣኔ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህን ውሣኔ የማድረግ ዘዴዎች በሚከተለው መንገድ ልንዘረዝራቸው እንችላለን፡፡

1/ መሪው ስላደረገው ውሣኔ ለቡድኑ ይነግራቸዋል፡፡

2/ መሪው ውሣኔ ያሳልፍና ቡድኑ ምንም ዓይነት ምርጫ ሳይኖራቸው እንዲቀበሉት ጫና ያደርጋል።

3/ መሪው ውሣኔ ያሳልፍና ቡድኑ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ያደርጋል። እንዲወያዩበትም ይጋብዛል፣ ያም ሆኖ ግን ቡድኑ ምንም መለወጥ የሚችሉት ጉዳይ አይኖርም።

4/ መሪው ለሙከራ ያህል ውሣኔ ቡድኑ ያሳልፍና እንዲወያይበት ያደርጋል። በሚሰጡት ሀሳብ አማካይነትም መጠነኛ ለውጥ ያደርጋል።

5/ በመጀመሪያ መሪው ችግሩን ለቡድኑ ከዘረዘረ በኋላ አማራጭ መፍትሔዎችን እንዲያቀርቡ ይጠይቃቸዋል። ከዚያ በኋላም እርሱ ራሱ ይወስናል።

6/ በመጀመሪያ መሪው አንድ ዓይነት ገደብ ወይም መመሪያ ያደርግና ቡድኑ ውሣኔ እንዲያደርጉ ይጋብዛቸዋል።

7/ መሪው ቡድኑ ሁኔታዎቹን እንዲያጠኑና፣ ችግሩን እንዲረዱ ያደርግና ከውይይቱ በሚገኘው ፍሬ በመመሥረት በተነጋገርነው መሰረት ውሳኔ ያሳልፋል፣ በዚህ ስልት መሪው ቡድኑን የሚመራው የቤተክርስቲያንን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው። ይኸኛው ትክክለኛ ውሣኔ የማሳለፍ ሂደት ነው።

6/ ከነህምያ የመሪነት ምሳሌ የምንመለከተው

ሀ/ እውነተኛ ክርስቲያኖች ውሳኔ በማሳለፉ ሂደት መሳተፍ የለባቸውም

ለ/ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ሲከዱን በእግዚአብሔር እንታመናለን

ሐ/ ውሣኔ ማድረግ ያለብን በተፈጥሮአዊ ነገሮች ብቻ ነው

መ/ ውሣኔ በማድረግ ሂደት ጌታ ሰዎችን ይመራል

7/ ይበልጥ ውጤታማ የሆነው ውሣኔ የማሳለፍ ስልት፣

ሀ/ የሚወሰነው እንደ ልዩ ሁኔታው ነው

ለ/ በመሪው ወይም አብረውት በሚሠሩት ብቻ የሚወሰን አይደለም

ሐ/ መሪው ጠንካራ ከሆነ ብቻውን ይወስናል

መ/ ብዙ ሰዎችን የሚያሳትፍ ዲሞክራሲያዊ ዓይነት አሰራር ነው

8/ ትክክለኛ የሆነውን መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ/ ትክክለኛ መሪዎች ፈጥነው ውሳኔ ያደርጋሉ።

ለ/ አብዛኛዎቹን ችግሮች ለመፍታት አንድ ትክከለኛ መንገድ ብቻ አለ።

ሐ/ ውሣኔ ከማድረጋችን በፊት ኃላፊነትን፣ ወጪውን፣ መመዘንና ማመዛዘን እምነት ማጣት አይደለም፡፡

**ልናስብባቸውና ራሳችንን ልንመረምርባቸው የሚገቡን ጥያቄዎች**

ስለውሣኔ አሰጣጥ ዘዴዎች የተሰጠውን ዝርዝር እንደገና ተመልክት፣ የእያንዳንዱን ስልት ተገቢ ሥፍራም ለመረዳት ሞክር፡፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከሌሎች ይልቅ ለግልህ የተሻለ ነው የምትለው ስልት አለን?

## የቡድን ኃይል

**ዓላማ 4 ተባብሮ ስለ መሥራት ሁለት ገጽታዎችን የቡድን ኃይል ምንነትን ለመግለጽ**

አብዛኛዎቹ ውሳኔዎች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከቡድን ጋር የተያያዙ እንደመሆናቸው መጠን መሪው ስለቡድንና የቡድን ኃይል ምንነት መረዳቱ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የመጀመሪያው መሠረታዊ እውነት ሰዎች ማሕበረሰባዊ ፍጡራን በመሆናቸው፣ አንዳቸው ለሌላው አስፈላጊ ናቸው፡፡ አብረው በመሥራትም የተሻለ ውጤት ያስገኛሉ፡፡ ሁለተኛው መሠረታዊ እውነት ደግሞ ቡድን ስንል እንዲሁ የሰዎች ስብስብ ብቻ ማለት አለመሆኑን ቡድን ማለት ለጋራ ዓላማ በጋራ ለመሥራት የተሰባሰቡ፣ አንዳቸው ለሌላው የሚያስፈልጉ የሥራ ባልደረቦች ማለት ነው፡፡ የቡድን ውሣኔ ሲባል ሁሉም የሚቀበሉት እንጂ የአንድ ሰው ውሣኔ ማለት አይደለም፡፡ የቡድኑ አባሎች በሚገባ የሚወያዩበትና በመጨረሻም ውሳኔ የሚያሳልፉበት ጉዳይ ማለት ነው፡፡

ስለ ቡድን አሠራር በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አንዱ አባሎቹ በግለሰብነታቸው የተለያዩ ሰዎች ቢሆኑም ይጠቅመናል ለሚሉት ዓላማ በጋራ ለመሥራት አንድ ዓይነት ፍላጎት ያላቸው ሰዎች መሆናቸው ነው፡፡ እምነትና የዓላማ አንድነት የማንኛውም መንፈሳዊ ሥራ መሠረት እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች ይልቅ በክርስቲያኖች መካከል ጎልቶ ሊታይ ይገባል፡፡ ሰዎች በአንድነት ሲሠሩ ኃይል ይኖራቸዋል፡፡ አንዱ የሌላው አካል እንደሆነ ያስባል፡፡ እንደ አንድ አካል ሆነው ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ሰዎች በቡድን ሆነው ሲሠሩ የሚኖራቸው ብርታትና እርካታ ብቻቸውን በመሥራት ከሚኖራቸው በጣም ይለያል፡፡

የቡድን ሥራ ጥቅም አባሎቹ የሚያገኙት እርካታ ብቻ ሳይሆን ሥራው ጥራት እንዲኖረው በማገዙም ጭምር ነው፡፡ አንዳንድ የቡድኑ አባሎች ከሌሎች የተሻለ እውቀትና ችሎታ ሊኖራቸው ስለሚችል እውነተኛ መሪ እያንዳንዱ ሰው የግሉን

አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ያበረታታል፡፡ ቡድኑ ላደረገው የተለያየ አስተዋጽኦ እንጂ ለግለሰቦች የተለየ ግምት ወይም ምሥጋና መስጠት የለበትም፡፡

ምናልባትም ምንም ችሎታ የለውም ወይም ደግሞ በጣም ትንሽ እውቀት አለው ብለን የምንገምተው ሰው እምነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ችግር በሚኖርበት ጊዜ ሌሎችን የማበረታታትና አይዟችሁ የማለት ስጦታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ብዙ ሰዎች ተጋግዘው አንድ ድልድይ መሥራት ይችላሉ፡፡ ምናልባት ድልድዩ ባለሞያ የሰራውን ያህል ላያምር ይችል ይሆናል፣ ሆኖም አገልግሎት ይኖረዋል፡፡

በአንጻሩ ስንመለከተው ደግሞ አንድ ከፍተኛ ሞያ ያለው መሐንዲስ ብቻውን ድልድይ መሥራት አይችልም፡፡ ምናልባትም ብቻውን ለመሥራት የሚያስበው ድልድዩ ሞያ የሌላቸው ሰዎች ከሚሰሩት ይልቅ የማያምር ሊሆን ይችላል፡፡ መሐንዲሱና ወዛደሮቹ እንደ አንድ ቡድን ሆነው በአንድነት ጠንካራ ድልድይ መሥራት ይችላሉ፡፡

**የቡድን ልዩ ልዩ ገጽታዎች**

ስለ ቡድን ግብረ ኃይል ስንናገር ልንገነዘባቸው የሚገቡ ሁለት ሃሳቦች ሠራተኞቹንና ሊሠራ የታቀደውን ሥራ ነው፡፡ እነዚህም የተለያዩ የቡድን ገጽታዎች ይባላሉ፡፡ አንደኛው ማሕበረሰባዊ ገጽታ ሲሆን ይህም እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ከሌሎች ጋር ያለውን ተቃርቦ፣ አንዱ ለሌላው የሚኖረው ስሜት፡ በቡድኑ ውስጥ ያላቸውን ሥፍራ ማወቃቸውን ማለታችን ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሥራውን ለማከናወን አባሎች ስለሚያደርጉት የተለያየ አስተዋጽኦ የሚመለከት ሥራ-ነክ ገጽታው የመሪው ኃላፊነት ነው፡፡

## ማሕበረሰባዊ ገጽታ

1. **አባሎቹን አበረታታ፡-** እርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ አግዛቸው፡፡ እውቅናን የምትሰጠው ለሁሉም አባሎች ይሁን፡፡
2. **እንደ ቡድን አባል አስብ፡-** አብሮ የመሥራት ስሜትን አሳይ፡፡ ግለሰቦች ያላቸውን ጥላቻና መናናቅ እንዲያስወግዱ እርዳቸው፡፡ አንዱን ከሌላው አታበላልጥ፡፡ በፍጹም አድልዎ አታድርግ፡፡ ራስህን እንደ ቡድኑ አባል አድርገህ ተመልከት፡፡

3. **ልዩነቶችን አስማማ፣ አስተባብር፡-** ያለምንም ግጭት የተለያዩ አስተሳሰቦችን እንዲቀበሉ እርዳቸው፡፡ ከዚህ ይልቅ ግን በሚስማሙበትና በጋራ በሚያምኑበት ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር አድርግ፡፡

4. **የመልእክት መቀበያና ማስተላለፊያ መንገዶችን ክፍት አድርግ፡-** ይህ እያንዳንዱ ሰው ሃሳቡን ለመግለጽ ነፃነትና ተቀባይነት እንዲሰማው ስለሚያደርግ በጣም ይረዳል፡፡

5. **መለኪያ ወይም መመዘኛ ይኑርህ፡-** አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አንዳንድ ሕጎችን አውጣ፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ነገር ተጀምሮ የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ገደብ አስቀምጥ፡፡ እርስ በርስ እንዲናናቁ አትፍቀድ፡፡ ውይይታችሁ ሀሳቦች ላይ እንጂ ግለሰቦች ላይ አይሁን፡፡ በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ጊዜ አታባክን፡፡ በሁሉም አቅጣጫ ክርስቲያናዊ መንፈስ እንዲሰፍን አድርግ፡፡

## ሥራ ነክ ገጽታ

1. **የሚሠሩ ሥራዎችንና ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ዓላማዎች አስቀምጥ፡-** ለችግሮች መፍትሔ በመሻት ረገድ ቡድኑን እርዳ፡፡ ሃሳቦችንና የአሠራር ቅደም ተከተሎችን አቅርብላቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው ተገቢውን ሥራ ስጥ፡፡ ሥራው የሚጠናቀቅበትን ጊዜ ወስን፣ በየጊዜውም ስለ ሥራው ሪፖርት ተቀበል፡፡
2. **በየጊዜው ተገቢውን መረጃ ስጣቸው፣ ተገቢውን እገዛም አድርግላቸው፡-** ራስህ ማቅረብ ያልቻልከውን መረጃ ቡድኑ ማግኘት የሚችልበትን መንገድ ምራው፡፡
3. **ተገቢውን ገለጻ አድርግላቸው፡-** ግራ የሚያጋቡ ነገሮችን ግለጽ፣ ምሳሌ ስጥ፣ ሃሳቦችን በተግባር ተርጉም፡፡
4. **ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያላቸውን ሃሳቦች በአጭሩ አስቀምጥ፡-** አብረው የሚሠሩት እንዴት ሊቀራረቡ እንደሚችሉ ለመርዳት ሃሳቦችን በግልጽ አቅርብ፡፡ የተስማሙበትን ነጥብ እንዲረዱና ግልጽ ውሳኔ እንዲያሳልፉ እርዳቸው፡፡
5. **አመስግናቸው፣ አበረታታቸው፡-** አንድ ዓይነት መሻሻል ሲያሳዩና ሥራው እንደሚገባ ሲጠናቀቅ በዝምታ አትለፍ፡፡ ሆኖም ዋናው ትኩረትህ በሥራው ላይ እንጂ በሠራተኞቹ ግላዊ ማንነት ላይ አይሁን፡፡
6. **የግምገማ ሥርዐት ይኑርህ፡-** ሠራተኞቹ ተስፋ ሳይቆርጡ በተገኘው ውጤትም ሳይኩራሩ ሐቅን በተመረኮዘ ሁኔታ ሥራውን የሚመዝኑበት ሚዛን እንዲኖራቸው አበረታታቸው፡፡ አስተዋጽኦዋቸውን እንዲያውቁ በዚያው ልክ

ደግሞ ክብሩን ለጌታ እንዲሰጡ አስተምራቸው። አዲስና የተሻለ እውቀት እንዲገበዩ እርዳቸው።

9/ ከሚከተሉት ውስጥ ማሕበረ-ሰባዊ ገጽታዎች ለሆኑ ቁጥር 1፣ሥራ-ነክ ገጽታዎች ለሆኑ ደግሞ ቁጥር 2 በመጻፍ አመልክት፡-

1/ ማሕበረ-ሰባዊ ገጽታ 2/ ሥራ-ነክ ገጽታ

------ሀ/ ከስብሰባው በፊት መሪው ወንበሮችን በክብ አስቀመጠ።

------ለ/ ከቡድኑ አባሎች ሁለት ሰዎች ለሰንበት ትምህርት ቤቱ አስፈላጊ ነገሮችን እንዲፈልጉ ተመረጡ።

----ሐ/ ለሚደረገው የወንጌል ሥርጭት መድረክ መሥራት የሚችሉበትን መንገድ መሪው ለሠራተኞቹ አስረዳ፣

-----መ/ በሚደረገው ስብሰባ መዘምራንን እንዲመራ መሪው አዲስ አባል የሆነውን ጠየቀ።

----ሠ/ እያንዳንዱ ሰው ስለጉዳዩ ያለውን ሃሳብ በሁለት ደቂቃ እንዲገልጽ መሪው ተናገረ።

--------ረ/ ለሚቀጥለው ዓመት ያላቸውን እቅድ መሪው በየሳምንቱ እንዲያጠናቅቁ ተናገረ።

**በቡድኑ እንዴት ውሳኔ እንደሚደረግ**

**ዓላማ 5 የውሳኔ አሰጣጥ ስልቶችን እንዴት መገምገም እንደሚቻል ለመግለጽ**

**በድምጸ-ብዙኀን የሚደረግ ውሳኔ**

በብዙ ማሕበሮች ዘንድ በጣም የተለመደው የውሣኔ አሰጣጥ ስልት በምርጫና በድምጽ ብልጫ ነው። ይህም የምክር ቤት ወይም የፓርላሜንት አሠራር መንገድ የሚከተል ስለሆነ መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖርህ ይረዳሃል።

ስብሰባው በምክር ቤት ወይም በፓርላሜንት አሠራር ደንብ የሚካሄድ ከሆነ መሪው ሊቀመንበር ይባላል። የመሪው ዋና ሥራ ሰዎች ተራ በተራ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ በማድረግ፣ ከዚያም ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ውሳኔ እንዲያሳልፉ ስብሰባውን

መምራት ነው፡፡ በአንድ ጊዜ የሚስተናገደው አንድ ዓይነት ሃሳብ ነው፣፡ የሚፈልግ ሁሉ ሃሳቡን በነጻነት ያቀርባል፣፡ በብዙሃኑ ምርጫ መሠረትም ውሳኔ ይደረጋል፡፡

ስብሳባውን የሚመራው ሊቀመንበር የራሱን ሃሳብ መስጠት ወይም ምርጫው ላይ ጫና ለማድረግ መሞከር የለበትም፡፡ ለውይይት የሚሆን ርዕሰ ጉዳይ ማቅረብ ይችላል፡፡ ምናልባትም የቡድኑ አባላት የወጣቶች ሽርሽር ፕሮግራም ለማዘጋጀት እቅድ ይኖራቸው ይሆናል፡፡ መሪው ደግሞ በአንዳንድ ዝርዝር ጉዳዩች ላይ ውሳኔ እንዲያደርጉ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ አንድ ሰው እጁን በማውጣት ወይም ተነስቶ በመቆም ለመናገር እንደሚፈልግ ይናገራል፡፡ መሪው ደግሞ እንዲናገር ይፈቅድለታል፡፡ የሽርሽር ፕሮግራሙ ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንዲሆን ሃሳብ አቀርባለሁ ሲል ተናገረ፡፡ ይህም ሲሆን ባቀረበው ሃሳብ ላይ እንዲወያዩበትና ምርጫ እንዲያደርጉ ሃሳብ ቀርቧል ማለት ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ በተለመደው የምክር ቤት ወይም የፓርላሜንት አሠራር በአንድ ጉዳይ ላይ አባሎቹ እንዲወያዩበት ከመፍቀዱ በፊት ሁለት ሰዎች እንዲስማሙበት ይስፈልጋል፡፡ ይህ ድጋሚ ይባላል፡፡ ሌላው የቡድኑ አባል "እኔም ይህን ሃሳብ በድጋሚ አቀርባለሁ" ማለት አለበት፡፡ ከዚያ በኋላ መሪው "**ይህ አቶ--- የሽርሽር ፕሮግራሙ ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንዲሆን ያቀረበው ሃሳብ ሁለት ድምፅ አግኝቷል፡፡ ጥያቄ ወይም እንድንወያይበት የሚያስፈልግ ነገር አላችሁ?**" ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ አባሎች ተራ በተራ እየተነሱ ሃሳባቸውን መግለጽ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ የሽርሽር ፕሮግራሙ ትምህርት ቤት ሳይዘጋ በፊት እንዲደረግ ይፈልጉ ይሆናል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የሽርሽር ፕሮግራም ከማዘጋጀት ይልቅ የስፖርት ውድድር እንዲዘጋጅ ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ሁሉም ሃሳባቸውን ከገለጹ በኂላ መሪው "**ምርጫ ለማድረግ ተዘጋጅታችኂል?**" በማለት ጥያቂ ያቀርባል፡፡

ምንም ዓይነት ተቃውሞ እንደሌለ ካረጋገጠ በኋላ መሪው "**የሽርሽር ፕሮግራሙ ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንዲሆን የምትፈልጉ እጃችሁን አውጡ**" ይላል፡፡ (ተነስቶ በመቆም፣ በድምጽ ወይም በወረቀት ላይ በመጻፍ ሃሳብን መስጠት ይቻላል) ማንኛውም የማይስማማ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ሀሳቡን መግለጽ ይችላል፡፡ አንድን ሃሳብ በቁጥር የሚበልጡ አባሎች ከደገፉት ወይም ከተስማሙበት ያልፋል፡፡

ብዙሃኑ በተስማሙበት ርዕሰ ጉዳይ ውሳኔን ማሳለፍ ትክክለኛና ምክንያታዊ እንደሆነ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ ልናውቃቸው የሚገቡ ችግሮችም አሉት፡፡ አንዳንድ

ሰዎች በድምጽ ብልጫ የተላለፈውን ውሳኔ ይቃወሙ ይሆናል፡፡ ምርጫ ማድረጉን እንደ አንድ ዓይነት ፉክክር ስለሚያዩት የተሸነፉ መስሎ ይሰማቸዋል፡፡ በቅንነት ከብዙሃኑ ጋር ከመስማማት ይልቅ አባሎቹን ይከፋፍላሉ፡፡ በተዘዋዋሪ መንገድ የራሳቸው ሃሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ ይህንም ተባብሮ ከመሥራት ይልቅ ለቡድኑ መከፋፈል ምክንያት ይሆናል፡፡

10/ በድምጽ ብልጫ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከሚከተሉት መግለጫዎች ከአንዱ መግለጫ በቀር ሁሉም ጠቃሚ ግምት አላቸው፡፡ ጠቃሚ ግምት የሌለው የትኛው ነው?

ሀ/ በቀረበው ጉዳዩ ላይ እንዲወያዩና ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡

ለ/ ምርታማነት ለተከተለ ውይይት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ጉዳዮችን በቅደም ተከተል በማስተካከል፣ በአንድ ጊዜ አንድ ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲወያዩበት ያደርጋል፡፡

ሐ/ ብዙሀኑ የሚያስተላልፉት ውሳኔ ያለጥርጥር ትክክል ስለሆነ መሪውን በድፍረት እንዲንቀሳቀስ ያደርገዋል፡፡

መ/ ብዙሀኑ የተሻለ ነው ብለው በሚያምኑበት መሰረት ውሳኔ ያሳልፋል፡፡

**በጋራ ስምምነት የሚደረግ ውሳኔ**

በብዙሃኑ ምርጫ ላይ ያለው ትልቁ ድክመት ውሳኔው ሁሉንም ማስደሰት አለመቻሉ ነው፣፡ አንዳንዶች ሃሳባቸው ተቀባይነት እንዳጣ ይሰማቸዋል፡፡ መሪው ውሳኔውን በጋራ ስምምነት መሠረት ቢያሳልፍ ግን እንዲህ ዓይነቱን ችግር ማስወገድ ይቻላል፡፡ የጋራ ስምምነት ሲባል ሁሉም ይስማሙበታል ማለት አይደለም፡፡ ውሳኔው በመፎካከር መንገድ ከሚያልፍ ይልቅ በጋራ ስምምነት ቢሆን የሰዎች አስተሳሰብና ዝንባሌ የተለየ መልክ ይኖረዋል ማለታችን ነው፡፡

የጋራ ስምምነት ማለት ምንም እንኳ ከሌሎች አማራጮች ሁሉ የተሻለ ነው የሚል እምነት ባይኖረውም እያንዳንዱ አባል ሃሳቡን እንዲገልጽና ምክንያቱንም እንዲያስረዳ ዕድል መስጠት ይኖርበታል፡፡ ስብሰባው የሚጠናቀቀው አባሎቹ እንደተረዱዋቸው እርግጠኛ ሆነው ከሆነ የአባሎቹን ውሳኔ በማስፈጸም ረገድ ይተባበራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በፉክክር አውቀው አንድን ነገር በመተዋቸው እርካታ ያገኛሉ፡፡ ሃሳባቸው ተቀባይነት አንዳገኘ ስለሚያስቡ በቡድኑ ሂደት አንዳንድ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

11. ለምሳሌ ያህል በጋራ ስምምነት ውሳኔ በሚተላለፍበት ስብሰባ ላይ እየተካፈልክ ነው እንበል፡፡ ያሉት አማራጭ መንገዶች ሁሉ አንድ በአንድ እስኪመረመሩ ድረስ ውይይቱ

ቀጥሏል፡፡ በመጨረሻም ግን አንድ ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡ በአሸናፊና ተሸናፊነት መንፈስ ከሚጠናቀቅ ስብሰባ ይልቅ እንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ የተለየ መልክ የሚኖረው እንዴት ነው? መልሱን በማስታወሻ ደብተርህ ጻፍ፡፡

**በአንድ ድምጽ የሚተላለፍ ውሳኔ**

መንፈሳዊ ሥራን ከሌሎች ድርጅቶች አሠራር ይልቅ በፍጹም ልዩ የሚያደርገው ነገር አለ፡፡ ክርስቲያኖች አንድ የጋራ የሆነ ዓላማ ብቻ አላቸው፤፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ላይ ስለሚደገፉም በሌሎች ያልተለመደ ዓይነት ስምምነትና አንድነት አላቸው፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከግል ልምምዳችን ሁልጊዜ ስምምነት ወይም አንድነት ሊኖር እንደማይችል እንረዳለን፡፡ በመሰረቱ ሁሉም ዝርዝር ጉዳዩች ላይ የግድ መስማማት አለብን ማለት አይደለም፤፡ ስለሆነም በአንዳንድ ነጥቦች ላይ እያንዳንዱ የቡድን አባል የተለየ አመለካከት ቢኖርህ ራስህን መውቀስ አይኖርብህም፡፡

ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት በጣም ንቁ መሆን አለብህ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ያለው ፍላጎት ምን እንደሆነ በኤፌ 4:3:12-13 ላይ የተጻፈው ቃል ሲገልጽ፡- "**በሠላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ፡---- ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ"** ይላል፡፡

12/ በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በመጻፍ ከመግለጫው ጋር አብሮ የሚሄደውን አመልክት

1) በድምጽ ብልጫ 2) በጋራ ስምምነት 3) በሙሉ ድምጽ

----ሀ/ መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡ ምንም እንኳ የሚደረግ ውሳኔ ፍጹም ነው ለማለት ባንደፍርም ሐቅ ላይ የተመረኮዘ ስምምነት ላይ በመሆኑ ተቀብለነዋል፡፡ ይህን ስምምነት ለመደገፍ ስላሳያችሁት ፈቃደኝነት ሁላችሁንም አመሰግናለሁ፡፡

----ለ/ ሁሉም የተስማሙበት ነጥብ ላይ ደርሰናልና የሚደረግ ውሳኔ ከእንግዲህ ወዲህ-- ------------------------

---ሐ/ ምርጫውን 16 ሰዎች ሲደግፉት 8 ሰዎች ተቃውመውታል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት እንቅስቃሴ እንጀምራለን፡፡

13/ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለውን “ተጨማሪ” ከሚለው ክፍል ”አንዳንድ የፓርላሜንት አሠራር ነጥቦች” የሚለውን ካነበብህ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ፡፡

ሀ/ አምስቱን የፓራሜንት ህጎች አስፈላጊ መመሪያዎች ዘርዝር?------------------------------------------------------------------

ለ/ ስንት የውይይት አስፈላጊ ሕጎች ተሰጥተዋል?-----------------------------

ሐ/ ስንት የድምፅ አሰጣጥ ዘዴዎች ተሰጥተዋል?--------------------------------

ስንት የድምፅ አሰጣጥ ዓይነቶች ተዘርዝረዋል?---------------------------------

ብልጫ ያለው ቢስማሙበትም ባይስማሙበትም ተቀባይነት የማያገኘው ድምጽ -------------------- ይባላል፡፡

መ/ ስብሰባ በሚመራበት ጊዜ ሊቀመንበሩ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ነህ ከማለት ይልቅ ------------------------ ማለት አለበት፡፡

ሠ/ ሊቀመንበሩ ወይም የጉባኤው ሰብሳቢ ለእያንዳንዱ ስብሰባ-------------- ያዘጋጃል

ረ/ ለአንድ ሥራ እንቅስቃሴ ቅደም ተከተል የማድረጉ ጠቀሜታ ---------ነው

**የሙከራ ፈተና**

እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጥ፡፡

-----1/ ነህምያ ለኢየሩሳሌም ፍቅርና ቅጥሯንም ለመጠገን ራዕይ ነበረው፣ የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ስለነበረ በድፍረት ነበር የሚንቀሳቀሰው፣ ይህም መለኮታዊ ጥሪ እንዳለው ማስረጃ ነው፡፡

-----2/ ነህምያ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኃላ የፈረሰ ቅጥሯን እንዲመለከቱና ቅጥሯንም ለመጠገን ሃሳብ እንዲያቀርቡ ተወካዮችን ልኳል፡፡ ይህም የአመራር ብቃቱን ያመለክታል፡፡

------3/ ምንም እንኳ ሀብታም ቢሆንም ነህምያ ድሆች የነበሩበት አስከፊ ሁኔታ ግድ የሚለው ሰው መሆኑ ለሌሎች አሳቢ መሆኑን ያሳያል፡፡

---4/ ነህምያ ንጉሡን ከማነጋገሩ በፊት ማድረግ በሚፈልገው ጉዳይ አስቀድሞ አስቦበታል፣ ይህም እቅድ ይባላል፡፡

----5/ ችግሩን ካመዛዘነ፣ መደረግ ያለበትን ከመረመረና ራዕዩንም ለሌሎች ካካፈለ በኋላ ነህምያ ሥራውን ለማከናውን ባለው የሰው ኃይል ተጠቀመ፡፡

----6/ ችግሩ ምንድነው? መደረግ ያለበት ምንድነው? በማለት ነህምያ ሁኔታውን በሚገባ መረመረ። ከዚያ በኋላም ሕዝቡን ለአንድ ዓላማ የሚያነሳሳ ንግግር አደረገላቸው።

---7/ አንድን ችግር ለመፍታት የመጀመሪያው ደረጃ ችግሩን መረዳት ነው። ይህም አጠቃላይ ሁኔታውን ማጤን፣ ችግሮቹን በተናጠል ማየትና በመጨረሻም ምን መደረግ እንዳለበት መወሰንን ያጠቃልላል።

---8/ ችግሩን ከተረዳን በኃላ ወደ ሁለተኛው ደረጃ እንሸጋገራለን፣፡ይህም መፍትሔውን በመፈለግ ሲሆን አማራጭ መንገዶችን መመርመር፣ መደረግ ያለበትን መምረጥንና ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል።

---9/ ችግሩን የመፍታት ሦስተኛው ደረጃ ድርጊቱ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት መመርመር ነው፣ እነዚህን ሦስት ደረጃዎች ካሟላን ውጤቱ መልካም ይሆናል።

---10/ አማራጭ መንገዶችን ከመረመርን መደረግ ስላለበት ጉዳይና ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ከተወያየንበት በኋላ ችግሩ መፍትሔ እንዳገኘ ቡድኑ እርግጠኛ መሆን ይችላል።

---11/ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል መፍትሔ ተብሎ የቀረበው ሃሳብ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ያለውን አስተያየት ለመግለጥ እድል ሊሰጠው ይገባል። ውጤቱ መልካም ከሆነ መሪው አድናቆቱን ይገልጻል። መልካም ካልሆነ ግን ተጨማሪ ጥረት እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል።

---12/ በአጠቃላይ ገጽታው ስንመለከተው ለችግር መፍትሔ የመሻቱ ሂደት ከዋና ዋና ጉዳዩች ጋር ሲያያዝ ውሳኔ ማሳለፍ ግን ለጥቃቅን ችግሮች መፍትሔ መሻትን ይመለከታል።

---13/ ነህምያ በቂ መረጃ ካሰባሰበና የሚያስከትለውንም ውጤት ካወጣ ካወረደ በኋላ ውሳኔ አደረገ፣፡ ጉዳዩንም አብረውት ለሚሰሩ ሰዎች አዋያቸው፣ ውሳኔያቸውን እንዲገልጡም እድል ሰጣቸው።

---14/ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ እንዳያደርጉ አንዳንድ እንቅፋቶች ይገጥሟቸዋል፣ ከእነዚህም መካከል ትክክለኛ የሆነ ዓላማ አለማስቀመጥ፣ እርግጠኛ አለመሆን ለውጥን መፍራትና ነገሮችን ለመመርመር እምነት ማጣት ሲሆኑ አንዳንዶች እንዳይወቅሷቸው መፍራት ይገባቸዋል።

---15/ አንድ ክርስቲያን መሪ ውሳኔ እንዲያደርጉ ቡድኑን ይመራል፣ በውሳኔ ማድረጉ ሂደት የሚያሳትፋቸው ግን አልፎ አልፎ ነው፡፡

---16/ በሁለት ዓይነት መንገድ ውሳኔ ማሳለፍ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያ በአንድ ሰው ብቻ የሚደረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ብዙሀኑን ለማሳተፍ የሚደረግ ውሳኔ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የተዋጣላቸው መሪዎች ግን ብቻቸውን ሆነው ነው ውሳኔ የሚያሳልፉት፡፡

---17/ ምንም እንኳ አባሎቹ ብቃትና ብዙ ልምድ ያላቸው ክርስቲያኖች ቢሆኑም የሥጋዊነትና የትዕቢት ምልክት ስለሆነ በውሳኔ ማድረጉ ሂደት ላይ ትልቅ ኃላፊነት ሊሰጣቸው አይገባም፡፡

---18/ የቡድን ኃይል ጽንሰ-ሃሳብ ሰዎች ማሕበራዊ ፍጡራንና እርስ በርስ የሚደጋገፉ፣ በአንድነት ሆነው በመሥራትም የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኙ የሚያመለክት ነው፡፡

--19/ ሰዎች ማሕበራዊ ፍጡራንና አብሮ መሥራትን የሚወድዱ ቢሆንም፡ ብቻቸውን ሆነው ከሚሠሩት ይልቅ የተሻለ ውጤት አያገኙም፡፡

---20/ አባላቱ እርስ በርስ ያላቸው ቅርርብ፣ አንዱ ለሌላው ያለው አመለካከት፣ ሥፍራቸው አስተዋጾዋቸውን ማወቅ የቡድን ኃይል ሥራ ነክ ገጽታ ነው

--12/ የሥራ መዋቅሩን የመዘርጋቱን ያህል ለሰዎች አድናቆትን መግለጽም የቡድን አሰራር ሥራ ነክ ገጽታ ነው፡፡

---22/ ድምፅ ብልጫውን መሠረት በማድረግ የሚተላለፍ ውሳኔ ያለበት በመሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ቅሬታ ያሳድራል፣ የተሸናፊነት ስሜት እንዲያድርባቸውም ያደርጋል፡፡

---23/ የጋራ ስምምነት ሰዎች ሁሉ በአንድ ሃሳብ ላይ መስማማታቸውን የሚያሳይ ሲሆን፡ በመካከላቸው መከፋፈል እንዳይኖር ይረዳል፡፡

---24/ በድምጽ ብልጫ የሚተላለፍ ውሳኔ አንዳንድ ድክመቶች ቢኖሩትም ጠቃሚ ጎኑ ያመዝናል፡፡

---25/ በሙሉ ድምጽ የሚተላለፍ ውሳኔ የእውነተኛ መንፈሳዊነት መለኪያ ነው፡፡ የመንፈሳዊ ብስለትና ሕብረት ማስረጃ ነው፡፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

6/-) እንደ ልዩ ሁኔታው ይለያያል፡

1/ሀ)6) ሌሎችን ማነሳሳት ለ/2) ብቃት ሐ/3) ጥሪ መ/ 1) ለሌሎች ማሰብ ሠ/4) ዕቅድ ማውጣት ረ/5) ማደራጀት

7/ ሀ) ሐሰት ለ) ሐሰት ሐ) እውነት

2/ለ) የቅጥሩ ሥራ ተደናቀፈ

ሐ/ ለግንበኞች ራሳቸውን የሚከላከሉበት መሣሪያ ሰጣቸው፡፡

8/ሀ/1) ማሕበራዊ ገጽታ ለ/2) ሥራ-ነክ ገጽታ ሐ/2) ሥራ-ነክ ገጽታ

መ/1) ለሌሎች ማሰብ ሠ/4) እቅድ ማውጣት ረ/5) ማደራጀት

3/ ሐ) ያለአግበብ መጠቀምን ከለከለ

መ) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲያከብሩ ተናገረ፡፡

9/ሐ) ብዙሃኑ የሚያሳልፉት ውሳኔ ያለጥርጥር ትክክል መሆኑ መሪው በልበ ሙሉነት ለመንቀሳቀስ ድፍረት ይኖረዋል፡፡

4/ በዚህ ክፍለ ትምህርት የተካተቱትን ሦስት ደረጃዎች ጥቀስ

10/ መልስህ 5/መ) ውሳኔ በማድረግ ሂደት ጌታ ሰዎችን ይመራል፡፡

11/ ሀ/2) የጋራ ስምምነት ለ/3) በአንድ ድምፅ የሚያልፍ ውሳኔ

ሐ/ 1) በድምጽ ብልጫ የሚያልፍ ውሳኔ፡፡

12/ሀ/1) ለሁሉም ጨዋነትና ፍትሕን ማሳየት

2) በአንድ ጊዜ አንድን ጉዳይ ብቻ መመልከት 3) ንዑሳኑ መደመጥ አለባቸው

4) ብዙሃኑ ማሸነፍ አለባቸው

5) ዓላማው የሥራ እንቅስቃሴን ማመቻቸት እንጂ እንቅፋት መሆን አይደለም፡፡

ለ/አምስት ሐ/ስምንት፣ አራት ብልጫ መ/"ሃሳብን አቀራረቡ ትክክል አይደለም"

ሠ/ አጀንዳ ረ/ሥራውን ያሻሽለዋል፣ ቀጣይነት እንዲኖረውም ይረዳል፣ የወቅቱን ውሳኔዎች ወደ ፊት ከሚደረገው ስብሳባ ጋር ያያይዛል፣ ለምንም ጫና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይረዳል፡፡

ሰ/ ወደሌላው ጉዳይ ከማለፋችን በፊት ያለውን እንደሚገባ መመርመር እንዲቻል ለቡድኑ በአንድ ጊዜ አንድ ጉዳይ ብቻ ነው መቅረት ያለበት፡፡

# <u>ክፍል ትምህርት ሰባት</u>

## *መሪዎች ኃላፊነትን ይቀበላሉ*

በስድስተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ *መሪዎች* ለችግሮች መፍትሔ እንደሚሰጡና ውሳኔ እንደሚያስተላልፉ በመግለጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የነህምያን ታሪክ በምሳሌነት በመውሰድ ለመንፈሳዊ መሪነት ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ከመመልከታችንም በላይ በቡድን ግብረ ኃይል ውስጥ ለጋራ ዓላማ አብሮ ስለ መሥራትና ስለ መፍትሔ አሰጣጥ ሂደት እንደዚሁም ውሳኔ ስለ ማስተላለፍ ዘዴዎች አስፈላጊውን ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

በዚህ በሰባተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ መሪዎች እንዴት ኃላፊነት እንደሚቀበሉ ለመገንዘብ ይረዳን ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የአስቴርን ምሳሌነት በመከተል ኃላፊነት መቀበል ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ስለ ዓላማዎች ባሕርያትና ዓላማዎችን እግብ ማድረስ አስፈላጊነቱ ምን ያህል እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የአስቴር ምሳሌነት
- ዓላማን እግብ የማድረስ አስፈላጊነት
- ኃላፊነትን የመቀበል አስፈላጊነት

-----------------------------------------------------------------

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

- ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማድረግ መቻል አለብህ፣ የአስቴርን ታሪክ መሠረት በማድረግ መሪነት የሚሆኑ መመሪያዎችን መግለጽና እነዚህን መመሪያዎች በመሪነት አገልግሎትህ ተግባራዊ ማድረግ
- ዓላማዎችን እግብ ማድረስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ውጤቱን መግለጽ
- ኃላፊነትን መቀበል ማለት ምን እንደሆነ መግለጽ

-----------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1. አስቀድመህ ያነበብኸው ቢሆንም ስለ መሪነት ብዙ ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ታገኝበታለህና መጽሐፈ አስቴርን እንደገና አንብብ። ስታነብም አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦችን ማስታወሻ ደብተር ላይ መያዝ ያስፈልግህ ይሆናል።
2. ለጥናት ማጠናከሪያ የተሰጡትን ጥያቄዎች መልስ፣ ክፍለ ትምህርቱን እንደጨረስክ የሙከራ ፈተናውን በመውሰድ መልሶችህን በመጽሐፉ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር በማስተያየት የተሳሳትካቸው ካሉ አስተካክል።

---------------------------------------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ**

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈሩትን ተከታታይ ትምህርቶች መከታተል ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ስለ መንፈሳዊ መሪነት እስከአሁን ያተኮርነው ሦስት ዋና ሃሳቦች ላይ ሲሆን፣ እነርሱም ስለሚመሩና ስለሚከተሉ ሰዎች፣ ስለሚሰራው ሥራ እና ስለ ዓላማዎች እንደዚሁም ሥራቸውንና ዓላማቸውን ወይም ግባቸውን መለያየት አይቻልም። ለምሳሌ ያህል ከአስቴር ታሪክ ሦስቱም በአንድነት ተጣምረው ሥራ ላይ ሲውሉ ነው የምንመለከተው።

**የአስቴር ምሳሌት**

**ዓላማ 1 ስለ መሪነት ባሕርያት፣ ስለሥራዎችና ግቦች ምሳሌ የሚሆኑን ለመግለጽ**

በተለያየ ሁኔታ ግለሰቦች የመሪነት ኃላፊነትን ይቀበላሉ። ብዙውን ጊዜ አንድ መሪ በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚነሳው ችግር ለመፍታት ነው። ችግሮቻችን ይፈቱልናል ብለው የሚያስቡ ሰዎች መሪዎችን ይከተሉዋቸዋል። የመሪዎች መኖር አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ዓላማዎችና ግቦች ሊኖሩ ይገባል። የመሪዎቹ ዓይነት እንደ ችግሩ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። ብዙ መሪዎች የሚጋሩዋቸው ባሕርያት አሉዋቸው፣ ከተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች እንደተመለከትነው ግን አንዳንድ መሪዎች ከሌሎች ልዩ የሚያደርጋቸው የግላቸው ባሕርይ አላቸው።

የአስቴር ታሪክ አንድን ችግር ለመፍታት ሁኔታዎች ያስገኙት መሪ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። መጽሐፉ የሚጀምረው አስቸጋሪ ሁኔታን በመግለጽ ነው። በዚህ የታሪክ አጋጣሚ የታየውን ያልተለመደ ሁኔታ በዓይነ-ሕሊናህ ለማሳየት ያህል ንጉሥ አርጤክስስ ብልጽግናውን፣ ኃይሉንና የሚስቱን ውበት ለማሳየት ባደርገው ግብዣ ላይ ንግሥት

አስጢን መገኘት አልፈለገችም። ስለዚህም ሊፈታትና ከቤተ መንግሥትም እንድትወጣ ሊያባርራት ወሰነ።

በዚያ አገር የንጉሥ ሕግ ዘላለማዊ ተደርጎ ስለሚታሰብ በርሱ በንጉሡ እንኳ መለወጥ አይችልም። ሚስቱን ማጣቱ አንድ ነገር አንደጎደለው ቢያደርገውም ቃሉን በማጠፍ እንደገና ሊመልሳት ግን አይችልም። ስለዚህም በአገሩ ካሉት ቆነጃጅቶች አንዷ እንድትመረጥና የንግሥቲቱን ሥፍራ አንድትይዝ መከሩት። የቁንጅና ውድድር ዓይነት ተደረገና አዲስ ልዕልት ተመረጠች።

በወቅቱ አይሁዳውያን የንጉሡ ምርኮኞች ነበሩ። ብዙዎች የምርኮኝነቱን ኑሮ ተላምደውታል፣ በነበራቸው እውቀትና ትጉ ሠራተኛነታቸውም አንዳንዶቹ ለመሪነት በቅተዋል። ከእነዚህም አንዱ መርዶክዮስ ሲሆን፣ የአጎቱ ልጅ አስቴር ገና ከልጅነቷ አባትና እናቷ ስለሞቱባት እንደ አባት ሆኖ ያሳደጋት እርሱ ነበር። መልከ ቀናና ውብ ስለነበረች ወደ ንጉሡ ፊት ከሚቀርቡት ቆነጃጅት አንዷ ሆኖ ተመረጠች። መረዶኪዮስ አይሁዳዊነቷን እንዳትገልጽ አስጠንቅቋታል። ንጉሡም ስለማንነቷ አልጠየቃትም። የንጉሡ ዋናው ትኩረት ቁንጅናዋና ሥነ-ምግባሯ ላይ ነበር። ከሌሎች አብልጦ ስለወደዳትም ንግሥት እንድትሆን መረጣት፣ የንግሥቲቱን ሥፍራ ያዘች። ልብሰ መንግሥት፣ አክሊልና የሚያገለግሏት ሴቶች ተሰጧት፣ ምቾቷን ለመጠበቅም የሚያስፈልጋትን ሁሉ ተሟላላት።

ከንጉሡ ታላላቅ ባለሥልጣናት አንዱ በትዕቢቱና በራስ ወዳድነቱ የሚታወቀው ሐማ የሚባል ሰው ነበር። ሐማ አይሁዳውያንን በጣም ይጠላል። መርዶኪዮስ ወድቆ ስላልሰገደለት በጣም ተቆጥቶአል። **"የሚገባኝን ክብር ከመፈለጉም በላይ አይሁዳዊ ነው፣ እርሱንም ሆነ ወገኖቹን አሳያቸዋለሁ"** በማለት ዛተ። ከዚያም አይሁዳውያን አደገኞችና ችግር ፈጣሪዎች እንደሆኑ ንጉሡን ለማሳመን ከፍተኛ ሙከራ አደረገ። ለመንግሥት አክብሮት ስሌላቸው ጨርሶ መወገድ እንዳለባቸው አሳሰበ። ንጉሡን አሳምኖ አዋጅ እንዲነገር በማድረጉም አይሁዳውያንን ለማጥፋት እቅድ ወጣ።

መርዶኪዮስ ይህንን ሲሰማ አይሁዳውያንን ለማዳን አንድ ዕድል ብቻ እንዳለ ተረዳ። አይሁዳውያንን ለማጥፋት የወጣው አዋጅ ንግሥቲቱ አስቴርን እንደሚጨምር ንጉሡ ካወቀ እርሷንና ሕዝቧን ለማዳን አንድ ነገር ማድረጉ አይቀርም። የወቅቱን ችግር

መፍታት የሚቻለው በእርሷ በኩል ብቻ ስለነበር፣ አስቴር ወደ ንጉሡ እንድትቀርብና ለሕዝቧ ምሕረት እንድትጠይቅ መርዶክዮስ ነገራት፡፡

እንዴት ይህን ማድረግ ትችላለች? ከንጉሡ ጥሪ ካልተደረገላት በቀር እፊቱ መቅረብ እንደማትችል መርዶክዮስ ያውቃል፡፡ እንደዚያ የሚያደርግ ሁሉ በሞት እንደሚቀጣ ያውቃል፣ የንጉሡ ሕግ አይለወጥም፡፡ አይሁዳውያንን ለማጥፋት የወጣው አዋጅም አይለወጥም፡፡ ታዲያ ምን ማድረግ ትችላለች? ንጉሡ ከፈለገ እፊቱ ለሚቀርብ ሰው የወርቅ በትረ መንግስቱን ይዘረጋለታል፣ ይህም ቢሆን የራሱ ችግር አለው፡፡ **“ላለፉት ሰላሳ ቀኖች ንጉሡ አልጠራኝም፣ ሳይጠራኝ ወደፊቱ ብቀርብ ደግሞ የሚያስከትለውን ችግር ታውቃለህ”** አለች አስቴር ለመርዶክዩስ፡፡

በፍጹም አይሁዳዊነቷን እንዳትረሳ መርዶክዮስ አጠንክሮ አሳሰባት፡፡ **”ንግሥት ስለሆንሽ ከሞት እንደማታመልጪ እወቂ፡፡ ወገኖችሽን ብትረጂ ግን አንቺም ከሞት ትድኛለሽ፣ ምናልባትም ለዚህ ሥልጣን የበቃሽው በእንደዚህ ዓይነቱ አስቸጋሪ ጊዜ ለወገኖችሽ መፍትሔ እንድትሆኚ ሊሆን ይችላል”** አላት፡፡

የአስቴር ስም ትርጉም ኮከብ መሆኑ የሚገርም ነው፡፡ እንደኮከብ ደምቃና ጎልታ እንድትታይ እግዚአብሔር ለዚህ ትልቅ ሥፍራ አብቅቷታል፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደጠራቸው ሌሎች ሰዎች ሁሉ አስቴርም ለዚያ ከፍተኛ ደረጃ የበቃችው የራሷን ምቾትና ተድላ ለማስጠበቅ አልነበረም፡፡ ኮከብነቷ በግሏ ወይም ለራሷ ብቻ ሳይሆን፣ ለወገኖቿም መጥቀም እንደተረዳች አስቴር እውነተኛ መሪ ለመሆን በፈቃዷ ቆርጣ ተነሣች፡፡ ምንም እንኳ ሁኔታው አደገኛ ቢሆንም ወደ ንጉሡ ለመሄድና በጎም ሆነ ክፉ የሚያስከትለውን ሁሉ ለመቀበል ወሰነች፡፡

አስቴር የመሪነት ባሕርያት ያሏት ብቻ ሳትሆን እንደ አንድ መሪ መንቀሳቀስ ጀምራለች፡፡ በአእምሮዋ እቅድ አውጥታለች፣ ሕዝቡ መሳተፍ እንዳለባቸውም ተረድታለች፡፡ የሕዝቡ ድጋፍና ትብብር ያስፈልጋታል፡፡ ለሦስት ቀን እንዲጾሙ ነገረቻቸው፡፡ እርሷና አብረዋት ያሉትም እንደሚጾሙ የተናገረችው ማንም ሊገባው በሚችል ቋንቋ ነበር፡፡

በእነዚህ ሦስት ቀናት አስቴር በጾም ብቻ አልተወሰነችም፡፡ እቅድ አወጣች፣ ዝግጅትም አደረገች፡፡ ማድረግ የምትፈልገውንም በቅደም ተከተል አስቀመጠች፣ ትክክለኛውን ጊዜና

ሁኔታ ለማመቻቸት ንጉሡንና ሐማን ምሳ ልትጋብዛቸው አሰበች ፣ ሠራተኞቿንም ዝግጅት እንዲያደርጉ አዘዘች፡፡

በሦስተኛው ቀን የንግሥት ልብሷን ለብሳ ወደ ንጉሡ ቀረበች፡፡ ደፋር፣ ሆኖም ግን ረጋ ያለችና ጥንቁቅ ነበረች፡፡ ንጉሡ ሳይጠራት እፊቱ ለመቅረብ በመወሰኗ ራሷን ለችግር አጋልጣለች፡፡ ለዚህም ልዩ የሆነ ዓላማ አላት፣ ያንን ዓላማ እግብ ለማድረስ ነበር ይህን ለማድረግ ቁርጠኛ ሆና የተነሣችው፡፡

የማያስፈልግ ቁጣ ላለማስነሳት ጥንቃቄ አድርጋለች፡፡ ለተገቢው ወቅት የሚስማማውን ልብስ ነበር የለበሰችው፡፡ አነጋገሯ ጨዋነትና ቁጥብነት የተሞላበት ነበር፡፡ ንጉሡ በሁኔታዋ ደስ ሰላለው በትረ መንግሥቱን ዘረጋላት፣ እርሷም ባገኘችው ድል ኩራት ሳይሰማት በአክብሮት በትረ መንግሥቱን ያዘች፡፡

አስቴር እቅዷን ረጋ ብላ ነበር ያጠናቀቀችው፡፡ ወገኖቿ እንዲጠፉ በመወሰኑ ሆድ ብሷት ንጉሡ ፊት አላለቀሰችም፡፡ የልቧን የምትናገርበት ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ንጉሡን ምሳ ጋበዘችው፡፡ ቀስ በቀስ ያለውን ችግር እንዲረዳና ስለ አይሁዳውያንም አንድ ነገር እንዲያደርግ ነገረችው፡፡

1/ የሚከተሉት መግለጫዎች ስለ አስቴር የመሪነት ባሕርያት፣ ሥራና ዓላማ የሚገልጹ ናቸው፡፡ በተሰጠው ስፍራ ቁጥሩን በማስቀመጥ አብረው የሚሄዱትን አመልክት፡፡

1) የመሪነት ባሕርያት 2) የሚሠራው ሥራ

3) ዓላማና ግብ

----ሀ/ አስቴር ሕዝቧ እንዲድኑ ትፈልጋለች

----ለ/ ደፋርና ቆራጥ ናት

---ሐ/ ንጉሱ አንድ ነገር እንዲያደርግ መንገር ነበረባት

----መ/ የሚገናኙበት ጊዜ አስቀድሞ ታቅዷል፡፡

---ሠ/ ግልጽ መመሪያ ሰጠች

----ረ/ ረጋ ያለችና ቁጥብ ነበረች

----ሰ/ ኃላፊነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ነች

---ሸ/ ምክንያታዊና ዘዴኛ ነበረች

**ዓላማን እግብ የማድረስ አስፈላጊነት**

**ዓላማ 2 ዓላማዎችን እግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ነገሮችን በቅደም ተከተል ለመግለጽ**

ከአስቴር ታሪክ የምንረዳው ሕዝቧን ለማዳን አስቴር ላደረገችው ነገር ሁሉ አጠቃላይ ዓላማ ሲሆን፣ ይህን ዓላማ ፍጻሜ ላይ ለማድረስ በሕዝቧ ላይ የታወጀውን የእልቂት አዋጅ ንጉሡ እንዲለውጥ ማስደረግ ነበረባት፡፡ ዋናው ዓላማ ፍጻሜ ላይ የምንደርሰው ጥቃቅን በሆኑ ሌሎች ዓላማዎች በኩል አልፈን ነው፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ የመጨረሻውና ዋናው ዓላማችን መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ስፋትም ያለው ነው፡፡ ይህን ማጠቃለያ ዓላማ መላውን ዓለም በክርስቶስ ወንጌል ለመድረስ ሲሆን፣ ወደዚህ ማጠቃለያ ዓላማ ለመድረስ ደግሞ በተለያዩ መንደርደሪያ ዓላማዎች በኩል ማለፍ ይኖርብናል፡፡

አስቴር ከአንድ ዓላማ እንዴት ወደ ሌላው ዓላማ ትሸጋገር እንደነበር መረዳት ያስፈልጋል፡፡ መጀመሪያ የንጉሡን ፈቃደኝነት ማግኘት ነበረባት፡፡ ንጉሡ ያወጣውን አዋጅ መለወጥ እንደማይችል ስለምታውቅ አዋጁን ሳትጋፋ ሕዝቧን ማዳን የምትችልበትን መንገድ ፈለገች፡፡ በመጨረሻም አይሁዳውያን ራሳቸውን እንዲከላከሉ በተወሰነ ጊዜ እንኳ ለንጉሡ ያላቸው ክብር እንደተጠበቀ ነበር፡፡ ግልጽና በጣም አስፈላጊ የሆነ ዋና ዓላማ ስለነበራት በተለያዩ ንዑሳን ዓላማዎች ማለፍ ነበረባት፡፡ እያንዳንዱ ነዑሳን ዓላማዎች ላይ ከደረሰች በኋላ ነበር ወደዋናውና አጠቃላይ ወደ ሆነው ዓላማ የደረሰችው፡፡

2/ በቤተክርስቲያን ትክክለኛ አመራር የሚጠይቅ ሁኔታ ምን ይመስልሃል?

3/ ከመርዶክዮስ ጋር የሚመሳሰለውን እንዴት ነው የምታየው?

4/ አጠቃላይ ዓላማ ማለት ምን እንደሆነ በአጭሩ ግለጽ፡፡

5/ ለምሳሌ ያህል በመንፈሳዊ መሪነት ለቤተክርስቲያን ማቋቋም ብትመረጥ ዓላማህን ፍጻሜ ላይ ለማድረስ የምታደርጋቸውን ነገሮች በጽሑፍ አስፍር፡፡

**ዓላማ 3 የዓላማዎችንና የግቦችን ውጤት ለመግለጽ**

ምንም እንኳ የመንፈሳዊ ሥራ መጨረሻ ዓላማ ግልጽ ቢሆንም ፣ ብዙ መሪዎች ግን የዓላማዎችንና የግቦችን አስፈላጊነትን የተረዱ አይመስልም፡፡ **"የጌታን ፈቃድ ማድረግ"** እና **"ነፍሳትን ለጌታ መማረክ ብቻ"** በቂ ይመስላቸዋል፡፡ አንዳንዶቹም ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነፃ መሆነ አለብን ስለሚሉ ለሥራቸው ግልጽ የሆነ ዓላማ

ለማስቀመጥ ቸልተኞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ስለ እቅድ ማውጣት ቀደም ሲል እንደተመለከትነው እቅዳችን የተሳካ እንዲሆን የመንፈሳዊ ምሪት ያስፈልገናል፡፡ ሰዎች ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማ ይዘው ከሠሩ ውጤታማ በሆነ መንገድ ደስ ብሏቸው ይሠራሉ፣ ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ ሥራ ያልተሳካና ውጤት አልባ የሚሆነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እንቅስቃሴያችንን ግልጽ በሆነ ዓላማ መመራቱ ለሥራችን ታላቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

1/ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች መኖር ያለአግባብ የሚባክን ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ይቆጥባል፡፡ ለሥራችን ግልጽ የሆነ ነገር ካለን ግራ መጋባትና ብኩንነትን እናስወግዳለን፣ የታቀደ ዓላማ ከሌለን አንዳንድ መሠራት ያለባቸውን በመርሳት ሌሎችን ደጋግመን እንሰራቸዋለን፡፡ ዋናው ችግር ሳይቃለል ገንዘባችን በከንቱ ይባክናል፡፡ አንዱ ብዙ ሲሠራ ሌላው ደግሞ ጥቂት ይሠራል፡፡

2/ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች መኖር ሰዎችን ያስተባብራል፡፡ ሰዎች ዓላማ ባለው ሥራ ላይ መሳተፍ ያስደስታቸዋል፡፡ መሪው እንዲሁ በደፈናው፡- **ሁላችንም ተባብረን እንሥራ** የሚል ከሆነ ግን አይተባበሩትም፡፡ የሥራቸው ወይም የጥረታቸው ውጤት ምን ላይ እንደሚደርስ አስቀድመው ካልተረዱ ተባብረን እንሥራ ማለቱ ብቻ ምንም አይማርካቸውም፡፡

3/ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች መኖር ሥራን በሚገባ ለመገምገም ያስችላል፡፡ አንድን ሥራ የተሳካ ነው ማለት የምንችለው የምንለካበት ወይም የምንመዝንበት ነገር ሲኖረን ነው፡፡ የሥራው ውጤት የማይገመገም ከሆነ ግን በጣም ዝቅተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ብቻ ስለሚታለፍ ወደ ተሻለ ውጤት አይገፋፋም፡፡ በእርግጥ ብዙ ሊሠራ ይችላል፣ ምን እንደተሠራ ግን አይታወቅም፡፡ የሥራውን ዓላማ አስቀድመን በግልጽ ካስቀመጥን ግን ውጤቱን በትክክል መገመገም ይቻላል፡፡ ይህ ሥራቸውን እንዲያሻሽሉ የሠሩትን እንዲያውቁ ከማድረጉም በላይ እርካታ ይሰጣቸዋል፡፡ የሥራውን ደካማ ጎን በማወቅ ለተሻለ ውጤት አስፈላጊውን ጥረት እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል፡፡

4/ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች መኖር የሰዎችን ችሎታና ስጦታ ለመረዳት ያስችላል፡፡ የሥራው ዓላማ በግልጽ ከተቀመጠላቸው ሰዎች ያንን ዓላማ ለመፈጸም ያላቸውን ችሎታ ያመዛዝናሉ፡፡ የራሳችንም ሆነ የሌሎችን ብቃት ለመለካት ያስችላል፡፡ አስቴር የችግሩን አስከፊነት ባታውቅ ኖር ማድረግ የምትችለውን ነገር ልትረዳ ባልቻለችም ነበር፡፡ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች ካሉን፣ ሰዎችን በችሎታቸው መሠረት ማሠማራት

ያስችላል። ሰዎችም በፈቃደኝነት በሥራው ከመሳተፋቸውም በላይ ብቃት ያላቸው አዳዲስ መሪዎች ይነሳሉ።

6/ እስጢፋኖስ አናጢ ነው እንበል፣ የቤተክርስቲያኑ መጋቢ ቤተክርስቲያኑን ለማደስ የሚረዱ ፈቃደኞችን ሲጠይቅ ከሰማ በኋላ ከሚከተሉት ማስታወቂያዎች ለየትኛው የበለጠ ምላሽ የሚሰጥ ይመስልሃል? ትክክለኛ ነው ብለህ በምታስበው መግለጫ ፊደሉን በመክበብ አመልክት።

ሀ/ ቤተክርስቲያኑን ለመሥራት ብዙ ሰዎች እንዲረዱን እንፈልጋለን፡

ለ/ ለመሥራት ካቀድናቸው አንዱ ስድስት መስኮቶችን ማደስ ነው፡

7/ ጥያቄው ተሰርዟል

8/ ዓላማዎችን በግልጽ ማስቀመጥ ሰላለው ጠቀሜታ ይበልጥ የሚገልጸውን መግለጫ ፊደሉን በመግለጽ አመልክት።

ሀ/ ዓላማን በግልጽ የማስቀመጥ ዋናው ጥቅም በአጭር ጊዜ ብዙ መሥራት እንዲቻል ነው፣

ለ/ የዓላማ መኖር ዋናው ጥቅም የመሪውን ሥራ ለማቃለል ነው።

ሐ/ የዓላማ መኖር ሥራው እንዲሠራና የሰዎቹም አመለካከት እንዲለወጥ ይረዳል

**ኃላፊነትን የመቀበል አስፈላጊነት**

**ዓላማ 4 ለአንድ ግልጽ ለሆነ ዓላማ ራስን መስጠት እንዴት ነጻነትን እንደሚሰጥ የሚገልጽ ምሳሌ ለመስጠት**

የመሪነት ከባዱ ሥራ ለራስህም ሆነ አብረውህ ለሚሠሩ ሰዎች ግልጽ የሆነ ዐላማ ማስቀመጥ ነው። ከባድ የሆነበትም ምክንያት ታማኝነትንና በፈቃደኝነት ኃላፊነትን መቀበልን ስለሚጠይቅ ነው። ወደአስቴር ታሪክ መለስ ብለን እንደገና ብንመለከት አስቴር ሰለወቅቱ ሁኔታ መርዶክዮስ ሲነግራት ለወገኖቿ ኃላፊነት ተሰማት። ሰዎች የቤተክርስቲያንን ዓላማ በትክክል ከተረዱ መደረግ ያለበትም ከተገለጸላቸው አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ለማድረግና ኃላፊነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ይሆናሉ።

አንድ የሥነ-አእምሮ አዋቂ ደስታ ከራቃቸውና ከማሕበረሰቡም ጋር መጣጣም ባቃታቸው ሰዎች ላይ ባደረገው ምርምር የችግራቸው ዋናው መንስኤ ሐቅን ለመጋፈጥ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንደሆነ ይናገራል። ያለማቋረጥ ሰበብ በማብዛት የችግራቸው ምክንያት ሌሎች ሰዎችና ያሉበት ሁኔታ እንደሆነ ይገምታሉ። አስቴር እንደዚህ ዓይነት

ዝንባሌ ቢኖራት ኖሮ፡- **ሴት ባልሆን ኖሮ ወይም ንጉሡ ግትር ባይሆን ኖሮ** የሚል ሰበብ ትሰጥ ነበር፡፡ እርሷ ግን ሐቅን ለመጋፈጥና አንድ ነገር ማድረግ እንዳለባትም ተገነዘበች፡፡ ውጤታማና የተሳካ ኑሮ ሊኖረን የሚችለው ሐቅን ወይም እውነታን ለመቀበል ፈቃደኛ ስንሆን ብቻ ነው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማንኛውንም ችግር ለመቋቋም ፈቃደኛ ከሆንን እርካታ ይኖረናል፡፡ ለአንድ ነገር ራስን መስጠት ነፃነት ከማስገኘቱም በላይ የሚያስከፍለውን ዋጋ በትክክል ማሰብና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ በራስ መተማመንን ይጠይቃል፡፡ መንፈሳዊ አመራራችን ውጤታማ የሚሆነው እኛ ክርስቲያኖች በራሳችን መተማመን የምናገኘው በእግዚአብሔር ከመተማመናችን የተነሳ ስለሆነ፣ ይህም የሚሰጠን ሌሎች ያላገኙትን ጠቀሜታ ነው፡፡

9/ አስቴር ራሷን ለአደጋ እንዳጋለጠች ብታውቅም ኃላፊነትን ለመቀበል ቆርጣለች፣ ይህን ውሳኔዋን ምን በማለት ነበር የገለጠችው?------------------- ይህ ቁርጠኛነቷስ ነፃነት ያስገኘላት እንዴት ነው? በአብዛኛው ከፍርሃት ነፃ እንደሆነች አይመስልህም? ከማንኛውም አይነት ሰበብ ራሷን ነፃ በማድረግ አስቸጋሪ ውሳኔ ለማድረግ እንኳ ብቃት እንደነበራት ለራሷ አረጋገጠች፡፡ በእምነት ወደፊት ለመራመድ ነፃ ነበረች፡፡

10/ የሚከተለውን መግለጫዎች መሠረት በማድረግ ለአንድ ዓላማ ራስን መስጠት የሚያስገኘውን ነፃነት በሚያመለክቱት ፊደሉ በመክበብ አመልክት፡፡

ሀ/ ዮሐንስ እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደጠራው ያስባል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመግባት ያደረገው ውሳኔ የሚያስከትለውን ውጤትም በሚገባ አመዛዝኗል፡፡ አሁን እቅዱን ሥራ ላይ ሊያውል እየተዘጋጀ ነው፡፡ ግልጽ ውሳኔ ስላደረገ በመወሰንና ባለመወሰን መካከል አልተወጠረም፡፡ አሁን ትኩረቱን ሁሉ በአንድ ዓላማ ላይ ማድረግ ይችላል፡፡

ለ/ ርብቃ ለወንጌል አገልግሎት ለመውጣት ፍላጎት ስላላት ሥራ ለማቆም ወስናለች፡፡ ከዚህ ውሳኔዋ ምንም ወደኋላ የሚጎትታት ነገር እንደሌለ ታስባለች፡፡ ነገሮች ሁሉ በእርሷ መንገድ እንደሚሄዱላት እርግጠኛ ነች፣ በውሳኔዋ ምንም ነገር ለማድረግ ነፃነት እንዳላት ታምናለች፡፡

ሐ/ ቶማስ ለወንጌል ሥራ ሙሉ ጊዜውን እንዲሰጥ እግዚአብሔር ተናግሮታል፡፡ ብዙ ከጸለየና ልቡንም ከመረመረ በኋላ ምንም ቤተክርስቲያን በሌለበት አካባቢ ቤተክርስቲያን ለመሥራት ወስኗል፡፡ ለዚህም ዓላማ ሥራውን ያቆማል፣ ከቤተሰቡና ከጓደኞቹም ይለያል፡፡ ምንም እንኳ ሁኔታዎች የተመቻቹና አስተማማኝ ባይሆኑም፣ ወደሌላ አገር

ለመሄድ ወስኗል። በጣም የሚገርመው ደግሞ ስለ ምግብ፡- ገንዘብና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች በፍጹም አይጨነቅም። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደሚያሟያላስት እምነት አለው።

መ/ ጴጥሮስ ለአገልግሎት ጥሪው ምን ምላሽ መስጠት እንደሚኖርበት ያስባል፣ ከነበረበት ውስጥ አእምሮውን ያሳረፈ ስለሚመስለው፡- **ብቁ አይደለሁም ሰዎችን ማናገርም እፈራለሁ። እንደሚገባኝ አልተማርሁም፣ ለእንደኔ ዓይነቱ ይቅርና ሥራው ብዙ ልምድ ላላቸው ሰዎች እንኳ አስቸጋሪ ነው። በጌታ ሥራ አይሳካልኝም፡ አሁን ባለሁበት ሁኔታ ግን የተሳካልኝ ስለሆንሁ ከሙያዬ መለየት ያለብኝ አይመስለኝም** የሚሉ ምክንያቶችን ይደረድራል። እነዚህንና ሌሎች ምክንያቶችን መሠረት በማድረግም ጉዳዩን ጨርሶ ለመርሳት ይሞክራል።

11/ ምናልባትም የሚከተሉትን ብትመለከት ከአንድ የተዋጣለት መሪ ስለሚጠበቁ ባሕርያት ያለህን ዝንባሌ ለማወቅ ይረዳሃል። ትክክለኛ ምላሽህን ለመግለጽ በተሰጠው ቦታ ጠንካራ ጎን ወይም ደካማ ጎን እያልክ በማመልከት ራስህን በትክክል ለመገምገም ሞክር።

1/ ጠንካራ ጎን 2/ ደካማ ጎን

ሀ/ በማንኛውም ሁኔታ ኃላፊነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ነህን?

ለ/ ለምትመራቸው ሰዎች ግልጽና ታማኝ ለመሆን ፈቃደኛ ነህን?

ሐ/ መልካም ነገር እንዲሆንላቸው ለምትመራቸው ሰዎች መስዋእትነት ለመክፈል ፈቃደኛ ነህ?

መ/ የሚፈለገው ግብ ላይ መድረስ እንዲችሉ ተከታዮችህ መስዋእትነትን እንዲከፍሉ በመጠየቅህ የሚሰነዘርብህን ማንኛውንም ነቀፌታ ለመቀበል ፈቃደኛ ነህን?

ሠ/ ምንም እንኳ ቤተክርስቲያንህ በፊት ትከተለው ከነበረው አሰራር ማፈንገጥ መስሎ ቢታይም ሰዎች እውነተኛውን የቤተክርስቲያን ዓላማ እንዲቀበሉ ለማደፋፈር ፈቃደኛ ነህን?

ረ/ እውነታን ለመቀበልና በጊዜው ባለህ ነገር ለመሥራት ፈቃደኛ ነህን?

ስ/ ተጨባጭ ግቦችና መለኪያዎችን በማስቀመጥ ግልጽ መመሪያዎችንም በመስጠት እንዴት ግቡ ላይ መድረስ እንዲችሉ ለማድረግ ፈቃደኛ ነህን?

ሽ/ አንድን ሥራ ከመጀመርህ በፊት የሚያስከትለውን ውጤት እንደሚገባ ብታውቅ በራስ መተማመን እንደሚኖርህና አመራርህም ውጤታማ እንደሚሆን ታስባለህን?

ቀ/ ሁኔታዎችን በማመዛዘንና ውጤቱን አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች በማሳወቅ ምን ያህል እውነታ ላይ የተመረኮዘ እንደሆነ ለመፈተን ፈቃደኛ ነህን?

በ/ ለሚያደርጉት መልካም ነገር ሁሉ አብረውህ የሚሰሩ ሰዎችን ለማበረታታት ምን ያህል ፈቃደኛ ነህ?

**እውነቱን መጋፈጥ**

**ዓላማ 5 እውነቱን መያዝና መጋፈጥ ማለት ምን እንደሆነ ለመግለጽ**

ምንጊዜም ቢሆን ዓላማዎቻችን እውነት ላይ መመሥረት ይኖርባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ በእምነት ብቻ ከፍተኛ ውጤት እንዳገኘን በድፍረት እንናገራለን፡ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት መግለጽ በእርግጥ መልካም ነው። ሰዎች በጣም ስሜታውያን ከሆኑና ከተጨበጠው ሐቅ የራቁ ነገሮችን የሚጠብቁ ከሆነ ግን በቀላሉ ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ። ለወደፊቱም በማንኛውም ሥራ ለመተባበር ፈቃደኛ ስለማይሆኑ መሪው የሌሎችን ስሜት ከመቀስቀሱ በፊት አስቀድሞ ስለራሱ እምነት መጠን እርግጠኛ መሆን አለበት። አብረውህ የሚሰሩትን ሰዎች ሪፖርትና የሥራ ውጤት በመከታተል ዓላማህ ምን ያህል እተጨበጠ ሐቅ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን መረዳት ትችላለህ። ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ዓላማህ ላይ መድረስ እንደሚቻል የምታስበው ተጨባጭ የሆነ ሁኔታ ሲኖርህ ነው።

ሊገጥሙን የሚችሉ አንዳንድ መሰናክሎች በግልጽ መታወቅ አለባቸው። ወደ አንድ ዓላማ ለመድረስ ሰዎችን የሚመራ ሰው ሥራውን አቅልሎ ወይም አድበስብሶ ለማቅረብ መሞከር የለበትም። ችግሩን በግልጽ የሚናገርና የሌሎችን እርዳታ፣ ሃሳብና ምክር የሚጠይቅን ሰው መሆን አለበት። አንድ ሰው ጥርጥሩንና ችግሩን ሲናገር መሪው ጉዳዩን ለማጣጣል መሞከር የለበትም። የዚያን ሰው ችግር መረዳትና ለሥራው ምን ያህል እንደሚያስብ መረዳት ተገቢ ነው። ነገርን ከማጣጣል ይልቅ መሪው፡- **ጉዳዩ አስቸጋሪ እንደሆነ እኔም አውቃለሁ** ቢል ግን ለሠራተኞቹ ብርታት ይሰጣቸዋል። **በጣም ቀላል ነው፡ ምንም ችግር የለበትም** በማለት ሐቁን ለመሸፋፈን የሚሞክርን መሪ ሰዎች ይንቁታል።

በምንም ዓይነት መንገድ ሰበብ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። ከኤደን ገነት ጀምሮ ሰዎች ክስ የማቅረብና ሌሎችን የመክሰስ ዝንባሌ አላቸው፣፡ ለችግራቸውና ለውድቀታቸው ምክንያቱ ሠይጣን፣ ሌሎች ሰዎች ወይም ሁኔታው እንደሆነ ያሳብባሉ።

ሰበብ ባቀረብን ቁጥር ከኃላፊነት ለመሸሽ መሞከራችን ከመሆኑም በላይ ራሳችንን ማቃለል ነው፡፡ ስለዚህም ሰበብን መቀበል ትክክል አይደለም፡፡ እውነተኛ መሪ ሰዎች ስለራሳቸው ድካም ኃላፊነትን እንዲቀበሉ ያስተምራል፡፡

እያንዳንዱ ሰው የተሰጠውን ሥራ ለማጠናቀቅ ብቃት እንዳለው ማሰብ አለበት፡፡ ሰበብ ማብዛት ግን ከሐቁ እንዲርቅ ያደርገዋል፡፡ የቤተክርስቲያን ሥራ የተሳካ ይሆን ዘንድ መሪው ግልጽ የሆነ ዓላማና ግብ እንደዚሁም መመዘኛ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አንድ ሰው ሰበብ ሲያቀርብ መሪው፡- **አዎን ትክክል ነህ** በማለት የድጋፍ ምልክት ማሳየት የለበትም፡፡ ለሰውየው ያለውን አክብሮትና ፍቅሩን በመግለጽ እንደሚጠበቅበት ተግባሩን በማከናወን እንዲኖረው ሊረዳው ይገባል፡፡ ይህም መሪውን ፍቅርና ትእግስት እንደዚሁም ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡

ሠራተኛው ላከናወነው ተግባር ሙሉ አድናቆትና ከበሬታን ሊሰጠው ይገባል፡፡ ጠንካራ ጎኑን በማበረታታት መሻሻል እንዲያደርግም ደካማ ጎኑን አስታውቀው፡፡ ከዚያም ከእርሱ የሚጠበቅበትን አስረዳው፡፡ ዐላማዎችና የሥራ መመዘኛ ይኑርህ፡፡ ግልጽ የሆነ መመሪያ መስጠትህንና የሰጠኸውን መመሪያ መረዳቱን አረጋግጥ፡፡ አብረኸው ጸልይ፡፡ ከእርሱ የምትጠብቀውንም በሚገባ እንዲረዳ አድርግ፡፡

12/ ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡ በሐቅ ላይ የተመሠረተ ዓላማ ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሀ/ የመሪውን እምነት የሚያመለክት ሐ/ ሁሉም ሰዎች የሚስማሙበት

ለ/ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ሊደረስበት የሚችል

13/ ትክክለኛውን መልስ ፊደሉን በመክበብ አመልክት፡፡ መሪው አብረውት የሚሠሩ ሰዎችን ዓላማውን ፍጻሜ ላይ እንዲደርሱ የሚረዳው እንዴት ነው?

ሀ/ ሥራው በጣም ቀላል እንደሆነ በመናገር ሐ/ ችግሮቻቸውን በመረዳት

ለ/ ጥርጥሩንና እርግጠኛ አለመሆኑን በመግለጽ

14/ እውነት በሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል ክበበው፡፡

ሀ/ በእውነታ ላይ የተመሠረተ አስተሳሰብ እምነትን ግምት ውስጥ አያስገባም

ለ/ በእውነታ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ ችግርና እንቅፋት ሊኖር እንደሚችል ይቀበላል፣ ምንነታቸውን ለማወቅ ይሞክራል፡፡ ለችግሮቹ መፍትሔ ለመሻትም የሌሎችን ጸሎትና ሃሳብ ይጠይቃል፡፡

ሐ/ በእውነታ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ፡ ሰበብን ማብዛት፣ ሰዎችን በራሳቸውም ድክመት ሌላውን ተጠያቂ እንዲያደርጉ ምክንያት መስጠት ስለሆነ በምንም ዓይነት ሰበብን ማቅረብ አይቀበልም፡፡

መ/ በሐቅ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ የሥራ መመዘኛ ያደርጋል፡ ሥራውን እንደሚገባ ላለመሥራታቸው የሚያቀርቡትን ሰበብ ይቀበላል

ሠ/ በእውነታ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ የሰዎችን ጥረት ያደንቃል፡፡ ገንቢ በሆነ ሁኔታም ብርቱ ጎናቸውንና ያሳዩትን መሻሻል ያበረታታል፡፡

## መሪነት የሚያስከፍለው ዋጋ

### ዓላማ 6 መሪነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ ለመግለጽ

መሪነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያቀርባቸው ምሳሌዎች ለመረዳት እንችላለን፡፡ የሚያስከፍለውን ዋጋ ተገቢና ቀላል የሚያደርገው ዓላማችንና ጥረታችን ሁሉ የሚያዘነብለው ወደ አንድ ዓላማ ሲሆን ነው፡፡ መንፈሳዊ መሪዎች እግዚአብሔር ለዓለም ባለው እቅድ መሠረት ምን መሠራት እንዳለበት ያውቃሉ፡፡ የእርሱም ሆነ የእነርሱ ዓላማ አንድ ቢሆንም የዓላማ መጨናገፍና ተስፋ መቁረጥ ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ በሐቅ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብን በጸሎት ለሕይወታችን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ አብዛኞዎቹን መሰናክሎች ማሸነፍ ይቻላል፡፡ ችግሮችና ግጭቶች ይኖራሉ፡፡ አስቴር እንዳደረገችው ሁሉ ሐቁን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልሆንን ውጤታማነታችን የሚያጠራጥር ይሆናል፡፡

**1/መሪዎች አገልጋዮች እንጂ ጌቶች አይደሉም፡፡** ሌላው ቀርቶ ንግድ ነክ በሆኑ ድርጅቶች እንኳ የሥራ መሪውን እንደ አለቃ መመልከት እየቀረ ነው፡፡ እቅድ የሚያወጣና ሠራተኞችን የሚያስተባብር መሪ እንደሆነ ብቻ ነው የሚታሰበው፡፡ ከብዙ ዘመናት በፊት ኢየሱስ ያስተማረውም የዚህ ዓይነቱን አመራር ነው፡፡ በዘመናት ሁሉ የነበሩ መንፈሳዊ መሪዎች ሕይወታቸውን እስከ መስጠት ድረስ ምሳሌቱን ተከትለዋል፡፡

**2/ መሪዎች ከሌሎች ይልቅ በርትተው መሥራት ይኖርባቸዋል፡-** አብዛኞቹን መሪዎች አንድ ስለሚደርጋቸው ነገር ጥናት ተደርጎ ነበር፡፡ መሪዎች የተለያዩ ብርቱ ጎኖችና የተለያዩ ስብዕናዎች እንዳሏቸው ተደርሶበታል፡፡ አንዳንዶቹ **"ሁሉንም እኔ ልሥራው"** ሲሉ፣ ሌሎች ደግሞ ከሌሎች ጋር አብረው መሥራትን ይወዳሉ፡፡ ጥናቱ እንዳረጋገጠው

ግን አንድ የጋራ ባሕርይ ብቻ አብዛኛዎችን መሪዎች ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል። ይህም ብርቱና ታታሪ ሠራተኞች መሆናቸው ነው። ብዙ ይሠራሉ፣ ብዙ ያጠናሉ፡ አብረዋቸው ከሚሠሩት ሰዎች ይልቅ ራሳቸውን ለማሻሻል ፍላጎት ስላላቸውም ብዙ ይጥራሉ።

3/ **መሪዎች ይነቀፋሉ፣ ይተቻሉ፡-** አንዳንድ ሰዎች ዓላማችንን አይረዱልንም። ስለዚህም ላይስማሙን ይችላሉ። ከዚህም በላይ ደግሞ ከስህተት የጠራን አይደለንም። ሳንፈልገው ሌሎችን ልናሳዝን እንችላለን። ራሳችንን ትክክለኛ አድርገን ለማቅረብ ብዙ ሙከራ ከማድረግ ይልቅ ይህን ሐቅ ብንቀበል፣ ከሚሰነዘርብን ነቀፋ ብዙ ልንጠቀም እንችላለን። ራሳችንን በትክክል ለማየትና አስፈላጊውን ለውጥ ለማድረግ የምንችልበትን ጸጋ ጌታ እንዲሰጠን መጠየቅ እንችላለን።

4/ **አንዳንድ መሪዎች ብቸኝነት ይሰማቸዋል፡-** በሕዝብ መካከል ስናያቸው መሪዎች የተለየ መብት ያላቸው ይመስለናል። እውነተኛ መሪዎች ግን ከማንም የበለጡ ብቸኛ ናቸው። አብዛኛዎቻችን ከሌሎች ጋር መወያየትና ሸክማችንንም ለሌሎች ማካፈል ያስደስተናል። ሥራን በተመለከተ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይህን ማድረግ ይቻላል። ከፍተኛ ውሳኔና ኃላፊነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ሲገጥመን ግን ከእግዚአብሔር በቀር ብቻችንን እንሆናለን። በቤተክርስቲያን ሥራ ቤተሰባችንና ጓደኞቻችንን ማሳተፍ የለብንም። ብቻችንን ብዙውን ጊዜና ጉልበታችንን ማጥፋት አለብን።

5/ **መሪዎች ውጥረት ይገጥማቸዋል፡-** ብዙ የሚሠራ አለ፣ በዚያው መጠን ደግሞ የጊዜ ጫና ይኖራል። ሰዎች ብዙ ይጠብቁብናል። ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው አብዛኞቹ መንፈሳዊ ሠራተኞች መካከለኛ መሪዎች ናቸው። በአንድ በኩል መሪ ናቸው፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተመሪ ናቸው፣ ይህም ያለባቸውን ጫና እጥፍ ከማድረጉም በላይ ብቁ አለመሆናቸው እንዲሰማቸው ያደርጋል፣ የተሳሳተ ውሳኔ እንዳያደርጉና እንዲፈሩ የማያወላውል አቋም ሊኖር ይገባል።

15/ ስለ መሪዎች የሚከተሉትን ተግባራዊ መግለጫዎች በራስህ ቃላት በማስታወሻ ደብተርህ ግለጽ።

ሀ/ መሪዎች አገልጋይ እንጂ ጌቶች አይደሉም

ለ/ መሪዎች ከሌሎች ይልቅ በርትተው ይሠራሉ

ሐ/ መሪዎች ነቀፌታና ትችቶች ይደርስባቸዋል

መ/ መሪዎች ብቸኞች ናቸው

ሠ/ መሪዎች ውጥረት ይደርስባቸዋል

ከትክክለኛው አስተሳሰብ ላይ የተመረኮዘ ያልነው ጉዳይ መንፈሳዊ ዓላማዎች ሊገጥማቸው የሚችለውን ችግርና መሰናክል የመረዳትን አስፈላጊነት የሚያመልክት ሲሆን፣ ኃላፊነትን መቀበል የምንችለው የሚጠበቅብንን እንደሚገባ ስናውቅ ነው። ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለመስጠት ፈቃደኛ ባልሆንበት ነገርና ብቃት እንደሌለን በምናስበው ነገር መሳተፍ አንፈልግም። አስቴር እንደተናገረችው፡- **ሥራው ምንም ያህል ትልቅ ቢሆንም ራሴን ሙሉ በሙሉ እሰጣለሁ። ማንኛውንም ውጤት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ** ለማለት መቻል አለብን።

16/ ስለመሪነት ከተመለከትናቸው አምስት ሐቆች በመሪዎች ላይ የሚደርሱ ችግሮች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። መሪነት ከባድ ሥራ እና ራስን መግዛት የሚጠይቅ ነው። ትችትና ነቀፌታ ሊኖር ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ዓላማችንን ስለማይረዱ ብቸኝነትና ውጥረት ይገጥማል። ከአስቴር ታሪክ እንደተመለከትነው፣ አስቴር ማንኛውንም ችግር ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነች፣ መሪ እንደመሆንህ መጠን ለምን ከመሪነት ችግር ጋር ለመጋፈጥ ፈቃደኛ እንደሆንህ በማስታወሻ ደብተርህ ግለጽ።

**የሙከራ ፈተና**

1/ ከአስቴር ታሪክ የተመለከትነው የመሪነት ምሳሌ፣

ሀ/ መሪዎች ልዩ ስብዕና ያላቸው እንደሆኑ

ለ/ ለግል ችግራቸው መፍትሔ ለመሻት እንደሚነሱ

ሐ/ ለችግር መፍትሔ ለመሻት እንደሚነሱ

መ/ ያላቸውን ታዋቂነትና ተቀባይነት መሠረት በማድረግ እንደሚነሱ ተመልክተናል።

2/ ወደ ንጉሡ እሄዳለሁ፣ ብጠፋም እጠፋለሁ ስትል አስቴር የትኛውን የተዋጣለት የመሪነት ባሕርይ ማሳየቷ ነበር?

ሀ/ መሪዎች በትላልቅ ዓላማዎች ይሳተፋሉ።

ለ/ ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍልም መሪዎች ኃላፊነትን ይቀበላሉ

ሐ/ መሪዎች ግብ ላይ ለመድረስ በርትተው ይሠራሉ

መ/ መሪዎች ችግር ሲደርስባቸው ብቻቸውን ለመቆም ፈቃደኛ ናቸው

3/ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር አስቴር በተግባር ያሳየቻቸው የእውነተኛ መሪ አሰራር ናቸው። ከእውነተኛ መሪዎች አሠራር አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ አንድ መሪ ሥልጣን የሚይዘው ለሕዝቡ ጥቅም ነው

ለ/ አንድ መሪ ሕዝቡን ያሳትፋል፣ ድጋፋቸውን ይጠይቃል፣ ማንኛውንም መረጃ ያካፍላቸዋል፡፡

ሐ/ አንድ መሪ ለሚገጥሙት ሁኔታዎች ሁሉ ቅደም ተከተል ያደርጋል

መ/ አንድ መሪ ደፋርና ወሳኝ ስለሆነ በፍጥነት እርምጃ ይወስዳል

4/ የአስቴር የመጨረሻ ዓላማ ማዳን ነበር፣ እንዲህ ዓይነቱን ዓላማ፡-

ሀ/ ማጠቃለያ ዓላማ ሐ/ መንደርደሪያ ዓላማ

ለ/ መንደርደሪያ ዓላማ መ/ ሌሎችን የመቀስቀስ ዓላማ እንለዋለን፡፡

5/ ወደ መጨረሻ ዓላማዋ ከመድረሷ በፊት አስቴር በተለያዩ ዓላማዎች አልፋለች፣ እነዚህን ዓላማዎች፡-

ሀ/ የመቋጫ ዓላማዎች ሐ/ ድርጅታዊ ዓላማዎች

ለ/ ማጠቃለያ ዓላማዎች መ/ የመንደርደሪያ ዓላማዎች እንላቸዋለን፡፡

6/ ከትምህርታችን እንደተመለከትነው ሁሉ ከአንዱ በቀር ዓላማን ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ ዓላማን ማኖር ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ያለ አግባብ ከማባከን ያድነናል፡፡

ለ/ ዓላማን ማኖር ሌሎች እንዲተባበሩንና ሥራው ለመመዘን ይረዳል

ሐ/ ባጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ለመሥራት ያስችላል

8/ አንድ መሪ እውነተኛውን የቤተክርስቲያን ዓላማ ሲረዳና ራሱን ሙሉ በሙሉ ሲሰጥ፡-

ሀ/ በእውነታ ላይ የተመረኮዘ አስተሳሰብ አለው ይባላል

ለ/ ኃላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ ሆኗል ይባላል

ሐ/ ለሌሎች እውቅና ስጥቷል ይባላል መ/ ተገቢ ምላሽ ስጦታል ይባላል

9/ የሚያስከትለውን ችግርና መሰናክል በመገንዘብ ክርስቲያን መሪዎች የሚያስቀምጡት ዓላማ፡-

ሀ/ ሁሉም ይቻላል ብሎ ማሰብ ሐ/ በሐቅ ላይ የተመሠረተ አሰተሳሰብ

ለ/ ራሱም ሆነ ሠራተኛው ከኃላፊነት እንዲሸሽ ማድረጉ ነው

ሐ/ ደግነት ከኃላፊነት ይልቅ አስፈላጊ እንደሆነ እያሳየ ነው

መ/ ፍቅር ሐቅን ከመጋፈጥ ይልቅ አስፈላጊ እንደሆነ እያሳየ ነው

11/ ቀጥሎ ያሉትን ቁጥሮች ከትክክለኛው ዐረፍተ ነገሮች ጋር ለማዛመድ ከ1-5 ያሉትን ቁጥሮች በባዶ ሥፍራው አስቀምጥ፡-

1) መሪዎች አገልጋይ እንጂ ጌቶች አይደሉም

2) መሪዎች ከሌሎች ይልቅ በርትተው ይሠራሉ

3) መሪዎች ነቀፌታና ችግር ይደርስባቸዋል

4) መሪዎች ብቸኞች ናቸው

5) መሪዎች ውጥረት ይኖራቸዋል

---ሀ/ መሪው በጌታ መታመንና፣ ምሪት ማግኘት እንዳለበት ያውቃል

---ለ/ በሥራው እንቅስቃሴ መሪው ረዳትና መመሪያ ሰጪ ነው

--ሐ/ አንዳንድ ጊዜ መሪው ሰዎች ዓላማውን ሊረዱለት እንደማይችሉ ያውቃል፣ ስለዚህም ሰዎች ለእርሱ ላላቸው አመለካከት ብዙ ግምት አይሰጥም

--መ/ መሪው ውጥረት ይደርስበታል፣ ይሁን እንጂ ሥራው የጌታ እንደመሆኑ መጠን ጌታ ብርታቱን እንደሚሰጠው ያውቃል

---ሠ/ በሚቻለው ሁሉ ለሌሎች ምሳሌ መሆን እንዲችል መሪው ሙሉ በሙሉ ራሱን መስጠት እንዳለበት ይገነዘባል

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

9/ ብጠፋም እጠፋለሁ

1/ሀ)3) ግብ  ለ/1) የመሪነት ባሕርያት ሐ/ለ) ግብ  መ/2) ሥራ  ሠ/2) ሥራ ረ/1) የመሪነት ባሕርያት ሰ/1) የመሪነት ባሕርያት ሸ/1) የመሪነት ባሕርያት

10/ ሀ) እና ሐ) ትክክል ናቸው። ለ) ግን ተነጻጻሪ ነው። ርብቃ ሙሉ ለሙሉ ራሷን አልሰጠችምና እውነተኛ ነፃነት አይኖራትም። መ/ ኃላፊነትን ላለመቀበል ሰለሚቀርብ ሰበብ አይነተኛ ምሳሌ። እግዚአብሔር የሚጠራን ብቁ ስለሆንን አይደለም። ግን ብቁ ስለሆንን አይደለም የሚጠራን። ብቁ ሊያደርገን ይጠራናል። ምንጊዜም ይህን አስታውስ። ወንጌል ያልደረሳቸው ብዙዎች ናቸው።

11/ ለነዚህ አስራ ሁለት ጥያቄዎች ያገኘኸውን በ24 እና 36 መካከል ከሆነ እውነተኛ መሪ ማድረግ የሚገቡትን ነገሮች ማድረግ አለብህ። ውጤትህ ከ24 በታች ከሆነ ግን ዝርዝሮቹን እንደገና አንብብ። በእግዚአብሔር ጸጋ ራስህን ለማሻሻል ሞክር።

3/ ችግሩን ይረዳል፣ ሥራውን የሚሰራ መሪም ይፈልጋል

12/ለ) በተጨባጭ ሁኔታ የሚደርስበት

-4/ መልስህ በበኩሌ ግን የዚያን አካባቢ ሰዎች ጌታን እንዲቀበሉ መርዳትና የሚያመልኩበትን ሥፍራ ማዘጋጀት የሚል መልስ ሰጥቻለሁ።

13/ሀ) ችግሮቻቸውን በመረዳት

5/ ምናልባትም መልስህ፡- 1) አካባቢውን የሚጎበኙ ቡድኖች ማደራጀት

2/ ስለግንባታው የሚነጋገር ኮሚቴ ማቋቋም የሚሉትን ያጠቃልል ይሆናል፡፡

14/ "ሀ" እውነት "ለ" ሐሰት "ሐ" እውነት "መ" ሐሰት "ሠ" እውነት

6/ ለ) ከግቦቻችን አንዱ ስድስት መስኮቶች መጠገን ነው

15/ መልሶችህ ከእኔ መልሶች የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በበኩሌ ያቀርብኳቸው መልሶች፡-

ሀ/ ራሴን ሁኔታዎችን እንደሚያመቻች ሰው እንጂ እንደተመልካች አላየውም

ለ/ ለሥራው ራሴን በመስጠት፣ ጊዜን በማክበርና በሌሎችም ምሳሌ እሆናለሁ

ሐ/ ሰዎች ዓላማዬን ባለመረዳት ሊነቅፉኝና ሊተቹኝ ይችላሉ፡፡ ስሕተቱ የእኔ ከሆነ ራሴን የማስተካክልበትን ጸጋ ጌታ እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ

መ/ ብቸኝነት ቢሰማኝም፣ ከጌታ ጋር ያለኝን ሕብረት በማጥበቅ አሸንፋለሁ

ሠ/ የሥራ ብዛት ውጥረት ቢያመጣብኝም፣ የሚደረስብኝ ውጥረት ብዙ ወደ ጌታ እንዲያቀርበኝ እንጂ ተስፋ ሊያስቆርጠኝ አልፈቅድም፡፡

7/ሀ) እና ሐ) ትክክል ናቸው

16/ መልስህ ፡፡ ብዙዎች እንደሚስማሙበት መሪነትን የተቀበሉት የጌታ ሥራ ራዕይ ሰላላቸው፣ ሌሎችን በወንጌል ለመድረስና ፍቅር ስላላቸው **"ማንን እልካለሁ?"** (ኢሳ 6፡8) ለሚለው የእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ለመስጠት፣ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ግብ ለመፈጸም ነው፡፡ ምንም እንኳ የተለየዩ ችግር ቢገጥማቸው ራሳቸውንም በመስጠታቸው እውነተኛ ነፃነት ያገኙበታል፡፡ ከዚህም በላይ በራስ መተማመን አላቸው፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያደርጋቸውም በጌታ ያላቸው እምነት ነው

8/ሐ) መልካም ግብ ሥራን እንደሚገባ ለማከናወን ይረዳል፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

## ዓላማን እግብ ለማድረስ የሚደረግ ጥረት

በሰባተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ መሪዎች እንዴት ኃላፊነት እንደሚቀበሉ ለመገንዘብ ይረዳን ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ የአስቴርን ምሳሌት በመከተል ኃላፊነትን መቀበል ማለት ምን እንደሆነ ከመመልከታችን በላይ ስለ ዓላማዎች ባሕርይና ዓላማዎችን እግብ ማድረስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

በዚህ በስምንተኛው ክፍለ ትምህርት ላይ ደግሞ የሐዋርያው ጴጥሮስን ምሳሌነት በመከተል በመንፈሳዊ ሥራ ሥርዓታዊ አቀራረብ ማለት ምን እንደሆነና ስለ ዓላማዎች ባሕርያት እንደዚሁም ዓላማዎችን እግብ ለማድረስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

**የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል**

- የጴጥሮስ ምሳሌት
- ሥርዓት ያለው መንፈሳዊ ሥራ
- ዓላማዎችን በመከተል ሥራን መምራት

---------------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች**

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ ከዚህ በታች የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፡፡

- የጴጥሮስን ታሪክ መሠረት በማድረግ ስለ መሪነት የምትረዳውን እንዴት በሕይወትና ተግባራዊ እንደምታደርገው መግለጽ፡፡
- በክርስቲያን አሠራር ስልታዊ አቀራረብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትማራለህ፡፡
- ግቦችህ ላይ የምትደርስበትን እቅድ ዝርዝር እንዴት እንደምታወጣና እንዴት ተግባራዊ እንደምታደርጋቸውም ትማራለህ፡፡

----------------------------------------------------------

## የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ሉቃስ 22፡24-32፣ ዮሐንስ 21፡15-22 እና 1ኛ ጴጥ 5፡1-4 አንብብ
2. በተለመደው ሁኔታ ለጥያቄዎቹ መልስ ስጥ
3. በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት መልሶች ጋር መልሶችህን አስተያይ

## የጴጥሮስ ምሳሌት

### ዓላማ 1 ኢየሱስ ለጴጥሮስ የሰጠውን መመሪያ በሚገባ መረዳት

የዚህ ትምህርት መሠረታዊ እውነት ክርስቲያናዊ አመራር ማለት የእግዚአብሔርን ዓላማ ይፈጽሙ ዘንድ ሰዎችን መረዳት ነው፡፡ ይህን እውነት ከየትኛውም ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በነበረው መቀራረብ ታይቷል፡፡ አብዛኞቹ የነገራቸው ነገሮች ሁለት ትርጉም አላቸው፡፡ የመጀመሪያው ለራሳቸው ለደቀመዛሙርቱ ሲሆን ሁለተኛው ግን ወንጌሉ ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ ሌሎችን ለማስተማር እንዲበቁ ለመርዳት ነው፡፡ ለዚህም ምሳሌ ከሚሆኑን አንዱ ሉቃስ 22 ነው፡፡

ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሚሞትበት ጊዜ ተቃርቧል፣ ይህም ለእርሱና ለደቀመዛሙርቱ ከፍተኛ የልብ ስብራት ቢሆንም ይበልጥ ያሳሰበው የእግዚአብሔር መንግሥት የወደፊት ሁኔታ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ለጴጥሮስ ለየት ያለ ፍቅር ቢኖረውም በኃላፊነት መጠራቱን ግን እንዲዘነጉ አላደረገም፡፡ በዚህ በመጨረሻው ሰዓት ደቀመዛሙርቱ ከመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ መከራከራቸው የሚገርምና የሚያሳዝን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር በእንደዚህ ዓይነት ሰዎች እንኳ መጠቀም እንደሚችል ያመለክታልና ጠቅሞናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይነተኛ የክርስቲያናዊ አመራር ምሳሌ አድርጎ ጴጥሮስን ተጠቅሞበታል፡፡

ጴጥሮስ በራሱ በጣም የሚተማመን ሰው ነበር፡፡ ለክርስቶስ ታማኝ መሆኑንና ከሌሎች አብልጦ እንደሚወደውም በድፍረት ተናግሯል፡፡ ይሁን እንጂ በራስ መተማመን ብቻውን የእውነተኛ ጥንካሬ ማስረጃ ሊሆን እንደማይችል ጨዋነት በተሞላ መንገድ ኢየሱስ ለጴጥሮስ አስረድቶታል፡፡ በአንድ ወቅት በሰይጣን እንደሚፈተንና እንደሚወድቅ ነግሮታል፡፡ ***"እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፣ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና"*** (ሉቃስ 22፡32) አለው፡፡ ከዚህ ጥቅስ ስለ አመራር ሁለት ዋና ዋና ትምህርቶችን እናገኛለን፡፡ በመጀመሪያ ከሚገባ በላይ በራስ መተማመን አደገኛ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የግል የሕይወት ተሞክሯችን ሌሎችን

ለማስተማር እንድንጠቀምበት የሚያሳስብ ነው፡፡ ትምህርት የምናገኝበትና ሌሎችን ለመጥቀም የምናውለው ከሆነ ውድቀት ራሱ እንኳ በረከት ነው፡፡

ኢየሱስ እንደተናገረው ጴጥሮስ በሠይጣን ወጥመድ ወደቀ፡፡ ምንም እንኳ እንደሰውነቱ ደካማ ቢሆንም ኢየሱስን በጣም ይወድዳል፡፡ ከውርደትና ከጸጸት ነበር የተማረው፡፡ ከዚያ በኂላ ደግሞ እምነትና ፍቅሩን ለሌሎች ለማካፈል ጽኑ ፍላጎት አደረበት፡፡ ኢየሱስም ይህን አጋጣሚ ይበልጥ ስለጥሪው ለጴጥሮስ ለማስተማር ተጠቅሞበታል፡፡ (ዮሐ 21፡15፡17) ተመልከት፡፡

**"ትወደኛለህን?"** በማለት ኢየሱስ ጠየቀው

**"አዎን ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ"** አለ ጴጥሮስ

ኢየሱስም **"ግልገሎቼን አሰማራ"** አለው፡፡

ኢየሱስ ጥያቄውን ሦስት ጊዜ ደጋግሞታል፡፡ ጴጥሮስ ደግሞ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጠው መልስ አንድ አይነት ነበር፣ እንደሚወደው ጴጥሮስ በነገረው በእያንዳንዱ ጊዜ ደግሞ የተለያየ ሥራ ይሰጠው ነበር፡፡ **"የምትወደኝ ከሆነ ግልግሎቼን አሰማራ፣ በጎቼን አሰማራ"** አለው፡፡ ፍቅር በጴጥሮስ ላይ ምን እንዳስከተለበት እናስብ፡፡

የመጠራት ዋናው ዓላማ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም እንደሆነ እስካሁን ከተመለከትናቸው ምሳሌዎች ተረድተናል፡፡ በጎቹን እንዲያሰማራ ኢየሱስ የነገረውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ የደህንነት እቅድን በተመለከተ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን ፈጽሟል፡፡ አስቀድመን እንደተመለከትነው የእግዚአብሔር ዓላማ ቤተክርስቲያንን መመሥረትና ኢየሱስ የጀመረው ሥራ ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ነበር፡፡ በዚህ ታላቅ እቅድ ውስጥ ሥራን በመስጠት ኢየሱስ ለጴጥሮስ ፍቅሩን ገለጸለት፡፡ ሥራውን በመቀበል ደግሞ ጴጥሮስ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ገለጸ፡፡

ኢየሱስ ለጴጥሮስ የተናገረው በምሳሌያዊ መንገድ ነበር፡፡ ግልገሎችና በጎች ሲል ስለሰዎች መናገሩ ነበር፡፡ **"አሰማራ"** ሲል ደግሞ ሰዎችን ስለ መርዳትና ማስተማር መናገሩ ነበር፡፡ ምሳሌያዊ ቋንቋ በመጠቀም በጣም ሰፊ የሆነውን መልእክት በአጭሩ አቀረበለት፡፡ እስቲ ስለእነዚህ ቃላት ትርጉም ሰፋ ባለ መልክ እንመልከት፡፡

1-4/ ትክክለኛ መልስ መሆን የሚችለውን ፊደሉን በመክበብ አመልክት

1/ ኢየሱስ በጎቼን አሰማራ ሲል ምን ማለቱ ነበር?

ሀ/ የተራቡ ሰዎችን አስብ

ለ/ ለቤተክርስቲያን ሥራዎች ሁሉ ኃላፊነት ይኑርህ

ሐ/ መንፈሳዊ ችግር ያለባቸውን አስተምራቸው፣ ምራቸው

2/ ለምንድነው ኢየሱስ በጎችን እንዲያስማራ ለጴጥሮስ የነገረው?

ሀ) ሰዎች የተራቡ በጎችን ያህል ችግር ስለነበረባቸው

ለ) ከሌሎች ይልቅ ጴጥሮስ ቃሉን ስለሚያውቅ

ሐ) ጴጥሮስ ከሌሎች ይልቅ ኢየሱስን ስለሚወድድ

3/ ለምንድነው ጴጥሮስ በጎቹን እንዲያስማራ ፈቃደኛ የሆነው?

ሀ/ ችሎታውን ለማሳየት ስለፈለገ   ሐ/ ኢየሱስን ስለሚወድ

ለ/ ያለፈ ውድቀቱን ለማስተካከል ስለፈለገ

4/ ግልገሎችና በጎችን እንዲያስማራ ኢየሱስ ለጴጥሮስ ሲነግረው ምን ዓላማ ነበረው?

ሀ/ ደቀመዛሙርቱ ደስታና እርካታ እንዲኖራቸው

ለ/ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለጴጥሮስ ኃላፊነትን መስጠት

ሐ/ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን ዓላማ መፈጸም

**ለሽማግሌዎች የሰጠው መመሪያ**

**ዓላማ 2 ጴጥሮስ ለሽማግሌዎች የሰጠው መመሪያ እርሱ ራሱ ከኢየሱስ የተማረው እንደሆነ ለመግለጽ**

ጴጥሮስ የጻፈውን መልእክት ስናነብ የምንረዳው በጠቅላላው ምን ያህል ለሌሎች ሰዎች ችግር ያስብ እንደነበር ነው። አቀራረቡ የአንድ መልካም መጋቢን ያህል ሞቅ ያለ ከመሆኑም በላይ ከኢየሱስ የተማረውን ትምህርት በሚገባ የተረዳ መሆኑን ያመለክታል። በብዙ መንገድ ማየት እንደሚቻለው የኢየሱስን ትምህርቶች የአገልግሎቱ አካል አድርጓቸዋል። ለዚህ ማስረጃ ከሚሆኑን ምሳሌዎች አንዱ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሰጠው መመሪያ ሲሆን፣ ለኢየሱስ ትምህርት ታዛዥ መሆኑንና ክርስቲያናዊ አመራርንም በሚገባ ለመረዳቱ ማስረጃ ናቸው።

**1/ የትሕትና ሕይወቱ**

ጴጥሮስ ሐዋርያ ከመሆኑም ሌላ ከሐዋርያት ዋናው የተባለ ቢሆንም፡- **“ከነርሱ ጋር ሽማግሌ የሆንሁ”** በማለት ራሱን በመጥራት መመሪያ ከሚሰጣቸው ሰዎች እንደ አንዱ እንጂ ራሱን የበላያቸው አድርጎ አልቆጠረም። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ለመንጋው ምሳሌ እንደ ሆኑ ሲነግራቸውም ይህንኑ ነበር አጥብቆ ያሳሰባቸው። ምሳሌ የመሆን

ዋናው ዓላማ ሌሎች መሪውን እንዲመስሉ መርዳት ነው፡፡ ይህም መሪውን ከተከታዮቹ ጋር በበለጠ ያቀርበዋል፡፡

**2/ የሌሎች ችግር መረዳት**

በዕብራውያንም ሆነ በግሪክ ማሕበረሰብ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሥራ ለሌሎች ችግር ማሰብ ነው፡፡ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሥራ ፍትሕና ገንዘብ ነክ የመሳሰሉ የሕብረተሰቡን ጉዳዮች ማስተዳደር ነው፡፡ አስተዳዳሪም አስተማሪም ናቸው፡፡ ይህ አሰራር ገና ከመጀመሪያው አንስቶ የቤተክርስቲያን አስተዳደር አካል ሆኗል፡፡ ጴጥሮስ ራሱን የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ብሎ መጥራቱ ለሌሎች ችግር ማሰብ እንደ ሌሎቹ ሁሉ የእርሱም ኃላፊነት መሆኑን መናገሩ ነው፡፡ ጴጥሮስ የነበረው ታላቅ ስደት በነበረበት ጊዜ እንደሆነና በዚያን ወቅት ደግሞ የመምህራኑ ቁጥር በጣም ጥቂት እንደነበር እናውቃለን፡፡ መሪዎች የመጋቢ ዓይነት ዝንባሌ ሊኖራቸው ይገባል፤፡ ትጉ ሠራተኞችና ጨዋዎችም መሆን አለባቸው፡፡ ***"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ"*** አላቸው፡፡

**3/ መንጋው የእግዚአብሔር መሆኑን መረዳቱ**

ሕዝቡ የእግዚአብሔር መንጋ መሆናቸውን ጴጥሮስ አበክሮ ተናግሯል፤፡ መንጋው ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በታች እንዲሆን ያደረገውም እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር "**መንጋዎቹ ክርስቶስ ሕይወቱን የሰጠላቸው ሰዎች እንደሆኑ ካሰባችሁ ልዩ ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ፡ ኃላፊነትም ይሰማችኋል**" ማለቱ ነበር፡፡ **በእናንተ ዘንድ ያለውን ማለትም በአደራነት የተቀበላችሁትን** የሚለውን ዓረፍተ ነገር ልብ ልንለው ይገባል፡፡ ጴጥሮስ እንደዚህ ሲል **ለችግሮቻቸው ሁሉ ጥንቃቄ እንድታደርጉላቸው በአደራ ሕዝቡን የሰጣችሁ እግዚአብሔር ነው** ማለቱ ነበር፡፡ እኛ መሪዎችም ሆንን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መንጋውን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ታላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ባርክሌይ "**እግዚአብሔር ሥራ ሰጥቶናል፤ የሰጠንንም ሥራ ልክ እርሱ ራሱ እንደሚሰራው ዓይነት ሆነን ልንሰራው ይገባል፡፡ የቤተክርስቲያን ዐቢይ አገልግሎትም ይኸው ነው**" ብሏል፡፡

**4/ ለአገልግሎት መገፋፋቱ**

የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በፈቃደኝነት እንዲያገለግሉ ጴጥሮስ ይናገራል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ምንም አዳጋች መስሎ ቢታይም ከአገልግሎት መሸሽ የለባቸውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ አገልግሎትን እንደ አንድ ዓይነት ከባድ ጫና ሊመለከቱት አይገባም፡፡ በሦስተኛ ደረጃ የሚያገኙትን ጥቅም ተስፋ በማድረግ ማገልገል የለባቸውም፡፡ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ለገንዘብ፣ ለሥልጣን፣ ለታዋቂነትና የተለየዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት መስገብገብ የለበትም፡፡ አንዳንድ ጊዜ የቤተክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ ሥልጣንን ለመያዝ ያላቸው ምኞት ገንዘብን ለማግኘት ከሚኖራቸው ምኞት ይልቅ አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ መሪ ልቡን ተወዳጅነትና ዝነኝነት ላይ ካደረገ ዋናው ዓላማው ከሆነው ለሰዎች ከመጠንቀቅ ሥራው ይዘናጋል፡፡ መሪነት ለግል ጥቅም የምናውለው ጉዳይ አይደለም፡፡ ክብር ስላለን ወይም ከሌሎች ስለበለጥን የምናገኘው ሀብትም አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ኃላፊነትና ፍቅራችንንም በተግባር የምንገልጽበት መንገድ ነው፡፡

**5/ ዓላማውን መገንዘቡ**

ጴጥሮስ አንድ መድረሻ ዓላማ እንደነበረው ከጽሑፎቹ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ ይህም ዓላማ ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ የሆኑትን ለመቀበል በሚገለጥበት ቀን ዝግጁ ሆኖ መገኘት ነው፣ **"የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ ---------"** በአደራ መልክ ሰጥቷቸው የነበሩ መንጋዎቹን ይቀበላል፡፡ በዚያን ጊዜ ***"የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ"*** ይላቸዋል፡፡

5. በክፍቱ ቦታ ቁጥሩን በማስፈር አብረው የሚሄዱትን አመልክት፡፡

1/ራስን ትሁት ማድረግ 2) ችግርን መረዳት 4) ትክክለኛ መነሣሣት

3/ መንጋዎቹ የእግዚአብሔር ናቸው 5) ዓላማን መገንዘብ

---ሀ/ ኢየሱስ በጎችን እንዲያሰማራ ለጴጥሮስ ተናገረ

--- ለ/ ኢየሱስ፡- **ትወደኛለህን?** በማለት ጴጥሮስን ጠየቀው

----ሐ/ የሰው ልጅ በማታስቡበት ጊዜ ይመጣልና----"

---መ/ ኢየሱስ፡- **በጎቼ** በማለት ተናገረ

---ሠ/ እንደሚክደው ኢየሱስ ለጴጥሮስ ነገረው

6/ በምሳሌያዊ አነጋገር አማካይነት ኢየሱስ የመሪነትን እውነተኛ ዓላማ ነገረው እንጂ እንዲሁ በደፈናው **ታላቅ መሪ ሁን አላለውም**፣ ያለው፡-

ሀ/ -----------------------------------------------------------------------------------------------

ለ/ ጴጥሮስ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በተመሳሳይ ምሳሌያዊ አነጋገር በመጠቀም ሲናገር-------------------------------

# ሥርዓታዊ አቀራረብ

**ዓላማ 3 ስለ ሥርዓታዊ አቀራረብ መግለጫ ለመስጠት**

ከትምህርቱ ስለዓላማዎች ግቦችና ተደጋግሞም ስለ ችግሮች ተመልክተሀል፡፡ ስለ አመራር ባደረግነው ጥናት እንዴት እንደተጠቀምንባቸውም አይተሃል፣፡ አሁን ደግሞ ሰፋ ባለ መልክ እንመለከታቸዋለን፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ ምን ያህል እርስ በርስ የተያያዙ መሆናቸውንም እናያለን፡፡ በትምሕርት ሰባት ስለ ዓላማዎች (ግቦች) ባሕርይና ጥቅም ተወያይተናል፡፡ በዚህ ትምህርት መሪዎች እንዴት ዓላማዎችን እንደሚያደርጉና ከሰዎች ጋር አብረው ሲሰሩም እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው እናያለን፡፡

**ሥርዓታዊ አቀራረብ**

ስልታዊ አቀራረብ ስንል የአንድን ድርጅት ወይም ማዕከል የሥራ እንቅስቃሴ በቅደም ተከተል የምንቆጣጠርበት ሥርዓት ማለታችን ነው፡፡ አብዛኞቹ መሪዎች የመርሐ ግብሮችን እቅድ በማውጣትና ሰዎችን በሥራ ለማሳተፍ ይሰራሉ፡፡ ከነርሱም ጥቂቶቹ **"ያከናወንነው ምንድነው?" "ጥረታችንና ድካማችንስ ምን ውጤት አስገኝቷል?"** በማለት ይጠይቃሉ፡፡

ድርጅቶች በሁለት መንገድ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ እንደ ድርጅትነቱ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ይሰራሉ፡፡ አትራፊና ውጤታማ ለመሆን ይጥራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የትኛው ሥራ ድርጅቱን ቀጣይነት እንዲኖረው እንደሚረዳና የትኛው ሥራ ሰዎችን እንደሚጠቅም መለየቱ ላይ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ግራ ይጋባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ አዲስ ፕሮጀክት ይጀምራሉ፣፡ ወይም ለእሁድ ት/ቤት የሚሆኑ ጽሑፎችን ካዘዙ በኂላ ለቤተክርስቲያን ምንም እንደማይጠቅም ይገምታሉ፡፡ ለምን? ምክንያቱም ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚጣጣም ወይም ዓላማው ምን እንደሆነ ከመረዳታቸው በፊት እያንዳንዱን የሥራ እንቅስቃሴ በተናጠል በመመልከታቸው ነው፡፡

ከእነዚህ መሪዎች አንዳንዶቹ የቤተክርስቲያንን እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ መረዳት ቢችሉ ሥራቸውም ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ያስባሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች ለንግድ ነክ እንቅስቃሴዎች፣ ለድርጅቶችና ለትምሕርት ተቋማት ብቻ እንደሚጠቅሙ ያስባሉ፡፡

በቅርቡ ክርስቲያናዊ ድርጅቶችን አስመልክቶ እንደዚህ ዓይነት ጥናቶች ተደርገው ነበር። በእያንዳንዱ ሁኔታዎች ውጤቶች ተመሳሳይ ሆነው ተገኝተዋል። አቢይ ማጠቃለያ ሆኖ የተገኘውም እያንዳንዱ እንቅስቃሴ መጀመርን ወይም መሠረትን የሚጠይቅ ሆኖ መገኘቱ ነው። ይህ እንቅስቃሴ ሂደት ይባላል። ከዚህ ሂደት አንድ ዓይነት ውጤት ይገኛል። ስለዚህም እያንዳንዱ ድርጅት ሂደትና ውጤት ይኖረዋል ማለት ነው።

እንግዲህ መልካም ውጤት ለማግኘት መልካም ሂደት ያስፈልጋል ማለት ነው። ቀጥሎ ያለው ማጠቃለያ ደግሞ አንድ መሪ የሥራው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ካላወቀ በቀር ሂደትን መቆጣጠር ወይም ማወቅ አይችልም ማለት ነው።

ይህን በተብራራ መልኩ ለማየት እንዲያስችለን እስቲ የእለት ከእለት ጉዳይ የሆነውን ወጥ መሥራትን እንመልከት። ለወጡ የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ድስት ውስጥ ይጨመራሉ፣ በሂደት ይቀላቀላሉ፡ መብሰል ያስፈልጋቸዋል፣ ውጤቱም ወጥ ይሆናል። እንግዲህ ምን ዓይነት ነገሮች እንደሚያስፈልጉ ለማወቅ ወጥ ቤቱ ምን ዓይነት ምግብ እንደሚሰራ ማወቅ አለበት ማለት ነው። ዳቦ የተለያዩ ነገሮች ድብልቅና ሂደት ውጤት ነው። ሾርባ ደግሞ የተለያዩ ድብልቆችና ሂደት ውጤት ነው።

አብዛኛዎቹ ወጥቤቶች የሚፈለገውን ውጤት ያውቃሉ። የሚፈለገው ዳቦ ይሁን ሾርባ ያውቃሉ። ስለዚህም ትክክለኛውን ድብልቆችና ትክክለኛውን ሂደት ያውቃሉ። በጣም የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ መሪዎች ትክክለኛ ግባቸውን ስለማያውቁ ትክክለኛና አስፈላጊ ነገሮችን አለማወቃቸው ነው። ግባቸውን ሳያውቁ እቅድ ያወጣሉ፣ እንቅስቃሴ ይጀምራሉ።

በዚህ ትምህርት መጀመሪያ ስለተመለከትነው የሚካኤል ምሳሌትን አስብ። ጥሩ የትምሕርት መሣሪያዎችና ጥናት እንደሚያስፈልግ ያምናል። መልእክት ለማዘጋጀትም እቅድ አለው። ውጤቱ ምን እንደሚሆን ግን አያውቅም። ትኩረቱ መልእክቱ ላይ እንጂ መልእክቱ እንዲደርሳቸው የሚፈለጉት ሰዎች ላይ አይደለም። ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴን ልክ እንደ አንድ ድርጅት ብንመለከተው ኖሮ ግን እንዲህ ዓይነቱን ስህተት ማስወገድ በተቻለ ነበር። ግልጽ ግብ ይኖራል፣፡ እዚያ ግብ

ለመድረስ የሚያስችሉ ነገሮችን እንመርጣለን። ክርስቲያናዊ ሥራን እንደ ስልት የምንወስድበት የተሻለና የበለጠ ምክንያት አለ። ክፍሎቹም የሚከተሉት ናቸው።

1/ **ከፍተኛ ግብ፡-** ግቡ ከፍተኛውን የእግዚአብሔር ዓላማ በቤተክርስቲያን አማካይነት መፈጸም ነው።

2/ **መቀራረብ፡-** ክርስቲያናዊ አመራር ከሰዎች ጋር መቀራረብን ይጠይቃል። ከክርስቶስ ጋር ካለን መቀራረብ የተነሳ ከሌሎች መሪዎች፣ ከአማኞችና በክርስቶስ ወንጌል ልንደርሳቸው ከምንፈልጋቸው ሰዎች ጋር ጥሩ መቀራረብ ይኖረናል። የተዋጣለት መሪ ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነትና መቀራረብ ሊኖረው ይገባል።

3/ **ችግር ወይም የጎደለ ነገር፡-** አሁን ባለንበት ሁኔታና ወደፊት ልንደርስበት በምንፈልገው ግብ መካከል ያለው አለመጣጣም ችግር ወይም የጎደለ ነገር ይባላል። ችግር ስላለ ነው የመሪዎች መኖርም አስፈላጊ የሚሆነው። አንድ መሪ ስለአንድ የሥራ እንቅስቃሴ እቅድ ሲያወጣ ለሰዎች ስለሚሰጠው ጠቀሜታ ማሰብ ይኖርበታል። ችግሩ ወይም የጎደለው ነገር ምንድነው? የምናደርገው እንቅስቃሴ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ችግሩን መፍታት ወይም የጎደለውን ነገር መሙላት ይችላል? በማለት መጠየቅ አለበት።

4/ **ዓላማዎች፡-** ትኩረታችን የሚያነጣጥርባቸው ጉዳዩች ዓላማዎች ይባላሉ። ዓላማዎች የሥራችን ውጤት ምን መሆን እንዳለበት ያለን ምኞት እንጂ፣ ልናደርግ የምንፈልጋቸው ነገሮች አይደሉም። ለምሳሌ ያህል ስብሰባ ማዘጋጀት ዓላማዎቹ አይደለም። ዓላማችን አንዳንድ ጉዳዩችን አስመልክቶ እልባት ለመስጠት ከስብሰባ እሚገኘው ውጤት ነው።

5/ **ተግባራት፡-** ተግባራት የምንላቸው ዓላማዎቻችንን ለመምታት የምናደርጋቸው ሥራ እንቅስቃሴዎች ናቸው። እቅዶቻችን የሚያካትቱ ሂደቶች ናቸው። መሪውና ሥራ የሚያካፍሉ ሌሎች ሰዎች የሚያከናውኗቸው ተግባሮች አሉ።

6/ **ግምገማ፡-** እያንዳንዱ ሥራ የራሱ ግምገማ አለው። ይህም ውጤቱን የምንለካበት መሠረት ነው። ዓላማዎቻችንን መትተናል? ችግሮቹስ መፍትሄ አግኝተዋል? መልካም ግንኙነት ተደርጓል? ተገቢው ሥራ ለተገቢ ሰዎች ተሰጥቷል? በተሻለ ሁኔታ መሥራት ይችሉ ኖሯልን? መሪው ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ በማግኘት ይበልጥ ሥራውን ማሻሻል ይችላል። በግምገማው መሠረትም ምናልባት ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ማስተካከል፣

አዲስ ዓላማዎችን ማዘጋጀትና ተገቢውን ሥራ ለተገቢው ሰዎች መስጠትን ሊኖርበት ይችላል።

ኢየሱስና ጴጥሮስ ካደረጉት ውይይት ለክርስቲያናዊ አመራር መልካም ምሳሌ የሚሆንን ሀሳብ መመልከት ይቻላል። የክርስቲያናዊ ሥራ እንቅስቃሴ ዐቢይ ግብ የጌታን ፈቃድ መፈጸም ነው። በኢየሱስና በጴጥሮስ መካከል ያለው ግንኙነት ተማሪውን የሚወድድ መምህርና መምሕሩን የሚወድ ተማሪ ግንኙነት ነበር። ችግሩ የሰዎች መንፈሳዊ ረሃብ ነበር። ግቡ ደግሞ እነዚህ መንፈሳዊ ረሃብ ያለባቸውን ሰዎች መመገብ ነው። ሥራው ወይም መደረግ ያለበት ነገር ለእነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ ምግብን መስጠት ነው።

7/ ስለ ሥርዓታዊ አቀራረብ የተማርነውን በአጭሩ ለማስቀመጥ በእያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ/ ሥርዓታዊ አቀራረብ ስንል ሁኔታዎችን በዘዴ መቅረብ ማለታችን ነው።

ለ/ የሥርዓት ዋናው ባሕርይ አንዱ ከሌላው ጋር ግልጽ ግንኙት መኖሩ ነው

ሐ/ ሥርዓታዊ አቀራረብ ማለት ድርጅቱ ልክ እንደ አንድ ዓይነት ማሽን ይንቀሳቀሳል ማለት ነው።

መ/ ሥርዓታዊ አቀራረብ መሪዎች ትክክለኛ ሥፍራቸውን እንዲያውቁና ከሌሎች መሪዎችና ሠራተኞች ጋር እንዴት መሥራት እንዳለባቸው ያሳያል።

ሠ/ ሥርዓታዊ አቀራረብ መሪዎች ትክክለኛ ዓላማ ላይ እንዲያነጣጥሩ ይረዳል

ረ/ ስለ ሥርዓታዊ አቀራረብ የተማርንበት ዋናው ምክንያት ሥራችንን ለማሻሻል ስለምንችልባቸው መንገዶች ለማወቅ ነው

8/ ስለ ራስህ ድርጅት ወይም በቅርቡ ስለምታውቀው ድርጅት አስብ። በዚህ ትምህርት በተማርከው መሰረት እንዴት ትገመግመዋለህ? ሰዎቹ ምን ያህል እርስ በርስ የተቀራረቡ ናቸው? በሠራተኞቹና በመሪዎቹ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት አለን? መፍትሔ ማግኘት የሚገባው የሰዎቹ ችግር ምንድነው? ችግሮች ስንል ዕድሜን፣ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ ማሕበረሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችንና ሌሎች ጉዳዩችንም እንደሚያጠቃልል አትርሳ። አንዳንድ ዓላማዎችን መዘርዘር ትችላለህን? ዓላማዎች ላይ ለመድረስ ምን ዓይነት የሥራ እንቅስቃሴ ያስፈልጋል? ውጤቱን

እንዴት ትገመግመዋለህ? ለወደፊቱ እንዲጠቀሙህ መልሶችህን በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር፡፡

## የሰዎችን ችግር መረዳት

### ዓላማ 4 ችግሮችን ለማወቅ የሚረዱ መንገዶችን ለመግለጽ

መጋቢውና ሚካኤል ብዙ ቀን ክርስቲያን መሪዎች የሚፈጽሙትን ስሕተት ፈጽመዋል ማለታችን አስታውስ፡፡ ስሕተቱ ምን እንደሆነ ለማየት እንድትችል ታሪኩን እንደገና አንብበው፡፡

9/ መጋቢውና ሚካኤል የፈጸሙት ስሕተት ምን እንደነበር ታስባለህ? መልሶችህን በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር፡፡ የሰጠኸው መልስ መልእክትን ወይም ሃሳብን ለማስተላለፍ ከተማርነው ትምሕርት ጋር ይስማማልን? አንድን መልእክት ለሰዎች ለማቅረብ አስቀድሞ ስለሰዎቹ ማወቅ ይኖርብሃል፡፡ መጋቢውም ሆነ ሚካኤል ግን መልእክቱን ስለሚቀበሉ ሰዎች ባሕርይ ወይም ፍላጎት ምንም የጠቀሱት ነገር የለም፡፡

እኛ ክርስቲያኖች ንግድ ነክ ለሆኑ እንቅስቃሴዎች ሃሳብን ወይም መልእክትን ለማስተላለፍ ከሚፈልጉ ሰዎች ይልቅ የበለጠ ዕድል አለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይመራናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ሁሉ ስለሚያውቅ ስናጠናና ስንጸልይ ምን መልአክት ማዘጋጀት እንዳለብን ይመራናል፡፡ ብዙ ቅን ክርስቲያኖች በዚህ መሠረታዊ እውነት ብቻ ነው የሚደገፉት፡፡ ይሁን እንጂ የተዋጣለት መልእክት ለማዘጋጀት ጊዜያችንን ስንሰጥ መልእክቱ ስለሚቀርብላቸው ሰዎች ፍላጎት አለማሰብን እርስ በርሱ የማይጣጣም ጉዳይ ነው፡፡

በክርስቲያናዊ ሥራ በጣም የምንዘነጋው ነገር ቢኖር የሰዎችን ችግር ነው፡፡ የሰዎችን ችግር እንደሚገባ ካልተረዳን በቀር ትክክለኛ ዓላማ ወይም ግብ ሊኖረን አይችልም፡፡ ከወንጌል እንደምንመለከተው ኢየሱስ ይበልጥ ያተኩር የነበረው መልእክቱ ላይ ሳይሆን ሰዎች ላይ ነበር፡፡ ለጴጥሮስ የነገረውም ከውድቀቱ እንዲማር ብቻ ሳይሆን የተማረውን ለሌሎች እንዲያስተምር ጭምር ነበር፡፡ በጎችን እንዲመግብ እንጂ እንዲሁ በደፈናው ጥሩ መሪ መሆን አለብህ አላለውም፡፡ ኢየሱስ የሰዎችን

ዕድሜና ያሉበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ አስገብቷል። እርግጥ ነው ሁሉም ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃል።

ይሁን እንጂ **"መሠረታዊ የደህንነት መንገድ"** ላይ ብቻ አልነበረም የሚያተኩረው። ለተጠሙ ውሃን፣ ለተራቡ ምግብን፣ ለታመሙ ፈውስን ሰጥቷል። ጴጥሮስም የኢየሱስን ምሳሌነት በመከተል መልእክቱን ለሚቀበሉ ሰዎች ያሉበትን ስደትና መከራ ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር የጻፈላቸው።

ኢየሱስ የሰዎችን ችግር ለማወቅ ልዩ ጥናት ማድረግ አላስፈለገውም። ምናልባትም እኛ የሰዎችን ችግር የመረዳቱን አስፈላጊነት ችላ የምንለው የክርስቶስን መለኮትነት ትክክል ባልሆነ መልኩ ስለምንወስደው ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ በተረዳው መንገድ ሰዎችን እንዳገለገለ ሁሉ እኛም በተረዳነው መንገድ ሰዎችን ማገልገል አለብን።

**ችግሮችን የምንረዳባቸው ዘዴዎች**

ስለሰዎች ችግር ለማወቅ የሚያስችሉን ቀጥተኛ ያልሆኑ መንገዶች በተጨማሪ ስለአመራርና አስተዳደር ጥናት ያደረጉ ምሁራን የሰዎችን ችግር ለመረዳት የሚያስችሉን አንዳንድ ቀጥተኛ መንገዶችን አቅርበዋል። ከእነዚህ መንገዶች አንዳንዶቹ በክርስቲያናዊ ሥራ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝተዋል። በሥራ እንቅስቃሴህ አንተም በተገቢው መንገድ ሁኔታ ልትጠቀምባቸው ትችላለህ። የሰዎችን ችግር ለመረዳት ስለሚያስችሉንን አራት ነጥቦች እንመለከታለን።

**1/ የመጀመሪያው እንቅስቃሴ**

አንድ ሰው ከዚህ በፊት ወደማያውቀው አካባቢ ሄዶ በመሪነት እንዲያገለግል ታስቦ ይሆናል። ምናልባትም በዚያን ሥፍራ ቤተክርስቲያን ለመመሥረት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለመጀመር ወይም ደግሞ ተከታታይ ስብሰባዎች ለማድረግ ታስቦ ይሆናል። ስለሰዎች ችግር ወይም ስላሉበት ሁኔታ ግን ምንም የሚያውቀው የለውም። እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥመው መሪው የተለያዩ ሰዎችን በማናገር እውነተኛ ችግራቸውን ለማወቅ መረጃ ያሰባስባል። ምናልባትም በአንዳንድ አጋጣሚ ሰዎቹ ትክክለኛ ችግራቸውን እንደሚያውቁ ይገምታል፣ ይህ ግምቱም እውነት ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ችግራቸው ምን እንደሆነ እንደሚገምቱ ማወቅ

አለበት፡፡ መሪው ሰዎቹን እንደሚገባ ማድመጡ ለሥራው መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

**2/ ችግር ተብሎ የሚታሰበው ነገር**

ይህ ዘዴ የሚጀምረው በኃላፊነት ላይ ያሉት ሰዎች ችግር ብለው በሚያስቡት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንንም መሪው የተረዳው ሌሎች ሰዎች ከሰጡት መረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ የእነዚህን ችግሮች ዝርዝር ያወጣና ችግሮቹንም በትክክል መኖራቸውንና ችግሮችንም ለማቃለል ምን መደረግ እንደሚቻል ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፡፡ ይህን በመሰለ ሁኔታ መሪው የሰዎችን ስሜትና ምን ዓይነት እንቅስቃሴ መወሰድ እንዳለበት ይረዳል፡፡ ችግሮቹ መፍትሄ ካላገኙም ሌላ ዘዴ ይፈልጋል፡፡

**3/ ግልጽ የሆኑ ችግሮች**

ምናልባትም ዓላማ ላይ ለመድረስ አልተቻለ ይሆናል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲገጥመው መሪው ሐቁን ለመጋፈጥ ድፍረት ያስፈልገዋል፡፡ ሌሎች ሐቁን እንዲቀበሉም ያበረታታቸዋል፡፡ እርሱ ችግሩን በተረዳበት መንገድ ሌሎቹም መረዳት እንዲችሉ ችግሩን ሁሉ ለጠቅላላው ቡድኑ ገላልጦ ይነግራቸዋል፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ የሚገጥሙን አንዳንድ ችግሮች በጣም የታወቁ በመሆናቸው ጥያቄ ማቅረብ እንኳ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ መሪው ማድረግ ያለበት ችግሮቹን ለማስወገድ ስለሚቀመጡት ዓላማዎችና ስለ አሰራር ሂደቱ ማብራራት ብቻ ነው፡፡

**4/ ችግሮቹን ማወዳደር**

ችግሮቹን በማወዳደር ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን ማወቅ አለብን፡፡ ለዚህም መሪው ሰዎችን በትክክለኛው ስፍራ ማስቀመጥና ጊዜንና ገንዘብንም እንደአስፈላጊነታቸው ሊጠቀምባቸው ይገባል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው ለየትኞቹ ችግሮች ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ከሰዎች ጠይቆ በመረዳት ነው፡፡

10/ ችግሮችን ስለመረዳት የተማርኸውን ለማስቀመጥ በእያንዳንዱ ትክክለኛ አረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል ክበብ፡-

ሀ/ መሪዎች ደንታ ስለሌላቸው ለሕዝቡ ችግር ጥንቃቄ አያደርጉም፡፡

ለ/ ትክክለኛውን ዓላማ ከማስቀመጣችን በፊት ችግሮችን እንደሚገባ መረዳት አለብን፡፡

ሐ/ ችግሮችን ገምግሞ መረዳት በቅዱሳት መጽሐፍትም የተደገፈ ነው፡

መ/ ትክክለኛ ችግራቸውን ከሰዎች ጠይቆ መረዳት መሪውን ይበልጥ በሥራው ውጤታማ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡
ሠ/ በገንዘብና በጊዜ እንደሚገባ መጠቀም እንዲችል ለየትኛውም ችግር ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት እንዲያውቅ መሪው ችግሮቹን በሚገባ መረዳት አለበት፡፡

**በዓላማዎች ላይ የተመሠረተ አመራር**

**ዓላማ 5 በዓላማዎች ላይ የተመሠረት አመራርን ለመግለጽ**

ችግሮችና ዓላማዎች በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ ተወራራሽ መሆናቸውን ተመልክተናል፡፡ ውጤታማና ተገቢ በሆነ መንገድ እንድናገለግላቸው ከተፈለገ የሰዎችን ችግር መረዳት አለብን፡፡ ችግራቸውን እንደሚገባ ከተረዳን በኂላ ደግሞ ዓላማ ማዘጋጀት እንችላለን፡፡ ዓላማውን የሚወስነው ከሥራው ልናገኝ የምንፈልገው ውጤት ነው፡፡ በትምህርት 7 ላይ ስለዓላማዎች አስፈላጊነት ተምረናል፡፡ ዓላማዎች የጠቅላላው ስልት ክፍል በመሆናቸው አሁን ስለ አስፈላጊነታቸው ይበልጥ ማወቅ ችለናል፡፡

ሥራው እንዲጠናቀቅ መሪዎች ኃላፊነት አለባቸው? አስተዳደራዊ ሥራ የምንለውም ይህን ነው፡፡ አስተዳደራዊ ሥራ ስንል ዓላማዎችን ለመተግበር የታቀደውን ዓላማ ለመምታት የምናደርገውን የሥራ እንቅስቃሴ ማለታችን ነው፡፡ ምናልባትም ይህ ማንኛውንም ሥራ በብቃት ለመወጣት በጣም አስፈላጊ ነው በክርስቲያናዊ ሥራ ውስጥ ብዙ ችግሮች የሚፈጠሩት መሪዎች ዓላማ ስለሌላቸው ወይም በዓላማዎችና በሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚገባ ባለመረዳታቸው ነው፡፡ ዓላማዎች አሏቸው፣ እነዚህ ዓላማዎች ተግባራዊ ከሆኑ ጌታን እንደሚያስከብሩ ያውቃሉ፡፡ የሚገባውን ያህል ውጤታማ መሆን አለመሆናቸውን ግን አያውቁም፡፡

በመጀመሪያ አንተና አብረውህ የሚሰሩ ሰዎች ችግሩን ተረዱ፣ ዓላማዎችም ይኑራችሁ፡፡ ከዚያም በኂላ እግብ ላይ የምትደርሱበትን ዘዴ ታወጣላችሁ፡፡ እስቲ እንደገና የአስቴርን ታሪክ አስብ፡፡ የነበራት ግብ የሕዝቧ መዳን ነበር፡፡ የምታደርገው

ነገር ዓላማው ሁሉ ይኸው ነበር። እዚህ የመጨረሻ ግቧ ላይ ለመድረስም የንጉሡን ፈቃደኝነትን ማግኘት ሌሎች ዓላማዎችን መምታት ነበረባት።

እስቲ አንድን ስብከት ስለማዘጋጀት እናስብ። የስብከቱ ዋና ግብ ሰዎች ክርስቶስን እንዲቀበሉ ማድረግ ነው። ለዚህም ዓላማ ይኖረናል፣ ዓላማውም የተዋጣለት ስብከት ማዘጋጀት ነው። ይዘቱ መልካም መሆንና አቀራረባችንም ያማረ መሆን አለበት። እነዚህ ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ ዓላማዎች ናቸው። የስብከቱ ይዘት የተሟላ እንዲሆን መጽሐፍ ቅዱሳችንን እንደሚገባ ማጥናት አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያና ሌሎችም ነገሮች ያስፈልጉን ይሆናል። ለዚህ ሁሉ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ማንበብ መቻል ይኖርብናል። ጥሩ አቀራረብ። እንግዲህ አጠቃላይ ግቡ ላይ ለመድረስ የተለያዩ ዓላማዎችን መምታት እንደሚገባን ተምረናል ማለት ነው። አንድ መሪ ይህን ማወቅና ለሌሎች ለማስተማርም መቻል ይኖርበታል ማለት ነው። ግቦች ላይ ለመድረስ አስተዳደር አሠራር የተባለውም ይኸው ነው።

**ዓላማዎችን በመከተል እንዴት እንደምትመራ**

**1/ ያለፈውንና የአሁኑን ሁኔታ አጥና፦** ድርጅትህንና ባለፈው ጊዜ ያከናወናቸውን ነገሮች በሚገባ መርምር፡፣ አሁኑ ያለበትን ሁኔታም እንደሚገባ ለመገምገም ሞክር፣ ምን ያህል ተሳክቶልሃል? የትኛው የሥራው ክፍል ነው የተሳካልህ? የትኛውስ መሻሻል አለበት?

**2/ በእውነታ ላይ የተመሠረቱ ዓላማዎች ይኑሩህ፦** ልታገለግላቸው የምትፈልገውን ሰዎች ችግር ለማቃለልስ ምን መደረግ አለበት? በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ በመደገፍ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ምን ውጤት ማግኘት እንዳለብህ ዘርዝር። ላቅ ያሉ ግቦች ይኑሩህ፣፡ ሆኖም እውነታን ለመቀበል አታመንታ፣ ሰዎችን አነሳሳ፣ በጌታ ስላለህም እምነት እርግጠኛ ይሁኑ፣ መድረስ የሚችሉበት መስሎ የሚታያቸውን ግቦች ካቀረብህላቸው ተስፋ ይቆርጣሉ።

**3/ ዓላማዎችህ መመዘን የሚችሉ መሆን አለባቸው፦** ገና ከመጀመሪያውኑ ጊዜ ገደብና ስኬታማነትህን የምትለካበት ሚዛን ይኑርህ። አለበለዚያ ግን ግቦችህን መምታትህን ማወቅ ያቅትሃል። ለተወሰነ ቀን ምን ማከናወን እንዳለብህ እቅድ አውጣ።

**4/ አብረውህ የሚሰሩ ሁሉ ዓላማዎችህን በሚገባ መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን፡-** አንድ መሪ ራዕዩንና ዓላማውን ለሌሎች ማካፈል አለበት፡፡ ሰዎች ተሳትፎ ለማድረግ የሚነሳሱት እንደሚገባ በተረዱዋቸው ግቦች መሆኑን በሚቀጥለው ትምህርታችን እንመለከታለን፡፡

**5/ ዓላማዎችህ ላይ ለመድረስ እቅድ አዘጋጅ፡-** እቅድህን እንዴት ተግባር ላይ ለማዋል እንዳሰብህ አብረውህ ለሚሰሩ ሰዎች አዋያቸው፡፡ ለእያንዳንዱም የተወሰነ የሥራ ድርሻ ስጣቸው፡፡ ያንን ሥራ በመፈጸም ረገድ እያንዳንዱ ምን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችሉና እርስ በርስ ስለሚኖራቸው ግንኙነት ይወቁ፡፡ ሃሳብህን፣ የሥራ ስሜትህንና እምነትህን ይረዱ፡፡

**6/ እንቅስቃሴህን ከትክክለኛው አቅጣጫ ጀምር፡-** አንድ መሪ ነገሮች እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡ መስበክና ማስተማር ብቻ በቂ አይደለም፡፡ ለሁኔታው የሚያመች ሥራም ያስፈልጋል፡፡ እቅድ በማውጣትና እቅድን ተግባር ላይ በማዋል መካከል ጊዜ የሚባክን ከሆነ የሠራተኞቹ የሥራ ፍላጎት ይዳከማል፡፡ ስለዚህም እቅድ እንዳወጣህ ወዲያውኑ ሥራ ጀምር፡፡

**7/ የሥራ እንቅስቃሴህ ዓላማህ ላይ ያነጣጥር፡-** ሰዎች አስቀድሞ የሚያውቋቸውን ነገሮች በተለምዶ የመሥራት ዝንባሌ ስላላቸው አንዳንድ ጊዜ ለምን እንደሚሰሩ እንኳ አያውቁም፡፡ አንድ መሪ ግን ዓላማዎቹን ከዘረዝረ በኋላ ወዲያውኑ የሚረሳ ዓይነት ሰው መሆን የለበትም፡፡ አላማዎቹ ላይ ለመድረስ እንዲሰሩ የሥራ ጓደኞቹን ደጋግሞ ማሳሰብና ማበረታታት አለበት፡፡ ዘወትር ስሜታቸውን ማነሳሳትና የሥራ ስሜታቸውን ማነቃቃት ይጠበቅበታል፡፡

**8/ የሥራ እንቅስቃሴ ውጤቶችን አመዛዝን፤ በጽሑፍም አስፍር፡-** አንድ መሪ ውጤቶችን የሚያመዛዝን ከሆነ ተገቢውን ቅደም ተከተል፣ ሰዎች የተሰጣቸውን ሥራ በትክክል መሥራታቸውን፣ ወይም ደግሞ በተለያየ መልኩ ዓላማውን መለወጥ ይገባው እንደሆነ መረዳት ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የዓላማ አለመሳካት የብቃት ማነስ ወይም ለሥራው አለመትጋት ውጤት ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህም መሪው ውጤቶቹን በፍጹም ቅንነትና እውነተኛነት ነው ማመዛዘን ያለበት፡፡ ለሥራው መሻሻል ላቅ ያሉ ግቦች ላይ ለመድረስ የተሻለው መንገድ ይኸው ነው፡፡

**9/ ግቦቹ ላይ ለመድረስ የተሳተፉትን ሰዎች አስተዋጽኦ አድንቅ፣ አበረታታ፡-** ሰዎችን ማመስገን ያለብህ እንደ ሥራው አስተዋጽኦ እንጂ እንደ ሰውነታቸው መሆን የለበትም፡፡ ይህን በመሰለ መንገድ ሰዎች ዓላማዎችን የማስቀመጥ አስፈላጊነትንና ዓላማዎቹ ላይ በመድረስ እርካታንም ያገኛሉ፡፡

**10/ ሰዎች የየግላቸውን ዓላማ መምታት የሚችሉት አጠቃላይ ግብ ላይ ለመድረስ ከሌሎቹ ጋር አብረው በመሥራታቸው እንደሆነ አሳይ፡-** በተለያዩ ዓለማዊ የሥራ እንቅስቃሴዎች ሰዎች የግላቸውን ዓላማ መምታት መጠቅም የሚችሉት ድርጅቱ ግቡን በመምታቱ እንደሆነ ለማስረዳት ብዙ ጥረት ይደረጋል፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ ግን ችግሩ ይህን ያህል ትልቅ አይደለም፡፡ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሁሉ ተመሳሳይ ግቦች ላይ ለመድረስ ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ ሁሉም እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይፈልጋሉ፤፡ አብዛኛዎቹም ራሱን በቻለ መንገድ ሊያገለግሉት ፈቃደኞች ናቸው፡፡ ስለዚህም የመሪው ድርሻ የሥራው ዓላማ ራስን ለመጥቀም ሳይሆን፣ የቤተክርስቲያንን እንቅስቃሴ ማስፋፋት እንደሆነ ማሳየት ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ክርስቲያኖች እቅድና የሥራ እንቅስቃሴ መዋቅር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህ ግቦች ላይ ለመድረስ የሚደረግ አስተዳደራዊ እንቅስቃሴ አስደናቂ ገጽታ ነው፡፡ መሪው ሰራተኞቹን ወደ ግቡ ለመምራት ይረዳዋል፡፡ የክርስቲያናዊ አሰራርን ሥርዓት ምክንያትና ዓላማም ለመከተል ይረዳቸዋል፡፡ እንደ መሪነትህ ትልቁ ዋጋህ በእግዚአብሔር እቅድ መሰረት ዋናው ግብ ላይ ለመድረስ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ችግራቸው ሲቃለልና የራሳቸውንም መንፈሳዊ ግብ ሲመቱ መመልከት ነው፡፡

11/ በተማርነው መሰረት ዓላማ የሚለውን ቃል በተሻለ ሁኔታ መግለጽ የምንችለው፡-

ሀ) ማድረግ የምንፈልገው ነገር ሐ) የታቀደው ሥራ ውጤት መመዘኛ

ለ) ከሥራው የምንጠብቀው ውጤት

12) በግልህ ለምታውቀው ሁኔታ ተስማሚ ናቸው የምትላቸውን ሁለት ዓላማዎች በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር፡፡

13) የቤተክርስቲያን ግቦችን ለመምታት በምታደርገው የሥራ እንቅስቃሴ አንተ ራስህ በግል ሕይወትህ እደርስባቸዋለሁ የምትላቸውን ሁለት ዓላማዎች በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር።

14/ ዓላማዎችን እፍጻሜ ላይ ለማድረስ የአመራር የሥራ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት መሆኑን በአጭሩ ግለጽ።

**የሙከራ ፈተና**

1/ ጴጥሮስ ***"ጌታ ሆይ ከአንተ ጋር ወደ እስርም ሆነ ሞት ለመሄድ ፈቃደኛ ነኝ"*** ሲል ከዚህ አባባሉ ስለመሪነት የምንማረው፡-

ሀ)አንድ ሰው ፈጥኖ ከፍተኛ መንፈሳዊ ውሳኔ ማድረግ እንደማያስፈልገው
ለ)አንድ ሰው ታማኝነቱን በድፍረት መናገር እንደሌለበት
ሐ) ድርጊት በጣም አስፈላጊ ቃላት ግን ዋጋ የሌላቸው መሆኑን
መ) አንድ ሰው ከሚገባ በላይ በራሱ መተማመን እንደሌለበት ነው
2) ጌታ ጴጥሮስን ***"ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥርህ ፈለገ፣ ከተመለስህ በኋላ ወንድሞችህን አጽና"*** ብሎት ነበር። ከዚህ አባባሉ ስለመሪነት የምንማረው ሁለተኛው ጉዳይ የግል ተሞክሮን፡-
ሀ/ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ለማሳየት ልንጠቀምበት እንደማይገባ
ለ) ሌሎችን ለመጥቀም ልናውላቸው እንደሚገባ
ሐ) የአንድን ሰው መንፈስ ነፍስና ሥጋን የሚያዳክም መሆኑን
መ) ከፍተኛ መንፈሳዊ ድል የሚያስገኝ ሁሉ ብኩን መሆኑን
3) በመካከላችሁ ያሉትን የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች **"እኔም እንደ እናንተ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የሆንሁ---"** በማለት ጴጥሮስ ሲጽፍ ያሳየው ከፍተኛ የመሪነት ባሕርይ፡-

ሀ) የሌሎችን ችግር የሚረዳ መሆኑን ሐ) ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ማወቅን
ለ) ትሁት መሆኑን መ) ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ያለውን ተነሳሽነት ነው
4/ ጴጥሮስ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በጻፈላቸው ምክር "**በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ**" ብሏቸዋል፣ ይህንንም ሲል፡-

ሀ) በመሪዎቹ ሥር ያሉት ሰዎች የእግዚአብሔር መንጋ መሆናቸውን ያሳስባል።

ለ) ሰዎች እንደበጎች ስለሆኑ ኃላፊነት መቀበል የማይችሉ ፍጥረታት መሆናቸውን ማሳሰቡ ነው።

ሐ) ሰዎች እንደ ሕፃናት ስለሆኑ ኃላፊነት የማይሰማቸው መሪ ያስፈልጋቸዋል

መ) አንድ ሰው ኃላፊነትን ከተቀበለ በኋላ ኃላፊነትን መተው እንደማይችል ማሳሰቡ ነበር

5/ ጴጥሮስ የእረኞች አለቃ ስለሚገለጥበት ቀን መናገሩ ሌላው የክርስቲያን መሪነት ባሕርይ ነው። አንድ መሪ የሥራ ብርታትና ውጤታማነት እንዲኖረው ከተፈለገ፡-

ሀ) በጎቹን ደስ ለማሰኘት መጣር አለበት

ለ) ልፋቱ ሁሉ ዋጋ እንዳያጣ መጠንቀቅ አለበት

ሐ) ጊዜው አጭር እንደመሆኑ መጠን ግቦቹም አጫጭር መሆን አለባቸው

መ) ለዋናውና ለአጠቃላይ ግቡ ዘወትር ትኩረት መስጠት አለበት

6) በተማርከው መሠረት ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ግቦች ላይ ለመድረስ አስተዳደራዊ እንቅስቃሴን፣ ስልታዊ እንቅስቃሴን በተሻለ ሁኔታ መግለጽ የሚችሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ) የአንድ ማሽን ያህል እንቅስቃሴን መቆጣጠር

ለ) የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሥርአታማነት መምራት

ሐ) ከሰዎች ይልቅ በኮምፒውተር በመሥራት ብዙ ድካምን ማስወገድ

መ) በሁለት ዋና ዋና ነገሮች ማለትም ግቦችን ማስቀመጥና ግቦችን በመገምገም ላይ መደገፍ

7/ ሥርዓታዊ ግምገማ ላይ ጥናት ያደረገው ድርጅቱ፡-

ሀ) ለምን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንደሚሠራና እንደማይሠራ ለማወቅ

ለ) ምን ያህል እንደተሠራ ግምገማና አስተያየት ለማስተናገድ

ሐ) ግቦችንና የሥራ እንቅስቃሴዎችን ለመምረጥ

መ) አንዱ ከሌላው ጋር እንዲሁም ከጠቅላላው አሰራር ጋር መቀራረብ እንዲኖረው

8/ ችግሮችን ስለማወቅ ቀጥሎ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ከአንዱ በቀር ሁሉም ትክክል ናቸው። ትክክል ያልሆነው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ) ትክክለኛ ዓላማዎችን ለማዘጋጀት አንድ ሰው ችግሮቹን ማወቅ አለበት

ለ) ሰዎች ችግራቸውን ራሳቸው እንዲናገሩ ማድረግ መሪው ሥራውን ውጤታማ ከሚያደርግባቸው መንገዶች አንዱ ነው

ሐ) ችግሮቹን መረዳት አንድ ሰው ትክክለኛ ቅደም ተከተል እንዲያደርግ፣ በጊዜውና በገንዘቡም በሚገባ እንዲጠቀም ያስችለዋል፡፡

መ) መሪዎች ግዴለሾች ስለሆኑ የሰዎችን ችግር ችላ ይላሉ

9) ዓላማዎችን ለመምታት እቅድ እንድታወጣ ብትጠየቅ ኖሮ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ትመርጥ ነበር?

ሀ) የመጨረሻ ግብን መወሰንና ግቡ ላይ ለመድረስ የሚያስፈልጉ ዓላማዎችን ማዘጋጀት

ለ) ግብን መምረጥ፣ ለሥራ እንቅስቃሴዎች እቅድ ማውጣት፣ እንቅስቃሴዎችን ቆም ብሎ ማየት፣ ማስተካከልና መገምገም

ሐ) የምትፈልገውን ውጤት መዘርዘር፣ መረጃዎች ማሰባሰብ፣ ሰዎችን መጠየቅ የሥራ እንቅስቃሴ እቅድ ማውጣት እና መርሐ ግብር ማዘጋጀት

መ) ግብን መግለጥ፣ የራስህንና የድርጅቱን ግብ ማጣጣም፣ የሥራ እንቅስቃሴን እቅድ ማውጣት፣ ቆም ብለህ የእቅድህን ውጤታማነት ማየት፣ እንደአስፈላጊነቱ የእንቅስቃሴ ለውጥ ማድረግ

10) የአሰራር ዘዴውን ከትክክለኛው ገለጻ ጋር አዛምድ

1/ ዐቢይ ግብ 2/ መቀራረብ 3/ ችግሮች 4/ ዓላማዎች 5/ ሥራዎች 6/ ግምገማ

---ሀ/ ከሥራችን የምንጠብቀው ውጤት

---ለ/ መሪውንና ሰራተኞቹን የሚያስተሳስረው

----ሐ/ ውጤቱን የምንለካበት

----መ/ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለው ከፍተኛ ዓላማ

---ሠ/ ዓላማዎች ላይ ለመድረስ የምናደርገው

---ረ/ አሁን ባለንበት ጊዜ ባለው ሁኔታና ልንደርስበት በምንፈልገው ዓላማ መካከል ያለው ልዩነት፡

**የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች**

7/ሀ) እውነት ለ) እውነት ሐ) ሐሰት መ) እውነት ሠ) እውነት ረ) እውነት

1/ ለ) መንፈሳዊ ችግር ያለባቸውን ሰዎች መምራትና ማስተማር 8) መልስህ

2/ሀ) የተራቡ በጎችን ያህል ሰዎቹ ችግር ነበረባቸው

9/ ምናልባት መልስህ እኔ ከሰጠሁት መልስ በመጠኑ ይለያይ ይሆናል፡፡ በበኩሌ የሚከተሉትን መልሶች ሰጥቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ወንድሞች አንዱም እንኳ መልእክቱ ስለሚደርሳቸው ሰዎች ያሰቡት ነገር የለም፡፡ ምናልባት መልእክት እንዲያቀርብ በመጋበዙ መጋቢው ለሚካኤል ውለታ እንዳደረገለት አስቦ ይሆናል፡፡ ወይም ደግሞ ስብከቱን ለሚካኤል ሰጥቶ ራሱ ማረፍ ፈልጎ ይሆናል፡፡ ሚካኤል መልእክቱን ለማዘጋጀት ትልቅ ጉጉት አለው፣፡ መልእክት ማዘጋጀት የላቀ ግብ ግን የለውም፡፡ ይህ ነው የሚባል ውጤት እንኳ አይጠብቅም፡፡

3/ሐ) ኢየሱስን ወደደ

10/ ሀ) ሐሰት ለ) እውነት ሐ) እውነት መ) እውነት ሠ) እውነት

4/ ሐ) እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን ዓላማ መፈጸም

11/ ለ) ከሥራው የሚጠበቀው ውጤት

5/ሀ)2) ችግሩን መረዳት ለ/4) ትክክለኛ ተነሳሽነት ሐ/5) ዓላማን መረዳት

መ/3) መንጎቹ የእግዚአብሔር ናቸው ሠ/1) ትሕትና

12) መልስህ፡፡ ይህ ምሳሌ ሊሆንህ ይችላል፡፡ የእኔ ግብ የቤተክርስቲያኔ ሰዎች ትክክለኛና አጠቃላይ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንዲኖራቸው ነው፡፡

6/ሀ) "ግልገሎቼን አሰማራ" ለ) "የእግዚአብሔርን መንጋ አሰማሩ"

13/ መልስህ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማን እግብ ለማድረስ አንድ ሰው በግሉ የሚያዘጋጃቸው ሁለት ዓላማዎች፡- 1) ለመመስከር እድል ሲገጥመን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በንቃት መጠባበቅ አለብን፡፡ 2) ዘወትር በመጸሐፍ ቅዱስ በጥናትና በጸሎት ከጌታ ጋር የግል ግንኙነትን ማዳበር

14/ መልስህ፡፡ አጠቃላይ ግብ ላይ ለመድረስ የተለያዩ ዓላማዎች መምታት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ ይህንን በግላችን መረዳትና ለሌሎች ለመግለጽ መቻል አለብን፡፡

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## መሪዎች ተነሳሥተው ሌሎችንም ያነሳሣሉ።

በስምንተኛው ክፍለ ትምህርት የጴጥሮስን ምሳሌነት በመከተል ለመንፈሳዊ መሪነት የሚያገለግሉ መመሪያዎችን በመመልከት በክርስቲያን ሥነ ሥርዓትን የተከተለ የአቀራረብ መንገድ ምን ማለት እንደሆነና እንዴት በሥራ እንደሚተረጎም ተመልክተናል። በዚህ በዘጠነኛው ክፍለ ትምህርት ላይ የምናተኩረው ደግሞ የጳውሎስን የመሪነት ተምሳሌት በመከተል ከዚህ የምናገኛቸው መመሪያዎች በሥራ እንዴት እንደምንተረጉም ግንዛቤ ማግኘት ይሆናል። መንፈሳዊ መሪዎችንና ሠራተኞችን ዓላማቸውን ከግብ እንዳያደርሱ የሚያግዱአቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ ለመግለጽና እንዴት እንደሚወገዱ እንመለከታለን።

**የክፍለ ትምህርቱን አከፋፈል**

- የጳውሎስ ምሳሌነት
- ሥርዓት ያለው መንፈሳዊ ሥራ
- ዓላማዎችን በመከተል ሥራን መምራት
- --------------------------------

**የትምህርቱ ዓላማዎች**

- የጳውሎስን ሕይወት መሠረት በማድረግ አመራርን መማርና ትምህርቶቹን ለሕይወትህ ተግባራዊ ማድረግ፣ መሪዎችና የሥራ ባልደረቦቻቸው ያሰቡት ግብ ላይ እንዳይደርሱ ስለሚገጥሙዋቸው ፈተናዎች መረዳትና እነዚህን ችግሮችን ለማስወገድ መዘጋጀት መቻል፣ ስለ ተነሳሽነት ጽንሰ ሃሳብና ከመሪነት ጋር ስለሚያያይዛቸው አንዳንድ ዋና አስተያየቶች መረዳት፣
- የታሰበው ግብ ላይ እንዲደርሱ አብረውህ የሚሰሩትን ሰዎች ማነሳሳት

-------------------------------------------------------

**የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች**

1/ ለዚህ ትምህርት መሠረት ይሆንህ ዘንድ ዘኁ 11፡26-19 ኢሳ 40፡28-31፣50፡4፣ሉቃ 22፡31-34፡ ዮሐ 21፡20-22 የሐዋ ሥራ 14፡11-15 ፣ 20፡2-28፣2፡37-22፡1 27፡1-2 13-14፡ ሮሜ 8፡35፣ 1ቆሮ 9፡27፡ 11፡2፣12፣4-11፣

2ቆሮ 7፡14፣ 11፡25-29፣ 13፡10፣ ገላ 6፡1-10፣ ፊሊ 3፡13-14፣ 2ጢሞ 4፡7-8፣ 1ጴጥ 5፡1-11 አንብብ፡

2/ ትምህርቱን እንደሚገባ ካጠናህ በኋላ በተለመደው መንገድ ጥያቄዎችን መልሰህ ከጨረስህ በኋላ መልሶችህን ከተሰጠው መልስ ጋር አመሳክር።

**የክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ - የጳውሎስ ምሳሌት**

**ዓላማ 1 ከጳውሎስ ሕይወት የመሪነት ባሕርያትን ለመግለጽ**

ኢየሱስ ስለጀመረው ሥራና ስላስተማረው ትምህርት ቀድሞ ጽፎት በነበረው መጽሐፍ እንደገለጸ የሐዋርያት ሥራ ፀሐፊ ይናገራል። በሐዋርያት ሥራ ላይ ደግሞ በመንፈስ በተሞሉ ተከታዮቹ አማካይነት ኢየሱስ ጀምሮት የነበረውን ሥራና ትምህርት እየቀጠለ እንደሆነ ይናገራል። ይህ ኢየሱስ የሰጠውን ትእዛዝ በመቀጠሉ ረገድ የሐዋርያት ሥራ አንደኛው ምዕራፍ ነው ማለት ይቻላል። ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ የእርሱ መሄድ እንደሚሻል ተናግሮአል። ከዚያም በአንድ ሥፍራ የማይወሰነው መንፈስ ቅዱስ በቤተክርስቲያን አማካይነት ሥራውን በዓለም ሁሉ ያስፋፋል። እነዚያ የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ምን ያህል ለሥራው ራሳቸውን የሰጡ መሆናቸውን ከመገንዘቡ በጣም ይከብዳል። ዓላማቸው የእግዚአብሔርን ዓላማ መፈጸም ነበር፣፡ ይህን ዓላማ ለመፈጸምም ከሰዎች ጋር አብረው ሰርተዋል፣፡ ከእንቅስቃሴያቸው መመልከት እንደሚቻለው የውጤታማ መሪ ተግባርን አካትተዋል።

የጳውሎስ መታሰርና እስረኛ ሆኖ ወደሮም መጓዝ የመሪነት ባሕያትን ከሚያመለክቱ ነገሮች አንዱ ነው። ጳውሎስ በተያዘበት ወቅት የነበረውን እምነት፣ ራስን መስጠትና እርጋታ ማሳየት ይቻለናልን? ተቃዋሚዎቹ እየጎተቱ ከመቅደስ አወጡት፣፡ ወታደሮቹም በሁለት ሰንሰለት አሰሩት፣፡ በቁጣ ከተነሳሱት ሰዎች በኃይል ነጥቀው ማዳን ነበረባቸው። በዚህ ሁሉ ግን በተረጋጋና ጨዋነት በተሞላ አነጋገር **"አንድ ነገር እንድናገር ትፈቅዱልኛላችሁን?"** ነበር ያለው።

እንዲናገር አዛዡ ከፈቀደለት በኋላ ደረጃው ላይ ወጣና ሕዝቡ ሁሉ ጸጥ ብለው እንዲያደምጡት ጠቀሳቸው። ወዲያውም ጸጥ አሉ። ድፍረቱን ወይም ለሰማዕትንት መዘጋጀቱን ለማሳየት ብቻ አልነበረም ይህን ያደረገው። እፊት ለፊታቸው የቆመው እግዚአብሔር የመረጠው መሪ ነው። ጳውሎስ በሰዎች ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድር የእግዚአብሔር ኃይል ነበር የሚንቀሳቀሰው። በመለኮታዊ ኃይሉ እግዚአብሔር ሰዎቹን

ጸጥ ሲያሰኛቸው፣ ሌላው ቀርቶ ሊያጠፋቸው እንኳ ችሎታ ነበረው። ይሁን እንጂ በሰው መሣሪያነትን መጠቀምን ፈቅዷል፤፡ የዚያም ሰው ምሳሌነት ደግሞ ለእኛ አርአያ እንዲሆነን በጽሑፍ ሰፍሮልናል።

ጳውሎስ ሰዎች ላይ አልዛተም፡ አላስፈራራም። ለመስበክም ሆነ እንደእግዚአብሔር መልእክተኛ እንዲቀበሉት አልሞከረም። በመጀመሪያ እርሱ ራሱ አይሁዳዊ እንደሆነ ተናገረ። ከዚያም በኋላ ደግሞ እንዴት በጌታ እንዳመነ መለከረላቸው። እውነትን ያለምንም ፍርሀት አቀረበ። አቀራረቡ የተረጋጋና ራሱን የቻለ ዓላማ ነበረው።

ጠቅላላው ታሪኩን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበቡ በጣም ይጠቅምሃል። እዚህ ላይ የምናነሳው ግን በጣም ጥቂቶቹን ዋና ዋና ነጥቦች ብቻ ነው። ጳውሎስ ስለራሱ ሲናገር ምንም እንኳ እስረኞቸው ቢሆንም ባለሥልጣኖችና ተራው ሕዝብ በአክብሮት አደመጡት፤፡ እንዴት በጌታ እንዳመነ፣ በኃይል ተሞልቶ ልምምዱን ሲነግራቸውም ልባቸው ተነካ። የሙሴን ሕግ ምን ያህል ጠንቅቆ ማወቁንም አስመሰከረ፤፡ ያለአንዳች ቁጣና ብስጭት እርሱም እንደሌላው ሁሉ የዜግነት መብት እንዳለው አስረዳ።

በመጨረሻም እስረኛ ሆኖ በመርከብ ወደሮም ይሄድ በነበረበት ጊዜ መቶ አለቃው እንደእስረኛ ሳይሆን እንደሥራ ባልደረባው ነበር የተመለከተው። እስቲ በዚያ በማዕበል በምትናወጥ ጀልባ በሰዎች ሁሉ ፊት ቆሞ እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸውና ምንም አደጋ እንደማይደርስባቸው ሲያረጋጋቸው በዓይነ-ሕሊናህ ተመልከተው።

እንደምንመለከተው በልዩ ልዕል-ተፈጥሮአዊ መንገድ ስለእግዚአብሔር አልሰበከም። አስደናቂ ፀሎት አልፀለየም። ታዲያ ሰዎቹ ንግግሩን የተቀበሉት ለምን ይመስልሀል? ልክ እንደ አንድ በመንፈስ የተሞላ መሪ ሆኖ ነበር ፊታቸው የቆመው፤፡ ሰዎች ሊረዱት ሆኖም ሊቋቋሙት በማይችሉት አቀራረብና ሥልጣን ነበር የተናገራቸው። መርከቡን ለቅቀው እንዳይሄዱ ተናገረ። ለማንኛውም ነገር ዝግጁ ሆነው እንዲገኙና እንዲመገቡ ነገራቸው። ምን ያህል ለሰዎች ያስብ እንደነበር መመልከት ይቻላል፤፡ የሰዎችን ሕይወት ለማዳን ተግተው እንዲሰሩም መከራቸው።

በመጨረሻም ሁሉም በሠላም ወደ ወደቡ ደረሱና እሳት አንድደው መሞቅ ጀመሩ። ማንም **"ጳውሎስ በጣም ነው የምናመሰግንህ"** እንዳለው አናነብም። ይሁን እንጂ በጳውሎስ መሣሪያነት ተጠቅሞ እግዚአብሔር ሰዎቹን እንዳዳነ ለሁላችን ግልጽ ነው። የተጠቀመበት ዘዴም ለታላቅ መሪነቱ ማስረጃ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቡን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ እንደሚያስተምር እንመለከታለን። በተአምራዊ ችሎታው እግዚአብሔር ማዕበሉን ጸጥ ማሰኘት እንደሚችል ግልጽ ነው። ይህን ስትመለከት ስለክርስቲያናዊ አመራር ምን ትማራለህ? በእንዴት ዓይነት ሁኔታስ መንፈስህን ያነሳሳዋል? ምን ያህል ራስህን በፊቱ ዝቅ እንድታደርግ ያደርግሃል?

1/ ጥያቄዎቹን በሚገባ አስብባቸው፡- ለእግዚአብሔር ያለህን አክብሮት ግለጽለት፣፡ ማስተዋልን እንዲሰጥህ ጌታን ጠይቀው። ከዚያም በኋላ መልሶችህን በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር።

2/ ወደ ትምህርት አንድ ተመለሰና **"መሪዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?"** የሚለውን ክፍል ከልስ። ከዚያ በኋላ ደግሞ የጳውሎስን ምሳሌነት መሠረት በማድረግ የጳውሎስን የመሪነት ባሕሪያት የሚያመለክቱ ሲሆኑ ተስማሚ ጥቅሶቹን ከጎኑ አስፍር።

ሀ/ ለሌሎች ማሰብ ----------- ለ/ ግብን መምታት ---------- ሐ/ ብቃት ----------------

መ/ የስሜት መረጋጋት --------------------- ሠ/ አባል መሆን -------------------

ረ/ መሪነትን ከሌሎች መጋራት ---------- ሰ/የሥራ ትጋትና ታማኝ መሆን

3/ ከጳውሎስ ተሞክሮ የምንመለከታቸውን የመሪነት ባሕርያት ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገልጡት የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ ከጳውሎስ ልምምድ የምንመለከተው የመሪነት ችሎታ አስፈላጊነት ሥልጣኑን በተገቢው መንገድ በመጠቀሙ ሌላው ሰው ማግኘት የማይችለውን ዕድል ለማግኘት አስችሎታል፣፡ ከዚህም የተነሳ ነበር ለመመስከር በሩ የተከፈለት።

ለ/ ሰዎችን መቆጣጠር መቻሉ የጳውሎስ ትልቁ ችሎታ ነበር፡፣ ይህም ግቡን ለመምታት አስችሎታል።

ሐ/ ከጳውሎስ መሪነት የምንመለከተው ጠቃሚው ነገር ወንጌልን ይሰሙ ዘንድ እግዚአብሔር በጳውሎስ ባሕርይ መጠቀሙ ነው።

## መሰላቸት በክርስቲያናዊ ባሕርይ የሚያስከትለው ችግር

### ዓላማ 2፣ ለውጤታማ አመራር ምሳሌ የሚሆኑ ባሕርያትና ችግሩን ማስወገድ የሚቻልበትን መንገድ ለመግለጽ

ጳውሎስ እስረኛ በነበረበት ጊዜ እንኳ የመሪነት ችሎታውን በመጠኑም ቢሆን ተመልክተሃል። መሪዎች ሁልጊዜ ዝነኛና ተወዳጅ ይመስሉናል፡፣ ይህ ግን በፍጹም የተለየ ታሪክ ነው። በሌሎች ጽሑፎቹ ሁሉ መሪነቱ ለችግሮችና ለአደጋዎች

እንዳጋለጡት ጳውሎስ ጽፏል፡፡ ይሁን እንጂ ሲያጉረመርም አንመለከተውም፡፡ እንዲያውም እግዚአብሔር ለሰጠው አገልግሎት መከራ ለመቀበል በመታደሉ ሲመካ ነው የምንመለከተው፡፡ (1ቆሮ 11፡25-29) እኛ ከዚህ ልንማረው የሚገባን የማንኛውም መሪ ሕይወት ችግርና መከራ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

እኛን የሚገጥሙን ችግሮች ጳውሎስን ከገጠሙት ችግሮች ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ በጦርነትና በስደት ወቅት ዛቻ ይደርስብን ይሆናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ግን ችግሩ በመንፈሳዊ ሕይወታችን፣በጌታ ላይ ባለን ደስታና በክርስቲያናዊ ግቦቻችን ላይ ነው የሚቃጣው፡፡ ብዙዎች ችግሮችን በነዚህ ሁለት መደቦች ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ራስ ወዳድነትንና ጀብደኝነትን ይመለከታል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ራሳችንን እንድንጠራጠር፣ ራሳችንን እንድንነቅፍና በመጨረሻም ተስፋ መቁረጥን ሊያስከትልብን ይችላል፡፡ ይህም በሥራችን ስሜት እንድናጣና እንድንሰላች ያደርገናል፡፡ ይህ ችግር ግባችን ላይ ለመድረስ ተገቢውን ተነሳሽነት የማጣት ችግር ነው፡፡

**ከተሳሳተ ዓላማ የሚመጡ ችግሮች**

1ቆሮ 3 እና 1ጴጥ 5፡1-11 ተመልከት

1/ **እኔነት እና ትዕቢት፡-** መሪዎች ስንሆን ብዙውን ጊዜ ራሳችንን ከሌሎች አስበልጠን የመመልከት ችግር ይገጥመናል፡፡ ዐይናቸውን ሥራው ላይ ከማድረግ ይልቅ አንዳንድ መሪዎች ራሳቸውን ከሌሎች ጋር ያወዳድራሉ፡፡ ሥራው የጌታ ሳይሆን የራሳቸው ይመስላቸዋል፡፡ **"የእኔ ሥራ" "የእኔ አገልግሎት" "የእኔ ጥሪ"** በማለት መናገርን ያዘወትራሉ፡፡ **"መሪያችሁ እንደመሆኔ መጠን ልትታዘዙኝ ---- ይገባል"** በማለት ይናገራሉ፡፡ ሰዎች እንዲነቅፏቸውም ሆነ ከነሱ የተለየ ሀሳብ እንዲያቀርቡ አይፈልጉም፡፡ ልዩ መብትና ክብር እንዲሰጣቸው ይጠብቃሉ፡፡ አንዳንድ ግዜም ሌላው ቀርቶ በመንፈሳዊ ስጦታዎቻቸው እንኳ ይታበያሉ፡፡

2/ **ክሚገባ በላይ በራስ መተማመን፡-** ይህን ችግር ከጴጥሮስ ሕይወት ተመልክተናል፡፡ አቀራረቡ እምነት ስለሚመስል ከሌሎች የትዕቢት ዓይነቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይነቱ ሥራውን በተመለከተ ከሌሎች የበለጠ ልምምድ ያለው ይመስለዋል፡፡ በራሱ አስተሳሰብ ይደገፋል፣፡ ውሳኔዎቹንም ያለምንም ማንገራገር ሌሎች እንዲቀበሉት ይፈልጋል፡፡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ይህ ለአንድ መሪ አስፈላጊ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስሕተቱን መቀበል ሲያቅተውና ሁሉንም

ነገር በራሱ መንገድ ለማድረግ ቢፈልግ ግን ውጤታማነቱን ያጣል፡፡ ለዓላማችን መቆምና ግትርነት በፍጹም የተለያዩ መሆናቸውን ማስታወስ አለብን፡፡

3/ **ተወዳጅነትና ምሥጋናን መጠበቅ፡-** ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባው ምሥጋና ለርሱም ሆነ ለሌሎች ሲሰጥ ጳውሎስ በጣም ይበሳጭ ነበር፡፡ **"ማንም እራሱን አያታልል.... ማንም በሰው አይመካ"** (1 ቆሮ 3፡18-25) በማለት ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸውም በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ በልስጥራን በነበሩበት ጊዜ ሰዎች ጳውሎስንና በርናባስን እነደአማልክት ስለቆጠሩዋቸው ሊያመሰግኑዋቸው ነበር፡፡ እነርሱ ግን ልብሳቸውን እንደቀደዱና መስዋእት እንዳያቀርቡላቸው ሕዝቡን እንዳስጣሉ እናስታውሳለን፡፡ (ሐዋ ሥራ 14፣11-15) አንድ መሪ ተወዳጅነትን ለማግኘት ከጣረ የግል ሕይወቱን ይጎዳል፡፡ ከዚህም በላይ ደግሞ ዓላማው ሰዎችን ማስደሰት ስለሆነ እውነትን ያድበሰብሳል፡፡ ስሊዚህም ሥራው ይጎዳል፡፡ ነገሮችን በጌታ ዓይን ከማመዛዘን ይልቅ አድሏዊ ይሆናል፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ተወዳጅ ስለሆነ ብቻ ብርቱ ነኝ ብሎ የሚያስብን መሪ ያህል ማንም ደካማ የለም፡፡

የልስጥራን ሰዎች እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬም ቢሆን ብዙ ቅን ሰዎች ለመሪዎች ክብርና ምሥጋና ይሰጣሉ፡፣ እንዲህ ያለውን አዝማሚያ መቆጣጠርና ማጋለጥ የመሪዎች ኃላፊነት ነው፡፡ ለራሳቸው ትኩረት መሳብ አይገባቸውም፡፡ ቤተክርስቲያን ስታድግና ውጫዊ ድርጅቷም ሲሰፋ በዚያው ልክ ስዎች ይመሰገናሉ፡፣ ይወደሳሉ፡፡ የጌታ ትእዛዝ በመሆኑ ምእመኖቿ መሪዎችን እንዲያከበሩ ቤተክርስቲያን ማስተማር አለባት፡፡ በተገቢው መንገድ መዎችን ማክበርና ለችግራቸው መጠንቀቅ ተገቢ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከልኩ ማለፍ የለብንም፡፡ ማንኛውም መሪ የጳውሎስ መንፈስ ሊኖረው ይገባል፣ በመንፈሳዊ ስኬቶቻችን፣ እግዚአብሔር በሰጠን ስጦታዎችና በቤተክርስቲያን በምንሰጠው አገልግሎት ክብሩን ለግላችን መውሰድ አይገባም፡፡

4) **ቅንዓት፡-** ለምሳሌ ያህል ላደረግኸው አስተዋጽኦ የመመስገን ፍላጎት የለህም እንበል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ባንተ ልፋትና አገልግሎት ሌላው ሲመሰገን ምን ይሰማሃል? ተፈጥሮአዊ ባሕርያችን ቅር ይሰኛል፡፡ ስሜታችንም ይጎዳል፣ ያንን ሰው በጥላቻ እንመለከተዋለን፡፡ ይህ ብዙውን ጊዜ መሪዎችን ከሚገጥማቸው አደጋ ሁሉ የከፋ ነው፣፡ ቅሬታው እያደገ ይሄድና ቅንዓት ደረጃ ይደርሳል፡፡

የሚቀኑ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለሌላው ማካፈልን ይፈራሉ፣፡ የሥልጣን ክፍፍል ከሌለ ደግሞ የጌታ ሥራ ይጎዳል፡፡ ስለዚህ ቅንዓት የሚጎዳው ራሱ

ቀናተኛውንና የእግዚአብሔርን ሥራ ጭምር ነው ማለት ነው፡፡ ቀናተኛ መሪዎች ሌላው ከእነርሱ በልጦ እንዳይታይ ስለሚፈሩ ብቻቸውን ነው ጎልተው መታየት የሚፈልጉት፡፡ በአንድ ወቅት ጴጥሮስ በእንደዚህ ዓይነት የሠይጣን ወጥመድ ሊወድቅ ተቃርቦ እንደነበር ታስታውሳለህን? ዩሐ 21፡ 20-22 አንብብ ፡፡ ሙሴ ግን ለእንደዚህ ዓይነት አደጋ እጁን ከመስጠት አሻፈረኝ ብሏል፡፡ (ዘኍ 11፡26-29)

5) **ኃይልና ሥልጣንን መመኘት**፡- መሪዎችን የሚገጥሙዋቸው አብዛኞቹ ችግሮች በአንድ መንገድ ሠይጣን ለአዳምና ለሄዋን ከጠነሰሰላቸው ኃጢአት ጋር ይያያዛል፡፡ ኃይልና ሥልጣንን እጃቸው እንዲያስገቡ ነበር ሰይጣን አዳምና ሔዋንን የፈተናቸው፡፡ ይህ የሰው ልጆች ሁሉ ችግር መሆኑን አስተዋይ ክርስቲያኖች አይዘነጉትም፡፡ ሌላው ቀርቶ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንኳ **"ከመካከላችን የሚበልጠው ማነው?"** በማለት ተፎካክረዋል፡፡ የዚህ ዓለም ፍርድ የሚያተኩረው በእውነተኛ ባህርይ ላይ ሳይሆን ሰዎችን ከሰዎች በማወዳደር ላይ ነው፡፡ **"ጥሩ"** ሰው መሆን ማለት ከሌሎች ሰዎች የበለጠ ማለት እንደሆነ እናስባለን፡፡ የዚህ ትምህርት አዘጋጅ በተለያየ ጊዜ **"ለመሆኑ በትምህርታችሁ "A" ብታገኙ ምን ይሰማችኋል?"** በማለት በየጊዜው ለተማሪዎቹ ጥያቄ በማቅረብ ጥናት አድርጓል፡፡ ከጥቂቶቹ በቀር አብዛኞቹ ተማሪዎች ከትምህርቱ በጣም ጠቃሚ እውቀት እንዳገኘንበት ይሰማናል የሚል መልስ ነበር የሰጡት፡፡ አብዛኞቹ ከሌሎች ይልቅ ልቀው የመገኘት ስሜት እንደሚኖራቸው ተናግረዋል፡፡ አብዛኞቹ ንግድና ማህበረሰባዊ ነክ እንቅስቃሴዎች ለሰዎች ደመወዝ የሚከፍሉት በውጤታቸው ልክ ሳይሆን ምን ያህል ከሌሎች በልጠው ወይም አንሰው በመገኘታቸው ነው፡፡ በአብዛኞቹ የማሕበረሰቦቻችን መለኪያ መሠረት ነገሮች ተከናወኑልን ማለት ከሌሎች በለጥን ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ለቤተክርስቲያን እንዲህ ያለ ፍላጎት የለውም፡፡ (ገላ 6፡3-4 ተመልከት)

4) ከሚከተሉት ምሳሌዎች ምን ዓይነት መሪነትን የሚመለከት አደጋዎች ናቸው የሚታዩት? የተማርካቸውን አምስት የመሪነት ችግሮች በመገንዘብ ለእያንዳንዱ ምሳሌዎች የሚስማሙበትን አስቀምጥ፡፡

*ሀ/ ወንድም... ወደዚህ መጥቶ በጸሎት እንዲመራን እጠይቃለሁ፡፡ ወንድም____ ብዙዎችን ወደጌታ ያመጣ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነው፣፡ የኮሌጅ ዲግሪ አለው፣ በብዙ ትልልቅ አብያተክርስቲያናትም ሰብኳል፡፡*

ለ/ "ለመሆኑ እርሷን የመረጣት ማነው?" አለች…. "እንደሚታወቀው ከእርሷ በፊት እኔ እዚህ ነበርሁ፣ ሌተ ተቀን መድከሜንም ሁሉም ያውቃል።"

ሐ/ ቡድኑን በሊቀመንበርነት በመምራት ላይ ነው፣ የተመረጠውም በከፍተኛ ድምጽ እንደሆነም ሰው ሁሉ እንዲረዳለት ይፈልጋል፡፡---------------------------

መ/ የታቀደው የወጣቶች ፕሮጀክት ውጤት አልባ እንደሆነ ቢረዳም ይህን ማንም እንዲያውቅበት አይፈልግም፡፡ ወቅቱ የምርጫ ወቅት እንደመሆኑ መጠን ድጋሚ እንዲመረጥ ፍላጎት አለው፡፡-------

ሠ/ ለብዙ ዘመን በመሪነት ሲያገለግል ቢኖርም እፊት ለፊት ያሉት ወንበሮች ላይ እንዲቀመጥ ስላልተደረገ ቅሬታ አድሮበታል፡፡----

ረ/ በመሪነት ችሎታው የተደነቀ ሰው ነው፣፡ ከሌሎች የሚበልጥ ብቸኛ ውሳኔ እንዳደረገና ያለምንም እርዳታ ሥራውን እንደሚገባ ማከናወን እንደሚችል አስታወቀ፡፡-----------------------------

## ዝለትና መታከት

### ዓላማ 3 በክርስቲያን ሠራተኞች መካከል የሚታየውን ዝለትና የሞራል መላሸቅ መረዳት

**"ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም *ሥራን* ለመ*ሥራ*ት አንታክት"** (ገላ 6፡9)፡፡ ይህ ከላይ የተመለከትነው ጥቅስ ሐዋርያው ጳውሎስ መታከት የሚያስከትለውን ችግር መረዳቱን ያመለክታል፡፡ መሰልቸትንና የ*ሥራ* ተነሳሽነትን አስመልክቶ ማንኛውም ጥናት ከመደረጉ ብዙ ዘመናት በፊት ሰዎች "መልካም *ሥራን*" ለመ*ሥራ*ት ከታከቱ ዝለት እንደሚገጥማቸው ተገንዝቦ ነበር፡፡ የ*ሥራ*ቸው ሁሉ ግብ የሆነውን ለማሳየት ነበር እንደዚያ የተናገረው፡፡ ለዓላማ ሊያነሳሳቸውና ሊያበረታታቸው ይፈልጋል፡፡ ስኬት የሚገኘው ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማ በአእምሮ ሲኖር እንደሆነ ተረድቷል፡፡ ስለዚህም ሌሎችን መርዳትን እንዳይዘነጉ ክርስቲያኖች ያሳስባቸዋል፡፡

አንዳንድ ክርስቲያን ሠራተኞች *ሥራ*ቸውን እርግፍ አድርገው ለመተው ያስባሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ብዙ ይጠብቁባቸዋል፡፡ የራሳቸው ችግርና ደካማነት ቢኖርባቸውም ሌሎችን እንዲረዱ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አንዳንዴ ደግሞ በጥንቃቄ ያወጡት እቅድ ዋጋ ቢስ ይሆንባቸዋል፡፡ ሰዎችን የመርዳት ፍላጎት አላቸው፡፡ ሰዎች

ግን ምንም ዓይነት መሻሻል ሲያደርጉ አያዩም። ከረዷቸው መካከል አንዱም እንኳ "አመስግናለሁ" ሲላቸው አይሰሙም። በዚህ ጊዜ ተስፋ የቆረጠ መሪ **"ምን ዋጋ አለው?"** በማለት ራሱን ይጠይቃል። **"ልፋቴ ሁሉ የትም አላደረሰኝም። ምናልባትም ብቁ ሆኜ ባልገኝ ይሆናል"** ይላል።

በትምህርት 7 ላይ በእውነታ ላይ ስለተመረኮዘ አስተሳሰብ ተነጋግረናል። በዚህ ትምህርት የተመለከትነው ሃሳብ መታከትና ችግርን በተመለከተ አስተዋጽኦ አለው። ክርስቲያን እንደ መሆናችን መጠን ተስፋ መቁረጣችን ራሱ እንኳ የበደለኛነት ስሜት እንዲያድርብን ያደርገናል። ራሳችንን እንወቅሳለን፣ እምነት ስለሌለንም እፍረት ይሰማናል። ሰዎች እንደመሆናችን መጠን ደካማነታችንን ማወቅና ለምን አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን ታካችነት እንደሚያጠቃቸው መመርመሩ ጠቃሚ ነው።

1) **ከፍተኛ ውጥን ስለሚኖረንና ከፍተኛ ውጤት ስለምንጠብቅ፡-** አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ከፍተኛ የሥራ ውጥን ይጀምራሉ፣፡ ከፍተኛ ስሜትና ተስፋ ይኖራቸዋል። እግዚአብሔር ተስፋ እንደማያስቆርጠን ማንኛችንም እናውቃለን። ስለዚህም የተለያየ ችግር ሲገጥመን ራሳችንን እንወቅሳለን። መንፈሳዊነታችን ንና ጥሪያችንንም እንጠራጠራለን።
2) **የተለያየ ፈተናና ችግር ስለምንመለከት፡-** ሰዎች የእኛን እርዳታ ለማግኘት ችግራቸውን ያዋዩናል። ልንረዳቸውም ሙከራ እናደርጋለን። አንዳንድ ጊዜ የረዳናቸው ቢመስለንም ወዲያውኑ ችግራቸው ውስጥ ይገባሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እርዳታችንን አይቀበሉም። የአንዳንዶቹም ችግር ከአቅማችን በላይ ስለሚሆንብን ልንረዳቸው እንደማንችል ይገባናል።
3) **በቂ ነገሮች ሳይኖሩን ሥራ ስለምንጀምር፡-** ብዙውን ጊዜ ሥራችንን የምንጀምረው በቂ ገንዘብ ሳይኖረን ወይም ያለምንም ገንዘብ ይሆናል። ለሥራው የሚያስፈልገን ነገር ይሟጠጣል፣ አንዳንዴም ከሥራው ስፋት አንፃር በጣም ጥቂት ሠራተኞች ብቻ ይኖሩናል። ይህ ሁሉ ተደራርቦ ውጥረትና የዓላማ መጨናገፍ ያስከትልብናል።
4) **በሰዎች ተስፋ እንቆርጣለን፡-** የክርስትና ሥራ ከሰዎች ጋር የሚሰራ ሥራ ነው፣፡ ሰዎች ደግሞ ሁልጊዜ እንደምንጠብቅባቸው አይሆኑልንም። እንበሳጫለን፣ ስሜታችንም ይጎዳል። ፍርዱን ለእግዚአብሔር ከመስጠት ይልቅ በራሳችን መስፈርት መሠረት ሰዎች ላይ መፍረድ እንጀምራለን።

5) **አካላዊና ስሜታዊ ኃይላችን ይሟጠጣል፡-** ታላቅና ብርቱ የእግዚአብሔር ሰው እንኳ አንዳንድ ጊዜ ዝለት እንደሚገጥመው ነቢዩ ኤልያስ ምሳሌያችን ነው። (1ነገ 19፡3-5፣ 10፡14) ብዙ እንሰራለን፣ ሥራችን ግን የተጠበቀውን ውጤት አያስገኝም። የጌታን ሥራ በመሥራታችን ድል አድራጊነት ሲሰማንም ገና ብዙ መሥራት እንዳለብን ስናይ አንረካም። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ደግሞ ውሎ አድሮ የሥራ ወኔ መላሸቅን ያስከትላል። ኤልያስ እንዳደረገው ሁሉ ሞታችንን እንመኛለን። በመጨረሻም **"ምን ዋጋ አለው? እዚህ ላይ ማቆም አለብኝ"** የሚል ውሳኔ ላይ እንደርሳለን። ይህ ብዙ ክርስቴያን ሠራተኞችን በየጊዜው የሚገጥማቸው አደገኛ ችግር ነው።

6) ቀጥሎ ራስህን ለመመርመርና ለመገምገም የሚረዱ አንዳንድ ሃሳቦች ቀርበዋል። በጥንቃቄ አንብባቸውና መልስህን ደብተርህ ላይ አስፍር። መታከትና ተስፋ መቁረጥ የደረሰብህን ጊዜ ታስታውሳለህ? የዚህ ምክንያቱ ምንድነው?-------------
-----------------------------------

7) በእያንዳንዱ እውነተኛ ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ/ ክርስቲያን ሠራተኞች መሰላቸትን ማስወገድ መቻል አለባቸው።

ለ/ አገልግሎትን ለማቆም በመፈለጉ እግዚአብሔር ኤልያስን ገስጾታል።

ሐ/ አካላዊ ችግር ወደ መሰላቸት ሊያደርሰን ይችላል።

መ/ ራስን መጠራጠርና መውቀስ ትሕትና አይደለም።

ሠ/ አንድን ሰው ለመርዳት መፈለግና ለመርዳት አለመቻል አንድን እውነተኛ ክርስቲያን በጣም ያሳዝነዋል።

ረ/ በሌሎች ላይ መፍረድ በራሳችን ላይ ችግር ያመጣል።

ሰ/ በጌታ ሥራ ውጤት ካገኙ በኋላ መሰላቸት ሊያድርባቸው ይችላል

ሸ/ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሕንፃዎች ለመሳሰሉ ቁሳዊ ነገሮች ደንታ የላቸውም።

## ተነሳሽነት፡- የስኬታማ አመራር ቁልፍ

## ዓላማ 4 የተነሳሽነት ጽንስ ሃሳብን ለመግለጽ

ተነሳሽነትን በጽንስ ሃሳብ ደረጃ ያስቀመጥንበት ምክንያት ምንም እንኳ ስለተነሳሽነት የምናውቀው ነገር ቢኖረንም በቀጥታ ልናየው ወይም እንደሚገባ

ልንገልጸው ባለመቻላችን ነው። ፍቅርንና ርህራሄን እንደመሳሰሉ ጽንስ ሃሳቦች ሁሉ ተነሳሽነትንም የሰዎችን ጸባይ በመመልከት ልንረዳው ብንችልም ልንገልጸው ግን አንችልም። ከሰዎች የሥልጣኔ እንቅስቃሴ ተነሳሽነት እንዳለ እናውቃለን። በመጠኑም ቢሆን እንኳ ተነሳሽነትን የምንገልጽበት መንገድ ከአንድ የሥራ እንቅስቀሴ ወይም ጸባይ በስተጀርባ ያለ ግፊት በሚለው ዐረፍተ ነገር ነው።

በአንድ መንገድ ይሁን በሌላ ስዎች ሁሉ ተነሳሽነት አላቸው። አንድ ሰው ተነሳሽነት የለውም ስንል በማንኛውም ነገር ስሜት እንደሌለውና ምንም ዓይነት የሥራ እንቅስቃሴ ሲያደርግ አንመለከተውም ማለት ነው። ክርስቲያኖችም ተነሳሽነት ሲያጡና በቀላሉ ተስፋ ሲቆርጡም ተመልክተናል። በአንድ ወቅት በጣም አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸው ግቦች ላይ ለመድረስ የነበራቸው ጉጉትና ፍላጎታቸው ቀዝቅዟል። አእምሯቸውን ግባቸው ላይ ማድረግ ለክርስቲያኖች ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ሐዋርያው ጳውሎስ የሰጠውን ምክር አንብበናል። ተነሳሽነታቸው እንዲያይልና እንዲበረታ ይመከራቸዋል። ክርስቲያን መሪዎች ተነሳሽነትን እንዲያዳብሩና የመታከትና የመዛልን ችግር የሚያስወግዱባቸው አንዳንድ ተግባራዊ ሃሳቦች ተሰጥተዋል። ቀጥሎ ያሉትም ጥቂቶቹ ናቸው።

1/ መሪነት ጥሪ መሆኑን አትዘንጋ።

2/ ስለመንፈሳዊ ስጦታዎች እግዚአብሔርን አመስግን፤ ዘወትር ተጠቀምባቸው።

3/ በግልህ ከእግዚአብሔር ጋር የምታሳልፈው ጊዜ ይኑርህ።

4/ መጽሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ አንብብ፤ እውቀትህን ለማዳበርም በአጋዥ የጥናት መጽሐፍት ተጠቀም።

5/ ጠቃሚ መንፈሳዊ መጻሕፍትና ክርስቲያን ጽሑፎችን አንብብ።

6/ ዘወትር መንፈሳዊ የአምልኮ ፕሮግራሞችን በታማኝነት ተከታተል።

7/ ሊረዱህ የሚችሉ ኮንፈራንሶችና ሴሚናሬዎችን ተካፈል።

8/ ከቤተሰብህና ከቅርብ ወዳጆችህ ጋር ጣፋጭ ጊዜ ይኑርህ።

9/ ለጤናህ ትኩረት ስጥ፤ ለሰውነትህም አስፈላጊውን እንክብካቤ አድርግ።

10/ ለጌታ ታማኝ መሆንን እንጂ ከራስህ ፍጹምነትን አትጠብቅ

7/ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ አንበባቸው፣ አሰላስላቸው፣ ራስህን ለመመርመሪያም ተጠቀምባቸው ። ከዚያም ለእያንዳንዱ ጥያቄ የምትሰጠውን መልስ በማስታወሻ ደብተርህ አስፍር።

ሀ/ ባለፈው ጊዜ የገጠመህን ዝለትና መሰላቸት እንዴት ነበር የተወጣኸው?
ለ/ አሁን ወይም ወደፊት የሚገጥምህን ተስፋ መቁረጥና መሰላቸት እንዴት እንድምትወጣው ታስባለህ?
8/ ከሚከተሉት ውስጥ ተነሳሽነት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ በትክክል ሊገልጽልን የሚችለው የትኛው ነው?
ሀ/ ከአንድ ሰው በስተጀርባ ሆኖ ሥራውን በቀላሉ ለማከናወን እንዲችል የሚያግዝ የድርጅት መሪ
ለ/ አንድ ሰው በአንድ አቅጣጫ ሲንቀሳቀስ ወይም ሥራን ሲያከናውን የሚያሳየው ስሜትና ጉጉት
ሐ/ በተፈጥሮ ችሎታ፡ በሥራ ወይም በሥልጠና ባገኘው እውቀት አማካይነት ሥራውን ለማከናወን የሚያስችል ኃይል

**የተነሳሽነት ገለጻ አስተያየት**

**ዓላማ 5 ስለ ዋና ዋናዎቹ የተነሳሽንት ጽንስ ሀሳቦች ምሳሌ የሚሆኑ ነገሮችን ለመግለጽ**

ክርስቲያን መሪ ቀና ግፊት እንዳለውና እግብ ላይ ለመድረስም ብርቱ ተነሳሽነት ሊኖረው እንደሚገባ ተመልክተናል፡፡ ይህ ግን ጅማሬ ብቻ ነው፡፡ ከዚያም ሌሎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸውም መርዳት አለበት፡፡ ይህን ለማድረግም ስለተነሳሽነት ምንነትና አንዳንድ ሰዎች ለምን ተነሳሽነት እንደሚጎድላቸው መረዳት ይኖርበታል፡፡

ብዙውን ጊዜ ሰዎች የሚጠበቅባቸውን ያህል ምሬት አይቀበሉም፤፡ ለምሳሌ ያህል አንዳንዶች ይቀራሉ፤ ሌሎች ዘግይተው ይመጣሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ በሚገባ አይዘጋጁም፤ አንዳንዶች የተሰጣቸውን መመሪያ በትክክል አይከተሉም፤ ወይም ከሌሎች ጋር ተስማምቶ መሥራት ያቅታቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሲገጥመው መሪው **“የተነገራቸውን በትክክል አይሠሩም፤ ትክክለኛ ግንዛቤ የላቸውም፤ የጌታን ሥራ ለመሥራት ቅንዓት የላቸውም”** የሚል መደምደሚያ ላይ ይደርሳል፡፡

ከዚህ በኋላ ደግሞ በርትታችሁ ሥሩ በማለት ስብከት ይጀምራል፡፡ ስለ ተቀድሰው ክርስቲያናዊ ተግባር አጠንክሮ ይናገራል፡፡ ምናልባትም ሰዎች እንደሚገባ

የማይሰሩት ፈቃደኝነት ስለሌላቸው ይመስለዋል፣፡ ይህ ግን ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

ሰዎች መሪውን እንደሚገባ የማይከተሉት ችሎታ ስለሌላቸው፣ በቂ መረጃ ስላላገኙ፣ በግል ችግራቸው ወይም ደግሞ በሌሎች መሰናክሎች ሊሆን ይችላል፡፡ ለምን ሠራተኞቹ እንደሚገባ እንደማይሰሩ፣ በእቅዱ መሰረትም ሥራው ለምን እንደማይከናወን መርምሮ ማግኘት ከመሪው ከሚጠበቅ ኃላፊነት አንዱ ነው፡፡ በስብከትና ሠራተኞችን በማለዋወጥ ችግር ሁሉ ይቃላላል ብሎ ማሰብ ትልቅ ስሕተት ነው፡፡ ሰዎችን ለዓላማ ማነሳሳትና ተነሳሽነታቸውንም በተገቢው ሥፍራ ማዋል ለችግሩ የተሻለ መፍትሔ ይሆናል፡፡ ስለተነሳሽነት የተለያዩ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡ ምናልባትም ሁሉም ሙሉ ለሙሉ ትክክል ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ውስብስብ ጉዳዩ በተሻለ መልክ ለመገንዘብ የየራሳቸው አስተዋጾ አላቸው፡፡

**ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ጽንስ ሃሳብ**

እያንዳንዱ ሰው ራሱን የቻለ ፍላጎት አለው፣፡ ይህንንም ፍላጎቱን ማሟላት ይገባል፡፡ ምናልባትም ፍላጎቱን መሠረት በማድረግ ከቀረቡት ሕገ-ነቢቦች በጣም የታወቁት ማስሎው የሚባል ምሁር ያቀረባቸው ናቸው፡፡ በማስሎው ሕገ-ነቢብ መሠረት ሰዎች አምስት ዓይነት ፍላጎቶች አሏቸው፡፡ እነርሱም፡-

1/ ቁሳዊ ፍላጎቶች (ምግብን... ወዘተ የመሳሰሉ)፣ 2/ አካላዊ ደህንነትን የማግኘት ፍላጎት ፣ 3/ ማሕበራዊ ዋስትናን የማግኘት ፍላጎት፣ 4/ በሌሎች ተቀባይነት የማግኘትና የመከበር ፍላጎት፣ 5/ የስኬትና የመከናወን ፍላጎት ናቸው፡፡

በዚህ ጽንስ ሃሳብ መሠረት ሰዎች እነዚህ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ተነሳሽነትን ያሳያሉ፡፡ የሌሎችን ፍላጎት ለማርካት ከመነሳሳቱ በፊት ለአንድ ሰው የምግብ ፍላጎቱን የመሳሰሉ መሠረታዊ ችግሮቹን ማሟላት ይገባል፡፡ ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ከተራብ የምግብ ፍላጎቱን ማሟላት እንጂ አንድ ዓይነት የፈጠራ ሥራ ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ ተነሳሽነት ላይኖርው ይችላል፡፡ ስሜቱ ከተጎዳ ወይም ሰዎች በትክክል እንዳልተረዱት ካወቀ ደግሞ ግቦች ላይ ለመድረስ መሪው በሚያቀርበው ሃሳብ ስሜት አይኖረውም፡፡

ሌላው ፍላጎትን መሠረት በማድረግ የቀረበው ደግሞ የኤፍ ኤል ሐርዝ በርግ ሕገ-ነቢብ ነው፡፡ እንደዚህ ሰው አስተሳሰብ ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሰዎች

ሁለት ፍላጎቶች አሏቸው፡፡ አንደኛው ከሥራው የሚያገኘው እርካታ ነው፡፡ ይህም ማለት ሰዎች የተወሰኑ ጥቅሞችንና ኃላፊነትን ካገኙ ከሥራቸውም ምሥጋናና ታዋቂነትን ካገኙበት ለሚሰሩት ሥራ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በሥራው ዙሪያ ያሉ ሁኔታዎች የመስተካከል ፍላጎት ነው፡፡ ንግድ ነክና አትራፊ በሆነው ዓለም ይህ ደመወዝንና የስራ ሁኔታን ለመለካት ይችላል፡፡ በክርስቲያናዊ ሥራ ግን ከመሪውና ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ያለውን መቀራረብና የተሰጠውን ሥራ እንደሚገባ ለመወጣት የሚያስችሉ ነገሮች አቅርቦት ሊሆን ይችላል፡፡

**ሽልማትና ቅጣት መሠረት ያደረገ አስተያየት**

የመሸለምና የመቀጣት ጽንስ ሃሳብ ሰዎች ደስታን ወይም ሽልማትን የሚያስገኝላቸውን ሥራ ሲሰሩ ጉዳት፣ ሕመም፣ ቅሬታ ወይም ቅጣት የሚያስከትልባቸውን ሥራ ያስወግዳሉ የሚለውን ሃሳብ ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በሥራው ዓለም ይህ ጽንስ-ሃሳብ ያለውን አንድምታ ስንመለከተው ደግሞ ለመልካም ፀባይ መሸለም የማይፈልግ ነገር ግን በቸልታ ማለፍ ወይም አለመሸለም ማለት ነው፡፡

**ግብን መሠረት ያደረገ ጽንስ ሃሳብ**

ይህ ግብን መሠረት ያደረግ ሕገ-ነቢብ ዓላማዎችን ስለመምታት ከተማርነው ጋር በጣም ይቀራረባል፡፡ ይህንን ሃሳብ መልክ ባለው ሁኔታ ያስቀመጠው እ.ኤ. ሎክ የተባለ ሰው ሲሆን፣ የደረሰባቸውም ግኝቶች ሰዎች ግልጽና ጥርት ያለ ግብ ከተቀመጠላቸው ለስኬታማ የሥራ እንቅስቃሴ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ ከቀላል ግቦች ይልቅ አስቸጋሪና ተፈታታኝ የሆኑ ግቦች ሠራተኞቹን ይበልጥ ያነሳሳሉ ይላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ግቦቹ ተጨባጭና እውነታ ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው የሠራተኞች የሥራ ውጤትና ያደረጉት ጥረት በሪፖርት መልክ ከተገለጸላቸው እግቦቹ ላይ ለመድረስ የበለጠ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ የመሪው ድጋፍና በሥራው የሚያደርገው ተሳትፎ የተሻለ የሥራ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይበልጥ ያነሳሳቸዋል፡፡

***ግንዛቤን መሠረት ያደረገ ጽንስ ሃሳብ***

በሰዎች ፀባይ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን እንደሚሉት አንድ ሰው ያለው ፀባይ በሙሉ የአካባቢው ውጤት ነው፡፡ እንዲሁ ላይ ላዩን ስንመለከተው ይህ አባባል በጣም ቀላልና ተራ ይመስላል፡፡ ይሁን እንጂ የግለሰቦች ግንዛቤ ምን ያህል የተለየየ እንደሆነ ስንረዳ የሚመስለንን ያህል ቀላል እንዳልሆነ እናውቃለን፡፡ እንዲህም ሲባል የተለያዩ ግለሰቦች አንድን አካባቢ በተለያየ አመለካከት ያዩታል ማለት ነው፡፡ (ይህንንም ይበልጥ ለመረዳት በትምህርት 5 ስለ ግንዛቤ የተሰጠውን መመልክት ትችላለህ)

አንዲት በሰሜን አሜሪካ የምትኖር ሴት ከሞቃታማ አካባቢ የመጣችን ልጅ ደስ ለማሰኘት ካላት ፍላጎት የተነሳ ይዛት ወደ ከተማ ሄደችና አንድ ዓይነት ምግብ ገዛችላት፡፡ ምግቡ ወተትና ስኳር የተቀላቀለበትና በጣም የቀዘቀዘ ነበር፡፡ ተመሳሳይ ምላሽ ከልጅቱ እየጠበቀችም **“እንቺ ይህን አይስክሬም”** አለቻት፡፡ ልጅቱ አይስክሬሙን አፏ ውስጥ አስገባችው፡፡ ወዲያውኑም **“በጣም ያቃጥላል”** በማለት ተፋችው፡፡ ይህች ከሐሩራማ አካባቢ የመጣች ልጅ እንደዚያ ያለ ምንም ዓይነት ቀዝቃዛ ነው ብላ ለሰጠቻት ምግብ ልጅቱዋ ግን ደስ የማይልና የሚያቃጥል ግንዛቤ ነበር ያሳደረባት፡፡

በዚያ ሥፍራ ብትሆን ኖሮ ልጅቱን መቆጣትና ለተደረገላት ነገር ምስጋና ቢስ እንደሆነች ልትነግራት አትችልም፡፡ ቀዝቃዛውን ከሞቃት ለይታ ባለማወቋም ልትገስጻት አትችልም፡፡ ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ መሪዎች የዚህ ዓይነት ስህተት ሲፈጽሙ ይታያል፡፡ ሰዎች ለምን የዚያ ዓይነት ግንዛቤ እንዳላቸው ለመረዳት ከመሞር ይልቅ ይቆጣሉ፤፡ ሊሰብኳቸውም ይጀምራሉ፡ እዚህ ላይ ነገሮችን በሰዎች ሥፍራ ሆኖ መመልከትንና በእነርሱ ዓይን ማየት ይጠይቃል፡፡

እዚህ ላይ አካባቢ ስንል ሌሎች ሰዎችንም ጨምሮ እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡ ምናልባትም ልጅቱ ሴትየዋ ልትጠቅማት ሳይሆን ልትጎዳት እንዳሰበች ገምታ ይሆናል፡፡ ይህም ሊያስቆጣት ወይም ሊያናድዳት ይችል ይሆናል፡፡ ስለዚህም ከሰዎች ጋር ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጡና መግባባቱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በድጋሚ ሊያሳስበን ይገባል፡፡ (እንዴት እንደምንናገርና እንደምናደምጥ)

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ሰዎች እኛ ወዲያውኑ ልንረዳው የማንችለው ዓይነት የራሳቸው የተለየ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ባለበት ደረጃ ወይም ስራ ብቁና

በጣም አስፈላጊ ነው የምንለው ሰው ስለራሱ ያለው ግንዛቤ የማይጠቅምና ለምንም የማያስፈልግ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው ደግሞ ሌሎቹን የሚረዳ ዓይነት ሰው እንደሆነ ያስባል፣፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ችግር ፈጣሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ከሰዎች ጋር ለመሥራት ከፈለገ መሪው የእነዚህን ሦስት የግንዛቤ ዓይነቶችን አስፈላጊነት መረዳት ይኖርበታል፡፡ እነርሱም የአካባቢው ግንዛቤ፡ ስለሰዎች ያለን ግንዛቤ (መሪውን ጨምሮ) ስለራሳችን ወይም ሌሎች ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤ ናቸው፡፡

9/ እያንዳንዱ የተነሳሽነት ጽንስ ሀሳብ በትክክለኛው ምሳሌ ፊት አስፍር፡-

1/ ግንዛቤን መሠረት ያደረገ ሕገ-ነቢብ

2/ መሸለምና መቀጣትን መሠረት ያደረገ ሕገ-ነቢብ

3/ ግብን መሠረት ያደረግ ሕገ-ነቢብ

4/ የሰዎችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ሕገ-ነቢብ

--------ሀ/ አንድም ቀን እንኳ ከክፍል ቀርቶ ባለማወቅ ሪኮርድ የተያዘለት አስተማሪ ስም በአክብሮት ማስተወቂያ ሠሌዳ ላይ ተጠቀሰ፡፡

----ለ/ የሌሎችን ያህል ብቁ ነኝ ብላ ባለማሰብዋ ማሪያ የተሰጣትን ሥራ መቀበል አልፈለገችም፡፡

----ሐ/ በቡድኑ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑን እንዲያውቅ መሪው አንድን አዲስ ክርስቲያን በኮሚቴው ውስጥ እንዲሰራ መረጠው፡፡

---መ/ መሪው "እስከሚቀጥለው የልደት በዓል ድረስ በርትተን ከሰራን በእሑድ ትምህርት ቤታችን ውስጥ 300 ተማሪዎች ሊኖሩን ይችላሉ" አለ፡፡

**መሪዎች ሌሎችን እንደሚያነሳሱ**

**ዓላማ 6 ስለ አመራር ያሉን ሦስት የምላሽ ዓይነቶች**

በጌታ ሥራ የተሳካ ውጤት ከማስመዝገቡም በላይ ሥራውን በቀና ዓላማ የመሥራትን አስፈላጊነት ተመልክተናል፡፡ መሪዎች ሥራቸውን የሚሰሩት ለጌታ ባላቸው ፍቅርና ለጥሪያቸውም በመታዘዛቸው መሆን አለበት፡፡ ተመሳሳይ ዓይነት ተነሳሳሽነት እንዲኖራቸውም ሌሎችን ይረዳሉ፡፡ ይህንንም ለማድረግ ሰዎች ስለአመራር ያሉዋቸውን ሦስት ዓይነት አመለካከቶች መረዳቱ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

**1/ ጭፍን ታዛዥነት፡-** ብዙ ሰዎች ተቀባይነት ለማግኘት መልካም ነገር ማድረግን ይፈልጋሉ፡፡ መሪው ሥራቸውን እንዲቀበልላቸው ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህም በተቻላቸው መጠን ተባባሪ ሆኖ ለመገኘትና ማንኛውንም ዓይነት አለመግባባት ለማስወገድ የሚሰጣቸውን መመሪያ አሜን ብለው ይቀበላሉ፡፡

መሪው የነገራቸውን ሁሉ ይሰራሉ፡፡ ይህ ግን ራሱን ለዓላማ ያልሰጠ ተዛዥነት ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ምላሽ የሚያገኑ መሪዎች ብርቱና ተቀባይነት እንዳገኑ ያስባሉ፡፡ ትእዛዝ ይሰጣሉ፣ ሰዎችም ይቀበሏቸዋል፡፡ ሥራውም ይሰራል፡፡ እርግጥ ነው እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አስፈላጊ የሚሆንበት ወቅትም አለ፡፡ ሁልጊዜ ሰዎች የመሪውን ዓላማ አይረዱም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሰዎች በመሪው ላይ የሚታመኑበትና የነገራቸውን ሁሉ ሥራ ላይ የሚያውሉት መሪ በመሆኑ ብቻ አንድ ሕፃን ወላጆቹ የነገሩትን እንደሚቀበል ሁሉ እንዲህ አይነት ሰዎችም ያለምንም ጥያቄ የመሪውን ትእዛዝ ይቀበላሉ፡፡ እውነተኛ መሪዎች እንደዚህ ዓይነቱን ነገር አይቀበሉም፡፡ መሪው በተናገረው ሁሉ በሚስማሙ ሰዎች ይከበባል፣፡ እንዲያድግ አይረዱትም፡፡ አብረውት ከሚሰሩት ሰዎች ጭፍን ታዛዥነትን የሚጠብቅ መሪ ብርቱ የሆነና ተቀባይነት ያገኘ ቢመስለውም በጣም ደካማ በሆነ መሠረት ላይ ነው ሥራውን የመሠረተው፡፡
**2/ መሪውን ለመምሰል የሚደረግ ሙከራ፡-** የዚህ ዓይነት ሰዎች ሥራቸውን የሚሰሩት በስራው ስሜት ኖሯቸው ሳይሆን ለመሪው ካላቸው አድናቆት ብቻ ነው፡፡ በሁሉም ነገራቸው እርሱን መስለው መገኘትን ይፈልጋሉ፡፡ ከመሪው ጋር ጓደኝነትን የመመስረት ፍላጎት አላቸው፡፡ ይህንን የሚያደርጉት በአክብሮት የተነሳ ስለሆነ ከጭፍን ታዛዥነት ይለያል፡፡ የሚሰሩት ለመሪው እንጂ ለዓላማ ወይም ለግብ ራሳቸውን በመስጠታቸው አይደለም፡፡ መሪው ሳያውቀው እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ሊያበረታታ ይችላል፡፣ ውሎ አድሮም ሥራው ይዳከማል፡፡ መሪውም ሆነ የሥራ ባልደረቦቹ ከዓላማቸው ይመለሳሉ፡፡
**3/ የዓላማ አንድነት፡-** ሥራው ይበልጥ ውጤታማ መሆን የሚችለው ሠራተኞቹ የመሪውን ዓላማና ግብ እንደራሳቸው ዓላማና ግብ ሲቀበሉት ነው፡፡ የመሪው ዓላማ የሠራተኞቹ ዓላማ ይሆናል፡፡ ለጌታ ያላቸውን ፍቅር የሚገልጡበት እንደሆነ ስለሚያስቡ ችሎታና ስጦታዎቻቸውን ሁሉ ሥራው ላይ ያውላሉ፡፡ የመሪው ሥራ መመሪያና አንዳንድ ሃሳቦችን መስጠት ብቻ ነው፡፡ እርሱ ራሱ በሥራው እምነት ሰላለው፡ የራሱ

ክርስቲያናዊ ግቦች ላይ ለመድረስም መመሪያዎችን ለመቀበል ግንዛቤ ሰዎች ውስጥ ማሳደር ከቻለ እውነትም የተሳካለት ክርስቲያን መሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

10/ እስካሁን ድረስ ሰዎች ስለአመራር ያላቸውን ሦስት አመለካከቶች ተመልክተናል፡፡ እነዚህን ሦስት አመለካከቶች በቃልህ ከያዝካቸው በራስህ አላለጽ ማስታወሻ ደብተርህ አስፍር፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻልህ ግን እንደገና ተመልከታቸውና የራስህን ገለጻ ለማስፈር ሞክር፡፡ ይህም የተማርኸውን ለመረዳት ያስችልሃል፡፡ ስለዚህም ከትምህርቱ የምታገኘው እውቀት በቃላት ብቻ አይወሰንም፣፡ በቀላሉ ለሌሎች የምታካፍለው የራስህ ሃሳብ ይኖረሃል ማለት ነው፡፡

**እውቀትን ተግባር ላይ ማዋል**

**ዓላማ 7 ሠራተኞችን የሚያነሳሱ የመሪነት ባሕርያት**

ስለ ጽንሰ ሃሳብ ወይም አስተያየት የምናጠናበት ምክንያት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ መሠረት እንዲሆነን ነው፡፡ የአስተያየቱ እውቀት የአንድ ነገር ውጤት ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችለናል፡፡ ለምሳሌ ያህል በፍላጎቶቻቸው መሟላት ሰዎች እንደሚነሳሱ ካወቅን ፍላጎታቸውን ለማወቅና በክርስቲያናዊ አገልግሎት አማካይነትም ለማሟላት ሙከራ እናደርጋለን፡፡ ተጨባጭና በእውነታ ላይ በተመሰረቱ ግቦች ለመሳተፍ ሰዎች ፈቃደኛ እንደሚሆኑ ካወቅን ተገቢውንና ተስማሚውን እቅድ እናወጣለን፡፡

ስለተነሳሽነት ፅንሰ-ሃሳብ ካወቅንና ሰዎች ስለ አመራር ያላቸውን አመለካከት ከተረዳን የታቀደው ግብ ላይ ለመድረስ እንዲሰሩ ማነሳሳት እንችላለን፣ እንደመሪዎችም ምን ዓይነት ፀባይ ማሳየት እንዳለብን እናውቃለን፡፡ ቀጥሎ ያሉት በተማርነው እውቀት ላይ የተመሰረቱ ከአንድ መሪ የሚጠበቁ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚሀ ነጥቦች በሥራውም ዓለም ሆነ በክርስቲያናዊ ሥራ እንቅስቃሴ ተግባራዊና ውጤታማ እንደሆኑ ተደርሶበታል፡፡

1/ **ብቁነት፡-** መሪው የሚሰራውን ማወቅና ብቁነቱን በሚያሳይ ሁኔታ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ እንዲህ ስለተባለ ግን መሪው ምንም ስህተት የማያደርግ ፍጹም መሆን አለበት ማለት አይደለም፡፡ መሪው በራስ የመተማመን ችሎታ ቢጠበቅበትም በምንም ዓይነት ትዕቢተኛ መሆን የለበትም፡፡ ሰዎች ችሎታ ያለውንና አስፈላጊውን መረጃ ለመስጠት የሚችል መሪን ለመከተል ይነሳሳሉ፡፡

2/ **ዓላማ፡-** ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማዎች ካልተቀመጡላቸው ሰዎች እንደሚገባ አይሰሩም፡፡ መሪው ዓላማ ሊኖረውና በተማርነው መሰረትም ዓላማውን በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ መቻል አለበት፡፡

3/ **ሌሎችን ማሳተፍ፡-** ስለፍላጎት ባደርግነው ጥናት ሰዎች ተቀባይነትን ለማግኘትና የፈጠራ ችሎታቸውን የማሳየት ፍላጎት እንዳላቸው ተመልከተናል፡፡ ሥራውን በሚመለከት ውሳኔ የማሳለፉ ተግባር ላይ መሳተፍም ይኖርባቸዋል፡፡ መሪው ሥራንና ኃላፊነትን ማከፋፈል ይኖርበታል፡፡

4/ **ሥልጠናና የእድገት እድል መስጠት፡-** ከሚሰሩት ሥራ የሚማሩና በግላቸውም የሚያድጉበት ከሆነ ሰዎች የተሻለ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ሥራውን እንዴት እንደሚሰሩ በቂ እውቀት ካላቸውም በሥራው ስሜት ያድርባቸዋል፡፡ ስለዚህም ሥልጠናና የመማር እድልን የሚሰጥ መሪ መጨረሻው ግብ ላይ ለመድረስ በሁለት አቅጣጫ እየሰራ ነው ማለት ነው፡፡

5/ **መሸለም፣ እውቅና መስጠትና ማድነቅ፡-** በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ሰዎች አንድ ሽልማት ለማግኘት ነው የሚሰሩት፡፡ ጳውሎስ ከተናገረው እንደተማርነውም መጽሐፍ ቅዱስ አእምሮአችንን ዘላለማዊ ሽልማቶቻችን ላይ እንድናደርግ ነው የሚያበረታታን፡፡ እውነተኛ መሪዎችም ሰዎች ለጌታ በሚያደርጉት አገልግሎት ሁሉ ሽልማት የሚያገኙበት እንደሆነ ያሳስባሉ፡፡

ስለመዛልና መሰላቸት፣ እንዲሁም ግንዛቤዎችን በተመለከተ ካደርግነው ጥናት ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ይደክማሉ፣ ተስፋም ይቆርጣሉ፡ ዋጋ ወይም ተቀባይ እንደሌላቸው ያስባሉ፡፡ ይህም ከዓላማቸው ያዘናጋቸዋል፡፡ እውነተኛ መሪ ሠራተኞቹን ያደንቃል፣ አድናቆቱንም በአንደበቱ ይገልጽላቸዋል፡፡ ጳውሎስ አብረውት ለሚሰሩ ሰዎች አድናቆትን የመግለጽ ልማድ እንደነበረው ከተሰጡት መጽሐፍት ምንባቦች ተመልክተናል፡፡ ሥልጣንን የተቀበለው ለማነጽና ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ እንዳልሆነ የተናገረውን አሰተውል፡፡ (2 ቆሮ 13፡10)

ትክክለኛ ዓይነት ተነሳሽነትን በትክክለኛ ዓይነት ሽልማት ማበረታታት እንደሚቻል ተመልክተናል፡፡ የተጋነነ ምሥጋናና ሙገሳ ወደ ትዕቢት ሊመራ በእውነት ላይ የተመሠረተ ምሥጋና ግን ሰዎችን በተሻለ ሁኔታ ለዓላማ ያነሳሳቸዋል፡፡

6/ **ስለሥራው ሁኔታ መረጃ መስጠት፡-** የሥራቸውንና የጥረታቸውን ውጤት ሲረዱና ከመጀመሪያ አንስቶ እስከመጨረሻ ድረስ የሥራውን ልክ ሲያውቁ ሰዎች በበለጠና

በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ፡፡ ለሥራዎች የጊዜ ገደብ መስጠትና በየጊዜውም ሪፖርት ማቅረብ ሞቅ ካለ ንግግር ይልቅ ሰዎችን ለሥራ እንደሚያነሳሳ መልካም መሪ በሚገባ ያውቃል፡፡ አንድ ሥራ መሰራት ካለበት ሰዎች የሥራቸውን ውጤት ማወቅ አለባቸው፣፡ ተገቢው ግምገማም ሊደርግላቸው ይገባል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ሥራ ይሰጣቸዋል፣፡ የተሰጣቸውን ሥራ በወቅቱ መፈጸማቸውን እንዲያውቁም ወቅታዊ ሪፖርት ይደረግላቸዋል፡፡ እንደዚህ ከተደረገ በአዲስ ስሜት ይነሳሳሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ ያለማቋረጥ ሲሰሩና በትክክል ይስሩት አይስሩት ሌሎች ደንታ የሌላቸው መሆኑን ሲያውቁ ነው፡፡

11-14 በእያንዳንዱ ትክክለኛ መልስ ፊት ያሉትን ፊደሎች ክበባቸው፡፡

11/ ሰዎች ለመከተል የሚነሳሱት፡-

ሀ/ በማንኛውም ሁኔታ ብቁ የሆነውን ሰው ነው

ለ/ ብቃት እንደሌለው የሚነግራቸውን ሰው ነው

ሐ/ በሚሰራው ሁሉ በራሱ የሚተማመነውን ሰው ነው

መ/ ያለምንም ትዕቢት ብቃቱን በሚያሳይ ሰው ነው

12/ ሰዎች ለመከተል የሚነሳሱት

ሀ/ መሪው ትልቅ እምነት እንዳለው የሚያመለክቱ ግቦችን ነው

ለ/ አስቸጋሪ፣ ሆኖም ግን እውነታ ላይ የተመሰረቱ ግቦችን ነው

ሐ/ በቀላሉ የሚደረስባቸውን ግቦች ነው

መ/ ንግግር የማድረግ ችሎታ ያላቸው መሪዎች የሚያቀርቡትን ግቦች ነው

13/ የሰዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገው ሕገ-ነቢብ እንደሚለው መሪዎች፡-

ሀ/ የሰራተኞቻቸውን ፍላጎት ሁሉ ማሟላት አለባቸው

ለ/ ለሁሉም ሠራተኞች እኩል የሥራ ድርሻ መስጠት አለባቸው

ሐ/ ሥራቸውን እየሰሩ ፍላጎታቸውን የሚያሟላ ዕድል መስጠት

መ/ ችሎታ ላላቸው ሠራተኞች ከባዱን የሥራ ድርሻ መስጠት አለባቸው

14/ የሥራ ጊዜ ገደብና ሪፖርት ማቅረብ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት፡-

ሀ/ ስለሥራቸው እንዲያውቁና የሥራ ኃይላቸውን እንዲያድሱ ነው

ለ/ መሪው ብቁ እና ለሥራው ራሱን የሰጠ መሆኑን ስለሚያሳይ ነው

ሐ/ በቤተክርስቲያኒቱ ጊዜ ሠሌዳ መሠረት ሥራው መጠናቀቅ ስላለበት ነው

መ/ የሥራው ቀጠሮ በተሰጠው ጊዜ መከናወን ስላለበት ነው

15/ እያንዳንዱን ከመሪነት የሚጠበቁ ባሕርያት (ከ1-6) ከትክክለኛው ገለጻ ጋር (ከሀ-ረ) ካሉት ጋር አዛምድ፡- 1/ ብቁነት 2/ ዓላማ 3/ የተሳትፎ ዕድልን መስጠትና ሠራተኞችን ማሳተፍ፣ 4/ ሥልጠናና የእድገት ዕድልን መስጠት፣ 5/ ሽልማት፣ ታዋቂነትንና አድናቆትን መግለጽ 6/ መረጃና ተሐድሶን መስጠት

---ሀ/ ሥራቸውንና የጥረታቸውን ውጤት ሲያውቁና የሥራውንም ሂደት ጅማሬ አንስቶ እስከ መጨረሻ ድረስ አጥርተው ማየት ከቻሉ ሰዎች የተሻለ የሥራ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ።

----ለ/ አንድ እውነተኛ መሪ ሠራተኞቹን ያደንቃል፣ አድናቆቱንም ይገልጽላቸዋል

---ሐ/ ሠራተኞቹ ለመከተል የሚነሳሱት ችሎታ ያለውንና ሌሎችን መርዳትና አስፈላጊውን መረጃ መስጠት የሚችልን መሪ ነው።

---መ/ ሰዎች በግል ሕይወታቸው መማርና ማደግ ከቻሉ በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ። እንዴት እንደሚሰሩ ካወቁም በሥራው የበለጠ ስሜት ይኖራቸዋል።

---ሠ/ መሪው ለሠራተኞቹ በአንዳንድ ሁኔታዎችን ኃላፊነትን ማካፈል አለበት

---ረ/ በእውነታ ላይ ወደተመሰረቱ ግቦች የሚያደርሱ ግልጽና ጥርት ያሉ ዓላማዎች ካሉዋቸው ሰዎች በጣም በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ።

## ሩጫ የሚያሻው ግብ

አንድም ጊዜ እንኳ ቢሆን ጳውሎስ በስራው ዝለት ወይም መሰላቸት ደርሶበት አያውቅም። ይህም የሆነበት ምክንያት ብዙ የሚዝናናበት ጊዜ ስለነበረው ወይም ስራውን አቅልሎ በመመልከቱ ሳይሆን እርሱ ራሱ እንደተናገረው ሩጫ የሚያሻው ግብ ስለነበረው ነው። ስለመልካም ተጋድሎ ተናግሯል፣ ስለዚህም ግቦቹ ቀላል አልነበሩም ማለት ነው። ምንም ዓይነት ዋጋ ቢያስከፍለውም በመጨረሻ የተዘጋጀለትን ሽልማት ያውቃል።፣ ስለዚህም ስሜቱ አልቀዘቀዘም (ሮሜ 8፡31-39 እና 2 ጢሞ 4፡7-8) ።

ከጳውሎስ ሕይወትና አገልግሎት እንዲሁም በዚህ ኮርስ ከተመለከትናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርያት ሥራና አገልግሎት እንዳየነው መሪዎች በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ስፍራ አላቸው። አንድም ጊዜ እንኳ ጸሎት ብቻውን ወይም ተአምር ብቻውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ፈጽሞ አያውቅም። እቅዱን ለመፈጸም ኃላፊነቱንና መብቱን ያስቀመጠው እርሱ ራሱ ከአፈር ባበጃቸው ሰዎች እጅ ነው። ከአብዛኛው ሁኔታዎች እንደምንመለከተው እግዚአብሔር በመሪዎች ተጠቅሟል፣፡ እነዚሀ መሪዎች

የሰሩት ብቻቸውን ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር፤፡ ጳውሎስ እንዳደረገው ሁሉ ከሌሎች ቀድመው ወደፊት እየገሰገሱ *"ከአሸናፊዎች እንበልጣለን"* የሚል የድል ጩኸት አሰምተዋል፡፡

**የሙከራ ፈተና**

1/ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙት ለምሳሌ ያህል መታሰሩን በተመለከተ ጳውሎስ ከሚከተሉት ከአንዱ በቀር የመሪነት ችሎታውን ያመለክታሉ፡፡ ጳውሎስን በተመለከተ ትክክል ያልሆኑት ዐረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ/ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጳውሎስ ስለ ሰዎች ኃጢአት፣ ለሌላው ስላላቸው ንቀትና መንፈሣዊ እውርንት ይሰብክ ነበር፡፡

ለ/ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ረጋ ያለ ሰው ነበር

ሐ/ ጳውሎስ ስለሙሴ ሕግ፣ ለለዜጎች ነፃነትና መሠረታዊ የሰዎች ተፈጥሮ ሰፋ ያለ እውቀት ነበረው፣ ስለዚህ የሰጠው ምላሽ በወንጌል ምክንያታዊነት ላይ ያለህን እምነት ያሳያል

መ/ ጳውሎስ ራሱን ከአድማጮቹ ጋር ለማመሳሰል በመፈለጉ እንዴት በጌታ እንዳመነ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታና ያለምንም ፍርሃት ምስክነቱን ሰጥቷል፡፡

2/ ወደ ሮም ባደረገው ጉዞ ጳውሎስ ምርጥ የመሪነት ባሕርያትን አሳይቷል፡፡

ሀ/ የመቶ አለቃውና የመርከቡ አዛዥ ጥሩ ውሳኔ ለማድረግ ችሎታ እንዳልነበራቸው ከተረጋገጠ በኃላ ጳውሎስ  ውሳኔ የማድረጉን ኃላፊነት ያዘ፡፡

ለ/ ተግባራዊ ምክርን ሰጠ፣ ችግር በነበረበት ጊዜ እንኳ እርጋታውን አሳየ፣ አብረው ይጓዙ ለነበሩ ሰዎች ምን ያህል ያስብ እንደነበር ከማስመስከሩም በላይ ለአንድ ግብ እንዲሰሩ አበረታታቸው፡፡

ሐ/ መሪዎቹ ችሎታ አንዳልነበራቸው እስኪረጋገጥ ድረስ ጠበቀ፡፣ ከዚያ በኋላ ለውጤታማነት የሚያቃውን የራሱን ዘዴ ቀየሰ፡፡

መ/ ሁኔታዎቹ እየተባባሱ ሲመጡ ገለልተኛ ሆኖ ተመለከተ፤፡ የእርሱን ምክር ለመጠየቅ እስኪመጡ ድረስም ቆየ፡፡

3/ በደረሰው የመርከብ አደጋ እግዚአብሔር በሚከተሉት አማካይነት በሥፍራው ለነበሩ ሁሉ ተናግሯል፡፡

ሀ/ ሕዝቡን በተአምር ከአደጋ በማዳን     መ/ በመንፈስ የተሞላ አመራርን መስጠት

ለ/ ማዕበሉን ጸጥ በማድረግ የተፈጥሮን እንቅስቀሴ በመግታት

ሐ/ ከአደገኛዎቹ የባሕር ዓለቶች ጋር እንዳትጋጭ መርከቧን በመምራት

4/ በሚከተሉት አራት ምርጫዎች ውስጥ መሪዎችና ሠራተኞች የታቀደው ግብ ላይ እንዳይደርሱ እንቅፋት የሚሆኑ አምስት መሰናክሎች ውስጥ ከሚከተሉት አራት ምርጫዎች ሦስቱ ተዘርዝረዋል፡፡ በትምህርቱ ውስጥ ከተመለከትናቸው መሰናክሎች አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ እኔነት/ትዕቢት ለ/ ታዋቂነትና ምሥጋናን መፈለግ

ሐ/ ፖለቲካዊ ግጭቶችና ሐይማኖታዊ መናናቅ መ/ ቅናትና ሥልጣንን መፈለግ

5/ ይህ የምንኖርበት ዓለም የፉክክር /ውድድር/ መንፈስን የሚበረታታበት ምክንያት፡-

ሀ/ በእያንዳንዱ ግለሰብ ውሰጥ ያለ ተፈጥሮ በመሆኑ

ለ/ የሥራ አፈጻጸማቸው መሠረት በመሆኑ

ሐ/ ከቤተሰቦቻቸውና ከሥልጣናቸው ያገኙት በመሆኑ

መ/ ራሳቸውን ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚያስተያዩበት በመሆኑ

6/ ሰዎች መልካም ነገርን ከማድረግ እንደሚታከቱ ጳውሎስ ሰለተረዳ፡-

ሀ/ ዓላማቸውን እንደሳቱ ሊያሳስባቸው ይሞክራል፡፡

ለ/ ዓላማቸውን በአእምሮአቸው እንዲይዙና ሰዎችን እንዲረዱ ሊያበረታታቸው ይሞክራል፡፡

ሐ/ ስለተሸናፊነት ዝንባሌያቸው ንስሐ እንዲያደርጉና በአዲስ ኃይል እንዲነሳሱ ሊያሳስባቸው ይሞክራል፡፡

7/ ከሚከተሉት ምርጫዎች ከአንዱ በቀር ክርስቲያን ሠራተኞች ከሚታክቱበት ምክንያቶች አንዱ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ/ ክርስቲያን ሠራተኞች ተነሳሳሽነት ስለሚጎድላቸውና ብዙ ስለሚሰሩ

ለ/ በዙሪያቸው ብዙ ችግርና መከራ ሰለሚያዩና አካላዊና ስሜታዊ ድካም ስለሚደርስባቸው፡፡

ሐ/ በቂ ኃይል ሳይኖራቸው ብዙ ስለሚሰሩና በሰዎች ተስፋ ስለሚቆርጡ

መ/ አመለካከታቸው በሙሉ ተስፋ በመሆኑና ብዙ ስለሚጠብቁ

8/ ውጤታማ አመራር እንዲኖር ከተፈለገ መሪዎችን ሥራዎችንና ሠራተኞችን ማነሳሳታቸው በጣም ጠቃሚ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ትምርት መሠረት ተነሳሽነት ሰንል፡-

ሀ/ ከፍተኛ ሰብአዊ ምኞት

ለ/ ሠራተኞች ለመሪው እንዲታዘዙና ሥራው እንዲሰራ ማድረግ

ሐ/ አንድ ሰው ለምን ኃላፊነትን እንደሚቀበል የሚያቀርበውን ምክንያት ማለታችን ነው

9/ አንዳንድ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ሲሟሉላቸው ሰዎች ተነሳሳሽነት ይኖራቸዋል የሚለው አስተያየት፡-

ሀ/ ግብን መሰረት ያደረገ አስተያየት ለ/ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አስተያየት

ሐ/ ሽልማትና ቅጣትን መሰረት ያደረገ አስተያየት

መ/ ግንዘቤን መሰረት ያደረገ አስተያየት

10/ ሰዎች አንድ ዓይነት ደስታን የሚያስገኝላቸውን ነገር ይሰራሉ፣፡ ችግርን ወይም ቅጣትን የሚያስከትልባቸውን ነገር ግን ያስወግዳሉ የሚለው አስተያየት

ሀ/ ግንዛቤን መሰረት የደረገ አስተያየት ሐ/ ግብን መሰረት ያደረገ አስተያየት

ለ/ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አስተያየት መ/ ሽልማትና ቅጣትን መሰረት ያደረገ

11/ ሰዎች ግልጽና ጥርት ያለ ዓላማ ካላቸው ዓላማውንም እንደሚገባ ከተረዱና አብረዋቸው በሚሰሩ ሰዎችም ዓላማውን እንደተቀበሉ ከተረዱ የተሻለ የስራ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የሚለው አስተያየት፡-

ሀ/ ግብን መሰረተ የደረገ ነው ሐ/ ግንዛቤን መሰረት ያደረገ ነው

ለ/ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ነው መ/ ሽልማትና ቅጣትን መሰረት ያደረገ ነው

12/ ሰዎች አካባቢያቸውን ስለሚመለከቱበት ሁኔታ ግምት ውስጥ የሚያስገባ አስተያየት፡-

ሀ/ ሽልማትና ቅጣትን መስረት ያደረገ ነው ሐ/ ግንዛቤን መሠረት ያደረገ ነው

ለ/ ግብን መሠረት ያደረገ ነው መ/ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ነው

13/ አንዳንድ ሰዎች ለመሪው የሚታዘዙት ሕፃናት ለወላጆቻው

ሀ/ ማድረግ ሰላለባቸው ብቻ የሚያደርጉት ታዛዥነት

ለ/ ጭፍን ታዛዥነት

ሐ/ ከመሪው ጋር ተመሳሳይ ለመሆን የሚደረግ ታዛዥነት

መ/ በመገደድ ላይ የተመሰረት ታዛዥነት

14/ ሌሎች ደግሞ ስለሥራው ምንም ደንታ የላቸውም፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች መሪውን በጣም ከማድነቃቸውም በላይ በሁሉም ነገራቸው እርሱን መስለው ለመገኘት ነው የሚሞክሩት፡፡ እንዲህ ያለ ታዛዥነት፡-

ሀ/ ጭፍን ታዛዥነት   ለ/ ታማኝነት   ሐ/ የዐላማ ተነሳሽነት  መ/ መሪውን መስሎ ለመታየት የሚደረግ ሙከራ ይባላል።

15/ ስለ መሪ ሊኖረን የሚገባው ትክክለኛ አመለካከት የመሪውን ዐላማና ግብ የራሳችን ዓላማና ግብ አድርገን መቀበል ነው፣፡ የዚህን አይነቱ ታዛዥነት፡-

ሀ/ መሪውን መስሎ ለመገኘት የሚደረግ ታዛዥነት

ለ/ ጭፍን ታዛዥነት  ሐ/ ስሜታዊ ታዛዥነት   መ/ የዓላማ ተመሳሳይነት ይባላል፡

16/ የሚከተሉትን ቀና ያልሆኑ ዓላማዎች ከትክክለኛ ገለጻቸው ጋር አዛምድ፡-

1/ እኔነት/ትዕቢት   2/ከሚገባ በላይ በራስ መተማመን   3/ ታዋቂነትንና ከሌሎች ምሥጋና መጠበቅ  4/ ቅንዓት 5/ ሥልጣን ፈላጊነት

---ሀ/ ራሱን ከሌሎች ጋር በማወዳደር ምን ያህል ከሌሎች የተሻለ እንደሆነ ለማሳየት ይሞክራል።

----ለ/ ስህተቱን አይቀበልም፡፣ ሁሉንም ነገር በራሱ መንገድ መሥራት ይፈልጋል

----ሐ/ ለሚያደርገው ሁሉ ከሌሎች ምሥጋናና ውዳሴን፣ የተለየ መብትን ይጠብቃል፣ በሰዎች ነቀፋ በቀላሉ ይጎዳል፣ በመንፈሳዊ ስጦታዎቹም ይመካል።

----መ/ ስለዚህ ዓይነቱ ባሕርይ ጳውሎስ ሲናገር "**በሰዎች መመካት አይቻልም**" ብሏል። እንዲህ ዓይነቱ መሪ ከሰዎች ክብርን ይፈልጋል።

---ሠ/ በዚህ ተግባር ምክንያት መሪዎች ብቁ ለሆኑ ሰዎች አመራርን አያካፍሉም፣ መልካም የሥራ አስተዋጽኦ በሚያደርጉ ግለሰቦችም ላይ ቅሬታ ያድርባቸዋል።

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

8/ለ) አንድ ሰው ስሜቱን ወይም ፍላጎቱን ሲያሳይ 1/ መልሶችህ

9/ሀ) 2) ሽልማትና ቅጣትን መሰረት ያደረገ አስተያየት

ሐ/4) ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አስተያየት

ለ/1) ግንዜቤን መሰረት ያደረገ አስተየየት ሕገ-ነቢብ

መ/3) ግብን መስረት ያደረገ አስተያየት

2/ የሰጠሃቸው መልሶች በትምህርት አንድ ወይም ዘጠኝ ከተሰጡት የጳውሎስ ጥቅሶች ወይም ደግሞ ከዚህ ትምህርት የተረዳኸውን መሰረት ያደረጉ ሊሆኑ ይገባል፣ የሚከተሉት ለምሳሌ ያህል ቀርበዋል፡-

ሀ/ ገላ 6፣2   ለ/ ፊል 3፣14   ሐ/ 1ኛ ቆሮ 9፣24-27፣2ኛ ጢሞ 2፣15

መ/2ኛ ጢሞ 4፣5 ሠ/ ኤፌ 4፣16፣1ኛ ቆሮ 12፣4-12 ረ/ፊል 4፣1-3፣ ቆላ 4፡7-14 ሰ/ ሉቃ 9፣62፣ 1ኛ ቆር 15፣ 58 ኤፌ 4፣14

10/ የአንተ መልስ 11/መ/ጳውሎስ ያሳየው ጠቃሚ የመሪነት ባሕርይ ይህ ነው

4/ሀ/ ምስጋና ለ/ ቅንአት ሐ/ ትዕቢት፣ ታዋቂነት፣ እኔነትና ስልጣን

መ/ ታዋቂ የመሆን ፍላጎትና ኃይል ሠ/ ኩራት፣ ምቀኝነትና እኔነት ረ/ በራስ መመካት፣ ኩራትና ኃይል

12/ ለ/ አስቸጋሪ ቢሆኑም እውነት ላይ የተመሰረቱ ናቸው

5/ መልስህ፡- ይህ አይነት ስሜት ሊያድርብህ የቻለው በዚህ ትምህርት ከተዘረዘሩት አንዳንድ ነገሮች የተነሳ ይሆን? ወቅታዊ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ባሻገር የመጨረሻውን ግብ መመልከትን እንደምትማር ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ካልዛልን 13/በሥራው በመሳተፍ ላይ እያሉ ሠራተኞቹ ችግሮቻቸውን የሚያሟሉበት ዕድል ሰጣቸው፡፡

6/ሀ/ ሐሰት (ማንም ሰው ከድካም ወይም ከዝለት ነጻ አይደለም)

ለ/ ሐሰት (በአካልና በነፍስ እንዲጠነክር ጌታ ብርታትን፣ እረፍትንና መጽናናትን ሰጠው) ሐ/ እውነት መ/ እውነት ሠ/እውነት ረ/ እውነት ሰ/ እውነት ሸ/ ሐሰት(እነዚህ ለእለታዊ ኑሯችን የሚያፈልጉን ነገሮች ናቸው) ጌታ እንደሚረዳን መታመንና ከሚገባ በላይ ሊያሳስበን አይገባም፡፡

14/ መረጃንና ተሐድሶ የማግኘትን እድል ይሰጣሉ

7/ መልስህ፡- ከእግዚአብሔር ቃል፣ ከጸሎትና ከሌሎች አማኞች ጋር ሕብረት በማድረግ እንደተጠቀምህ አምናለሁ፡፡ ከተሰጡት የሃሳብ ዝርዝሮችም ወደፊት ሊገጥምህ የሚችለውን በችግር ጊዜ ልትቋቋም የምትችልበትን ዕይታ እንዳገኘህ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ጳውሎስ ያለፈ ስህተቱን በመርሳት ይጽናና ነበር፡፡ በዚህም ምሳሌቱን እንድንከተል ያሳስበናል (ፊል 3፡13፣15)፡፡

15/ ሀ/6) መረጃና ተሐድሶ ለ/5) ሽልማትና ታዋቂነት ሐ/1) ብቃት

መ/4) ሥልጠናና የዕድገት ዕድል መስጠት ሠ/3) ሥልጣንን ማካፈልህ ሠራተኞቹ ተሳትፎ ማድረግ የሚችሉበትን ዕድል መስጠት 2/ ዓላማ

## የሙከራ ፈተና መልሶች

## ትምህርት አንድ

1/ሐ/ ዓላማውን ተግባራዊ የሚያደርግበት መንገድ ነበረው

2/ለ/ ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የመረጣቸው፣ የመራቸውና ኃይል ሰጣቸው

3/ሀ/ ዓላማውን አስቀድሞ ያውቃል፣ እንደት እንደሚፈጽመውም ያውቃል

4/መ/ የሰዎችን ባሕል ማክበር ከመሪነት የሚጠበቅ ነው

5/ለ/ ሌሎች መሪዎችን ይከተላል፣ ሁሉም ጌታን ይከተላሉ

6/ሀ/ ባለሥልጣኖችን ማክበር ለእግዚአብሔር ፈቃድም መገዛት

7/ሐ/ ለሌሎች ማሰብና መጠንቀቅ

8/ሐ/ ለሰዎች መራራት፣ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ያለውን ሥፍራ መረዳት፣ ይቅር ማለትና መውደድ 9/ ትዕግሥትና ጥበብ

10/ ሐ/ ቀድሞ ስላየው ሕልምና ትንቢት ወንድሞቹን አሳሰባቸው

11/ ስሜታዊ መረጋጋት

12/ መሪነትን ከሌሎች ጋር መጋራት

13/ ለሌሎች ማሰብ

14/ ጽናትና ሌሎች እምነት የሚጥሉበት ዓይነት ሰው

15/ ግብን መምታት (ግብ ላይ መድረስ) 16/ የቡድን ሥራ

17/ ብቁ ሆኖ መገኘት

## ትምህርት ሁለት

1/ መ/ ለመርዳት አብሮት መሆን

2/ሐ/ የእግዚአብሔርን ጥሪ አልተቀበለም

3/ሀ/ የበፊቱ ስሜታቸው ይቀዘቅዛል

4/ለ/ ከሌሎች መሪዎች ጋር መካፈል አለበት

5/ለ/ ወደ ጦርነት የማሄዱ መካከለኛ መሪዎች

6/ መ/ ራዕዩን ለማካፈል በሌሎች መታመን

7/ ሐ/ ሙሴ በሕይወት ይኖር ነበር፣ የሰዎቹ ችግርም መፍትሔ ያገኝ ነበር

8/ሀ/ በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለ መልካምን የማድረግ ባሕርይ

9/ ለ/ እግዚአብሔር መሪዎችን የሕዝቡ ኃላፊዎች አደረጋቸው

10/መ/ ስለሕዝብህ የበለጠውን ነገር ተጠባበቅ

11/ መ/ ስለሕዝቡ ያለው እምነት ወይም ግንዛቤ

12/ሐ/ በመሰረቱ ሰዎች እምነት የሚጣልባቸውና መልካሞች ናቸው

13/ ለ/ ከሰዎች ክፍተኛ ነገር መጠበቅ

14/ ምናልባትም ክበብ ያደርግኸው ለ/ እና ሐ ይሆናል፡፡ ግምገማህ ከእኔ በመጠኑም ቢሆን ይለይ ይሆናል፡፡

15/ ምናልባትም ክበብ ያደረግኸው ሀ እና መ ይሆናል፡፡

16/ በአንድ ሰው ዙሪያ የተማከለ የአመራር ስልት

17/ በብዙሐኑ ዙሪያ የተማከለ የአመራር ስልት

18/ በአንድ ሰው ዙሪያ የተማከለ የአመራር ስልት

19/ በብዙሃኑ ዙሪያ የተማከለ አመራር 20/ እውቅና መስጠት

## ትምህርት ሦስት

1/ለ/ሌሎች ችሎታቸውን እንዲያዳበሩ መርዳት

2/ ሐ/ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተለየዩ ችግሮች የተለያየ አመራርን ይጠይቃሉ

3/ ለ/ በየጊዜው በቁጥር የሚያድጉ የሰለጠኑ መሪዎች

4/ ሀ/ በግል መመሪያና ምክር መስጠት

5/ለ/ ለመሪነት ችሎታው ንቁ ነበር

6/ መ/ "ከጥሪው" መሪው የሚያገኘው

7/ሐ/ ሥፍራውንና አካባቢውን ማዘጋጀት

8/ መ/ የሌሎች ሕይወት 9/ሠ/ ከላይ የተጠቀሱት በሙሉ

10/ ለ/ እንደሚገባ አይሰራም 11/ መ/ ለሰዎች በማሰብ ላይ የተመሠረተ

12/ ሠ/ "እንደ ችግሮቹ ሁሉ ውሳኔዎችንም ከሕዝቡ መሸሸግ"

13/ለ/ ሌሎችን ማሳደግ፣ ውጤታማነትህን እንደሚያሰፋልህ ማወቅ

14/ ሀ/ ሌሎችን ይረዳል፣ ብቃት ባላቸው ሠራተኞች ዙሪያ ይሆናል

15/ መ/ "ይህ የእኛ ሥራ ነው" ማለት ያስችልህ ዘንድ ግቦችህንና ውሳኔዎችህን ለሌሎች ማካፈል

## ትምህርት አራት

1/ ሐሰት፡፡ (እኛ ራሳችን ሥራ ላይ ከማዋችላን በፊት እግዚአብሔር ችሎታዎችንና ኃይላችንን ያውቃል፡፡ ይሁን እንጂ የሕይወት ተሞክሮዎቻችን

ጠቃሚ እውቀት ይሰጠናል፣ ይህም ለወደፊቱ አመራራችን ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፣)

2/እውነት 3/ ሐሰት 4/ እውነት 5/ ሐሰት

6/ ሐሰት (ተገቢ ዝግጅት ካላደረግን በቀር ሥራው ዋጋ አይኖረውም)

7/ እውነት 8/ እውነት

9/ ሐሰት (መልካም መሪዎች እቅድና እያወጡ ስለሥራው ያስባሉ፣ ከዚያ በኋላ እቅዳቸውን ተግባራዊ ያደርጋሉ)

10/ ሐሰት(የሚፈለገውን ያህል ወጪ ቢጠይቅም የተሳታፊዎቹ ቁጥር የቱንም ያህል ቢሆንም እቅድ በጣም አስፈላጊ ነው። ጥረታችን መመሪያና ዓላማ ያለው እንዲሆን ያደርጋል፣ አንድን ሥራ ከመጀመሩ በፊት ውጤቱን መገምገም አስፈላጊ ነው)

11/ ሐሰት (እቅድ ማውጣት ማሰብም በጽሑፍ ማስፈርም ነው፣ ብዙውን ጊዜ በሂደት ያለ እቅድ በጽሑፍ ማስፈርንም ይጠይቃል) 18/ እውነት

12/ ሐሰት 13/ እውነት 14/ እውነት 15/ ሐሰት (እንዲህ ያለ ዝግጅት አጠቃላዩን ይረዳ ይሆናል፣ ይሁን እንጂ ማንኛውም እቅድ ቢሆን "ፍጽም" እና የግድ ለጥሩ ውጤት ያበቃል ማለት አይደለም። 16/ እውነት 17/ እውነት 18/ እውነት 19/ ሐሰት (ሰውዬውን ከእርሱ በላይ ወዳለው መሪ ይመራዋል፣ ወይም ደግሞ በውይይቱ እንዲካፈል መሪውን ይጋብዘዋል) 20/ እውነት

**ትምህርት አምስት**

1/ ሐ/ ስለመታዘዝ አጠንክሮ ተናገረ

2/ መ/ በጽሑፍ የሰፈሩ ሃሳብ አስተላላፊዎች

3/ ሀ/ ተምሳሌታዊ ሃሳብን ወይም መልእክትን ለሕዝብ ማስተላለፊያ መንገዶች

4/ ለ/ የመልእክቱን ትርጉም እንደሚገባ መረዳት

5/ ሐ/ ቃላትን በተመሳሳይ መንገድ መረዳት

6/መ/ የግንኙነት መስመሩ ተቋርጧል 7/ ሐ/ ተቀባይ የሚገነዘበው

8/ ለ/ የሚናገሩት ሁሉ በትክክል ለሰሚዎቹ ይደርሳል

9/ መ/ መልእክቱን መረዳት፣ ልባችን መዝገብ ውስጥም ማኖር

10/ የሚያገኘው ምላሽ መሪው ሁኔታዎችን እንዲመዝን ይረዳዋል

11/ ሀ/ 7)ስብዕና ለ/ 6) አድሜና ፆታ ሐ/1) ቋንቋ መ/4/ ትችት

ሠ/3) ባሕሎች ረ/5) ደረጃ ሰ/2) ተምሳሌቶች

12/ ሀ/2) አድማጮችህን ማወቅ ለ/4/አጥር ምጥን ባለ ቋንቋ መጠቀም

ሐ/5) ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት መ/ 3)አድማጮችን ማክበር ሠ/1) የምትናገርበትን ጉዳይ ማወቅ

13/ እውነት 14/ እውነት 15/ እውነት 16/እውነት 17/ሐሰት

## ትምህርት ስድስት

1/ እውነት 2/ ሐሰት 3/ እውነት 4/ እውነት /

5/ ሐሰት (ከሥራ እንቅስቃሴም በጥንቃቄ የተደራጀ ድርጅት እንደነበር እንመለከታለን፣ በአጋጣሚ የተደረገ ነገር የለም) 6/ እውነት 7/ እውነት 8/ እወነት 9/ ሐሰት (አንዳንዴ ትክክለኛ ችግሩን መረዳት ትክክለኛ ውሳኔ መስጠትና ትክክለኛ እርምጃ ሁኔታ መውሰድ ሊከብድ ይችላል)

10/ ሐሰት፡- 11/ እውነት 12/ ሐሰት 13/ እውነት 14/ እውነት

15/ ሐሰት፣ (እንደሁኔታው የቡድኑ ተሳትፎም ይለያያል፡፡ ይሁን እንጂ የቡድኑ ብቁነት መጠን ኃላፊነት ይሰጣቸዋል) 16/ ሐሰት 17/ ሐሰት 18/ እውነት 19/ሐሰት

20/ ሐሰት(እነዚህ ነገሮች ስለ ማሕበረሰባዊ ገጽታ የሚገልጹ ናቸው)

21/ እውነት

22/ ሐሰት (እንደሚገባ ከተደራጀ ውሳኔ በማሳለፉ ረገድ ብዙዎቹ በመሰረታዊ ነገሮች ላይ ይግባባሉ፡፡ በዚህ መጀመሪያ ነጥብ ውሳኔ ለማሳለፉ እንዲረዳቸው በአሰራር ቅደም ተከተሉ ላይ ይወያያሉ፡፡ ቀጥሎ በሚያደርጉት ስብሰባ ግን የአሰራር ቅደም ተከተላቸውም ሆነ ያሳለፉት ውሳኔ በቂ ሆኖ ላያገኙት ወይም እንደገና መታየት እንዳለበት ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ብዙ ቡድኖች የሚቀበሉት አሰራር ድምፅ ብዙሃንን ነው) 23/ ሐሰት 24/ እውነት 25/ ሐሰት

## ትምህርት ሰባት

1/ ሐ/ ችግርን ለመፍታት ይወጣሉ

2/ለ/ ምንም ዓይነት ቢጠይቃቸውም መሪዎች ኃላፊነትን ይቀበላሉ

3/ መ/ መሪው በድፍረትና በቆራጥ ውሳኔ መንቀሳቀስ አለበት

4/ሀ/ ድርጅታዊ ዓላማ 5/መ/ የሚከናወኑ ዓላማዎች

6/ ሐ/ ዓላማን ማስቀመጥ ቀላል ሥራ ነው 7/ሀ/ ሥራው እንዲሠራ መርዳት

8/ ለ/ ከኃላፊነት መሸሸ 11/ ሀ/ 4/ መሪዎች ብቸኝነት ይደርስባቸዋል

ለ/ 1/ መሪዎች አገልጋዩች እንጂ ጌቶች አይደሉም

ሐ/ 3/ መሪዎች በሌሎች ይነቀፋሉ ይወቀሳሉ

መ/ 5/ መሪዎች ውጥረት ይደርስባቸዋል

ሠ/2/ መሪዎች ከተመሪዎች ይልቅ ተግተው መሥራት ይኖርባቸዋል

**ትምህርት ስምንት**

1/መ/ ከመጠን በላይ በራስ ከመተማመን መጠንቀቅ አለበት

2/ ለ/ ሌሎችን መርዳት አለባቸው 3/ ለ/ ትሕትና

4/ ሀ/ በመሪው ሥር ያሉ ሰዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ ናቸው

5/ መ/ ዘወትር ግብ ላይ ማተኮር

6/ ለ/ በድርጅቱ የሚከናወነውን ነገር የምንቆጣጠርበት መንገድ ነው

7/ መ/ የጋራ ግብ ላይ ለመድረስ መቀራረብ

8/ መ/ መሪዎች ጥንቃቄ ስለሚያደርጉ የሕዝቡን ችግር ችላ ብለዋል

9/ ሀ/ የመጨረሻ ግብህን አስብ፣ ወደዚያ ለመድረስ የሚያስችልህን አላማዎች አዘጋጅ

10/ ሀ) 4/ አላማዎች ለ)2/ ተቃርቦ ሐ) 6/ ግምገማ መ1/ አቢይ ግብ ሠ/5/ ዐቢይ ተግባራት ረ/3/ ችግሮች

**ትምህርት ዘጠኝ**

1/ሀ/ ጳውሎስ በማንኛውም ዕድል ተጠቀመ

2/ለ/ ተግባራዊ ምክሮች ሰጡ

3/ መ/ በመንፈስ የተቀባና የሚመራ አመራር

4/ ሐ/ ፖለቲካዊ ብጥብጥና ሐይማኖታዊ መናናቅ

5/ መ/ ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር

6/ለ/ በአእምሮአቸው እንዲይዙ ማበረታታትና ማነሳሳት

7/ሀ/ ክርስቲያን ሠራተኞች እንደሚገባ አይነሳሱም

8/ሐ/ ከድርጊቱ በስተጀርባ ያለው ሂደት

9/ለ/ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሕገ-ነቢብ

10/ መ/ ሽልማትና ቅጣትን መሠረት ያደረግ ሕገ-ነቢብ

11/ ሀ/ ግብን መሠረት ያደረግ ህገ-ነቢብ

12/ሐ/ ግንዛቤን መሠረት ያደረግ ሕገ-ነቢብ

13/ ለ/ ጭፍን ታዛዥነት

15/ መ/ የአላማ አንድነት

16/ ሀ/ 5/ ሥልጣን ለ/ 2/ ከሚገባ በላይ በራስ መተማመን

ሐ/ 1/ እኔነት - ትዕቢት መ/ ታዋቂነትና ምሥጋና መፈለግ ሠ/ 4/ ቅንአት